# ካ ፖ ር ቱ

እና

# ሌሎች አጫጭር ታሪኮች

(ትርጉም)

በመስፍን ዓለማየሁ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

፲፱፻፸፰

አዲስ አበባ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ / TEL. 11 27 19 ፖስታ ሣ.ቁ. / P. O. Box 30933

አዲስ አበባ ADDIS ABABA
ኢትዮጵያ ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
ALL RIGHTS RESERVE

የሽፋን ሥዕል — ሰብለ ገብረ ሕይወት

ንግድ ማተሚያ ቤት

መታሰቢያነቷ
ለሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ ይሁን

# ማውጫ


| አሮጊቷ | ገጽ |
|---|---|
| ፑሽኪን | 7 |
| ካፖርቱ | |
| ጉጉል | 39 |
| የማልረሳት ልዩ ወጣት | |
| ኩሮሌንኮ | 103 |
| ሴማጋ እንዴት እንደ ተያዘ | |
| ጉርኪይ | 144 |
| ኩርኔይ ቫሲሊየቭ | |
| ቶልስቶይ | 160 |
| በሽለቆው መኻል | |
| ቼኮቭ | 198 |

# አሌክሳንደር ፑሽኪን

(1799—1837)



በ1799 ተወለደ ። በጊዜው ተራማጅ አስተሳሰብ የነበረው ፑሽኪን፥ ሕይወቱን ለሩሲያ ሥነ ጽሑፍ ዕድገት ያዋለ በመሆኑ ፤ የሀገሪቱ የመጀመሪያዉ የፈጠራ ጽሑፍ ጠቢብ ለመባል በቅቷል። የፑሽኪንን የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች የምዕራባውያን ባለቅኔዎችና የብዕር ሰዎች ተጽዕኖ የዳሰሳቸው ቢሆንም ፤ አርኣያና ምሳሌ ለመሆን በበቁት ፤ በቅኔው ፤ በተውኔቱ ፤ በልቦለድና አጫጭር ድርሰቶቹ ጥልቀትና ምጥቀት ፤ ብሔራዊ ባለቅኔነቱን ለማስመስከር ችሏል ። ፑሽኪን በሰፊ የሥነ-ግጥምና የስድ ጽሑፍ አዝመራው አማካይነት ዘመናዊዉን ሥነ - ጽሑፋዊ ቋንቋ ለሩሲያ ያበረከተ ታላቅ የፈጠራ ሰው በመሆኑ ፤ ‘ የሩሲያ ሥነ-ጽሑፍ ታላቁ ጴጥሮስ ’ እያሉ የሚጠሩትም አልታጡም ። የዛሬዋ ሶቪዬት ኅብረት ደራሲያንም ፤ ‘ የሕዝባችን ነፍስ ’ የሚል ስያሜ የሰጡት ያለ ምክንያት አይደለም ። የአርበኝነትን ባሕርይ ፤ ጠንካራ ብሔራዊ ኩራትንና ለሩሲያ ዐፈር ያለውን ጥልቅ ፍቅር ከአብዮታዊ ስሜቶች ጋር በማዋሐድ በቅኔዎቹ ይገልጥ ስለ ነበር ነው። ይህም ስለ ሥራውና ስለ ሕይወቱ በሚተርኩ ገድሎች

---

በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ዓመተ ምሕረቶች በሙሉ በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ላይ የተመሠረቱ ናቸው ።

ውስጥ ተመዝግቧል። በተለይም በከፍተኛ ስሜት ይደግፈው በነበረው ፣ “ የታኅሣሣውያን ንቅናቄ ” እየተባለ በሚጠራው ፣ የ1825 እንቅስቃሴ ውስጥ ታላቅ ተጋድሎ ላደረጉት አርበኞች ጓደኞቹ መታሰቢያነት የጻፋቸው ቅኔዎች ለዚህ ቋሚ ምስክር ናቸውና ሊጠቀሱ ይገባል ።

ፑሽኪን ኢትዮጵያዊ ደም ነበረው ። በአገራችን በይበልጥ የሚታወቀውም ፣ በኢትዮጵያዊዉ ቅድመ አያቱ በአብርሃም ሃኒባል ታሪክ እንጂ ፣ እምብዛም በኪነታዊ ሥራዎቹ አይደለም ። ወደ አማርኛ ከተመለሱት ጥቂት አጫጭር ታሪኮቹ በስተቀር ዋነኛዎቹ የፑሽኪን የጥበብ ውጤቶች ፣ በተለይም ድንቅ ቅኔዎቹ እስከ ዛሬ በአገራችን ልሳናት አልተተረጎሙም ።

ፑሽኪን ፣ ከሥራዎቹ መካከል የሚበረክቱትን ያቀረበው በሥነ-ግጥምና በአጫጭር ድርሰት ቅርጽ ሲሆን ፣ “ እሮጊቷ ” በሚል ርዕስ በዚህ ቅጽ ውስጥ የቀረበው አጭር ልቦለድ ታሪክ ከግንባር ቀደም ሥራዎቹ አንዱ ነው። ልዩ ተሰጥኦ የነበረውን የዚህን ታላቅ ከያኒ ሥራዎች ፣በተለይም ቅኔዎቹን በርካታ ምሁራንና የሥነ-ጽሑፍ አፍቃሪዎች ዛሬ በመላው ዓለም እንደሚያስተጋቧቸው ሁሉ፣ ይህ አጭር ድርሰቱም በመላው ዓለም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ከመተርጎሙም ሌላ በተንቀሳቃሽ ፊልም ተቀርጾ በመታየት ሁለንተናዊ አድናቆትን ያተረፈ ነው ።

የፑሽኪን መጨረሻ ድንገታዊና የሚያሳዝንም ነበር። ለአንዳንድ ምክንያቶች የተነሣ ፣ ዳንቴስ ከሚባል ሰው ጋር የከረረ አለመግባባት ይፈጠርና ሁለቱ ጠበኞች በተኩስ ለመፋለም ይወስናሉ። እኒሁ ግለሰቦች የካቲት 8 ቀን 1837 ባደረጉት የተኩስ ፍልሚያ የ38 ዓመቱ ጐልማሳ ደራሲ ለሊጋንቱ ተቀጨ ።



# አሮጊቷ

በፈረሰኛ ዘቦች ምድብ ውስጥ መኮንን በሆነው በናሩምቭ መኖሪያ ቤት ውስጥ የካርታው ጨዋታ ሲቀልጥ አድሯል ። ቁማሩ ክፉኛ በመሟሟቁ የተነሣ ፣ ረጅሙ የክረምት ሌሊት መገባደዱ ለተጨዋቾቹ አልታወቃቸውም ። ለአራት ተዘጋጅቶ የነበረውን ምግብ ለመብላት ምድረ ቁማርተኛ በማዕዱ ዙሪያ ሲቀመጡ ከንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ሆኗል ። በሌሊቱ ጨዋታ ያሸነፈው የቀረበለትን ምግብ ደኅና አድርጎ ይጠርጋል ። ያልቀናው ወገን ደግሞ ሳህኑን በደረቅ ዐይኑ እያየ ቀልቡ ባክኖ ፣ የሚያደርገው ጠፍቶት በሐሳብ ወጀብ ይንገላታል ። ብቻ ሻምፓኝ በጠርሙስ ቀርቦ ስለ ነበር ፣ ቀስ በቀስ ጨዋታው እየደራ ሲሔድ፣ ሁሉም በአንድነት ማውካካት ቀጠሉ ።

“ ታዲያስ ሱሪይን ፣ እንዴት ነበር ዛሬ ? ” የቤቱ ባልቤት ጋባዦቹ ላንደኛዉ ጥያቄውን አቀረበ ።

“ ምን ታዲያስ ትለኛለህ ! ቀልጩልህ ። የኔ በየዕለቱ መክሰር ልምድ እየሆነ መጥቷል . . . አሁንስ በተፈጥሮዬ ዕድለ - ቢስ ነኝ ወደሚለውም ዕምነት እያዘነበልኩ ነው ። ለነገሩ እንኳ ሁልጊዜ የምመድበው ገንዘብ መጠነኛ ነው ። ስጫወትም ረጋ ለማለትና ስሜቴን ለመ

ቆጣጠር እሞክራለሁ ። ይሁን እንጂ አንድም ቀን ቀንቶኝ አያውቅም ። ”

“ እኔስ እንዲያው የኸርማን ነገር ብቻ ነው የሚያስደንቀኝ ” አለ ከካርታ አፍቃሪዎቹ አንደኛዉ ፤ የመሐንዲስ ሻለቃ ባልደረባ ወደሆነ አንድ ወጣት መኮንን በጣቱ እየጠቆመ ። “ ይገርማችሁዋል ። ኸርማንን ካወቅሁት ጊዜ ጀምሮ ቁማር ሲጫወት ቀርቶ ካርታ የሚባል በእጁ ሲነካ አይቸው አላውቅም ። ሌሎቻችን ስንጫወት ከመመልከት በቀር በውርርድ እንኳን ጣልቃ አይገባም ። በማየት ከሆነ ግን ሌሊቱንም ቢሆን ያነጋል ። ”

“ ሰዎች ካርታ ሲጫወቱ ማየት ያረካኛል ” አለ ኸርማን ቀበል አድርጎ ። “ ነገር ግን የተትረፈረፈ ሀብት አገኛለሁ በሚል አጉል ተስፋ ለሕይወት አስፈላጊ የሆነ ነገር ለማጥፋት ስለማልሻ አልጫወትም ። ”

“ ነገር ነገሩ እንኳን ወዲህ ነው ። ኸርማን ጀርመናዊ ስለሆነ ፤ ገንዘብ ለመቆጠብ ሲል ይመስለኛል የማይጫወተው ” አለ ቶምስኪ ። “ በነገራችን ላይ አንድ ነገር ላጫውታችሁ . . . የካርታ ጉዳይ ሲነሣ ፤ ሁልጊዜ ግራ የሚገባኝ የሴት አያቴ የአና ፌዶሮቭና አስደናቂ ነገር ብቻ ነው ” ሲል ቀጠለ ።

“ እንዴት ? . . . ምኑ ? . . . ” በማለትና በአንድ ድምፅ በመጮህ እንግዶቹ የተደራረቡ ጥያቄዎችን አቀረቡለት ።

“ አያቱ የካርታ ጨዋታ የሚባል ነገር ለምን እንዳስጠላት እስከ ዛሬ በፍጹም ሊገባኝ አልቻለም ” አለ ቶምስኪ ።

“እና ፤ ታዲያ ላንተ ትልቅ ታሪክ የሆነብህ ምኑ ነው ? የሰማኒያ ዓመት አሮጊት ካርታ ተጫወቱ ፤ አልተጫወቱ



ምንድነው የሚያስደንቀው ? ” ናሩሞቭ ጥያቄውን አቀረበ ።

“ እውን ፤ እስከ ዛሬ ስለ ሴት አያቴ ምንም ዐይነት ታሪክ ሲነገር አልሰማህም ማለት ነው ? ” ሲል ቶምስኪ የጥርጣሬ ጥያቄውን ለናሩሞቭ አቀረበ ።

“ ኧረ ምንም ! ” ናሩሞቭ እንደ መደንገጥ ብሎ በጥሞና መለሰ ።

“ ሁላችሁም የማታውቁት ከሆነ ብነግራችሁ ደስ ይለኛል ” አለና ጀመረ ቶምስኪ ። “ የዛሬ ስድሳ ዓመት ገደማ ነው ይባላል ። ሴት አያቴ ከባሏ ጋር ወደ ፓሪስ ትሔዳለች ። በዚያን የወጣትነቷ ጊዜ በውበቷ ወደር የለሽ ፤ በአለባበሷ ሽቅርቅር ነበረችና ፤ ፓሪስ እንደ ደረሰች አድናቂዎቿ ይበዛሉ ። በየደረሰችበት ሁሉ የሚሰጣት ክብር ልዩ ይሆናል ። እንዲያውም ውበት አፍቃሪዎቹ ፈረንሣውያን ‘ የመስኮቧ ቬኑስ ’ የሚል ቅጽል ስም እስከ መስጠት ይደርሳሉ ።

“ ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት ፤ በነዚያ ዘመናት ቅንጡ ወይዛዝርት ‘ ፋሮ ’ የሚባል የካርታ ጨዋታ ያዘወትሩ ነበር ። ታዲያ የኔም አያት አንድ ቀን ፤ ከኦርሌንሱ መስፍን ጋር ካርታ ተጫወተችና የማሸነፍ ነገር ሳይሳካላት በመቅረቱ ፤ ያላትን ገንዘብ አራግፋ ጨረሰች ። እንዲያውም ዕዳ ውስጥ በመግባቷ ፤ ዋስ ጠርታ ወደ ማረፊያዋ ተመለሰች ። ማረፊያ ቦታዋ እንደ ደረሰችም ለባሏ—ለወንዱ አያቴ ማለት ነው—በካርታ ጨዋታ መረታቷን ገልጣ የቀረውን ዕዳ በአስቸኳይ እንዲከፍል አዘዘችው ።

“ ይገርማችሁዋል ! ወንዱ አያቴ ለሴቷ አያቴ ባል ሳይሆን የሎሌ ያህል ነበር ። እንደ እንዳች መቅሠፍት ፤ እንደ እንዳች ክፉ ልክፍት ነበር የሚፈራት ። ይሁን እንጂ፣

ስለ ቁማርና ስለ ኪሣራው በሰማ ጊዜ ፣ ራሱን ለመቆጣ
ጠር አልቻለም ። አበደ ። በደም - ፍላት ተቆጣ ። ቱግ አለ፤
እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ ። እንደ ወትሮው ደካማና ታዛዥ
ሊሆንላት አልቻለም ። ወዲያው የሒሳብ ማስሊያውን አን
ሣና ወደ ፓሪስ ከመጡ ጊዜ ጀምሮ ስላባከኑት ገንዘብ መጠን
በመግለጽ በቁማር የመጣ ዕዳዋን እንደማይከፍል ዕቅጩን
ነገራት ። ሴቷ አያቴ ግን ኃይለኛና እልኸኛ ነበረችና በዚህ
ምላሽ ይበልጥ በመናደዷ ፣ የወንድ አያቴን ጆሮ ግንድ በጥፊ
አቃጥላ ዐይኑን ላለማየት ከመኝታ ክፍሏ አባረረችው ።

“ በተከታዩ ቀን ወንዱ አያቴ ሐሳቡን ለውጦ እን
ደሆነ በማለት ጥያቄዋን እንደገና ብታቀርብም አልሆንላ
ትም ። በምንም ዐይነት ሐሳቡን ልታስቀይረው እንደማ
ትችል የተረዳችው አያቴ ግራ ተጋብታ ፣ የምታደርገው
ጠፍቷት ፣ ከዕዳዋ ተፋጥጣ ቁጭ አለች ።

“ በመጨረሻ በዚያው በፓሪስ ከተማ ይኖር የነበረ
አንድ ወዳጅዋ የሆነ ሰው ትዝ ይላታል ። ሳን ዤርማ ይባ
ላል ። ብዙ ጥበባዊና አስደናቂ ሥራዎችን የሚፈጽም በመ
ሆኑ በመላው ዓለም ሰፊ ዝናን ያተረፈ ነበር ። ምናልባት
እናንተም ስሙንና ዝናውን ሰምታችሁ ይሆናል ። የሰው
ፍቅር ያለውና ተግባቢም ነበር ይባላል ። ታዲያ ሴት አያቴ
እስከ ዛሬ ድረስ ነፍሷ ምንጥቅ እስኪል ይህን ሰው ትወ
ደዋለች ። እሷ ፊት ስሙን በክፉ ቀርቶ፣በደግ እንኳን ማን
ሣት አይቻልም ። ሳን ዤርማ ባለብዙ ገንዘብ በመሆኑ
ድንገት ቢረዳኝ ብላ ፣ በዚያን በጭንቀቷ ወቅት ሴት አያቴ
ማስታወሻ ጽፋ እንዲያነጋግራት ትልክበታለች ።

“ ሽማግሌው ሳን ዤርማ መልእክቱ እንደ ደረሰው
ወደ ሴት አያቴ ዘንድ ይሔዳል ። በጣም ተበሳጭታና አዝና
ያገኛታል ። እርሷም የገጠማትን ሁኔታ በዝርዝር ትነግረ
ውና ዕዳዋን በመክፈል ፣ ከደረሰባት ውርደት ለመዳን የመ



ጨረሻ ተስፋዋን የጣለችው በእርሱ ላይ መሆኑን ትገል
ጥለታለች ።

“ ሽማግሌው ፣ በነገሩ ለጥቂት ጊዜ ካሰበበት በኋላ ፣
‘ ይህን በዕዳ የሚፈለግብሽን ያህል ገንዘብ ላበድርሽ እች
ላለሁ ። ይሁን እንጂ ያው ዞሮ ዞሮ ዕዳ ስለሚሆንብሽ ፣ ለኔ
ለመክፈል ስትይ ደግሞ ፣ ሌላ ጭንቀት ውስጥ መውደቅሽ
አይቀርም ። ስለዚህ የተሻለ አማራጭ የሚሆነው ቁማር
ጨዋታውን በመቀጠል ዕዳሽን መክፈል ነው ’ ይላታል ።

“ ሴቷ አያቴ ግን ቀበል ታደርግና ፣ ‘ሐሳቡ እንኳ
ደግ ነበር ። ነገር ግን እንኳንስ ለቁማር መጫወቻ የምመ
ድበው ይቅርና ፣ ለውሎ የሚሆን ሰባራ ሳንቲም በጄ የለም ’
ስትል ትገልጽለታለች ። ”

“ ጥበበኛው ሳን ዤርማንም ፣ ‘ ገንዘቡን ለመመለስ
ለሚደረገው ጨዋታ ምንም የመነሻ ገንዘብ አያስፈልግም ።
የምንጠቀመው በሌላ ዘዴ ነው ’ ይልና አንድ ብርቱ ምስ
ጢር ለሴት አያቴ ይነግራታል ። ”

በዚህ ጊዜ ፣ የናሩሞቭን መኖሪያ ቤት የሞሉት ወጣት
ቁማርተኞች የታሪኩን መጨረሻ ለመስማት ከመጠን በላይ
አቆበቆቡ ። ጒጒታቸው ከመጀመሪያው የባሰ ሆነ ። ቶምስ
ኪም ፒፓውን እያይዞ ጢሱን እንዴ ማገና ታሪኩን በር
ጋታ ቀጠለ ።

“ በዚያኑ ምሽት ፣ ሴት አያቴ ቨርሳይ ወደሚገኘው
ዝነኛ የቁማር ሥፍራ አመራች ። ባለፈው ምሽት ከረታት
የኦርሌዎ መስፍን ጋር ተገናኘች ። ፀቀጥታ ወደ ጉዳይዋ
በመግባት የሚፈለግባትን ገንዘብ ያልያዘች መሆኑን ገልጾ፣
ለዚህም ምክንያት የፈጠረችውን አጭር ታሪክ በማቅረብ
ካሳመነችው በኋላ ፣ ለምሽቱ የዱቤ ቁማር ተቀመጡ ። ሴት
አያቴ ፣ በሳን ዤርማን በተሰጣት ምክር በመጠቀም ሦስት

ካርታዎችን መርጣ በቅደም ተከተል በየተራ ተጫወትችባቸው ። በሦስቱም ካርታዎች መደዳውን በማሸነፍ የተዘፈቀችበትን ዕዳዋን በመክፈል ነጻ ከመሆኑዋም በላይ ፣ ትርፍ ገንዘብ ይዛ ቤቷ ገባች ። ከዚህ ቀን በኋላም ቁማር የተባለ ነገር እርም ብላ አቆመች ። እንኳንስ ልትጫወት ይቅርና ካርታ የተባለ በዞረበት ላትዞር መሐላዋ ሆነ ” ሲል ቶምስኪ ታሪኩን ደመደመ ።

“ ይሄ ተራ ያጋጣሚ ዕድል ነው ” በማለት ከእንግዶቹ አንደኛው አስተያየቱን ጣል አደረገ ።

“ ያፍ ታሪክ ... ተረት እንጂ ሌላ ምንም አይደል ! ” አለ ቁማር የማይወደው ጀርመናዊው ኸርማን ።

“ ምናልባት በአያትህ ካርታዎች ላይ ምልክት ተደርጎባቸው ሊሆን ይችላል ። ” ሌላው የቤቱ አስተያየት ነበር ።

“ በጭራሽ አይደለም ” ብሎ ቶምስኪ መልሱን በኩራት ሰጠ ።

“ በጣም የሚያስደንቅ ነው ! ” ሲል አስተናጋጁ ናሩሞቭ ቀበል አደረገው ። “ በተከታታይ ለመርታት ስለሚያስችሉ ሦስት ጓደኛ ካርታዎች የሚያውቁ አያት እያሉህ አንተ ግን ስለ ምስጢሩ ምንነት ቅንጣት ነገር አለማወቅህ በጣም የሚያስደንቅ ነው ” አለው ።

“ እውነትም ምስጢሩን አለማወቄ ያስደንቃል ። ይሁን እንጂ ፣ ነገሩ እንዲህ ቀላል አይደለም ። ” ቶምስኪ ማስረዳት ይጀምራል ። “ ሴት አያቴ አራት ወንድ ልጆች ነበሯት ። አንዱ የኔ አባት ነው ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አራቱም ልጆቿ የለየላቸው ቁማርተኞች ነበሩ ። ሴት አያቴ ግን የካርታዎቹ ምስጢር የሚጠቅማቸው መሆኑን ብታ



ውቅም እንኳን ለአንዳቸውም አልገለጸችላቸውም ። ይህን በመሐላ ጭምር የነገረኝ አጐቴ ኢቫን ኢሊች ነው ። የሚገርመው ግን ለቤተሰባችን ምንም ዝምድና ለሌለው ለቻፕሊትስኪ ፣ አያቴ የካርታዎቹን ምስጢር ገልጻለታለች ይባላል ። መቼም ከመካከላችን ሟቹን ቻፕሊትስኪን የማያስታውስ ያለ አይመስለኝም ። በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘቡን በቁማር አውድሞ በድኅነት ሲማቅቅ የኖረ ሰው ነውና ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ።

“ ታዲያ ፣ ይኸው አሲዳም ቻፕሊትስኪ አንዴ ፣ በወጣትነቱ ጊዜ ነው ፣ ሦስት መቶ ሺህ ሩብል በቁማር ያሟጥጥና ባዶ እጁን አጨብጭቦ ቁጭ ይላል ።ክፉኛ ተስፋ ይቆርጣል ። አያቴ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ወጣቶች በብኩንነታቸው ለሚደርስባቸው ችግር የማትጨነቅና ርኅራኄ የሌላት ብትሆንም ፣ በቻፕሊትስኪ ላይ የደረሰው ሁኔታ ግን በጣም አሳዘናት ። በዚህ ምክንያት ቻፕሊትስኪ ገንዘቡን ካስመለሰ በኋላ ፣ ለወደፊቱ ቁማር የሚባል ባለበት ድርሽ እንዳይል አስጠንቅቃ ፣ የሦስቱን ካርታዎች ምስጢር ትነግረዋለች ።

“ ቻፕሊትስኪ በቀጥታ ወደ ቁማር ቤት ይሔዳል ። ሴት አያቴ በነገረችው መሠረት የመጀመሪያውን ካርታ በመሳብ ፣ ሺህ ሃምሳ ሺህ ሩብልስ* ይመድባል ። ያሸንፋል ። በሁለቱ ካርታዎች አከታትሎ በመጫወትም ተበልቶ የነበረ ገንዘቡን በሙሉ አስመልሶ ትርፍም ያገኛል ።”

ቶምስኪ ንግግሩን ሲፈጽም ፣ የምግቡን ጠረጴዛ የከበበው ቁማርተኛ ሁሉ ፣ በነገሩ ተማርኮ በመፍዘዝ ይመለከተው ነበር ። በመጨረሻም ፣

---

* ሩብል ፣ የሶቪየት ኅብረት ገንዘብ ነው ። አንድ ሩብል ዛሬ ሦስት የኢት/ብር ገደማ ይመነዝራል ።

" እንግዲህ ለዛሬ የሚበቃን ይመስለኛል ። ለዐሥራ ሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ስለሆነ መተኛቱ አይከፋም " በማለት ቶምስኪ ሐሳቡን ደመደመ ።

ወጣቶቹ ፣ በየብርጭቆአቸው ውስጥ ያለውን መጠጥ ጨላልጠው እያዛጉ ሲበታተኑ ፣ የንጋት ብርሃን ክፍሉን ወገግ አድርጎት ነበር ።

— 2 —

አሮጊቷ የቶምስኪ አያት በመልበሻ ክፍሏ ውስጥ ፣ ከመስተዋቱ ፊት ለፊት ተቀምጣለች ። ሦስት ደንገጡሮቿ ዙሪያዋን ከበው ያጊያጊጡዋታል ። አንዷ የጸጉር ማስያዣዎች ፣ ሌላዋ ቅባትና መኳኳያ ይዛ ቆማለች ። ሦስተኛዋ ደግሞ፣ፍም የመሰለ ቀይ ጥብጣብ ያለው የሴት ባርኔጣ አንጠልጥላለች ። በአሮጊቷ ገጽ ላይ የወጣትነቷ ጊዜ ውበት ለዐመል ያህል እንኳን አይታይም ። ሙልጭ ብሎ ረግፏል ። በአፍላነቷ የነበሩት የውበት ጸዳልና ትኩስ ሙቀት በእርጅና መሥመሮችና ቅዝቃዜ ከተተኩ በጣም ረጅም ጊዜ ሆኗል ። የቀራት ነገር ቢኖር ፣ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በየዕለቱ ስትፈጽመው የኖረችው የመጊያጊያጥ ልምዷ ብቻ ነው ።

በየቀኑ ለመተጣጠብ ፣ ለመኳኳል ፣ ለመቀባባትና ለመከሸን የምታጠፋው ጊዜና የምታባክነው ጉልበት ፣ በወጣትነቷ ጊዜ—ከስድሳ ዓመታት በፊት—ከነበረው ቅንጣት አልተለወጠም ። ከአሮጊቷ ዕልፍ ብሎ አንዲት ወጣት ኰረዳ ከመስኮቱ አጠገብ ተቀምጣለች ። ከአሮጊቷ ጋር የምትኖርና የቅርብ ረዳቷ ናት ።



" እንደ ምን አደሩ አያቴ ! " ወጣቱ መኮንን ፖል ቶምስኪ ወደ ክፍሉ እየገባ ሰላምታውን አቀረበ ። " ጤና ይስጥልኝ ወይዘሪት ሊዝ . . . የዛሬው አመጣጤ አንድ ነገር እንዲያደርጉልኝ አያቴን ለማስቸገር ነው " አለ ።

" ምንድነው የምትሻው ፖል ? " አለች አሮጊቷ ፣ ድክም ባለ ድምፅ ።

"አንድ የቅርብ ጓደኛ አለኝ ። ዓርብ ማታ በሚደረገው ግብዣ ላይ ተገኝቶ ከእርስዎ ጋር እንዳስተዋውቀው መልካም ፈቃድዎን ነው የምጠይቀው ። "

" ታዲያ ምናለ ! ለዚህ ነው ጭንቁ ? . . . በቀጥታ ወደ ግብዣው ቦታ አምጣውና ከኔም ጋር እዚያው ታስተዋውቀዋለህ ። " አሮጊቷ በሰለቸ አንደበት መልሱን እንደ ዘበት ወርወር አደረገችና ፣ የጀመረችውን መጊያጊያጥ ለማጠናቀቅ ፣ በሦስቱ ደንገጡሮቿ ታጅባ በመጋረጃ ወደ ተከለለ ሌላ ክፍል ገባች ። ቶምስኪና ወጣቷ ሊዝ ብቻቸውን ቀሩ ።

" ማንን ነው ከአያትህ ጋር ለማስተዋወቅ የፈለግሽው ? " ወጣቷ ሊዛቬታ ኢቫኖቭና ድምጿን ለስለስ አድርጋ ጠየቀች ።

" ናሩሞቭ የሚባል ነው ። ታውቂዋለሽ ? " ቶምስኪ በጥያቄ መለሰላት ።

" አላውቀውም ። ለመሆኑ ወታደር ነው ሲቪል ? "

" ወታደር ። "

"ተዋጊ መሐንዲስ ? "

" አይደለም ፣ ፈረሰኛ ነው ። ግን መሐንዲስ የሚለውን ከምን አመጣሽው በይ ? "

ወጣቷ ልጃገረድ በመጠኑ ሣቅ አለች ። መልስ ግን አልሰጠችውም ።

ቶምስኪም መልሱን ሳይጠብቅ ፤ ከአሮጊቷ የመልበሻ ክፍል ወጣ ።

ሊዛቬታ ኢቫኖቭና በመልበሻ ክፍሉ ውስጥ ብቻዋን ቀረች ። በእጅዋ የያዘችውን ጥልፍ ለጥቂት ጊዜ ስትተበትብ ቆየችና ድንገት ሳይታወቃት ዐይኖቿን ከሥራዋ ላይ ነቅላ ፤ በሐሳብ ቅዝዝ በማለት በመስኮቱ በኩል ታስትውል ጀመር ። ወዲያው አንድ ሎጋ መኮንን ፤ የመሐንዲስ ክፍል መለዮና የደንብ ልብሱን ለብሶ ፤ ባሻገር ከሚታየው ጉዳና ካንደኛው ጥጋት በኩል ብቅ አለ ። የሊዝ ጉንጮች ድንገት ፍም መሰሉ ። አንገቷን ሰበር አድርጋ በሥራዋ ላይ አቀረቀረች ። ወዲያው አሮጊቷ በአማሩ ልብሶች ተሸትራ ከመጋረጃው ጀርባ ብቅ አለች ።

“ ሊዛቬታ ፤ ለሽርሽር ወጣ ስለምንል ፤ ሠረገላው እንዲቀርብ ትእዛዝ ስጪ ” አለቻት ። ሊዝ የምትሠራውን ጥልፍ ወደ ጐን አኖረችና ከተቀመጠችበት ተነሥታ ዕቃዎቿን መሰብሰብ ጀመረች ።

ሊዛቤታ ኢቫኖቭና ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በመስኮት በኩል የተመለከተችው መልከ ቀና የተዋጊ መሐንዲስ መኮንን ፤ በየዕለቱ ከቤቱ ባሻገር መንገዱ ላይ እየተገተረ የአሮጊቷን መኖሪያ ማስተዋል ከጀመረ ብዙ ቀናት ዐልፈውታል ። ሊዛ ፤ ይህን የደስ ደስ ያለው መኮንን በሌላ አጋጣሚና ቦታ ባታውቀውም ፤ በየዕለቱ ከቤታቸው ባሻገር ቆሞ አያሌ ሰዓቶችን ባሳለፈ መጠን በርሷም ላይ ልዩ ስሜት እያሳደረባት ሔደ ። ከዚያ ጊዜ በፊት የማታውቀው ዐይነት ስሜት ስለ መኮንኑ ይሰማት ጀመረ ። ለብዙ ቀናት መኮንኑን ወደ ቤታቸው አካባቢ የሚያመጣው ምክንያት



ግልጽ ሳይሆንላት ቢቆይም ፤ በመጨረሻ የመኮንኑ ዐቢይ ዓላማ እሷን መፈለግ እንደሆነ ከልቧ አመነችበት ። አንድ ቀን ጧት መኮንኑ በተለመደው ቦታ እንደ ቆመ ፤ ሊዛ ለመጀመሪያ ጊዜ ሞቅ ያለ ፈገግታዋን ጋበዘችው ።

ይህ በየቀኑ በአሮጊቷ መኖሪያ ላይ አፍጥጦ የሚውለው መኮንን ጀርመናዊው ኸርማን ነው ። የካርታ ጨዋታ ደስ ቢለኝም እንኳን በቁማርነቱ ስለማልወደው ፤ ለመጫወት አልሻም የሚለው ኸርማን ፤ ቶምስኪ የአሮጊት አያቱን ሦስት ካርታዎች ታሪክ ሲያወጋ ከሰማበት ሌሊት ጀምሮ ስለ ካርታ ጨዋታ የነበረው አስተያየት ተለውጦዋል ። የእነዚያን ሦስት ካርታዎች ምስጢር ለማወቅና ፤ ቢቻልም ሊጠቀምባቸው የመፈለግ ስሜቱ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ከፉኛ ተንሣሥቷል ።

“ እኒያ አሮጊት የካርታዎቹን ምስጢር ቢገልጡልኝ ምንኛ መልካም በሆነ ነበር ” አለ ኸርማን ፤ ታሪኩን ከቶምስኪ ከሰማ በኋላ አንድ ቀን ለብቻው ሆኖ ። “ አሮጊቷ ዘንድ በቀጥታ ሔጄ ብጠይቃቸው ፤ የካርታዎቹን ምስጢር ሊገልጡልኝ ፈቃደኛ የማይሆኑበት አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይችልም ። የብዙ ገንዘብ ባለቤት ለመሆን ያለኝን ፍላጐትና ምኞት ሁሉ በዝርዝር ብነግራቸውና አጥብቄ ብለምናቸው ሊያዝኑልኝም ይችላሉ ” ሲል አሰበ ፤ ብቻውን ከሕሊናው ጋር እየተሟገተ ።

ይህን ሐሳቡን አውጥቶ አውርዶ በሰፊው አውጠንጥኖ ሲያበቃ ፤ የቶምስኪን አያት ለመተዋወቅና የፍላጐቱን ለመጠየቅ የግሉን ውሳኔ አሳለፈ ። በዚህም መሠረት ነበር ፤ በየቀኑ ወደ አሮጊቷ መኖሪያ አካባቢ እየሔደ ተገትሮ ፤ መዋል የጀመረው ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ከቤቱ ፊት ለፊት በሚቆምባቸው ቀናት ሁሉ ፤ ሊዛን ከመስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ ያያታል ። የቤት ልጅ መሆኗ ይገባዋል ። ከዚያች መልከ

ቀና ልጅ ጋር ወዳጅነት ቢመሠርት ደግሞ ፡ ወደ አሮጊቷ
ዘንድ ቀርቦ ለመተዋወቅና ጥያቄውን ለማቅረብ መንገዱ
ይበልጥ ቀና እንደሚሆንለት ይገምታል ። ስለዚህ የቅድ
ሚያ ትውውቁን ከሊዛ ጋር ለማድረግ ወሰነ ።

አንድ ቀን ፡ ሊዛና አሮጊቷ ለሽርሽር ወደ ውጭ ለመ
ሔድ ከቤት ወጥተው መንገድ ዳር በመቆም ሠረገላው እስኪ
ቀርብ ይጠብቃሉ ። ሠረገላው ቀርቦ አሮጊቷ ቀድማ ወደ
ሠረገላው ስትገባ ፡ ሊዛ ወደ ኋላ ቀረት ብላ ነበርና በእጅዋ
መዳፍ ውስጥ አንዲት ወረቀት ሽጕጥ ሲደረግላት ተሰማት።
ወረቀቱን በእጅዋ ውስጥ ያስቀመጠውን ሰው ለማየት ዞር
ስትል ፡ ለብዙ ቀናት በመስኮት በኩል በሩቅ ስታየው
የቆየችው ወጣት መኰንን አጠገቧ ቆሟል ። ሊዛ የመሸ
በርም ሆነ የሌላ ስሜት ምልክት ሳታሳይ ወረቀቱን በእጅ ፡
ሹራቧ ( ጓንቷ ) ውስጥ ሻጥ አድርጋ ቀልጠፍ በማለት
ወደ ሠረገላው ገባች ።

ከሽርሽሩ መልስ በኋላ ፡ ሊዛ በፍጥነት ወደ መኝታ
ክፍሏ ገብታ የኸርማንን ወረቀት አወጣች ። መልእክቱን
ለማወቅ ቸኩላ ነበረና የተጣጠፈውን ወረቀት በፍጥነት
ዘረጋግታ ንባብ ጀመረች ። ደብዳቤዉ ኸርማን ለመልከ
ቀናዋ ጉብል ያለውን አክብሮትና ፍቅር በሚገልጹ ቃላት
የተሞላ ነው ። ጽሑፉ በመላ ከአንድ በጀርመንኛ ቋንቋ
የተጻፈ ዕውቅ ልቦለድ ውስጥ ተቆንጽሎ የተገለበጠ ነበር።
ሊዛ ግን ይህን አታውቅም ነበርና ፡ ጽሑፉ የራሱ የኸርማን
መስሏት ፡ በወጣቱ መኰንን የሥነጽሑፍ ችሎታና መልእ
ክቱ ስለ ተቀነባበረበት ቋንቋ ውበት ክፉኛ ተደነቀች ።

በደብዳቤዉ ደስ የተሰኘችው ሊዛ ወዲያውኑ መልስ
ጻፈች ። በተከታዩ ቀን ኸርማን በተለመደ ሥፍራው እንደ
ቆመ ፡ ሊዛ ወረቀቷን በመስኮቱ በኩል ጣል አደረገቻት ።
በጉጉት ይጠባበቅ የነበረው መኰንን፡ ወዲያውኑ መንገዱን



አቋርጦ ወደ ቤቱ ጥግ ቀረበና ወረቀቷን ብድግ አድርጎ
በአካባቢው ወደምትገኝ አንዲት ሱቅ በመግባት ማንበብ
ጀመረ ።

ከሦስት ቀናት በኋላ ሌላ ደብዳቤ ለሊዛ ደረሳት ።
ሁለተኛዉ ደብዳቤ የመጣላት በአንዲት ትንሽ ልጅ አማ
ካይነት ነበር ። መልስ ግን አልሰጠችውም ። ይሁን እንጂ
ኸርማን አመቺ በሆኑ መንገዶች ሁሉ እየተጠቀመ ደብ
ዳቤዎች በተከታታይ መላኩን ቀጠለ ። በደብዳቤዎቹም
ዘወትር የሚገልጠው በቅድሚያ ለሊዛ ያለውን ፍቅርና
አድናቆት ሲሆን ፡ ከዚያ በማያያዝ ደግሞ፡ ፍላጐቱን ከግብ
ለማድረስ ይረዳው ዘንድ የሩቅ ትውውቃቸው በቅርብ ግን
ኙነት እንዲጠናከር፡ በግልና በቅርብ ሊያገኛት የሚችልበ
ትን ቀጠሮና ቦታ እንድትገልጥለት ይጠይቃል ።

ኸርማን ፡ ለደብዳቤዎቹ መልስ ባያገኝም ያለ መሰል
ቸት ደብዳቤዎች መላኩን ቀጠለ ። አንድ ቀን ጥያቄዉ
መልስ አገኘ ። ሊዛ በቅርብ ልትገናኘው ፈቃደኛ መሆ
ኗን የሚገልጠው ደብዳቤዋ ደረሰው ።

“ ዛሬ ማታ ” ይላል ፡ ሲናፍቀው የቆየው የሊዛ ደብ
ዳቤ ፡ “ ዛሬ ማታ የ . . . አገር አምባሳደር በሚያደርጉት
የዳንስ ግብዣ ላይ ለመገኘት ፡ ከእማማ ጋር አምባሳደሩ
መኖሪያ እንሔዳለን ። በዚያም እስከ ሌሊቱ ስምንት ሰዓት
እንቆያለን። እኛ ወደ ግብዣ እንደ ሔድን የቤቱ ውስጥ ሠራ
ተኞችና አሽከሮችም በሙሉ ወደ የመኖሪያቸው ይሔዳሉ ።
የሚቀር ሰው ቢኖር ዘበኛው ብቻ ነው ። እሱም ቢሆን ወደ
ክፍሉ ሔዶ ዐረፍ ይላል እንጂ ፡ በሩ ላይ ተገትሮ እያመ
ሽም ። ስለዚህ ለመገናኘት አመቺ ሁኔታ ይኖረናል ። ወደ
ቤት ውስጥ የምትገባበትም ዘዴ እንዲህ ነው ።

“ ልክ ከምሽቱ 5 ሰዓት ተኩል ሲሆን ትመጣለህ ።
ዋናውን የቤቱን በር ከፍተህ በመግባት ወደ ፎቅ ትወጣ
ለህ ። ድንገት ሰው ቢያጋጥምህ ቀልጠፍ ብለህ እማማን
እንደ ምትፈልግ ተናገር ። በቤት ውስጥ አለመኖሯንና
ግብዣ ቦታ መሔዷን ስለሚነግሩህ ፥ ምንም ችግር ሳይገ
ጥምህና ሳይነቃብህ ፤ ይቅርታ በመጠየቅ ተመልሰህ ለመው
ጣት ትችላለህ ። ነገር ግን ምንም እንደማይገጥምህ እም
ናለሁ ። ስለዚህ ፎቁ ላይ ከወጣህ በኋላ ፥ ከአዳራሹ በስተ
ግራ በኩል በማምራት ወደ አሮጊቷ መኝታ ክፍል ትደር
ሳለህ ። ክፍሉ ውስጥ ስትገባ በመጋረጃ የተከለሉ ሁለት
በሮችን ታገኛለህ ። በስተቀኝ ያለው ወደ አሮጊቷ የጥና
ትና የንባብ ክፍል የሚያስገባ ስለሆነ ፥ እርሱን በመተው
በስተግራ ያለውን ከፍተህ ወደ ውስጥ ዕለፍ ። እዚያም
በምታገኛት ደረጃ ወጥተህ የምትደርስበት የኔ መኝታ ክፍል
ነው ። በዚህ ሁኔታ ገብተህ እክፍሌ ውስጥ ቁጭ ብለህ
ከግብዣው እስክንመለስ በትዕግሥት ትጠብቀኛለህ ። ”

ኸርማን የቀጠሮዉ ሰዓት ሲደርስ ፥ ንፉስ እንደሚያ
ርገበግባት ቅጠል የሠራ አካሉ ይንዘፈዘፍ ጀመር ። ሳያ
ውቀው ሁለመናው ተርበተበተ ። ይሁን እንጂ ፥ ምንም
እንኳን መንፈሱና አካሉ ቢረበሽም ፥ ለረጅም ጊዜ የደ
ከመበት ዓላማውን ከግብ ማድረስ ስላለበት ፥ ጊዜ ሳያ
ባክን አካሉን አረጋግቶና ስሜቱን ተቆጣጥሮ ወደ አሮጊቷ
መኖሪያ አመራ ። ሊዛቤታ ኢቫኖቭና የሰጠችውን መመ
ሪያ ቅደም ተከተሉን ሳያዛንፍ ተግባራዊ እያደረገ በዋ
ናው በር በማለፍ ፥ በሌሎቹ ክፍሎች አቆራርጦ አንድም
ነገር ሳይገጥመው፥ ምንም ግር ሳይለው አሮጊቷ መኝታ
ክፍል ደረሰ ። መኝታ ክፍሉ ውስጥ ከገባ በኋላ ግን ፥ የሊዛን
መመሪያ ከዳር ለማድረስ እምብዛም አልተጨነቀም ። በደ
ብዳቤዉ መሠረት በቀጥታ ወደ ሊዛ መኝታ በማምራት



ፋንታ፥ሐሳቡን ቀይሮ፥በአሮጊቷ ክፍል ውስጥ በሚገኝ ከግ
ድግዳው ጋር አብሮ በተሠራ የልብስ ማስቀመጫ ቁም
ሣጥን ውስጥ ገብቶ ተደበቀ ።

ሰዓቱ ቶሎ አልደርስ አለው ። ኸርማን ቁም ሣጥኑ
ውስጥ ሆኖ የአሮጊቷን መምጣት በጉጉት ይጠባበቃል ።
በመጨረሻ አንድ ሠረገላ ወደ ቤቱ እየተቃረበ ሲመጣ
ድምፁ ተሰማው ። ብዙም ሳይቆይ መብራቶች ታዩት ።
ቀጥሎም አሽከሮች ወዲያ ወዲህ ሲሉ በሚያሰሙት መተረ
ማመስ አሮጊቷ መምጣቷን አረጋገጠ ። ወዲያው አሮጊቷ
ወደ መኝታ ክፍሏ ተደጋግፋ ስትገባ በቀዳዳ ተመለከተ ።
ከድካም የተነሣ በፍጹም ዝላለች ። ደንገጡሮቿ ፥ ልብሶቿ
ንና ጌጣጌጧን እያወላለቁ ለመኝታ ያዘጋጇዋት ጀመር ።
ኸርማን ሁሉንም ነገር ልቅም አድርጎ እሱ ሳይታይ ያስ
ተውላል ። ብቻ ከአጉል እምነት ጋር የተቀላቀለ ፍርሃት
ዐልፎ ዐልፎ ሰውነቱን ወረር ሲያደርገው ይታወቀዋል ።
በመጨረሻ አሮጊቷ የሌሊት ልብሷን አጥልቃና ቆቧን
ደፍታ ቁጭ አለች ። ለዳንሱ ግብዣ ሰማያዊ የሆነ ጌጠኛ
ልብስ ለብሳ በነበረ ጊዜ የሚታይባት የመከበድና የልዩ
ነት ሁኔታ ተለውጦ፥ ለዐይን በመጠኑ ቀለል አለች ።

በየምሽቱ አልጋው ላይ ጉኗን ከማሳረፏ በፊት ማድ
ረግ እንዳስለመደችው ፥ በአንድ ጠረጴዛ አጠገብ በሚ
ገኝ ምቹ ወንበር ላይ በጸጥታ ቁጭ አለች ። ደንገጡሮቿ
ተግተልትለው ከክፍሉ ወጡ ። ብቻዋን የቀረችው አሮ
ጊት በተቀመጠችበት ወንበር ላይ ሆና ቀስ በቀስ ወደ ፊት፥
ወደ ኋላ መወዛወዝ ጀመረች ። በሐሳብ ከመዋጥ ወይም
በዕድሜ ብዛት ከመደንዘዝ የተነሣ ፥ አእምሮዋ አካባቢዋን
ጨርሶ የዘነጋ ይመስላል ። እንዲህ ባለ ሁኔታ እያለች አሮ
ጊቷ ዐይኖቿን ከድና በወንበሯ ላይ ወደፊት ፥ ወደ ኋላ ስት
ወዛወዝ ፥ ኸርማን ከተደበቀበት ቁም ሣጥን ቀስ ብሎ ወጣ ።

ኩሽታ የሰማችው አሮጊት ፣ ዐይኖቿን ገለጠችና እን
ቅልፍ ባደበዘዘው አመለካከት ቤቷን ደፍሮ የገባውን ሰው
ታስተውለው ጀመር ።

" በእግዜር ይፁንብዎና አይደንግጡ ! " አለ ኸርማን
ረጋ ባለ ድምፅ ፣ " አመጣጤ እርስዎ ላይ ጉዳት ላደርስ
ሳይሆን አንድ ውለታ እንዲያደርጉልኝ ለመለመን ነው ። "

አሮጊቷ በጸጥታ ትመለከተዋለች ። የሚናገረው ሁሉ
ምኑም ምኑ የገባት አትመስልም ። ኸርማንም በበኩሉ
ደንቆሮ ትሆናለች የሚል ሐሳብ በአእምሮው ስለ መጣበት ፣
ወደ አንደኛው ጆሮዋ ጠጋ ብሎ የመጀመሪያውን ንግግ
ሩን ጐላ ባለ ድምፅ ደገመው ። አሮጊቷ ላይ ግን ቅንጣት
ለውጥ አልታየም ።

" እርስዎ አንዲት ሰባራ ሳንቲም ሳያወጡ እኔን ከበ
ርቴ ለማድረግ ይችላሉ ። " ወጣቱ ልመናውን ቀጠለ ።
" የሦስቱን ካርታዎች ምስጢር ከነገሩኝ በቂዬ ነው ።
በሌላ አላስቸግርዎትም ። ደግሞ .... "

አሮጊቷ ለመናገር የፈለገች ይመስል ፣ በጥብቅ
የተጋጠሙ ከናፍሯን ስታላቅቅ የተመለከተው ኸርማን
የጀመረውን ውትወታ ሳይጨርስ አንጠልጥሎ ተወው ።

" እውነት አይምሰልህ ። ሁሉም ነገር ፌዝ ነው ። ከፈ
ለግህ በእግዚአብሔር ስም እምልልሃለሁ ። የሰማኸው
ነገር ሁሉ ፌዝ ፣ ቀልድ ፣ ተረብ እንጂ ሌላ ምንም አይደ
ለም " የሚሉ ቃላት በነዚያ የጠወለጉ ከንፈሮች አማ
ካይነት ለኸርማን ተላለፉለት ። ።

" አይደለም ። የሰማሁት ነገር ፌዝ ፣ ቀልድ ፣ ተረብ
አይደለም ። በሙሉ እውነት ነው ። ለምሳሌ ያህል፣ከብዙ
ዓመታት በፊት ቻፕሊትስኪ የሚባል አንድ ብኩን ሰው



በቁማር የተነሣ የተዘፈቀበትን ዕዳውን በርስዎ ርዳታ መ
ፈሉ ትዝ አይልዎትም ? " አለ ኸርማን ።

ድንገት የአሮጊቷ ቀዝቃዛ ስሜት ተለዋወጠ ። ለአ
ንድ አፍታ ቦግ ያለው ውስጣዊ ስሜቷ ፣ በውጫዊ ገጽታዋ
ላይ ተከሠተና የሞቀ ሕይወት የዘራች መሰለች ። ግን ፣
ብዙም ሳትቆይ ወደ ቀድሞ ቅዝቃዜዋ ተመለሰች ። የግዴ
ለሽነት መንፈስ ጐልቶ ይታይባት ጀመር ።

ኸርማን ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ከቆየ በኋላ ትዕግሥት
ባጣ ድንፋታ ፣ "እነዚያ አዚመኛ ካርታዎች የትኞቹ እንደ
ሆኑ ትነግሪኛለሽ አትነግሪኝም ? " በማለት ጠየቃት ።

መልስ ግን አላገኘም ።

ወዲያው ወጣቱ ኸርማን አንድ ሽጉጥ ከኪሱ አወ
ጣና ፣ " ሙትተኛ ጠንቋይ ፣ በልመና እምቢ ካልሽ በግድ
ትናገሪያለሽ ! " ሲል አሮጊቷ ላይ አንባረቀ ።

አሮጊቷ ሽጉጡን ስታይ ለሁለተኛ ጊዜ የሠራ አካ
ላቷ በሕይወት ሙቀት የተመላ መሰለና ፣ ወዲያው ጭንቅ
ላቷን ወደ ኋላ አወናጭፋ ፣ ጥይቱን ለመከላከል በሚመስል
ሁኔታ ሁለት እጆቿን ወደፊት ዘረጋቻቸው ። ወዲያው
ደግሞ ሁለቱም እጆቿ ተዝለፍልፈው በግራና ቀኝ በኩል
ቁልቁል ተንጠለጠሉ ። በወንበሩ ላይ የተኰፈሰው አካሏ
እንቅስቃሴ አልባ ጸጥ አለ ።

ምንም ቢያደርግ ምንም መልስ ባለማግኘቱ የተበሳ
ጨው ኸርማን ፣ ጠጋ አለና ክማንገጭታት በማይሻል ሁኔታ
አንዱን ክንዷን ለቀም አድርጎ ማስፈራራቱን ሊቀጥል
ሲል ፣ አሮጊቷ በድን መሆኗን ተመለከተ ። ልብ ብሎ
ሲያስተውል በድንጋጤ መሞቷን ተረዳ ።

## —3—

ይህ ሁሉ በሚከናወንበት ወቅት፣ሊዛቤታ ኢቫኖቭና የዳንስ ልብሷን እንዳጠለቀች በመኝታ ክፍሏ ውስጥ ተቀምጣ ከሐሳቧ ጋር ትሟገታለች ። ከግብዣዉ ሥፍራ ከአሮጊቷ ጋር ከተመለሰችበት ጊዜ አንሥቶ፣በአእምሮዋ ብዙ ነገሮችም አውጥታ አውርዳለች ። ከግብዣዉ መልስ ወጣቱን መኮንን በመኝታ ክፍሏ ውስጥ እንደምታገኘው ገምታ ነበር ። ግን አላገኘችውም ። ቢሆንም ደግሞ በሁኔታው ቅር አልተሰኘችም ፤ አልተቆጨችም ። እንዲያውም መጠነኛ እፎይታ ተሰምቷታል ።

ይሁን እንጂ ፥ ፍጹም የአእምሮ እፎይታ ማግኘት አልሆነላትም ። ሐሳቧ በሰፊው ይባዝናል ። አእምሮዋ ብዙ ነገሮችን ያውጠነጥናል ። በተለይ በዚያን ምሽት በግብዣው ቦታ ከአሮጊቷ የልጅ ልጅ ከቶምስኪ ጋር ሲደንሱ ያጫወታት ነገር ነበር፣በይበልጥ በአእምሮዋ የሚመላለሰው ።

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣በሊዛና በኸርማን መካከል የተፈጠረውን የሩቅ ግንኙነት ጥሩ አድርጎ የተገነዘበ መሆኑን ቶምስኪ ከገለጠላት በኋላ፣የኸርማንን ልዝብ ጋኔልነት በዘዴ ጠቆም አድርጎታል ። “ ገጹ የናፖሊዮንን ውበት የያዘ ቢሆንም፣ልቡ ግን የሳጥናኤል ነው ” ያለው አነጋገር በአእምሮዋ ውስጥ እየደጋገመ ያስተጋባል ።

ኸርማን ድንቅና ማራኪ ሰው መሆኑ ባያጠያይቅም በሦስት የተለያዩ ወንጀሎች እንደሚታማ ቶምስኪ በምሽቱ ዳንስ ላይ ጨረፍ አድርጐላታል ። ስለ ኸርማን የተነገሩትን እነዚህን ሁኔታዎች ስትሰማ ያሳየችው መደናገጥ ፥ እርሷ ስለ ኸርማን ያላትን ስሜት ቶምስኪ በይበልጥ እንዲረዳው የሚያደርግ መሆኑም ገብቷታል ። የግብዣዉ ቦታ ውይይታቸው ባጋጣሚ ምክንያት ባይቋረጥ ኖሮ ፥ ስለ ኸርማን ሌላም ብዙ እንደምትሰማ ርግጠኛ ነበረች ።



ሊዛ ከግብዣው መልስ በኋላ ፥ በመኝታ ክፍሏ ውስጥ ሆና ከቶምስኪ ጋር ስላደረገችው ውይይትና ስለ ኸርማን ስለ ሰማቻቸው ጉዳዮች ስታንሰላስል ፥ የመኝታ ክፍሏ በር በድንገት ተከፈተ ። ሐሳቧ ተበታትኖ ወደ በሩ ፊቷን ስታዞር ኸርማንን ደጃፍ ላይ ተገትሮ አየችው ። በድንጋጤ ወደ ኋላ አፈገፈገችና በኃይል ትንቀጠቀጥ ጀመር ።

“ የት ነበርክ ? ” ፍርሃት ባፈነው ሹክሹክታ ጠየቀችው ።

“ አሮጊቷ መኝታ ክፍል ውስጥ ነው የቆየሁት . . . . በነገርሽ ላይ አሮጊቷ ሞታለች ። ” ረጋ ያለው የኸርማን መልስ ይህ ነበር ።

“ ሞታለች ! . . . ምንድነው የምታወራው በል ! ” ሊዛ ጮኸች ።

“ ሰበብ የሆንኩባት እኔ ነኝ ” አላት ።

የሊዛ አእምሮ ከመቅጽበት ወደ ብዙ አቅጣጫዎች በማተኮር ፥ የተለያዩ ጉዳዮችን መዳሰስ ጀመረ። በምሽቱ የዳንስ ጨዋታ ላይ ቶምስኪ የነገራት ሁሉ እንደ ቀትር ብርሃን ወለል ብሎ ታያት ። ኸርማን በዝግታ መስኮቱ ጠርዝ ላይ ቁጭ አለና ጠቅላላ ታሪኩን ከሥር ጀምሮ አጫወታት። ወጣቱ መኮንን ሲያወጋ ፥ ውቢቱ ሊዛ የምታዳምጠው በተሸበረ መንፈስና በጥላቻ ስሜት ነበር ።

እነዚያ ሁሉ የፍቅር ደብዳቤዎች ፥ ያ ሁሉ እሷን ለማጥመድ የገባች የወጣችበትን አሽትቶ መከታተል ፥ አላስቆም አላስቀምጥ ብሎ ለመተዋወቅ መማጠን ፥ ዓላማው ለእውነተኛ ፍቅር እንዳልሆነ በግልጽ ተረዳችው ። ኸርማን ከእርሷ ይፈልግ የነበረው ንጹሕ ፍቅር ሳይሆን አምሮቱ ሌላ እንደሆነ ገባት ። የኸርማን ፍላጐት ገንዘብ መሆኑ ተገለጠላት ። ምስኪኗ ሊዛ የተፈለገችው ፥ እሷ እንዳሰበችው

ፍቅር አጋር እንድትሆን ሳይሆን ፣ የኸርማንን የገንዘብ
ፍላጐትና የወንጀል ተግባር ለማሟላት የሚያስችል አገ
ልግሎት እንድታበረክት መሆኑ ተረጋገጠላት ።

ሊዛ ምርር ብላ ማልቀስ ጀመረች ። ኸርማን ጸጥ ብሎ
ያስተውላታል ። ይሁን እንጂ፣የእርሱንም ልብ እንዳች ነገር
ሲያሠቃየው ይሰማዋል ። ሥቃዩን ያስከተለበት የሊዛ እንባ
ወይም ኀዘን አይደለም ። በአሮጊቷ መሞትም ቢሆን ቅን
ጣት ጸጸት አልተሰማውም ። በዚያን ሰዓት የእሱን ልቡና
የሚያብጠለጥለው ፣ ለሕሊናው የሚታየው አንድ ነገር
ብቻ ነበር ። ለዕድሜው ሙሉ የሚያበቃውንና የሚያዝ
ናናውን ሀብት ለማግኘት የሚያስችሉትን ካርታዎች ምስ
ጢር ከአሮጊቷ ሳያገኝ መቅረቱ ነበር ።

“ አውሬ ነህ ! ” ሊዛ እንባዋን ከዐይኖቿ ላይ እያደ
ራረቀች ጮኸችበት ።

“ እመኚኝ ፣ ሊዛቬታ ኢቫኖቭና ። አሮጊቷን ለመግ
ደል ምንም ፍላጐት አልነበረኝም ። ተመልከች ፣ በሽጉጡ
ውስጥ ጥይት እንኳን የለም ” አላት ።

“ ለማንኛውም አሁን ከዚህ ቤት እንዴት ነው የምት
ወጣው ? ” ሊዛ ጥያቄዋን በመጨነቅ አቀረበች ። “ ሌሊቱ
እየነጋ ነው ። ትንሽ ከቆየህ ሰው ያይሃል ። ወደ ምስጢር
መተላለፊያው በር የሚደረሰው በአሮጊቷ የመኝታ ክፍል
አቋርጦ ነው ። እኔ ደግሞ አስከሬኗ በተጋደመበት በኩል
ለማለፍ ምንም ድፍረት የለኝም ” አለችው ።

ኸርማን እንደ ልማዱ ረጋ ብሎ ፣ “ ግድ የለም ፣ አቅጣ
ጫውን ንገሪኝና አንቺን ሳላስቸግር እኔው መንገዱን አገኘ
ዋለሁ ” አላት ።

ሊዛ የስውር መተላለፊያዎቹን አቅጣጫ በዝርዝር
አስረድታ፣ማንም ሳያየው ወደ ዋናው ጉዳና የሚያስወጣ



ውን የምስጢር በር ቁልፍ ሰጠችው ። ወጣቱ መኮንን
የደም ዝውውሩ የተቋረጠበት ይመስል ፣ እንደ በረዶ የቀዘ
ቀዘውን የሊዛን እጅ ጨበጠና ከክፍሉ ወጣ ።

— 4 —

የአሮጊቷ ሞት ፣ በአካባቢዋና በሚያውቋት ሰዎች
ዘንድ እምብዛም መተራመስንና መደናገጥን አልፈጠረም።
በጣም አርጅታ ስለ ነበር ፣ ሞቷ ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ ቆይ
ቷል ።

ቀብሩ ከሦስት ቀናት በኋላ ሲፈጸም፣ ኸርማንም በሥነ
ሥርዓቱ ላይ ለመገኘት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራ ። ከሌ
ሎች ለቀስተኞችና አጃቢዎች ሠልፍ ውስጥ ተቀላቀለና
ክዳኑ በተከፈተ የሬሣ ሣጥን ውስጥ በጀርባው የተንጋ
ለለውን የአሮጊቷን አስከሬን ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰና
በት ተራውን ይጠባበቅ ጀመር ። ተራው ሲደርስ ጠጋ
ብሎ በሣጥኑ አጠገብ ተንበረከከና የአሮጊቷን የገረጣ ገጽ
ይመለከት ጀመር ። ወዲያው ፊቱ ሁሉ ተለዋወጠና መብ
ረቅ የመታው ያህል ክው አለ ። ያጋጠመው ሁኔታ ልዩና
እንግዳ ነገር ነበር ። ኸርማን ተንበርክኮ አስከሬኑን ሲመ
ለከት ፣ ሟቿ አሮጊት በማሾፍ መልክ አንድ ዐይኗን ከፍታ
ጠቀሰችው ። በድንጋጤ የደነበረው ኸርማን ከተንበረከከ
በት ተነሥቶ ሊሔድ ሲል፣አንዱ ደረጃ አደናቀፈውና ወለሉ
ላይ ተዘረረ ። ዙሪያውን የነበሩ ሰዎች አፋፍሰው አነሡት ።
በዚያኑ ቅጽበት ሊዛቬታ ኢቫኖቭናም ሕሊናዋን ስታ በመ
ውደቋ ኀዘንተኞች የወሳንሳ ይዘው ከቤተክርስቲያኑ አወ
ጧት ።

በዚያን ቀን ኸርማን እንደ ቀፈፈው ፣ እንደ ተረበሸ
ዋለ ። የወትሮው ረጋ ያለ ስሜቱና መንፈሱ ሊመለስለት

አልቻለም ። ሰላም ሸሸው ። ለዐይን ያዝ ሲያደርግ ከአንዷት ሰዋራ ሆቴል ገብቶ ራቱን ከቀማመሰ በኋላ አእምሮውን ለማሳረፍ ሲል ቪኖ ሲቀመቅም አመሸ። ወደ ቤቱ ሲመለስ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ነበርና እንዴት እንደ ገባም አልታወቀው ። ብቻ ከነልብሱ በአልጋው ሙሉ ተዘረጋ ።

ደረቅ ሌሊት ላይ ከእንቅልፉ ባንኖ ነቃ ። የጨረቃዋ ብርሃን ወደ መኝታ ክፍሉ በመግባቱ ፤ በውስጡ የሚገኘው ነገር ሁሉ ደብዘዝ ብሎ ይታያል ። አንድ ሰው በመስኮቱ በኩል ለቅጽበት ተመለከተውና እልም ብሎ ጠፋ ። ኸርማን ነገሬም አላለው ። ወዲያው ወደ ቤቱ የሚያስገባው ዋናው በር ሲከፈት ተሰማው ። በመጀመሪያ ፤ አሽከሩ እንደ ልማዱ ሲሰክር ካመሸበት መመለሱ መስሎት ነበር ። በኋላ ወደ ቤቱ ውስጥ የገባውን ሰው አረማመድ ሲያዳምጥ ግን ፤ የሚያውቀውና የለመደው የአሽከሩ ርምጃ አለመሆኑን አረጋገጠ ። የቀላል ነጠላ ጫማ ድምፅ ወደ ጆሮው እየተቃረበ መጣ ።

የመኝታ ክፍሉ በር ተከፈተና ነጭ ልብስ ያጠለቀች ሴት ገባች ። ሴትዮዋ ወደ አልጋው ስትቀርብ ፤ ማን እንደ ሆነች ኸርማን ወዲያው ዐወቀ ። ሟቿ አሮጊት ነበረች ! ኸርማን ክው ብሎ ቀረ ።

“ አንተ ዘንድ የመጣሁት ያለ ፍላጎቴ ነው ” አለችው አሮጊቷ ፤ ፈጠን ባለ አነጋገር ። “ ፍላጎትህን እንዳሟላና ለጥያቄህ መልስ እንድሰጥ በመታዘዜ ብቻ ለመምጣት ተገደድሁ ። ለማወቅ የምትፈልጋቸው ሦስቱ ምትሐታዊ ካርታዎች ሦስት ፤ ሰባት ፤ የከ ናቸው ። በነዚህ ሦስት ካርታዎች በተከታታይ ከተጫወትህ ያላንዳች ጥርጣሬ አሸናፊ ትሆናለህ ። ግን አንድ ሕግ ማክበር አለብህ ። በሐያ አራት ጊዜ ውስጥ የምትጫወተው በአንዱ ካርታ ብቻ ፤ ያውም አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። በዚህ ዐይነት በሦስት ተከ



ታታይ ቀናት በሦስቱ ካርታዎች በየተራ ከተጫወትህ በኋላ ፤ እስከ ሕይወትህ ፍጻሜ ድረስ ካርታ ጨዋታ የሚባል ነገር በዞረበት መዞር አይኖርብህም ። ”

የአሮጊቷ ኤኬራ ( መንፈስ ) ይህን ተናግሮ በመጣበት ተመለሰ ። የውጪው በር ሲዘጋ የሰማው ኸርማን ወደ መስኮቱ ዞር ሲል ፤ ያው የአሮጊቷ ኤኬራ ውልብ ብሎ ሲያልፍ ታየው ። ዞረበት ፤ ተማታበት ።

በመጨረሻ እንደ ምንም ተግተርትሮ ከአልጋው ተነሣና ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍል ሔደ ። በሩ ዝግ ነው ። በስካር እንቅልፍ ድብን ብሎ ከሚያኮርፈው አሽከሩና ከራሱ በቀር አንድም ሰው በቤቱ ውስጥ የለም ። ወደ አልጋው ተመለሰና ሻማውን አብርቶ ሰላየውና ስለ ሰማው ፤ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ መጻፍ ጀመረ ።

## — 5 —

በቁሳዊው ዓለም ውስጥ ሁለት የተለያዩ አካላት አንድን ቦታ በአንድ ጊዜ ለመያዝ እንደማይችሉ ሁሉ ፤ ሁለት የተለያዩ ሐሳቦችም በአንድ ጊዜ በአእምሮአችን ውስጥ ተመሳሳይ ሥፍራ ለመያዝ አይችሉም ። በመሆኑም የወጣቱን መኮንን አእምሮ ሲያስጨንቁ የነበሩት የሟቿ አሮጊት ጉዳይና ሌሎች ሐሳቦች የያዙትን ሥፍራ ለአዲስ ሐሳብ ለቀቁ ። ሦስት ፤ ሰባት ፤ የከ ። እነዚህ ቁጥሮች በኸርማን አእምሮ ነገሡ ። ጧት ፤ ቀን ፤ ማታ ፤ በቁሙ የሚታዩት እነዚህ ቁጥሮች ብቻ ናቸው ። ሌሊት ተኝቶ በሕልሙ ፤ በቅዠቱ የሚፈራረቁበት ሦስት ፤ ሰባትና የከ ብቻ ናቸው ። እንዴ እንደ አበባ ዐይኑ ሥር ይፈነዳሉ ። እንዴ በኅብረ ቀለም አሸብርቀው ፤ በወርቀ ዘቦ አጊጠው ሲንቦገቦጉ

ይታዩታል ። የዚህና የሌላውም ሁሉ ቅዠቱ ማሠሪያና ማጠቃለያ ግን አንድና ዋናው ምኞቱ ነበር ። በነዚህ ቁጥሮች አማካይነት የብዙ ገንዘብ ባለቤት መሆን ። በሦስቱ ቁጥሮች ቁማር ተጫውቶ ማሸነፍ ። መክበር ።

በዚያን ዘመን ፣ በሞስኮ ከተማ የሚገኙ ከፍተኛ ቁማርተኞች እየተሰበሰቡ የሚጫወቱበት አንድ ዝነኛ የቁማር ቤት ባለንብረት የሆነው ቼካሊንስኪ፣ዕድሜውን በመላ የካርታ ቁማር ሲጫወትና ሲያጫውት መኖሩ ይነገርለታል ። ዝናው በድፍን ሩሲያ ወጣቶችና ቁማርተኞች ዘንድ የታወቀ ነበር ።

የአሮጊቷ ሌኬራ ኸርማንን ከጐበኘ በኋላ ፣ ጥቂት ቀናት ቆይቶ ዝነኛው ቼካሊንስኪ ወደ ፒተርስበርግ ይመጣል ። የከተማው ወጣት መዋያና ማደሪያ የቼካሊንስኪ ቤት ሆነ ። በረቺዎቹና በተረቺዎቹ መካከል የሚዘዋወረው ገንዘብ መጠን ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ሔደ ። በእንግዳ ተቀባይነቱ ፣ በሰፊ የቁማር ልምዱ ፣ በደግነቱ ፣ በጥልቅ የቁማር ጥበቡ ፣ በጠባየ ሸጋነቱ የታወቀው ቼካሊንስኪ ፒተርስቡርግ ከመልቀቁ በፊት እንዳያመልጠው በማለት የከተማው ቁማርተኛ ውሎና አዳር በቼካሊንስኪ ቤት ሆነ ።

ቼካሊንስኪ ፒተርስቡርግ ከገባ በሁዋላ ጥቂት ቀናት እንዳለፉ ፣ የካርታ ጨዋታ ሱሰኛ የሆነው ናሩሞቭ ጓደኛውን ኸርማንን ጋብዞ ወደ ወደ ዝነኛው ቁማርተኛ ቤት ወሰደው ። ሁለቱ መኮንኖች ወደ ቁማሩ ቤት ሲደርሱ እያንዳንዱ ክፍል ጢም ብሎ ሞልቷል ። ታላላቅ የመንግሥት ሹማምንት ካርታዎቻቸውን ዐይኖቻቸው ሥር ዘርግተው ይጫወታሉ ። ወጣቶች በየሶፋው ተንጋለው ያጨሳሉ ፤ ይጠጣሉ ። በትልቁ የቁማር አዳራሽ ደግሞ ፣ ሐያ የሚሆኑ ሰዎች በከበቡት የግብር ጠረጴዛ ላይ ዋናው ቁማር



ይቀልጣል ። ባንድ ወገን ካርታ ይበወዛል ፤ በየሰዉ ፊት ይጣላል ። የገንዘብ ዘር በሌላ ወገን ተከምሯል ።

ቼካሊንስኪ ፣ የዚህኛው ቡድን መሪ አጫዋች ነበር ። ዕድሜው ወደ ስድሳ የተጠጋ ግራጫ ጠጉር ያለው የሚከበር ዐይነት ሰው ነው ። ፍም በሚመስለው ፊቱ ላይ ቀልደኛና ተጨዋች የመሆኑ ባሕሪ ጐልቶ ይነበባል ። ዘወትር ብርሃን ከማይለያቸው አንጸባራቂ ዐይኖቹ ዝቅ ብሎ፣የማያቋርጥ ፈገግታ በከንፈሮቹ ዙሪያ ይታያል ። ናሩሞቭ ኸርማንን ከቼካሊንስኪ ጋር አስተዋወቀው ። ዝነኛው ቁማርተኛ፣ሞቅ ባለ መንፈስ የኸርማንን እጅ ጨብጦ፣በቤቱ ውስጥ እንዳሻው ከመሆንና ከመዝናናት እንዳይቆጠብ ካበረታታው በኋላ፣የካርታ ጨዋታውን ወደ መምራቱ ተመለሰ ።

የተጀመረው ጨዋታ ሲያበቃ ፣ ካርታዎቹ ተበወዙና ሌላ አዲስ ዙር ተጀመረ ።

“ እኔም ካርታ እንድስብ ቢፈቀድልኝ ” አለ የመጀመሪያዉን ጨዋታ ሲመለከት የቆየው ኸርማን ፣ በአንድ ወፍራም ቁማርተኛ አዛውንት አናት ላይ እጁን ዘርግቶ ። አጫዋቹ እጅ በመንሣት አዎንታዊ መልስ ሰጠው ።

ለብዙ ጊዜ የጠበቀው ዕለት መድረሱን የተረዳው ኸርማን አንድ ካርታ ለብቻው አይቶ ሳበና ፣ የሚመድበውን ገንዘብ መጠን በመጻፊያው ሰሌዳ ላይ በጠመኔ ጫር ጫር አደረገ ።

“ ይቅርታ ጌታዬ የጻፏቸው ቁጥሮች በደንብ ስላልታዩኝ ፣ የመደቡት ምን ያህል እንደሆነ ቢገልጡልኝ ” አለ አጫዋቹ በትሕትና ።

“ ዐርባ ሰባት ሺህ ሩብልስ ” አለ ኸርማን ፣ በቀዝቃዛ ሁኔታ ። በአዳራሹ ውስጥ የነበሩ ዐይኖች በሙሉ ወደ ርሱ አፈጠጡ ።

“ ይህ ሰው አብዱል መሰለኝ ? ” አለ ጓደኛዉ ናሩሞቭ
ባሳቡ ።

“ ይቅርታ ጌታዬ የመደቡት ገንዘብ በጣም የበዛ
ይመስለኛል ፤ በዚህ አካባቢ በአንድ ጨዋታ ይህን ያህል
ገንዘብ ተመድቦ አያውቅም ” አለ ቼካሊንስኪ ፣ ያን
ዘለዓለማዊ የሚመስል ፈገግታውን እያሳየው ።

“ እና ቢበዛስ ? . . . ዋናው ቁም ነገር በዚህ መደብ
ለመጫወት ትፈልጋላችሁ ፣ አትፈልጉም የሚለው ጥያቄ
ነው ። ” ኸርማን ጥቂት በስጨት ብሎ መለሰ ።

“ነገሩስ ማለፊያ ነው” አለ ቼካሊንስኪ ቀበል አድ
ርጎ ፣ “ ይሁን እንጂ ፣ በዚህ መደብ መጫወት ካስፈለገ
ለሙተማመን እንዲረዳና የኋላ ጭቅጭቅን ለማስወገድ
እንዲያመች ፣ የመደቡን መጠን በጽሑፍ ከመግለጽ ይልቅ
ጥሬውን ገንዘብ ጠረጴዛው ላይ ማድረጉ የሚሻል ይመስ
ለኛል ። ”

ኸርማን ፣ የባንክ ቼክ አወጣና ለቼካሊንስኪ ሰጠው ።
ቼኩን አገላብጦ ከመረመረው በኋላ ፣ ኸርማን በሳበው
ካርታ ላይ አስቀመጠው ። ተስማሙ ።

የመጀመሪያው ካርታ በስተቀኝ በኩል ሲጣል ዘጠኝ
ሆነ ። ሁለተኛው በስተግራ በኩል ሲጣል ሦስት ቁጥር ወጣ ።

“ ሦስት አልባብ ወጥቷል ። ቁጥሩ የኔ ነው ። ” ኸር
ማን የሳበውን ካርታ ሲገለብጠው ሦስት መሆኑ ተረጋ
ገጠ ።

አዳራሹን የሞላው ሰው እንዴ ተተራመሰ ። ሁሉም ያል
ጉመጉም ጀመር ። በድንጋጤ የተመታው ቼካሊንስኪ
ለአንዲት ሰከንድ ያህል ፊቱ የሞት ያህል ተከፋና እንደ
ገና የተለመደ ፈገግታውን ለበሰ ። ያላንዳች ጭቅጭቅ
ዐርባ ሰባት ሺህ ሩብልስ ለኸርማን ቆጥሮ አስረከበው ።



ኸርማን ፣ አንዲት ብርጭቆ የሎሚ ጭማቂ ጠጣና በፍጥ
ነት ከአዳራሹ ወጣ ። በሁኔታው የተደነቀው ጓደኛው ናሩ
ሞቭም በቆመበት ፈዝዞ ቀረ ።

በተከታዩ ዕለት ምሽት ፣ ኸርማን ወደ ቁማሩ ቤት
አመራ ። ጨዋታው ደርቶ ቼካሊንስኪ ያስተናግዳል ፤ ያጫ
ውታል ፤ ይበላል ፤ ያስበላል ። ኸርማን ወደ መጫወቻው
ጠረጴዛ ተጠግቶ ሲቆም ፣ ጠረጴዛውን የከበበው ተጨዋች
በሙሉ መንገድና ቦታ ለቀቀለት ። አስተናጋጁ ቼካሊን
ስኪ ሞቅ ባለ ስሜት ተቀበለው ።

የተጀመረው ጨዋታ አብቅቶ አዲስ ጨዋታ ሲጀ
መር ፣ ኸርማን የሚፈልገውን አንድ ካርታ ሳበና ፣ ዘጠና
አራት ሺህ ሩብልስ በጥሬ ገንዘብ መደበ። ግማሹ የቀድሞ
ንብረቱ ፣ ግማሹ ደግሞ ባለፈው ምሽት ያሸነፈው ተዳምሮ
መሆኑ ነው ።

ቼካሊንስኪ ካርታውን በወዘና አንድ በስተቀኝ ለራሱ
ጣለ ። ሼይባ ወጣ ። አንድ ካርታ በስተግራ ለኸርማን
ሲመታ ሰባት ቁጥር ሆነ ።

ኸርማን ፣ የሳበውን ካርታ ለሁሉም አሳየ ። ሰባት ነው !
አሁንም አሸነፈ ።

በአዳራሹ ውስጥ ያልደነገጠ ፣ ያልተገረመ ፣ ወይም
ሁኔታውን ለራሱ ያልተመኘ አልነበረም ። ቼካሊንስኪ
በሕይወቱ ሙሉ ፣ በተለይም በቁማር ጨዋታ ላይ ከተሠ
ማራበት ጊዜ አንሥቶ ታይቶበት በማያውቅ ሁኔታ ተረ
በሸ ። ነገር ግን ፣ ምንም የሚያደርገው ነገር ስላልነበረው ፣
ዘጠና አራት ሺህ ሩብልስ ቆጥሮ አንዳችም የመደነቅ ምል
ክት ለማይታይበት ለኸርማን አስረከበው ። ወጣቱ መኮ
ንን በአንድ መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ሩብልስ ኪሱን አሳ
ብጦ ወጣ ።

በሚቀጥለው ምሽት፡ ኸርማን እንደ ሁለቱ ቀን ልምዱ
ሰዓቱን ጠብቆ፣ በሕይወቱ ውስጥ የመጨረሻና ወሳኝ ለሚ
ሆነው ጨዋታ በቁማሩ ቤት ተገኘ ። ምድረ ቁማርተኛ
ይሆን " ጉደኛ " የተባለ ሰው አቆብቁቦ ይጠባበቀዋል ።
ባለፉት ሁለት ምሽቶች የተፈጸመውን ልዩ የሆነ የቁማር
ታሪክ ሰምተው ፣ ነገር ግን የዐይን ምስክር ለመሆን ባለ
መብቃታቸው የተቆጩ ሌሎች ሰዎችም ተጨማምረዋል።
ታላላቅ የመንግሥት ሹማምንት የተለመደውን ረጋ ያለ
ጨዋታቸውን ትተው በሰፊው የተወራለትን የኸርማንን
'ያልተለመደ ዐይነት' ጨዋታ ለመመልከት በጠረጴ
ዛው አካባቢ ቆመዋል ። በየጥጋቱ ተበታትነው የነበሩ
ወጣት መኮንኖችም አመቺ ቦታ ይዘዋል ። በቁማሩ ቤት
ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ፣ ወንድ አሳላፊዎች በሙሉ
ሥራቸውን እየጣሉ ተመልካች ሆነዋል ።

ኸርማን ፣ ወደ ትልቁ ጠረጴዛ እንደ ደረሰ ለመጫወት
ዝግጁ መሆኑን ገለጸ ። ፊቱ ያለ ወትሮው ቢገረጣም እን
ኳን ፣ የሞት ሞቱን ፈገግታ ለማሳየት የሚሞክረው ቼካሊ
ንስኪ አዲስ ፓኮ ከፍቶ ያወጣቸውን ካርታዎች በጥንቃ
ቄና በጥበብ በወዛቸው ። ኸርማን ካርታዎቹን ቆረጠና
የሚጫወትበትን አንድ ካርታ ከሳበ በኋላ፣ በቁጥሩ በኩል
ጠረጴዛው ላይ ደፋው ። በላዩ ላይ አንድ መቶ ሰማኒያ ስም
ንት ሺህ ሩብልስ ጫነበት ። የምሽቱ መደብ መሆኑ ነው ።
ኸርማን በዓለም ላይ ያለውን ጠቅላላ ንብረት መደበ። ቼካ
ሊንስኪም ተመጣጣኝ ገንዘብ ሲመድብ ፣ የምሽቱ ጨዋታ
የሚካሔደው በሦስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሩብልስ ላይ
ሆነ ። በዚያን ጊዜ ሁለቱን ሰዎች ለሚያዩዋቸው ሁሉ
ቁማር ለመቆመር ሳይሆን በተኩስ ለመፋለም የተፋጠጡ
መሰሉ ። በቤቱ ውስጥ የመቃብር ዐይነት ጸጥታ ነገሠ ።



ቼካሊንስኪ ፣ በሚንቀጠቀጥ እጅ ጨዋታውን ጀመረ።
የመጀመሪያውን ካርታ በስተቀኝ በኩል ሲጥል 'ንግሥት
ባለ ጦር' ብቅ አለች። ሁለተኛውን ካርታ በስተግራ ሲመታ
'የክ' ወጣ ።

" አልባብ ወጥቶልኛል ! . . የክ ደባላል ! " አለ
ኸርማን ፣ የሳበውን ካርታ ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ለሕ
ዝቡ እያሳየ ።

" አ ! . . . . . ንግሥትህን ገድያታለሁ " አለው
ቼካሊንስኪ ረጋ ባለ አኳኋን ።

ኸርማን ዕጭ ዱብ አለ ። ፊቱን የሞላው ደም ከመ
ቅጽበት ቁልቁል ወርዶ ገጹ ነጭ ሆነ ። ቀስ ብሎ እንዴ
ጠረጴዛው ላይ ያሉትን ካርታዎች ፣ እንዴ ደግሞ በእጁ
የያዘውን ካርታ በየተራ ተመለከታቸው። ዐይኖቹን ለማመን
አልቻለም ። በጨዋታው መጀመሪያ ላይ የሳበው ካርታ
የክ መስሎት ነበር ። አሁን እንደሚያየው ግን ፣ የርሱ ካርታ
'ንግሥት ባለ' ጦርናት።ንግሥት ደግሞ ለቼካሊንስኪ ገብታ
ለች ። በዓለም ላይ ያለ ንብረቱ እንዳለ የቼካሊንስኪ ሆኗል።
በሁለት ቀናት ዕድሜ ከፋኛ በልጽጎ ባጭር ቅጽበት የደ
ኸየው ኸርማን እንዲህ ያለ ጥፋት ፣ ይህን መሳይ ስሕተት
እንዴት ሊፈጽም እንደቻለ አልገባህ አለው ። ተማታበት ።

ናላው ዞር ፣ አእምሮው ተበጥብጦ ፣ በሁኔታው ግራ
ተጋብቶና ድንዝዝ ብሎ የተረታበትን የሴት ሥዕል ያለ
በት ካርታ ትክ ብሎ ሲያስተውል ፣ ድንገት ካርታው ላይ
የተሣለችው ሴት እየሣቀች ስታሾፍበትና ፣ በአንድ ዐይኗ
ስትጠቅሰው ያየ መሰለው ። ከዚህ ቀደም በዐይኗ ጠቅሳ
ያሾፈችበት አሮጊት መልክ ትዝ አለው ። በቤተ መቅደስ
ውስጥ ተጋድሞ የነበረውን የአሮጊቷን አስከሬን ለመ
ሰናበት በተጠጋ ጊዜ ፣ ያጋጠመው ሁኔታ ድቅን አለበት።

በካርታው ላይ ያለው ምስልና ያ ትዝ ያለው መልክ ደግሞ ፍጹም አንድ ሆነው ታዩት ።

"አሮጊቷ !" በማለት በጭንቀትና በፍርሐት በተዋጠ ድምፅ ሳያውቀው ጮኸ ።

ቼካሊንስኪ ያሸነፈውን ሦስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሩብልስ ሰበሰበ ። ኸርማን ያላንዳች እንቅስቃሴ እንደ ዕቃ ተገትሮ ለረጅም ጊዜ ቆየ ። በመጨረሻም ከቤቱ ለመውጣት የቁም በድኑ ርምጃ ሲጀምር ፣ በምሽቱ በታየው ጨዋታ ተደንቀው 'ጉድ' የሚሉት ተመልካቾች መንገዱን በፍጥነት ለቀቁለት ። ወዲያው ካርታዎቹ ለሌላ ዙር ጨዋታ ተበወዙ ። ቁማሩም እንደገና በሰፊው ቀጠለ ።

ወጣቱ ኸርማን፣ በዚሁ ጠንቅ በማበዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ አቡኮቭ ወደ ሚባለው ሆስፒታል ገባ ። ውቢቱ ሊዛም አንድ ወጣት አግብታ የሞቀ ትዳር መሠረተች ። የአሮጊቷ የልጅ ልጅ ቶምስኪም ዕድገት ታይቶለት የሻምበልነት ማዕረግ ተሰጠው ። ኸርማን ግን ፣ በሽታው እየባሰበት በመሔዱ በየዕለቱ በሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ እየተዘዋወረ ከጧት እስከ ማታ ሲለፈልፍ ይውል ጀመር ። እጅግ አስደናቂ በሆነ "ፍጥነት እየደጋገመ "ሦስት.... ሰባት.... የክ... ሦስት.... ሰባት... ንግሥት" እያለ ሲያልጐመጉም ይውላል ። ሰው ሲያናግረውም ሆነ ሲጠይቀው የሚሰጠው መልስ "ሦስት.... ሰባት.... የክ" ፣ "ሦስት... ሰባት.....ንግሥት" የሚል ብቻ ሆነ ።

1833 እ.ኤ.አ 1974 እ.ኢ.አ

---

በያንዳንዱ ታሪክ መጨረሻ ላይ የሠፈሩት ዓመተ ምሕረቶች በስተግራ ያለው ድርሰቱ የተጻፈበት በአውሮፓ አቆጣጠር ፣ በስተቀኝ ያለው ደግሞ የተተረጐመበት ዘመን በኢትዮጵያ አቆጣጠር የሚያመለክቱ ናቸው ።



# ኒኮላይ ጐጐል

(1809—1852)



በ1809 በሩሲያ ፣ ፖልታቫ በተባለው ክፍለ ሀገር ተወለደ ። አባቱ አነስተኛ ባለርስት ነበር ። ኒዥን ወደሚገኘው ጂምናዚየም ገብቶ ትምህርቱን በሚከታተልበት ጊዜ ፣ በተማሪዎች ቲያትሮች ውስጥ በተዋናይነት ከመሳተፉ ሌላ ፣ አንድ መጽሔት ብጤ ለማዘጋጀትም ይሞክክር ነበር ። በ1828 ወደ ቅዱስ ፒተርስቡርግ ከተማ በመሔድ የጸሐፊነት ሥራ አግኝቶ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀጠረ ። በዚያም የሥነ ጽሑፍ ሥራውን ጀመረ ።

ጐጐል ፣ የቅርብ ወዳጁ የነበረውን የታላቁን ባለ ቅኔ የፑሽኪንን የድርሰት ፈለግ ተከትሎ፣ራሱ ከመረጠው ሥልት ጋር በማዋሐድ፣ ምፀታዊና ሐሳዊ ባሕርይ ባላቸው በሳል ድርሰቶች፣ የጥንታዊት ሩሲያን አስከፊ ገጽታዎች በድፍረት ይፋ በማውጣትና፣ የፊውዳላዊውን ሥርዓት ማኅበር ቅራኔዎች በጉልህ በማሳየት ፣ የበኩሉን ድርሻ ተወጥቶ ያለፈ ታላቅ የብዕር ሰው ነበረ ። ከዚህ ባሻገር ለሩሲያ

የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ፡ ጐጐል ያበረከተው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም ።

ማንም ሰው በቀላሉ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ ፡ በረጃጅም ዐረፍተ ነገሮችና በአስቂኝ ዘይቤዎች በመጠቀም ፡ ከጻፋቸው እንደ “ ታራስ ቡልባ ” እና “ ዋናው ተቆጣጣሪ ” ያሉ ድርሰቶች መካከል አንዱ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው ፡ “ ካፖርቱ ” የተባለ አጭር ድርሰት ነው ። ይህ የፈጠራ ሥራ በአያሌ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሕዝቦች ዘንድ በመነበብ ተወዳጅነትን ከማትረፉ ሌላ ፡ በመድረክ ተውኔትነትና በተንቀሳቃሽ ፊልም ተቀናብሮ ለመታየት በቅቷል ። ድርሰቱ በሩሲያ የሥነ ጽሑፍ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ በመሆኑ ፊዮዶር ዶስቶዬቭስኪ ፡ “ ሁላችንም የተገኘነው ከጐጐል ‘ ካፖርት ’ ነው ” የሚለውን አስተያየት መሠንዘር ግድ ሆኖበታል ።

ጐጐል የጽሑፎቹ ኃይለኝነት ባስከተለበት የፖለቲካ ተጽዕኖ የተነሣ ፡ በራሱ ፈቃድ የትውልድ አገሩን ሩሲያን ለቅቆ በመውጣት ፡ ለዐሥራ ሁለት ዓመታት በስደት በኢጣሊያ አገር ኖሯል ። በዚያም ሳለ እጅግ ዝነኛ ያደረገውን ፡ “ ሙት ነፍሳት ” የተሰኘ ዐቢይ ልቦለዱን ያሳተመ ሲሆን ፡ በለጠቁት ዐሥር ዓመታት የዚህን ልቦለድ ተከታይ ክፍል ለማዘጋጀት ጥረት ሲያደርግ ኖሯል ። ይሁን እንጂ ፡ ከመሞቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ የድርሰቱን ረቂቅ በእሳት ስላቃጠለው ፡ ሁለተኛው ክፍል ለኅትመት ሳይበቃ ቀረ ። ጐጐል በየካቲት ወር 1852 ዐረፈ ።



# ካ ፖ ር ቱ

የመሥሪያ ቤቱን መጠሪያ ስም ባልገልጽ እወዳለሁ። ብቻ በደፈናው ‘እንትን’ የሚባለው መሥሪያ ቤት እያልኩ እጠራዋለሁ ። መቼም እንደ መንግሥት መሥሪያ ቤት ፡ የጦር ክፍል፡የመንግሥት ድርጅት … ብቻ በአጠቃላይ እንደ መንግሥታዊ ተቋም ለቁጣ የሚፈጥን የለም ። በተለይም ዛሬ ፡ እያንዳንዱ ግለሰብ በተነካ ቁጥር ኅብረተሰቡም እብሮት የተነካ እየመሰለው ሔዷል ። ለምሳሌ ያህል ከጥቂት ጊዜ በፊት ስለተፈጸመ አንድ ጉዳይ በቅርቡ የሰማሁት ትዝ ይለኛል ። ለጊዜው ስሙን በማላስታውሰው አንድ ከተማ ውስጥ የሚኖር የፖሊስ ሻምበል ለበላዮቹ አቤቱታ ያቀርባል ። ሻምበሉ በአቤቱታው ላይ የጠቀሰው ጉዳይ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችና ተቋሞች በከፍተኛ አደጋ ላይ የሚገኙ መሆኑን የሚገልጽ ነበር ። እናም ለማስረጃ እንዲሆን በማለት ከአቤቱታው ጋር የፍቅር ታሪክ ያዘለ አንድ ሰፊ ጽሑፍ አቅርቦ ነበር ። በዚህ ጽሑፉም ውስጥ ደካማ ባሕርይ ስላለው አንድ ሰካራም የፖሊስ ሻምበል ፡ ከዐሥሩ ገጽ በአንደኛው ላይ ይጠቅሳል ። ይሁን እንጂ ፡ በእኔ በኩል አንዳንድ ደስ የማይሉ ሁኔታዎችን ላለማንሣት ስል በዚህ ታሪክ ውስጥ የሚቀርበውን መሥሪያ ቤት መጠሪያ ስም ሳልጠቅስ ማለፉን መርጫለሁ ።

እናም ታዲያ ፡ በዚህ ስሙን በማልጠራው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ፡ በጸሐፊነት ተቀጥሮ የሚሠራ አንድ ሰው ነበር ። የሚደነቅ ግሩም ተብሎ የሚነገርለት

ዐይነት ሰው አልነበረም ። ከቁመቱ ማጠር ሌላ ፊንጣጣ እንደ በላው ሁሉ ፊቱን ጠቃጠቆ አልብሶታል ። ዐይኖቹ እንደ መቦዝና መፍዘዝ ያሉ ናቸው ። ግማሽ ጭንቅላቱ ድረስ ከገባው መላጣው የተረፈው ጠጉሩ ቀለም ፥ ወደ ቀይ ነት ያደላል ። ጉንጮቹ ጨምደድ ጨምደድ ብለው ፥ የፊቱ ቀለም አብዛኛውን ጊዜ የኪንታሮት በሽታ በያዛቸው ሰዎች ላይ እንደሚታየው ያለ ነው ።

እንዲህ ያለው የመልክ ቀለም ፥ ከቅዱስ ፒተርስቡርግ ከተማ የአየር ጠባይ የሚመጣ በመሆኑ ምንም ማድረግ አይቻልም ። ይህ ሰው በሚሠራበት መሥሪያ ቤት ያለው ደረጃ ( መቼም በእኛ የሥራ ደረጃን ከሁሉ አስቀድሞ መጥቀስ የተለመደ ነው ። ) ዝንተ ዓለም የማይሻሻል ፥ የይስሙላ ፥ 'አማካሪ' እየተባለ የሚጠራው ነው ። ሁላችንም እንደምናውቀው ፥ ይህ የሥራ መደብ ራሳቸውን ለመከላከል በማይችሉት ላይ ፥ ውርጅብኝ ማውረድን ከልክ በላይ ልማድ ያደረጉ የተለያዩ ደራሲያን ፥ ለራሳቸው ርካታና ደስታ ሲሉ አዘውትረው የሚሣለቁበትና የሚያፌዙበት ነው ።

በዚህ ታሪክ ውስጥ የማስተዋውቃችሁ ሰው የቤተ ሰብ መጠሪያ ስም፥ ባሽማችኪን ይባላል ። የስያሜው ትር ጉም በቁሙ ሲታይ ፥ " ባሽማክ " ከሚለው የቦት ጫማ መጠሪያ የተወሰደ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም። ከጫማ ጋር የተዛመደው ይህ ስም ፥ መቼና በምን ሁኔታ ሳቢያ እንደ ተሰጠው ግን እቅጩን ለመናገር አይቻልም ። ከረጅም ጊዜ አንሥቶ አባቱ ፥ ቅድመ አያቱና አማቾቹ እንኳን ሳይ ቀሩ ፥ ብቻ በደፈናው የባሽማችኪን ቤተሰብ አባል የሆነ ሁሉ ቦት ጫማ ማድረግ ያዘወትሩ እንደ ነበር ይነገራል ። ጫማው ሲያረጅ ሶሉን እያስቀየሩ ይገለገሉበታል ። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለት ሦስቴም ቢሆን ሶሉን ያስ ለውጣሉ እንጂ ፥ አረጀ ብለው አይጥሉትም ነበር ይባላል።



ታዲያ ፥ የዚህ የምንተርክለት የቢሮ ጸሐፊ የቤተሰብ መጠሪያ ባሽማችኪን ይሁን እንጂ ፥ እርሱ ግን የሚታወቀው አካኪይ አካኪየቪች በሚል ስም ነበር ። ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚሰማው አንባቢ ይህ ስም እንግዳ ሊሆንበት ወይም ከሩቅ ሥፍራና ከጥንት ዘመን የተገኘ ሊመስለው ይችላል ፤ ግን ጉዳዩ በጭራሽ እንዲህ አለመሆኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ ። ለዚህ ሰው አካኪይ አካኪየቪች የሚለው ስም በወጣለት ጊዜ ቤተሰቡን የተለየ ሁኔታዎች አጋጥሞአቸው ስለነበር ፥ ከዚህ የተሻለ ስም ለመስጠት ምንም ምርጫ አልነበረም ።

አካኪይ አካኪየቪች የካቲት ወር በገባ በኻያ ሦስተኛው ቀን ደንገዝገዝ ሲል ተወለደ ። የተሳሳትኩ አይመስለኝም ፤ አባቱ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ የሚያገለግል ጸሐፊ ነበር ። በመልካም ምግባሯ ምስጉን የነበረችው የሕፃኑ እናት በደንቡ መሠረት ጊዜው እየተቃረበ ሲሔድ ፥ ልጅዋን ክርስትና ለማስነሣት ትዘገጃጅ ጀመር ።

የዕለቱ ዕለት እናትየዋ ፊቷን ወደ በሩ አዙራ ተኝታለች ። በመማክርት ሸንጎ ውስጥ ከሚሠሩት ከፍተኛ ጸሐፊዎች መካከል አንዱ የሆነውና ፥ በሚያውቁት ሁሉ ዘንድ መልካም ስም ያለው፥ኢይቫን ኢይቫኖቭች የሮሽኪን የሕፃኑ ክርስትና አባት እንዲሆን በመመረጡ ከናትየዋ በስተቀኝ ቆሟል ። ከጐኑ ደግሞ በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይገኙ ችሎታዎችና ተሰጥኦዎች እንዳሏት የሚነገርላት አሪና ሴሚዮኖቭና ባይሎብሩይሽኮቭ የክርስትና እናት እንድትሆን የሕፃኑ ወላጆች ያቀረቡላትን ጥያቄ አክብራ ተገኝታለች ። አሪና ሴሚዮኖቭና የአንድ የፖሊስ መኮንን ሚስት ናት ። በባህሉ መሠረት ስም የማውጣቱ ሥነ ሥርዓት ተጀመረና ልጅ በመውለዱ ለተደሰተችው እናት

በርካታ ስሞች ለምርጫ ቀረቡላት ። ሞኪ ፣ ሶሲ ፣ የሚባሉና የሰማዕቱ የሆዝዳዛት ስም ሳይቀር ተጠራ ። የሕፃኑ እናት ግን ፣ “ አይሆንም ። ሁሉም የማይረቡ ፣ ተራ ዐይነት ስሞች ናቸው ” በማለት ተቃወመች ። ፍላጐቷን ለማርካት ሲሉ ፣ ለክርስትናው የተሰበሰቡት ሰዎች የስም ዝርዝር የያዘ አንድ መዝገብ ብጤ ገልጠው የተለያዩ ስሞችን ይጠሩላት ጀመር ። ትሪፊሊ ፣ ዱላ ፣ ቫራሃሲይ . . . ሌሎችም ተደረደሩላት ። ይሁን እንጂ ፣ እንዱም የሚጥማት አልሆነም ። ስሞች በቅደም ተከተል በተጠሩ ቁጥር ፣ “ እንዴት ያለ ጣጣ ነው እባካችሁ ! ምን ምን ዐይነቶቹን ስሞች ነው የምትመርጡት ። አንዱ ከሌላዉ የባሰበት ” እያለች መነጫነጭ ብቻ ሆነ ። ሰዎቹ ከመዝገቡ ውስጥ ሌላ ገጽ ገለጡ ። ፓብሲካሂይ ፣ ቫፀቲሲይ የሚሉ ስሞች ተጠቆሙ ። ለእናትየዋ ግን አንዱም ሊያረካት አልቻለም ። በመጨረሻው “ በቃ ተውት ! ነገሩ ገብቶኛል ። የዐርባ ቀን ዕድሉ ቢሆን ነው ። ስለዚህ ሁሉም ይቅርና አካኪይ በሚለው የአባቱ ስም ቢጠራ ይሻላል ” በማለት የእናትነት ውሳኔዋን አሳለፈች ። በንዲህ ያለ ሁኔታ አካኪይ አካኪየቪች የሚለው መጠሪያ ለሕፃኑ ተሰጥቶት ክርስትና ተነሣ ።

ሃይማኖቱ የሚፈቅደው ሥርዓት ሲፈጸም አካኪይ ሞርር ፣ እርር ብሎ ማልቀስ ጀመረ ። ለአካለ መጠን አድርሶ ሥራ ሲይዝ ፣ ከተራ ጸሐፊነት እንደማያልፍ ትንቢት የታየው ይመስል ትንሿን ፊቱን ክፉኛ እያጨማደደ ሲንቆጫቆጭ ቆየ ። ጠቅላላው ጉዳይም በዚህ ሁኔታ ተከናውኖ ተፈጸመ ። እኛም የስም አወጣጡን በሚመለከት በዝርዝር ለመግለጽ የሞከርነው ያለ ምክንያት አይደለም ። በዚያን ወቅት ፣ ለሕፃኑ አካኪይ አካኪየቪች የሚለውን ስም ከመስጠት ሌላ አማራጭ እንዳልነበረና ፣ በውዴታ ሳይሆን



በግዴታ የተሰጠው መሆኑን ለአንባቢ ግልጽ ለማድረግ ያህል ነው ።

አካኪይ አካኪየቪች በዚያ መሥሪያ ቤት መቼና በማን አማካይነት እንደ ተቀጠረ ፣ ይግሞም ለስንት ዓመታት በአገልግሎት ላይ እንደ ቆየ ‘ዐውቃለሁ’ የሚልና ደፍሮ ለመናገር የሚቃጣ አንድም ሰው አይገኝም ። እርሱ ሥራ ከጀመረ በኋላ ፣ ብዙ ሥራ አስኪያጆችና ከፍተኛ ሹማምንት በዚያ መሥሪያ ቤት ተቀያይረዋል ። አካኪይ አካኪየቪቹ ግን ፣ በመጀመሪያ ዕለት ከተቀመጠበት ሥፍራ ሳይቀየር እያሌ ዓመታት ማለፉን ‘አሌ’ የሚለው የለም ። ደረጃው ቅንጣት ያህል ሳይሻሻል ፣ ከተቀጠረበት ቀን እንሥቶ የተመደበበትን የጽሑፍ ገልባጭነት ተግባር ሲያከናውን ነው የኖረው ። እንዲያውም “ አካኪይ አካኪየቪች እስከነፀራው ቀለም ገልባጭ፣ከራኒ ሆኖ የተወለደ ፍጡር ነው” የሚል አነጋገር በመሥሪያ ቤቱ አካባቢ የሚሰማውም በዚሁ የተነሣ ሊሆን ይችላል ። በመሥሪያ ቤቱ አካኪይ አካኪየቪችን የሚያከብረው ለዐመል ያህል አይገኝም ። ተላላኪዎቹ እንኳን፣ወደ ቢሮ በሚገባበት ጊዜ በአክብሮት ከተቀመጡበት ብድግ ብለው ሊያሳልፉት ይቅርና፣ዝንብ በመተሳለፊያው እንደ በረረ ያህል አድርገው በመቁጠር አይጨነቁለትም ነበር ። የአለቆቹም አስተያየት የንቀት በመሆኑ ፣ ትእዛዞችን የሚሰጡት በኩራትና በቀዘቀዘ መንፈስ ነበር ። ምክትል ዐቃቤ ጸሐፊው እንኳን ያቅሙን ያህል ይዘባነንበታል ። አንድ የሆነ ሥራ እንዲያከናውን ሲያዘው ጊዜ ፣ “ ይህን ጽሑፍ ብትገለብጠው ” በማለት ፋንታ፣ወይም መልካም ሥነ ምግባር በሚታይባቸው መሥሪያ ቤቶች እንደሚደረገው ፣ “ የምትወደውና ደስ የሚያሰኝህ ዐይነት ትንሽ ሥራ ይገኘልህ መጥቻለሁ ” ከማለት ይልቅ ፣ ወረቀቶቹን አፍንጫው ላይ ወርውሮለት ይሔ

ዳል ። አካኪይ አካኪየቪች ግን ፡ ወረቀቱን የወረወረለት
ወይም ትእዛዙን የሰጠው ሰው ማን እንደሆነ ለመመልከት
መብት እንደ ሌለው ሁሉ ፡ ካቀረቀረበት ቀና ሳይል ያላን
ዳች ቅሬታ ወረቀቱን አንሥቶ በጥሞና ያስተውለዋል ።
ወዲያው በሌላ ወረቀት ላይ መገልበጡን ይቀጥላል ።

በአካኪይ አካኪየቪች ላይ የሚደርሰው በደል ይህ
ብቻ አልነበረም ። አብረውት የሚሠሩ ወጣት ጸሐፊዎች፥
ከጧት እስከ ማታ ሲያፌዙበትና ሲያላግጡበት ይውላሉ።
ያችን ትንሽ አእምሮዋቸውን እየጨመቁ፥ ጠቅላላ ሁኔታ
ውን የሚመለከት ቀልድ እየፈጠሩ ይሣለቁበታል ። በአ
ድራጐታቸው የሚጸጸት ሕሊና ስላልነበራቸው ፡ የሚያፌ
ዙበትና የሚቀልዱበት ዞር ብለው ወይም ከበስተጀርባው
ሳይሆን እያያቸውና እየሰማቸው ነው ። ቀልዶችን በየቀን
ከመፍጠር አይቦዝኑም ። የሚኖርበትን ቤት ያከራዩት
የሰባ ዓመት ባልቴት ይደበድቡታል ፤ ሚስት የሚያገባበትን
ቀን እንዲነግራቸው ጧት ማታ ይነዘንዙታል ፤ አንዳንዴ
ደግሞ የወረቀት ቁርጥራጮችን በአናቱ ላይ እየነሰነሱ
በረዶ ነው በማለት እንደ ልጅ ያሾፉበታል ። ልዩ ልዩ ቀል
ዶችን እየተቀባበሉ ያውካኩበታል ። የነዚያ መገለጢጥ
ጸሐፊዎች ንቀት ወደር አልነበረውም ። አካኪይ አካኪየ
ቪች ግን ፡ በየጊዜው ለሚወርድበት ስድብ አንዳችም መልስ
ሳይሰጥ ምንም ነገር ያልተፈጸመበት ይመስል ፡ ሥራውን
በጸጥታና በትዕግሥት ያከናውናል ። ለዚያ ሁሉ የወጣ
ቶቹ ፌዝና ቧልት እምብዛም ቁብ ስላልነበረው ፡ ሙሉ ትኩ
ረቱን በሥራው ላይ አድርጎ ይጭራል ። ለዚህም ነው
በጽሑፍ ውስጥ ቅንጣት ስሕተት ፈጽሞ የማያውቀው ።
ዐልፎ ዐልፎ ግን፡ፌዙ ሲበዛበትና ቅጥ አጥቶ ሲንዛዛ ወይም
የወጣቶቹ ጋጠ ወጥ ድርጊት መረን ተለቆ በመሔድ እጁን
እየጐነተሉ ሥራውን አላሠራ ማለት ሲጀምሩ ፡ ልዩ በሆነ



ድምፅና ልቦናን በኀዘን ጠቅ በሚያደርግ አነጋገር ፡ "አባ
ካችሁን ተውኝ ! ለምን እንደዚህ ትሰድቡኛላችሁ ? "
በማለት ምሬቱን ይገልጻል ።

አንድ ጊዜ ፡ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ አዲስ የተቀጠረ
ወጣት ሠራተኛ፥ የጓደኞቹን አድራጐት በመከተል የበኩ
ሉን ፌዝ ሲሰነዝርበት ፡ አካኪይ አካኪየቪች ምርር ያለ ብስ
ጭቱን ይገልጻል ። አዲሱ ተቀጣሪ አስነዋሪ ነገር መፈ
ጸሙ ተሰማው ። ሕሊናው ክፉኛ ስለ ተነካ ፡ ከዚያን ቀን
በኋላ ሁኔታውን ይለውጣል ። ሁሉም ነገር ለየት ባለ መልክ
ሊታየው ይጀምራል ። አንድ ያልታወቀ ኢሰብአዊ ኃይል
ያስገደደው ይመስል ፡ አዲሱ ቅጥር እያደር መልካም አስተ
ዳደግ ያላቸውና የሠለጠኑ ከሚመስሉት ከቸሮ ጓደኞቹ
መራቅ ጀመረ ። በጣም ሞቅ ባለ ፌንጠዝያና ደስታ ላይ በሚ
ገኙባቸው ወቅቶች የዚያ ትሑትና ጠጉረ መላጣ ፡ ኲሳሳ
ጸሐፊ ቁመና ከፊቱ ድቅን እያለ እነዚያ የሚያሳዝኑ ንግ
ግሮቹ በዕዝነ ሕሊናው ያስተጋባሉ ። " እባካችሁ ተዉኝ
ለምን ትሰድቡኛላችሁ ? " የሚሉት ቃላት ደጋግመው ይጪ
ጩሁበታል ። ወይም አካኪይ አካኪየቪች አንዳንዴ የሚሰነ
ዝረው ፡ " እኔም እኮ ወንድማችሁ ነኝ " የሚል አንጀት
የሚበላ ንግግሩ ጐልቶ ይታወሰዋል ። ታዲያ እንዲህ ያለው
ሁኔታ በሚያጋጥመው ጊዜ ፡ ወጣቱ ሠራተኛ ፊቱን በእ
ጆቹ ይሸፍንና የሠራ አካላቱ ሲንዘፈዘፍ ይሰማዋል ። በሰው
ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ እጅግ የከፋ ኢሰብአዊ ባሕሪ ምን
ያህል ገንኖ እንደሚኖር ገሃድ ይሆንለታል ። በተለይም
ድንቅ በሚባለው መብለጥለጥና ላይ ላዩን ሲታይ ፡ የተገራ
ከሚመስለው ጨዋነት በስተጀርባ ተደብቆ የሚገኘው
የደለበ አረመኔአዊ ጭካኔ ቁልጭ ብሎ ይታየዋል ። ይህም
ብቻ ሳይሆን፥ በሕይወቱም ውስጥ ለብዙ ዘመናት ሁኔታው

ትዝ ባለው ቁጥር አካሉና መንፈሱ ሲርበተበቱበት እየተሰማው ኖሯል ።

አካኪይ አካኪየቪች፣ ትጉህ ብቻ ሳይሆን ሥራውን አክባሪና አፍቃሪም ነበር ። የሚሰጠውን የሥራ ድርሻ በወቅቱ አጠናቆ በማስረከብ በኩል የሚወዳደረው አል ነበረም ። ለሥራው የሚያሳየው ፍቅር ከልብ የመነጨ ነው ። በጣቶቹ መጻፊያውን ጨብጦ በወረቀቱ ላይ በሚያቀረቅርበት ጊዜ፣ ከዚያ ጽሑፍ የመገልበጥ ሥራው ባሻገር ውብና ማራኪ የሆነ ብሩህ ዓለም ጉልቶ ይታየዋል ። ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ፣ ገጹ በተለየ የደስታ ፀዳል ይፈካል ። አንዳንዶቹ ፊደሎች ደግሞ፣ ልዩ የሆነ የልብርካታ ይሰጡታል ። እንደዚህ ያሉትን ፊደሎች በሚከትብበት ሰዓት የሚሆነውን ያሳጣዋል ። እንደ መፈንደቅ፣ እንደ መፈንጠዝ ያሰኘዋል ። አፍና ለብቻው እንደ መሳቅም ይቃጣዋል ። ታዲያ ይህን ሁኔታውን ልብ ብሎ ላጠናና ለተከታተለ ሰው፣ በገጽታው ላይ የሚከሠተውን የስሜት ለውጥ በማየት ብቻ የሚነድፈው የትኛውን ፊደል እንደሆነ በግምት ለማወቅ አይሳነውም ። እንደ ታታሪነቱ፣ እንደ ሥራ ወዳድነቱና ትጉህነቱ ቢሆን ኖሮ፣ የመንግሥት አማካሪ ተብሎ በተሾመና ርሱን ራሱንም ባስደነቀው ነበር ። ይሁን እንጂ፣ ለዚያ ሁሉ ጥረቱና ብርቱ ሠራተኛነቱ ያገኘው ወሮታ ቢኖር፣ 'ከግንባሩ እስከ መሐል አናቱ የዘለቀው መላጣውና ከጭንቅላቱ በስተጀርባ የተከመረ ጠጉሩ ነው' በማለት እነዚያ ሙሉ የሥራ ባልደረቦቹ ያፌዙበታል ።

በእርግጥ ነገሩ ሁሉ እንዲህ ያለ ቢሆንም፣ ሙሉ በሙሉ የበላዮቹን ትኩረት አላገኘም ፤ ወይም ጉብዝናውን አልተረዱለትም ለማለት አይቻልም ። እንዲያውም አንድ ጊዜ በማለፊያ ጠባዩ የተወደደ አንድ ሥራ አስኪያጅ፣ የአካኪይ አካኪየቪችን የረጅም ዘመን ቅን አገልግሎት



በመመልከት፣ ጽሑፍ ከመገልበጥ በተሻለ ደኅና ሥራ ላይ እንዲመደብ ወስኖለት ነበር ። እንደ ዕድገት ተቆጥሮ የተሰጠው ሥራ፣ ለሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሚተላለፉ ያለቀላቸው ሪፖርቶችን አድራሻ ማስተካከልና አንዳንድ ስዋስዋዊ ግድፈቶችን ማስተካከል ነበር ። ይህ ዐይነቱ ሥራ ለአካኪይ አካኪየቪች በጣም ከባድ ሆነበት ። አዲሱን ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ፣ ላብ ክፉኛ ያጥለቀልቀዋል ። በሥራው ጣልቃ ወዙን ከግንባሩ ላይ እየጠረገ፣ 'ያንኑ የለመድኩትን ጽሑፍ የመገልበጥ ሥራ ቢሰጡኝ ይሻለኛል' የሚል ሐሳቡን እየደጋገመ ይሠነዝራል ። በዚህ የተነሣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ወደ ቀድሞ የቀለም ገልባጭነት ሥራው እንዲመለስ ተደረገና በዚያው ተወስኖ ቀረ ። ጽሑፍ ከመገልበጥ ሥራ ሌላ፣ በዓለም ላይ ምንም የተሻለ ሥራ ያለ ለማይመስለው ለአካኪይ አካኪየቪች ግን ትልቅ ደስታ ነበር ።

አካኪይ አካኪየቪች፣ ለአለባበሱ በፍጹም ስለማይጨነቅ፣ የመሥሪያ ቤት የደንብ ልብሱ አረንጓዴ ቀለም እየለቀቀ በመሔዱ የተገጣጠበ ግድግዳ ወይም የዛገ ብረት መስሎ ይታይ ነበር ። ኰሌታዎቹ እያለቁ በተለፉ ቁጥር መጠናቸው እያነሰ ከመሔዱ የተነሣ፣ አጭር አንገቱ ከልክ በላይ ረዝሞና ስግግ ብሎ ፣ የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ዘዋሪ ነጋዴዎች በጭንቅላታቸው ላይ ከሚሸከሙት ቅርጫት ውስጥ ብቅ ብለው፣ አንገታቸውን የሚያወዛውዙ የፈረንሣይ የድመት ግልገሎች መስሎ ይታያል ። በአካኪይ አካኪየቪች ልብስ ላይ አንዳንድ ነገሮች ተለጥፈው ማየት የዘወትር ትርዒት ነው ። የደረቀ ሣር ወይም የክር ብጥስጣሽ አይለየውም ።

በመንገድ ላይ በሚጓዝ ጊዜ፣ የአንዳንድ ቤቶች መስኮት በድንገት ተከፍቶ ቆሻሻና ጥራጊ ሲደፋ፣ ጉንበስ ብሎ

አደጋውን የማምለጥ ልዩ ፍጥነት ነበረው ። ቢሆንም ግን፣
ከሚደፋው ቆሻሻ ውስጥ አንድ ሁለት ነገር ባርኔጣው ላይ
ሳይለጠፍ አያልፍም ። የፍራፍሬ ልጣጭ ወይም ሌላ ዐይ
ነት ጉድፍ በባርኔጣው ተሸክሞ ሳይታወቀው መንዝ ዘወ
ትር የሚያጋጥመው ሁኔታ ነበር ።

እነዚያ ወጣት የሥራ ባልደረቦቹ፣በጉዳና ላይ በሚ
ኀዙበት ወቅት፣በአካባቢያቸው የሚከናወኑ ድርጊቶችንና
አንዳንድ ያልተለመዱ አጋጣሚዎችን ሆነ ብለው የመከ
ተልና የሚያሥቁ ነገሮች ሲያጋጥሟቸውም እየተጠቃ
ቀሱ የመሣለቅ ጠባይ ያላቸውን ያህል ፣ አካኪይ አካኪ
የቪች ግን ፣ ተመሳሳይ ልምድ አልነበረውም ። በየዕለቱ
ከቤት ወደ ቢሮዉ ፣ ከሥራዉ ወደ መኖሪያ ቤቱ በሚመ
ላለስበት ጉዳና ላይ የሚፈጸሙ ክንዋኔዎችን፣በሕይወቱ
ውስጥ አንድም ቀን አስተውሎ አያውቅም ። ዐልፎ ዐልፎ
ያውም ያጋጣሚ ጉዳይ ሆኖበት የሚመለከተው ነገር ቢኖር ፣
በንጹሕ እጁቹ ላይ የተጋደሙ መስመሮችን ብቻ ነው።አካ
ኪይ አካኪየቪች አካባቢውን ፈጽሞ የረሳ ሰው ነው ።
አንዳንዴማ በጽሑፍ መገልበጥ ሥራው ላይ አለመሆኑን
እንኳን የሚገነዘበው፣የጉዳናውን እምብርት ይዞ ወንተፍ
ወንተፍ ሲል፣ድንገት ሳይሰማው ከወደ ኋላው የደረሰ የሠ
ረገላ ፈረስ አፍንጫውን ወደ ጉንጮቹ አስጠግቶ ሲያና
ፋበትና ሲያኮርፍበት ብቻ ነው ።

ከሥራ መልስ ወደ ቤቱ እንደ ደረሰ የሚፈጽመው የመ
ጀመሪያ ተግባር ፣ ወንበሩን ወደ ጠረጴዛው አስጠግቶ በመ
ቀመጥ ሾርባውን በጾጥታ መምጠጥ ነው ። የምግቡን
ጣዕም ለማጣጣም እንኳን አይጨነቅም ። በምግቡ ውስጥ
ዝንብ ቢገባ ወይም አንዳች ነገር ቢቀላቀልበት አካኪይ
አካኪየቪች ደንታ አይኖረውም ። ከፊቱ የቀረበውን ዝም
ብሎ መዋጥ ብቻ ነው ። አካባቢውን ፈጽሞ የረሳ ነበር ።



በመላው ዓለም ላይ የሚያውቀውና የሚጨነቅለት አንደ
ነገር ቢኖር ፣ ጽሑፍ መገልበጥ ብቻ ይመስላል። ሆዱ እየሞላ
መሔዱና መጥገቡ ሲሰማው ፣ ብዙም ጊዜ ሳያጠፋ ከመ
ሥሪያ ቤቱ ተሸክሞ ያመጣቸውን ወረቀቶች ያቀርብና
ጽሑፍ የመገልበጥ ሥራውን ይቀጥላል ። አንዳንዴ ባዶ
እጁን ወደ ቤቱ ከገባ ፣ ቀደም ሲል ከገለበጣቸው ጽሑፎች
አንዱን ያነሣና እንደገና ሲገለብጥ ይቆያል ። ጽሑፍ የመ
ገልበጥ ሥራ ነፍሱ ነው ። በጣም የሚያስደስተው ደግሞ
የጽሑፉ የአጻጻፍ ሥልት መዋብ ሳይሆን ፣ ጽሑፉ የሚላ
ክበት አድራሻ ነው ። ከፍተኛ ግምት ወደሚሰጠው አካ
ባቢ የተጻፈ ደብዳቤ ከሁሉም ይበልጥ ያረካዋል ። ያለም
ንም ጥቅም ለግል ደስታው ሲል ብቻ፣የዚያ ዐይነቱን ጽሑፍ
እየከሸነ በመገልበጥ ጊዜውን ያሳልፋል ።

የቅዱስ ፒተርስቡርግ ሰማይ በጽልመት ተውጦ በከ
ተማው ምሽት ሲሰፍን ፣ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ምርጥ
በሆኑ ምግብ ቤቶች ራታቸውን ይቀማምሳሉ ። እያንዳ
ንዱ ሰው እንደየምርጫውና የኪሱ ዐቅም በፈቀደለት
መጠን ለመዝናናት በየአቅጣጫው ይሰማራል ።
በየመሥሪያ ቤቱ የሚሠሩ ጸሐፊዎች ሁሉ የዕለቱን
ተግባራቸውን ፈጽመው ፣ ቀኑን ሙሉ ሲቧጥጡ ለዋሉ
ብዕሮቻቸውና ለደከመ አካላቸው ዕረፍት ይሰጣሉ ።
የትርፍ ሰዓት ሥራ የሚያከናውኑት እንኳን የሚበቃቸውን
ያህል ከሠሩ በኋላ ፣ እፎይ የሚሉበትን ሥፍራ መርጠው
ወደዚያው ያመራሉ ። ደኅና ደኅና የሥራ ደረጃ ያላቸውም
የምሽት ጊዜያቸውን ማሳለፊያ እንዲሆናቸው አንድም
ወደ ቴአትር ቤቶች ያዘግማሉ ፤ አንድም ደግሞ ፣ በየጉዳ
ናው ሽርሽር እያሉ የቆነጃጅትን ዐይኖች በጥቅሻ ለመ
ሳብ ይሞክራሉ ። አንዳንዶች ከፍቅረኞቻቸው ጋር በመ
ሆን የውዳሴና የመውደድ ቃሎችን ሲደረድሩ ያመሻሉ ።

ብዙ የመንግሥት ሠራተኞች ደግሞ የተለየ የምሽት ልምድ
አላቸው ። በአንዱ ጓደኛቸው ቤት ይሰበሰቡና ኮሾ ብጤ
ብስኩቶችን በሻይ እየማጉ ፤ ፒፓቸውን እየሳቡ ካርታ
በመቀጥቀጥ ሌሊቱን ያጋምሳሉ ። በትልልቅ ሕንፃዎች
ሁለተኛና ሦስተኛ ፎቅ ላይ የሚገኙ ክፍሎችን ተከራ
ይተው የሚኖሩ ደኅና ሥራ ያላቸው ወጣቶች ፤ አብዛኛውን
ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ክፍሎች ከነማዕድ ቤቱ ይኖራ
ቸዋል። የጊዜውን ፋሽን በተከተሉ ማለፊያ ቁሳቁስ ቤታ
ቸውን ለመሙላት ይሞክራሉ ። ነገር ግን የብዙዎቹ ዕቃ
ዎች ዋጋ ከዐቅማቸው በላይ ስለሚሆንባቸው ፤ በተቻለ
መጠን ከዕለት ምግባቸው በመቀነስና ለረጅም ጊዜ ከመ
ዝናኛ ፕሮግራሞቻቸው ተቆጥበው በመቆየት ፤ አስፈላጊ
ውን ገንዘብ አጠራቅመው የፍላጐታቸውን ያሟላሉ ። ጌጠኛ
መብራቶች ፤ ትርኪ ምርኪ ኩተት ይሸምታሉ ። ታዲያ
እንዲያ ባሉ ዕቃዎች በተሞሉ መኖሪያ ቤቶች የሚሰበሰቡ
የመንግሥት ሠራተኞች ፤ አንዳንዴ በካርታ ጨዋታቸው
ጣልቃ ፤ ታላላቅ በሚባሉ ሰዎች አካባቢ ተፈጸመ ተብሎ
ሲወራ የጠለፉትን አስነዋሪ ድርጊት እንሥተው ፤ አንዱ
ከአንዱ አፍ በመቀባበል የነገር አንጀ ሲያመነዥኩ ያመ
ሻሉ ። በአድናቆት የሚወራለት ትኩስ ነገር ሲጠፋ ደግሞ፤
ጊዜው ያለፈበትን አሮጌ ቀልድ እያስታወሱ ፀማውካካት
ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ ።

ሌላዉ ዓለም በመላ እንዲህ እንዲህ እያለ ሲዝናና ፤
ሲደሰት ፤ አካኪይ አካኪየቪች ግን ፤ ከማንም ሁኔታ ጋር
ፀማይገጥም መንገድ ከሥራ ውጭ ያለ ሕይወቱን ይገፋል።
ከተጠቀሱት ፅርባና ቢስ ነገሮች በአንዱም አይካፈ
ልም ። አካኪይ አካኪየቪችን በግብዣና በዳንስ ድግስ
ላይ አየሁት ብሎ ለመናገር የሚደፍር ሰው በከተማው
ሙሉ ይገኛል ማለት ዘበት ነው ። ምሽት በመጣ ቁጥር



አካኪይ አካኪየቪች እንደ ተለመደው ጽሑፍ በመገልበጥ
ራሱን ሲያዝናና ይቆይና ፤ ሲበቃው ወደ መኝታው ሔዶ
ይጋደማል ። ማለዳ ሰዓቱን አክብሮ በሥራ ገበታው ላይ
ከተገኘ በኋላ ፤ የሚገለበጥ ጽሑፍ ሲደርሰው በዐይኑ ሕሊ
ናው ይመለከትና ፈገግ ይላል ። ወር ቆጥሮ የሚያገኘው
አራት መቶ ሩብል በቂ ሆኖትና በዚያው ረክቶ ሰላማዊ
ኑሮ የሚኖረው ፤ የአካኪይ አካኪየቪች ሕይወት እንዲህ
ይሁን ይመስል ነበር ። እርሱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ብዙ
ጊዜ የሚበልጡትንም ጭምር ሊያጋጥም የሚችል አን
ዳች ነገር እስካልመጣ ድረስ ፤ ይህን ዐይነቱ ኑሮው እስከ
እርጅና ዕድሜውም እንደሚዘልቅ የሚያጠራጥር አይመ
ስልም ።

እንደሚታወቀው ሁሉ ፤ በወር አራት መቶ ሩብልና
በዚያው አካባቢ የሆነ ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች
አንድ ኃይለኛ የጋራ ጠላት አላቸው ። ኃይለኛው የአገራችን
የሰሜኑ ብርድ ነው ። ለጤና ይበጃል ሲባል ሰምታችሁ
ይሆናል ። ነገር ግን ፤ ራሱን የቻለ የችግር ምንጭም ነው ።
ጧት ሁለት ሰዓት ሆኖ ፤ ጐዳናዎች ሁሉ ወደ ሥራ
ቸው በሚጣደፉ የየመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ ሲጣበቡ ብር
ዱም አብሮ ዕለታዊ ተግባሩን ይጀምራል ። መከላከያ የሌ
ላቸውን ምስኪን ሠራተኞች ፊት ፤ በተለይም አፍንጫ
አፍንጫቸውን መንደፉን ይቀጥላል ። ብርዱ በሚጨክን
ባቸው ወራት በከፍተኛ የሥራ ደረጃ ላይ የሚገኙና ሞቅ
ያለ ገቢ ያላቸው እንኳን ፤ የፊታቸው ቆዳ ተኰመታትሮ
ዐይኖቻቸው እንባ ያቀራሉ ። ታዲያ እንግዲህ እነርሱን
እንዲህ የሚያደርገው ውርጭ ለምስኪኖቹ ጸሐፊዎች ምን
ያህል ከባድ እንደሚሆንባቸው መገመት አያዳግትም ።
ስለሆነም ከብርዱ ለማምለጥ ያላቸው ምርጫ ፤ የተጐሳቆሉ
ስስ ካፖርቶቻቸውን ደርበው እንደ ጥንግ በመብረር አራ

ትና አምስት ጕዳናዎችን ከአቋረጡ በኋላ፡ወደ ሞቀው ቢሮ
ዎቻቸው ደርሰው አካላቸውን ማፍታታት ብቻ ነው ። ሥራ
ቦታቸው እንደ ደረሱ፣ ወደ ተላላኪዎቹ ክፍል በመግባት
ሰውነታቸውን እያሟሟቁ፣በብርዱ ቀዝቅዞ የረጋ የጸሐፊ
ነት ችሎታቸውን እንደገና በማጋጋል ለዕለቱ ተግባር ራሳ
ቸውን ያዘጋጃሉ ።

የዚህ ዐይነቱ ዕጣ ባለድርሻ የሆነው አካኪይ አካኪ
የቪች፣እያደር የብርዱ ኃይል እየተሰማው መሔድ ጀመረ።
ሠርክ በማለዳ ከቤቱ ተነሥቶ መሥሪያ ቤቱ እስኪደርስ
ድረስ፣የሚያንጠረጥረውን ብርድ በከፍተኛ ፍጥነት እየ
ተውዘገዘገ ለማምለጥ ቢጥርም፣እየዋለና እያደረ በትከሻ
ዎቹና በብራኳው አካባቢ ብርቱ ውጋት ይሰማው ጀመረ።
ለብዙ ዓመታት ሲለብሰው የኖረው ካፖርት ብርዱን በሚ
ገባ ለመከላከል ተስኖት እንደ ሆን በማለት ራሱን መጠ
የቅ የጀመረው ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው ።

አንድ ቀን፣ ወደ ቤቱ እንደ ተመለሰ ካፖርቱን እያገ
ላበጠ በጥንቃቄ ይመለከተው ጀመር ። ሁለትና ሦስት ቦታ
ዎች ላይ፣ በተለይም ትከሻውና ጀርባው አካባቢ ክፉኛ
ነትቧል ። ከፊት ለፊቱ ራቅ አድርጎ በመወጠር ሲያስተ
ውለው፡እንደ ሽክሽክ ጆንያ የሳሳው ካፖርት ብርሃን ማስ
ገባት የጀመረ መሆኑን ተረዳ ። ገበሩም በጥቂት ቀናት
የሚቆጠር ዕድሜውን ለማጠናቀቅ በጣር ላይ የሚገኝ
መሆኑ በግልጽ ታየው። ነገርን ነገር ያነሣዋል ነውና፡እዚህ
ላይ አንድ ጉዳይ ትዝ ይለኛል ። ከአካኪይ አካኪየቪች
ጋር የሚሠሩት ወጣት ጸሐፊዎች ዘውትር ለሚሰነዝ
ሩበት ቀልዶች አንዱ ምክንያት፣ይኸው አሮጌ ካፖርቱ
ነበር ። አንዳንዴ እንዲያውም ካፖርት በማለት ፋንታ
ፒጃማ የሚል ስም ይሰጡት ነበር ። እንደ እውነቱ ከሆነ
ልብ ብሎ ላስተዋለው ፣ የአካኪይ አካኪየቪች ካፖርት



እጅግ ከማርጀቱም በላይ የሚያስደንቅ ነበር ። ኮሌታው
ባለቀ ቁጥር እየታጠፈ በመሰፋቱ ፣ መጠኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ
እየቀነሰ ለምልክት ያህል የሚታይ እጥፋት ብቻ ነበር
የቀረው ። በተደጋጋሚ ከሚደረግለት ጥገና የተነሣ ፣ ካፖ
ርቱ የራሱን ትክክለኛ ቅርጽ ከማጣቱ በላይ ፣ እጃቸውን
ያሳረፉበትን ልብስ ሰፊዎች ጭምር ወደሚያስወቅስ ደረጃ
ደርሶ ነበር ።

አካኪይ አካኪየቪች ካፖርቱን እያገላበጠ አንዴ
ዐይኖቹ ሥር በማስጠጋት ፣ አንዴም ራቅ አድርጎ በማየት
ሁኔታውን በሚገባ ከገመገመ በኋላ በደንብ ለማስጠገን
ወሰነ ። ይህን ሥራ እንዲያከናውንለት የመረጠው ልብስ
ሰፊ፡እርሱ በሚኖርበት ሕንፃ አራተኛ ፎቅ ላይ የሚኖረውን
ፔትሮቪችን ነበር ። የልብስ ሰፊው ፔትሮቪች ፊቱ ሙሉ
ብጤና እንጀራ የሚመስል ጠቃጠቆ ነገር የለበሰ ነው ።
ማናቸውንም ነገር የጐሪጥ የማየት ዐመል ያለው ፔትሮ
ሮቪች፣ደኅና የኃላፊነት ሥራ ያላቸውም ሆኑ ሌሎች ተራ
ደንበኞች የሚያመጡለትን ሱሪዎችና ባለጅራት ኮቶች
በማደስ በኩል ድንቅ ባለሙያ መሆኑ ይነገርለታል ። በተ
ለይ ደግሞ፣ባልሰከረና አእምሮው በሌላ ሐሳብ በማይጠ
መድባቸው ጊዜያት የሚያከናውነው ሥራ ወደር የለውም
ይባላል ።

በጥንት ጊዜ ፔትሮቪች የአንድ ባለርስት ገባር ሆኖ
ሲኖር ሳለ፣የሚጠራው ግሪጐሪይ በሚል ስም ነበር ። ፔት
ሮቪች የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከገባርነት ነጻ ወጥቶ
በየበዓላቱ ቀን እንደ ልብ እየጠጣ መስከር ከጀመረ በኋላ
ነበር።በመጀመሪያ ጊዜ ትልልቆቹን ዐውዳመቶች እየጠበቀ
እንጂ ፣ በአዘቦቱ ሁሉ የመጠጣት ልምድ አልነበረውም ።
የኋላ ኋላ ግን በቀን መቁጠሪያው ላይ ፣ የመስቀል ምልክት
በተደረገባቸው ቀኖች ሁሉ ሳይሰክር ውሎ አያድርም ። ፔት

ሮቪች ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ወደ ቤቱ ሲገባ ሚስቱ የተለ
መደ ጭቅጭቋን ታነሣለች ፡ “ አንቺ መናፍቅ ጀርመን ”
የሚል ስድቡን ያከናንባትና አፏን ያስይዛታል ። በዚህ
አጋጣሚ ስለ ሚስቱ ካነሣሁ ዘንዳ፥ስለ እርሷም ማንነት ለማ
ሳወቅ ያህል አንድ ሁለት ቃላት መወርወር ይኖርብኛል ።
ስለ ማንነቷ እምብዛም የሚታወቅ ነገር አልነበረም፡ብቻ
ከሻሽ ይልቅ ክብ መሳይ የጨርቅ ቆብ አዘውትራ ራሷ
ላይ የምትደፋ መሆኗ ለየት ያደርጋታል ። ውበቷም ተጋና
የሚነገርለትና ሊያኩራራትም የሚችል ዐይነት አልነበረም ።
በመንገድ ላይ ስትሔድ እንኳን ፡ በአጠገቧ ከሚያልፉት
ሰዎች መካከል ከዚያ ክብ ቆቧ ሥር የሚታየውን ፊቷን
ተመልክተው፥ ሪዛቸውን በማነቃነቅ ልዩ ድምፅ የሚያ
ሰሙ ቢኖሩ ፡ በወታደሩ ክፍል ውስጥ የሚሠሩ ዘቦች ብቻ
ነበሩ ።

አካኪይ አካኪየቪች ካፖርቱን የማሳደስ ውሳኔ ከአ
ደረገ በኋላ ፡ ከሕንፃው በስተጓሮ የሚገኘውን ወደ ፔት
ሮቪች መኖሪያ የሚያደርስ ደረጃ ይዞ ወደ ላይ መውጣት
ጀመረ ። ደረጃዎቹ በሙሉ በፈሳሽ ነገር ተበክለው በኃይል
ያዳልጣሉ ። ደግሞ አንድ የሆነ የሚሰነፍጥ ሽታ ከደረጃ
ዎቹ ላይ እየተነነ ፡ አሁንም አሁንም አፍንጫንና ዐይንን
ጠቅ ያደርጋል። በቅዱስ ፒተርስቡርግ ከተማ በሚገኙ ሕንፃ
ዎች ፡ በተለይም በጓሮ ደረጃዎች ላይ ዘወትር የሚያጋ
ጥም ነገር ነው ። አካኪይ አካኪየቪች እያንዳንዱን ደረጃ
በወጣ ቁጥር ልብስ ሰፊው ለካፖርቱ እድሳት የሚጠይቀው
ዋጋ ምን ያህል እንደሚሆን ያሰላስላል ። በመጨረሻ ግን
የሆነው ቢሆን ከአንድ ሩብል የበለጠ ላለመክፈል በሆዱ
ወሰነ ።

የልብስ ሰፊው ሚስት ዓሣ ብጤ በመጠባበስ ላይ ስለ
ነበረች፥እንደ አንድ ነገር የሚግፈጠፈጠው ጢስ ቤቱን አፍ



ኖት ፀረሮና ጢንዚዛ እንኳን አይታይም ። ለጢሱ ሲባል
ፀሩ ተከፍቶ ስለ ነበር ፡ አካኪይ አካኪየቪች ምንም ችግር
ሳይገጥመውና የልብስ ሰፊው ሚስት ሳታየው ሰተት ብሎ
ወደ ውስጥ ገባ ። ፔትሮቪች ቀለም ባልተቀባ ትልቅ
ጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል ። እንደ ቱርክ ፓሻ እግሮቹን
አጥፍጥፍ አድርጎዋል ። ጫማም ሆነ ካልሲ ያላደረገ
ባቸው ባዶ እግሮቹ ብቅ ብለው ይታዩታል ። ከአውራ
ጣቶቹ በአንደኛው ላይ ጥፍረ መጥምጥ እንደ በሳው
የጠጠረ ወይም እንደ ዔሊ ድንጋይ የከረረ ጥፍር አለ ። ለአ
ካኪይ አካኪየቪች እንግዳ ትርዒት አልሆነበትም ። የጥጥና
የሐር ክሮች ቱባ ቱባውን በአንገቱ ዙሪያ አንጠልጥ
ሏል ። የጨርቅ ቁርጥራጮች ደግሞ ጉልበቶቹ ላይ ተደ
ርገዋል ። ለሦስት ደቂቃዎች ያህል በመርፌ ቀዳዳ ክር
ለማስገባት ቢታገልም ፡ ክፍሉ በቂ ብርሃን ስላልነበረው
አልሳካልህ አለው ። መበሳጨትና መነጫነጭ ጀመረ ።
“ ትገባ እንደሁ ግባ ፡ ገሃነም ግባና ! እኔን ለማሳበድ ያህል
አንተም ትበቃለህ ፡ ነጃሣ ! ” እያለ ሲያጉመተምት የሰ
ማው አካኪይ አካኪየቪች፥ ፔትሮቪች በቁጣ ላይ እያለ ፀመ
ምጣቱ ደስ አላለውም ። ፔትሮቪችን ሞቅ ብሎት ቢያ
ገኘው በወደደ ነበር ።

የፔትሮቪች ሚስት በቁጣ እየደነፋች ፡ “ ይሄ አንድ
ፀይና ዲያብሎስ ዛሬ ደግሞ እንደ ልማዱ ጠርሙሱን አንቆ
ነው የዋለው ” ከምትልባቸው ጊዜያት በአንደኛው ቢሆን
ደስ ባለው ነበር ። ፔትሮቪች ከደንበኞቹ ጋር በቀላሉ
ለመግባባትና ለመዋዋልም የሚችለው ከመጠጥ በኋላ
ነው ። በደፈናው ከሰው ጋር መግጠም የሚፈንለት
ሞቅ ሲለው ብቻ ይመስላል ። በሞቅታ ጊዜ ስምምነቱን
ሲገልጥ እንኳን ፡ ለጥ ብሎ እጅ በመንሣትና ልባዊ ምስ
ጋናውን በማቅረብ ነው ። ግን ደግሞ ፡ ፔትሮቪች እንደ

ባለ ስሜት ውስጥ በሚገኝ ጊዜ ፣ ሚስቱ በድንገት ጣልቃ ትገባና ፔትሮቪች በመስከሩ የተነሣ የተስማማበት ዋጋ ርካሽ መሆኑን እየገለጠች መነጫነጭ ትጀምራለች ። ታዲያ የዚህ መድኃኒቱ ዐሥር ኰፔክ ያህል ጭማሪ ለመክፈል ቃል መግባት ነው ። ይህ ከተደረገ ሁሉም ነገር ይቀርና የባልና ሚስትን ስምምነት ለማግኘት ይቻላል ።

አካኪይ አካኪየቪች ካፖርቱን ይዞ በሔደ ጊዜ ፣ ፔትሮቪች አንድም ጠብታ ያልቀመሰ በመሆኑ ፣ ጣራ የሚነካ ዋጋ እንደሚጠይቅ ግልጽ ነበር ። አካኪይ አካኪየቪች ጠቅላላውን ሁኔታ በሚገባ ከአጤነ በኋላ ፣ ጊዜ ሳያባክን ወደ መጣበት ተመልሶ ለመሸምጠጥ ከጅሎት ነበር ። ግን ፔትሮቪች ወደ ክፍሉ ውስጥ እንደገባ አይቶት ስለ ነበር ሐሳቡን ለመፈጸም አልተቻለውም ። ስለዚህ እየተጣደፈ ፣ "ጤና ይስጥልኝ ፔትሮቪች" የሚል ሰላምታውን አቀረበ ። "ይመስገነው እንደ ምን ዋልክ ጌታዬ" አለ ፔትሮቪች ፣ ምን ዐይነት ጨርቅ እንደ መጣለት ለማወቅ ዐይኖቹን አካኪይ አካኪየቪች እጆች ላይ ተክሎ ።

"እ . . እ . . . . . ዛሬ የመጣሁት ይሄን . . . " በማለት አካኪይ አካኪየቪች የመጣበትን ጉዳይ ለመግለጽ ሲል ፣ ብዙ ተውሳከ ግሶችንና መስተዋድዶችን እየደረደረ ትርጉም አልባ ልፍለፋውን ያወርደው ጀመር ። በተለይማ ሁኔታው በጣም አስቸጋሪ ቢሆንበት ኖሮ ፣ የጀመረውን ዐረፍተ ነገር እንኳን አይጨርሰውም ነበር ። አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት " ደኅና . . . . እየህ . . . ነገሩ እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ . . . . " የሚሉ የተቆራረጡ ቃሎችን ብቻ እነብንቦ ፣ ከልቡ ማውጣት የፈለገውን ሁሉ የተናገረ ይመስል በዚያው የማብቃት ዐመል ነበረው ።

" ይሄ ደግሞ ምንድነው ? " አለ ፔትሮቪች ካፖርቱን በመልካም ዐይኖቹ እየቃኘ ። ከኰሌታው አንሥቶ ፣ እጅ



ጌዎቹን ፣ ጀርባውን ፣ የቁልፍ ቀዳዳዎቹንና ሌላውንም የካፖርቱን ክፍል እያገላበጠ ተመለከተ ። ይህ መቼም ልብስ ሰፊዎች ከደንበኞቻቸው ጋር መደራደር ከመጀመራቸው በፊት የሚያደርጉት ልምድ ነው ። " እና እንግዲህ የመጣሁበት ጉዳይ እንዲህ ነው ፔትሮቪች . . . . ይህ የምታየው ጨርቅ . . . የኔ ካፖርት ነው . . . እና እንደምታየው አንዳንድ ቦታዎች ላይ ካልሆነ በቀር ገና ጥሬ ልብስ ነው ። ብቻ ትንሽ አቧራማ ስለ ሆነና ቆሸሽ ስላለ ያረጀ ይመስላል ። ግን እንደ እውነቱ ከሆነ ገና ጥሬ ነው ። እዚች ጋ ፡ ብቻ ትንሽ ፡ . . . አዎ ጀርባው ላይ . . . እና ደግሞ አንደኛው ትከሻ ላይ . . . አዎ ትንሽ እንደ ማለቅ ብሏል ። እና ደግሞ በዚህኛውም ትከሻ በኩል እንደዚሁ ይሄውልህ ፤ እንደምታየው ትንሽ . . . በቃ ይሄው ነው ። ብዙም ሥራ አያስፈልገውም . . . " አለ አካኪይ አካኪየቪች ።

ፔትሮቪች ያን ዝንጥል ጉፍታው ሊወጣ አንድ ሐሙስ የቀረውን ካፖርት ጠረጴዛ ላይ አንጥፎ በጥንቃቄ ይመረምረው ጀመር ። ራሱን ነቀነቀና ወደ መስኮቱ ተንጠራርቶ ከዳኗ ላይ የአንድ ጄኔራል ምስል ያለባት ሙዳይ የምታክል የሱረት ሣጥን አነሣ ። ከሱረቱ አንድ ጊዜ ደኅና አድርጎ ከማገ በኋላ ፣ ካፖርቱን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ በእጆቹ ወጥሮ በመያዝ በመስኮቱ ወደሚገባው ብርሃን አዞሮ ይመለከተው ጀመር ። እንደገና ራሱን ነቀነቀ ። በገበሩ ኩል አዞሮ ተመለከተና በድጋሚ ራሱን ነቀነቀ ። ሙዳይ የምታክለዋን የሱረት ሣጥን አንሥቶ ጥቂት ሱረት አፍንጫው ውስጥ በማኖር ከዳኗን ዘግቶ አስቀመጣት ። በመጨረሻም ፣

"አይቻልም ! ካፖርቱ አልቆለታል ። በምንም ተአምር ለመጠገንና አገልግሎቱ እንዲቀጥል ለማድረግ አይቻልም ። በፍጹም ነትቧል " አለ ።

አካኪይ አካኪየቪች ይህን መሳይ ንግግር ከፔትሮቪች አንደበት ሲሰማ ፥ ልቡ በድንጋጤ ስንጥቅ አለበት ።

“ እንዴት ፔትሮቪች ! እንዴት . . . ለምን ሊታደስ አይችልም ? . . . . ማለቴ . . . ማለቴ ትዳት የደረሰበት ትከሻው ላይ ብቻ ነው ። ለዚህ መጣፊያ የሚሆኑ ጥቂት ቁርጥራጭ ጨርቆች እንደማታጣ መቼም እምናለሁ ” አለ አካኪይ አካኪየቪች ፥ እንደ ሕፃን በመለማመጥና በመማጠን ዐይነት ድምፅ ።

“ ቁርጥራጭ ጨርቆችማ አሉኝ ። ግን ችግሩ ፥ ያ አይደለም ። በዚህ ካፖርትህ ላይ ሌላ ጨርቅ ደርቦ መጣፍ ፈጽሞ ዘበት ነው ። ክፉኛ ስለ ተዘነጣጠለ ፥ አንድ ጊዜ መርፌ ሲነካው ከናካቴው ብትንትኑ ይወጣል ” አለው ልብስ ሰፊው ፔትሮቪች ።

“ ቢበታተንም ምንም አይደለም ። እንደገና ሌላ ጨርቅ ትጥፍበታለህ ።” አካኪይ አካኪየቪች አሁንም መማጠኑን ቀጠለ ።

“ ነገሩ አልገባህም ። የሚጣፈው ጨርቅ ከምን ላይ ሊያርፍ የሚችል ይመስልሃል ? ቀድሞ ነገር የሚጣፈውን ጨርቅ አጥብቆ የሚይዝ ነፍስ ያለው ልብስ አልተረፈም ። ታይቶም ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ነው ካፖርቱን የጨረስከው ። እንደ እኔ ከሆነ ከአሁን በኋላ ልብስ ብሎ ለመጥራትም ያዳግታል ። ከናካቴው ከልብስነት ደረጃ ወጥቷል ። አንድ ቀን ኃይለኛ ንፋስ ቢያጋጥመው ዘጠኝ ቅንንሽ ጨርቅ ነው የሚሆንልህ ” አለ ፔትሮቪች ።

“እኮ ያም ቢሆን እንደ ምንም አድርገህ ብትጠግነው . . . ማለቴ በርግጥ እንትን ሊሆን አይችልም . . . ”

“ ምነው ነገር ቢገባህ ! ከአሁን በኋላ በፍጹም ሊጠገን አይችልም ነው የምልህ ። በኔ በኩል ምንም የማድር



ገው ነገር አይኖረኝም ” አለ ፔትሮቪች ቁርጠኛ [illegible] ላይ የደረሰ መሆኑን በሚያረጋግጥ አነጋገር ። “እ[illegible] ወደ ፊት ከረምቱ ሲገባ በልክ እየቆራረጥ[illegible] መጠቅለያ በማድረግ ብርዱን ብትከላከልበት [illegible] ይመስለኛል ። እርግጠኛ ነኝ ጥሩ ጥሩ ካልሲ [illegible] ። በተረፈ ግን ሌላ መላም የለው ። ደግሞም [illegible] ካፖርቶችን ጥሩ አድርጌ ዐውቃቸዋለሁ ። የጀርመ[illegible] ናቸው ። ብዙ ገንዘብ ከሰዎች ላይ ለመግፈፍ ሲሉ [illegible] ነው እንዲህ መናኛ አድርገው የሚሰፉት [illegible] ። ፔትሮቪች ጀርመኖችን ነካ ለማድረግ የሚ[illegible] ማናቸውንም አጋጣሚ ሁሉ ሳይጠቀምበት [illegible] ንለትም ነበር ። በመጨረሻም ፥ “ እና አሁንም [illegible] አዲስ ካፖርት ማሰፋት ብቻ ነው ” በማለት [illegible] ደመደመ ።

“ አዲስ ” የሚለውን ቃል ፀድጋሚ ሲሰ[illegible] አካኪየቪች እንደገና በድንጋጤ ክችች አለ ። [illegible] ዞረበት ። ክፍሉ ዙሪያውን የሚሽከረከር [illegible] ። ሁሉም ነገር ደበዘዘበት ። ግልጽ ሆኖ የሚታየው [illegible] ሙዳይ በምታክለዋ የፔትሮቪች የሱረት ሣጥን [illegible] የተሣለውና ከአንገቱ በላይ ወረቀት የተለ[illegible] ይታወቀው ጄኔራል ምስል ብቻ ነበር ። “ ግን [illegible] ስትል ምን ማለትህ ነው ? ” አለ ግራ ተጋብቶ ። “ [illegible] አዲስ ካፖርት ለማሰፋት የሚበቃ ገንዘብ የለኝ[illegible] ። ”

“ ይኸው ነው በቃ ! አዲስ ከማሰፋት ሌላ [illegible] አይታየኝም ” አለ ፔትሮቪች ፥ ቀዝቃዛ በሆነ [illegible]

“ ነገሩማ ደኅና ነው ፤ ብቻ . . . ብቻ እንዲ[illegible] ካፖርት ላሰፋ ብል ምን ያህል . . . . ማለቴ [illegible] ቀዋለህ . . . ”

“ ምን ያህል ገንዘብ ይፈጅብኛል ማለትህ ነው? ”

“ አዎ ! ”

“ መቼም ፣ ምኑንም ምኑንም ችሎ አንድ መቶ ሃምሳ ሩብል በቂ ነው ” አለ ፔትሮቪች ከንፈሮቹን እየጨመቀ ። ፔትሮቪች ደንበኞቹን በድንገተኛ የዋጋ ዱብ ዕዳ ማስደንገጥና በዚህም ሳቢያ በደንበኞቹ ገጽ ላይ የሚከሠተውን የስሜት መለዋወጥ በጐሪጥ መመልከት ያስደስተዋል ።

“ለአንድ ካፖርት አንድ መቶ ሃምሳ ሩብል ! ” አለ ምስኪኑ አካኪይ አካኪየቪች በጩኸት ። ዘወትር በለስላሳ ድምፅ ፣ በለሆሳስ የመናገር ልምድ ያለው አካኪይ አካኪየቪች እንደዚያ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲናገር ፣ ምናልባት ያ ቀን በሕይወቱ ውስጥ የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል ።

“ እንዴታ ጌታዬ !! እንዲያውም ከዚያ የበለጠ ሊያስወጣህም ይችላል ። በተለይ ውድ የሆነ የኦውሬ ጠጕር ከገባበትና የሐር ገበር ያለው የዝናብ መከላከያ ቆብ ከተሰፋለት ጠቅላላ ዋጋው እስከ ሁለት መቶ ሩብል ሊደርስም ይችላል ” አለ ፔትሮቪች ።

“ ምነው ፔትሮቪች እሱን ትተህ ለትንሽ ጊዜ እንዲያገለግለኝ አድርገህ እንኳን ይህንኑ ካፖርቴን ብትጠግንልኝ ” አለ አካኪይ አካኪየቪች ፣ የልመና ዐይነት ዜማ ባለው የሚያሳዝን ድምፅ ፣ የፔትሮቪችን ንግግር ሁሉ ላለመስማት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ።

“ በማይሆን ነገር ባታደርቀኝ ምናለ ! ያንተን ካፖርት ለመጠገን መሞከር ጊዜና ገንዘብ ከማባከን ሌላ ፋይዳ የለውም ! ” አለ ፔትሮቪች ።



አካኪይ አካኪየቪች ይህን የመጨረሻ ፍርድ ከሰማ በኋላ፣ መንፈሱ እንክትክት ብሎ ከልብስ ሰፊው መኖሪያ ወጣ ።

ደንበኛው ከቤቱ ከሔደ በኋላ፣ ፔትሮቪች ለረጅም ጊዜ ካለበት ሳይንቀሳቀስ ከንፈሮቹን እየነከሰ ያለሥራ ተቀመጠ ። ለደንበኛው ፍላጐት እጁን ባለመስጠቱና የልብስ ሰፊዎችን ሙያ የሚያስከብር ተግባር በመፈጸሙ በጣም ደስ አለው ።

አካኪይ አካኪየቪች ወደ ዋናው ጐዳና ሲወጣ ፣ ነገሩ ሁሉ ሕልም እንጂ እውነት አልመስልህ እያለው ነበር ። “ አዎ አንድ ነገር አለ ። ደግሞ ሁኔታው ሁሉ እንደዚህ ይሆናል የሚል ሐሳብም አልነበረኝ ” ይል ጀመር ለብቻው ። ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብሎ ቆየና ማነብነቡን ቀጠለ ። “ ግን ምን ያደርጋል ። ያሰብኩት ሳይሆን ያላሰብኩት ሆነ ” አለና እንደገና ለረጅም ጊዜ በብቸኝነት ስሜትና በጸጥታ ተዋጠ ። ቆየ ቆየና ደግሞ “ መቼስ እንዴ ሆኗል ! ... ወይ ! አሁን እስቲ ማን . . . . ምን ዐይነት . . . . ምን ያልታሰበ ነገር ነው ! ” ይህን ተናገረና ወደ ቤቱ በማምራት ፋንታ ፣ ወደ ሌላ አቅጣጫ ጉዞ ቀጠለ ። የሚሔድበትንና የሚያደርገውን ግን ለራሱም አያውቀውም ነበር ። በመንገዱ ላይ ከአንድ ቤት የጢስ መውጫ የሆነ ጥራጊ ነገር እላዩ ላይ ዱብ ብሎ ትከሻውን ጥቀርሻ አለበሰው ። ብዙም ሳይራመድ አዲስ ከሚሠራ ሕንፃ አናት ላይ አንድ አገር ኖራ በላዩ ላይ ተከለበሰበት። ይኼ ሁሉ ሲሆን በጭራሽ አልተሰማውም ። በሐሳብ ባሕር ጭልጥ ብሎ በመስመጡ ፣ አካባቢውን በፍጹም ዘንግቶ ነበር ” ከሐሳቡ የነቃው አንድ ተላላፊ ፖሊስ ከሱረት መያዣው ቀንድ ውስጥ ጥቂት ሱረት መዳፉ ላይ ለማ

ድረግ ብሎ ጦሩን መሬት ላይ ሊያስቀምጥ ሲል በተጋጩ ጊዜ ነበር ። “ ሰውየ እያየህ አትሔድም ! ወይስ መንገዱ አልበቃ አለህ ! ” ብሎ ፖሊሱ ሲያንባርቅ ፡አካኪይ አካኪየቪች ከሐሳቡ ድንገት ባንኖ አካባቢውን ተመለከተና በፍጥነት ወደ ቤቱ መመለስ ጀመረ ።

በጉዞው ላይ የተበታተነ ሐሳቡን ሁሉ በአንድ ሰበሰበና ሁኔታውን ሁሉ በተለየ መልክ ለማስተዋል ሞከረ ። እንደ በፊቱ በመወነባበድ ሳይሆን፡ ከልብ ወዳጅ ጋር በከፍተኛ ጉዳይ ላይ እንደሚወያዩ አድርጎ ፣ በጥሞና ከራሱ ጋር መነጋገር ጀመረ ። “ አዎ ፣ ሊሆን አይችልም ” አለ አካኪይ አካኪየቪች ። “ ከፔትሮቪች ጋር መነታረኩ ምንም ትርጉምና ውጤት አይኖረውም ። እርግጥ ነው ፔትሮቪችን ሚስቱ . . . አለ አይደል . . . ምናልባት ሚስቱ አንድ ደኅና ጡሜ አቅምሳው ይሆናል ። ስለዚህ እሑድ በጠዋት እንደ ገና ወደ ቤቱ እሔዳለሁ።ከቅዳሜ ማታ ስካሩ ሳያገግምና ዐይኑን እንኳን ሳይገልጥ ፣ እንዲያውም በደንብ ለመንቃት ተጨማሪ መጠጥ በሚፈልግበት ጊዜ ከች እል በታለሁ ። በዚያ ሰዓት ሚስቱ አንድም ቁራጭ ሳንቲም ስለማትሰጠው፡እኔ በጕን ዐሥር ኰፔክ ሸጕጥ ሳደርግለት ይሄ ዛሬ የቀባዠረ አእምሮው በትክክል ማገናዘብና ማሰብ ይችላል ። ያን ጊዜ ታዲያ የኔም ካፖርት . . . አለ አይደል . . ” አካኪይ አካኪየቪች እንዲህ እያለ ከራሱ ጋር በመመራመር እንደገና መንፈሱን ማረጋጋትና ዘና ማለት ጀመረ ።

መድረስ አይቀርም ፣ የተባለው እሑድ ደረሰ ። የፔትሮቪች ሚስት ከቤት እስክትወጣለት አካኪይ አካኪየቪች አድፍጦ ይጠባበቅ ጀመር።በመጨረሻ የልብስ ሰፊው ሚስት ለሆነ ጉዳይ እግሯ ወጣ ሲልለት፡ በፍጥነት ወደ ፔትሮቪች ዘንድ ሔደ ። ልክ እንደ ገመተው ፔትሮቪች ከዞረ ድምር ጋር ይታገል ነበር ። ዐይኖቹ በእንቅልፍ እየተስለመለሙ



ጭንቅላቱን ከብድ ብሎት አቀርቅሯል።ይሁን እንጂ [illegible] ከረኛው ካፖርት ጉዳይ ሲነሣ፡ሰይጣን እንደ ለከፈው ድንገት ቱግ ብሎ ፣ “አይቻልም። የመጀመሪያው ሆነ የመጨረሻ አማራጭ አዲስ ካፖርት ማሰፋት ብቻ መሆኑን ነግሬ ለሁ ” አለው ። አካኪይ አካኪየቪች ቀደም ሲል [illegible] ደው መሠረት ዐሥር ኰፔክ ከኪሱ አወጣና እጁ [illegible] አደረገለት ። “ በጣም አመሰግናለሁ ጌታዬ ። በዚች [illegible] ግዴህ ትንሽ ምናምን እገዛና መልካም ጤንነትህን [illegible] ኘሁ መቀምቀም ነው ። የዚያን የካፖርትህን ጉዳይ [illegible] ዳግመኛ እንዳታነሣብኝ ። ማደስ ፣ መጠገን [illegible] ነገር ፋይዳ የለውም ። የሞተ ጉዳይ ነው ። በሐሳብ [illegible] ስማማህ ዕጡብ ድንቅ የሆነ አዲስ ካፖርት በአጭር [illegible] አዘጋጅልሃለሁ ። ”

አካኪይ አካኪየቪች ምንም ሊገባው አልቻለም ። አሮጌ ካፖርቱ እንዲታደስለት ውትወታውን ቀጠለ [illegible] ሮቪች ስልችት ስላለው፡አቀራረቡን ለወጥ አደረገና [illegible] ግዲያስ በምንም ዐይነት ሁኔታ ቢሆን አዲስ ካፖርት [illegible] ፋልሃለሁ ። በኔ ይሁንብህ ። የተቻለኝን ሁሉ አድርጌ [illegible] ካፖርት ሳላለብስህ አልቀርም ። እንዲያውም አሁን [illegible] በመጣው ፋሽን ዐይነት አድርጌ እሰፋልህና ኰሌታው [illegible] ከብር የተሠሩ የካባ መቆለፊያዎችን አስገባበታለሁ [illegible] እያለ ሊያግባባው ሞከረ ።

አካኪይ አካኪየቪች ፣ የፔትሮቪችን ንግግር [illegible] አሮጌ ካፖርቱን የማሳደሱ ጉዳይ ማክተሙ ቁልጭ [illegible] ታየው ። አዲስ ካፖርት ከማሰፋት በስተቀር አንድም አማራጭ እንደ ሌለው ተገነዘበ። በጣም ከፋው ። ተስፋ ቀረጠ። ሐሳብ ገባው ። አዲስ ካፖርት ማሰፋቱስ ባልከፋ ፤ ግን ገንዘቡ ከየት ይመጣል ? በእርግጥ አንድ ተስፋ አለው ። መጪውን ዓመትባል ምክንያት በማድረግ ከደመወዝ ሌላ ለእ

ንዳንዱ ሠራተኛ ጉርሻ ሲሰጥ፡እሱም ጥቂት ሩብል ያገኛል።
ያም ቢሆን ግን፡የጉርሻውን ገንዘብ በሌሎች ጉዳዮች ላይ
ሊያውለው ቀደም ሲል ፕሮግራም አውጥቷል ። ለብዙ
ቀዳዳዎች መድፊኛ እንዲሆነው በየፈርጁ ሸንሽኖ መድቦ
ታል ። አዲስ ሱሪ ማሰፋት አለበት ። ጫማ ሰፊ ደንበ
ኛው የተቀደደ ጫማውን በዱቤ ስለ ሠራለት፡ የዚያን
ዕዳ ይከፍላል።ጥልፍ ወደሚጠልፉት ሴት ዘንድ ብቅ ብሎ
ሦስት ሸሚዞች ለማሰፋት ካሰበ ቆይቷል ። ምን ይሄ ብቻ
ሌላም አለ እንጂ!. . . ብቻ በጽሑፍ መግለጡ ደስ አይልም
ተብሎ ቢገመትም ፡ አንድ ሁለት የውስጥ ልብሶች ያስ
ፈልጉታል ። ባጭሩ ከጉርሻው ውስጥ ለካፖርቱ ማሰፊያ
ይቅርና ለቃብድ የሚሆን እንኳን አይተርፈውም ።

እንዲያው እንዳጋጣሚ ሥራ አስኪያጁ ደስ ብሏቸው
ወይም ቸርነቱን አብዝተውት ፡ ሊሰጠው ከሚገባው ዐርባ
ሩብል ፋንታ ዐርባ አምስት ወይም ሃምሳ ሩብል እንዲከ
ፈለው ቢያደርጉለት እንኳን፡ዞሮ ዞሮ የሚተርፈው ገንዘብ
ከካፖርቱ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በውቅያኖስ ውስጥ ጠብታ
ወይም “ ዶሮ በጋን ” እንደሚሉት ከመሆን አያልፍም ።
ብቻ ፔትሮቪች አንዳንዴ በጣም ከፍተኛና ከሚሠራው
ሥራ ጋር የማይመጣጠን ዛጥ ያለ ዋጋ የመጠየቅ ልምድ
እንዳለው ያውቃል ። እንዲህ በሚያደርግ ጊዜ ሚስቱ እን
ኳን ጣልቃ ትገባና ፡ “ ምነው ጃል ይሄ ሁሉ ! በሌላ ጊዜ
ከነጻ ባልተሻለ ዋጋ እየተዋዋልክ አሁን ግን ራስህ ብት
ሸጥ እንኳን የማታወጣውን ዋጋ መጠየቅ የጤንነት ነው?
ደደብ ! ” ብላ እንደምትወርፈው ቀደም ሲል ደጋግሞ
ሰምቷል ። ስለዚህ በዚያም ብሎ በዚህ፡ፔትሮቪች በዘዴ
ከተያዘ ግፋ ቢል ከሰማኒያ ሩብል ባልበለጠ ዋጋ ሊገላገል
እንደሚችል ርግጠኛ ነው ። ግን ሰማኒያው ሩብልስ ከየት
ይመጣል ? ዋናው ጥያቄ ይህ ነው ። እንዱን ከአንዱ አጣ



ጥቶና ከቅል አቀንድ ብሎ ምናልባት ግማሹን፡አለያም በጣም
ከበረታ ከግማሽ በላይ ትንሽ ነጠቅ ያደረገ ገንዘብ ያገኝ
ይሆናል ። ቀሪው ግማሽ ጉን እንዴት ይሟላል ?. . . .እዚህ
ላይ ወደ ሌላ ጉዳይ ከመዝለቃችን በፊት፡ስለ አካኪይ አካኪ
የቪች አንድ ልዩ ጠባይ ትንሽ መግለጽ የሚገባ ይመስለ
ኛል ። አካኪይ አካኪየቪች ለማናቸውም ጉዳይ በሚያ
ወጣው በእያንዳንዱ ሩብል መጠን ሁለት ኰፔክ የማጠ
ራቀም ልማድ ነበረው ። መቼም ይሁን ለምን፡አንድ ሩብል
ወጪ ሲያደርግ ክዳኗ ላይ የሣንቲም መክተቻ ስንጥቅ ባላት
ሣጥን ውስጥ ሁለት ኰፔክ ይጨምራል ። ከመቶ ሁለት
እንደ ማለት ነው ። በየመንፈቁ ደግሞ በዚህ ዐይነት ሁኔታ
ያጠራቀማቸውን የመዳብ ሣንቲሞች ከሣጥኗ አውጥቶ ከቆ
ጠራቸው በኋላ፡በተመጣጣኝ የብር ሣንቲሞች ይለውጥና
በዚያው ሣጥን ውስጥ ያስቀምጣቸዋል ። ይህ ልምዱ ለብዙ
ዓመታት አብሮት የኖረ በመሆኑ፡አዲስ ካፖርት ለማሰፋት
በወሰነ ጊዜ ዐርባ ሩብል ያህል ተጠራቅሞለት ነበር ። ከሚ
ያስፈልገው ገንዘብ ግማሹ ተገኘ። ቀሪው ግማሽ ግን ከየት
ይመጣል?መልስ ያላገኘው ጥያቄ ይህ ነው ። አካኪይ አካኪ
የቪች አእምሮውን መጭመቅ ያዘ ። ሲያርፍም ሆነ ሲሠራ
ማውጣት ማውረድ ጀመረ ። በውኑም በሕልሙም የሚታ
የው ይኸው ሆነ ። በመጨረሻ የዕለት ወጪውን ለመቀነስ
ወሰነ ። ቢያንስ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ጊዜ የሚያገለግል
የቁጠባ ፕሮግራም አወጣ ።

ከሥራ መልስ የለመደውን አንድ ኩባያ ሻይ ማቆም
አለበት ። ማታ ቤቱ ሲገባ ሻማ ማብራቱን መተው ይኖ
ርበታል ። ምናልባት በምሽት የሚያከናውነው ሥራ ቢኖ
ረው፡ ቤቱን ወደ አከራዩት ባልቴት መኖሪያ ክፍል ሔዶ
በርሳቸው ሻማ ሊጠቀም ይችላል ። ጫማው ቶሎ አልቆ
ወጪ እንዳያስከትል መጠንቀቅ አለበት ። በእግሩ በሚ

ኀዝ ጊዜ በመንገዱ ላይ የድንጋይ ንጣፍ ያለበትን ሥፍራ
ብቻ እየመረጠና ከተቻለም በአውራ ጣቶቹ ብቻ እየ
ረገጠ በዝግታ በመራመድ ጫማውን መቆጠብ ይኖር
በታል ። በተቻለ መጠን ልብሶቹን ቶሎ ቶሎ ማሳጠቡን
ያቆማል ። ስለዚህ ልብሶቹ በፍጥነት እንዳይቆሽሹ ከቢሮ
ተመልሶ ቤቱ እንደ ደረሰ፡ የሥራ ልብሶቹን አውልቆ ከጥጥ
በተሠራው ርካሽና አሮጌ የሌሊት ልብስ ይጠቀማል ።

እውነቱን ለመናገር ከሆነ፡ እነዚህን ገደቦች በሥራ ላይ
ባዋላቸው የመጀመሪያዎቹ ቀናት ራሱን ለማስገዛት አስቸ
ጋሪ ቢሆንበትም፡ ቀስ በቀስ ግን ሕጎቹን እየለመዳቸው ሔደ።
የማታ ራቱን ሳይበላ ጠሙን ማደር ጀመረ ። ስለሚያሰፋው
አዲስ ካፖርት የሚያያቸው ሕልሞች ደግሞ ይበልጥ ማለ
ፊያ ፊት ሆኑለት ። ሚስት ያገባ ይመስል ወይም ከደባል
ጋር መኖር እንደ ጀመረ ሁሉ፡ የብቸኝነት ኑሮው የተሟላ
ሆኖ ታየው። ብቸኛ በመሆን ፋንታ በቀሪው የሕይወቱ መን
ገዱ አብሮት የሚጓዝ አጋር ያገኘ መስሎ ይሰማው ጀመር ።
ይህ በመንፈስ የሚሰማው ጓደኛው፡ ከጠንካራ ገበር ጋር የሚ
ሰፋለት አዲሱ ካፖርት እንጂ፡ ሌላ እከሌ የሚባል ሰው አል
ነበረም ። የኑሮው ትክክለኛ ግብ ምን መሆን እንዳለበት
እንደ ወሰነ ሰው ሕይወቱ እየታደሰ ከመሔዱ ሌላ፡ የተልፈሰ
ፈሰ ባሕርይው እንኳን ጥንካሬ አገኘ ።በፊት ጊዜ በገጹ
ላይና በጠባዩ ውስጥ ይታዩ ከነበሩት የመጠራጠርና የመ
ወላወል ስሜቶች ጨርሶ ነጻ ሆነ ። ለአያሌ ዓመታት ሲመ
ኘው የኖረውን ጠጉራማ ኮሌታ ያለው ካፖርት ከጥቂት
ወራት በኋላ በትከሻው ላይ የሚደርብ መሆኑ በሚታሰበው
ጊዜ፡ ዐይኖቹ በደመቀ ብርሃን ይፈኩና በአእምሮው ውስጥ
የሰከኑ ጠንካራ ሐሳቦች ይመላለሱበታል ።

አዲስ ካፖርት ለማሰፋት ከወሰነ በኋላ ፡ ሐሳብ እየበ
ዛበት እምብዛም ከቀልቡ አልሆን አለ ። አንዳንዴ ሥራውን



እየሠራ እንኳን የካፖርቱ ነገር ትውስ ሲለው ፊደላት
እንደ መሳት ይሞካክረው ጀመር ። ስለ አዲሱ ካፖርት
ያደረበት ጉጉት እጅግ ኃይለኛ በመሆኑ ፡ ቢያንስ በወር
አንድ ጊዜ ወደ ፔትሮቪች መኖሪያ ይሔድና ስለ ካፖርቱ
ሰፊ ውይይት ያደርጋል ። ጨርቁን ከየትኛው ሱቅ ቢገዛ
እንደሚሻል ፡ ምን መሳይ ቀለም ቢመርጥ ተስማሚ እንደ
ሚሆን ፡ ለጨርቁ እስከ ስንት ቢከፍል እንደሚያዋጣው
ይመካከራሉ ። ይህን በሚያደርግባቸው ቀናት በጣም ደስ
ብሎት ወደ ቤቱ ይመለሳል። መንፈሱ ጥቂት እንደ መረበሽ
እያለ ቢያውከውም ፡ ጨርቁን ለመግዛት ገበያ ስለሚወጣ
በት ቀን ሲያስብና ፡ ኮቱ ተዘጋጅቶ ስለሚረከብበት ቀን
ሲያሰላስል ሁለመናው ይረካል ።

ያጋጣሚ ነገር ሆነና ያ ፡ የሚጠብቀው ቀን ከገመተው
ፈጥኖ ደረሰ ። የዓመት በዓል ጉርሻ ሲከፈለው በጣም ተገ
ረመ ። ያሰበው ከነበረው በላይ ተሰጠው ። እንደሱ ግምት
ዐርባ ወይም ዐርባ አምስት ሩብል መሆኑ ቀርቶ ስድሳ
ሩብል ተቀበለ ። የሥራ አስኪያጁ ውሳኔ ነበር ። አካኪይ
አካኪየቪች ለአዲሱ ካፖርት ያለው ጉጉት ለሥራ አስኪ
ያጁ በራዕይ ተከሥቶለት ወይም እንደ ትንቢት ተገልጦ
ለት ፡ አሊያም የዕድል ነገር ሁሉንም አገጣጥሞት ሊሆን
ይችላል ። ብቻ ያም ሆነ ይህ ፡ ነገሩ ሁሉ ከታሰበው ጊዜ
ቀድሞ ተሳካ ። ከማናቸውም ነገር ተገልሎ እንደ ባሕታዊ
በብቸኝነት ኑሮ ውስጥ የከረመው አካኪይ አካኪየቪች
ከሚፈልገው በላይ ሐያ ሩብል ትርፍ አግኝቶ ካፖርቱን
ለማሰፋት ዝግጁ ሆነ ። ልቡ አሁንም አሁንም በኃይል
ይመታ ጀመር ። ገንዘቡ በተዘጋጀ ማግሥት ከፔትሮቪች
ጋር ተያይዘው ለካፖርቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለመግ
ዛዛት ገበያ ወጡ ። ስድስት ወራት ሙሉ ባለማስተንጐል
ወደ ሱቅ ሔደው ጨርቅና ዋጋ ሳያማርጡ ያሳለፉት አን

ድም ወር ስላልነበረ ፡ ጥሩ ዐይነት ጨርቅ ለመግዛት ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም ። ፔትሮቪች እንኳን በምርጫው በጣም በመርካቱ ፡ እግራቸው እስኪነቃ ቢዞሩ ከዚያ የተሻለ ጨርቅ ማግኘት ውሸት መሆኑን ደጋግሞ ገለጠለት ። ለገበር እንዲሆን ከጥጥ የተሠራ ፡ ደስ የሚያሰኝና ለስላሳ፥ ግን ጠንካራ ጨርቅ መረጡ ። ኰሌታው ላይ ለማድረግ አስበውት የነበረው የጠጉር ዐይነት በጣም በመወደዱ በምትኩ የድመት ቆዳ ገዙ ።

አስፈላጊዎቹ ዕቃዎች በሙሉ ከተገዙ በኋላ ፡ ፔትሮቪች ሥራውን ለመጀመር ጊዜ አላባከነም ። ሁለት ሳምንታት ሙሉ ደከመበትና የካፖርቱ ሥራ ተጠናቀቀ ። ከነባቻውን ጠንካራ አድርጐ መስፋት ወይም በገበርና በዋናው ጨርቅ መኻል ተደራርተው የተሰፉ ጨርቆች ማስገባት ባያስፈልግ ፡ ወይም የአዝራርና የቀዳዳው ቁጥር መበርከት ጣጣውን ባያበዛው ኖሮ፥ ሥራው ያን ያህል ጊዜ ባልፈጀም ነበር ።

ፔትሮቪች የእጁን ዋጋ ዐሥራ ሁለት ሩብል ተቀበለ። ከዚያ በታች መቼም የአንዲት ኰፔክ ቅናሽ እንኳን አይታሰብም ነበር ። ጠቅላላው ካፖርት የተሰፋው በሐር ክር በድርብ ስፌት ከመሆኑም ሌላ፥ ፔትሮቪች በጥንቃቄ በነደፋቸው የእጅ ሐረጐች የተዋበም ነበር ። ፔትሮቪች ካፖርቱን አጠናቅቆ ያቀረበበት ቀን ፡ ለአካኪይ አካኪየቪች ምን ዐይነት ትርጉም ያዘለ እንደ ነበር በትክክል ለመግለጽ አይቻልም ። ባጭሩ ያ ዕለት በአካኪይ አካኪየቪች ሕይወት ውስጥ ፈጽሞ የማይዘነጋ ታላቅ የድል ቀን ነበር ቢባል ይቀላል ። ፔትሮቪች ካፖርቱን አዘጋጅቶ ያመጣው በጣም ማልዶ በመሆኑ፥ወደ መሥሪያ ቤት ለብሶ ለመሔድ ጥሩ አጋጣሚ ነበር ። በተለይም የካፖርቱ ሥራ የተጠናቀቀው ዝነኛው የቅዱስ ፒተርስቡርግ ብርድ በጀመረ



በት ጊዜ ስለ ነበረ፥አመቺነቱ ድርብ ሆነ። ማንኛውም መልካም የሚባል ልብስ ሰፊ እንደሚያደርገው ሁሉ፥በዚያ የተለየ ንጋት ፔትሮቪች ራሱ ካፖርቱን ቤቱ ድረስ ሲያመጣለት ፡ አካኪይ አካኪየቪች ከዚያ በፊት አይቶት የማያውቀው ዐይነት የረጋ ስሜት በገጹ ላይ ይነበብ ነበር ። ፔትሮቪች ጊዜያዊ ሳይሆን ታሪካዊና ነዋሪ የሆነ የልብስ ስፌት ተግባር ማከናወኑን የተረዳ ይመስላል ። ገበር ከማስገባትና እርጌ ከመጠገን በማያልፉና በፈጠራ ጥበብ ተጠቅመው አዲስ ልብስ የማዘጋጀት ችሎታ ባላቸው ልብስ ሰፊዎች መካከል ያለውን ጉልህ ልዩነት በተግባር ለማሳየትና ማንነቱን ለማረጋገጥ የበቃ መሆኑን የሚገልጽ ሁኔታ በፔትሮቪች ገጽ ላይ ይነበብ ነበር ።

ፔትሮቪች ካፖርቱን የያዘበትን በንጽሕና ታጥቦ የተዘጋጀ መሐረብ ፡ ለከርሞ እንዲያገለግለው በማለት በጥንቃቄ አጣጥፎ ኪሱ ውስጥ ከተተና ካፖርቱን በሁለት እጆቹ ራቅ አድርጐ በመወጠር በኩራት አስተዋለው ። ወዲያው በቅልጥፍና ቁልፎቹን ከፋፍቶ በአካኪይ አካኪየቪች ትከሻ ላይ ጣል አደረገና በእጆቹ ሳብ ፡ ሳብ ዳበስ ዳበስ በማድረግ እያስተካከለ ከላይ እስከ ታች ተመለከተው። ጸሐፊያችንን አዲሱ ካፖርት ተዋሐደው ። በላዩ ላይ የተሰፋ መሰለ። የአካኪይ አካኪየቪችን ሸክ ማለት የተገነዘበው ፔትሮቪች በአጋጣሚው ተጠቅሞ ትንሽ ጉራ እንደ መንፋት ሞከረው ። መኖሪያው በጉራንጉር አካባቢ በመሆኑና ልብስ ሰፊነቱን የሚገልጽ ጽሑፍ ከቤቱ መግቢያ ላይ ባለመስቀሉ ፡ በይበልጥም ደግሞ አካኪይ አካኪየቪችን ስለሚያውቀው እንጂ በትንሹ ያለፈው ፡ ኔቭስኪ ፕሮስፔክት አካባቢ የሚገኙት ልብስ ሰፊዎች ቢሆኑ፥ለእጅ ብቻ ሰባ አምስት ሩብል ያስከፍሉት እንደነበር እየተኩራራ ተናገረ ። ፔትሮቪች ከናዳ የከበደ የሚያስበረግግ ዋጋ በደን

በኞቹ ላይ እየቀለለ የሚያስከትለውን ጭቅጭቁን እንደገና እንዳያነሣበት የፈራው አካኪይ አካኪየቪች ፣ በዚህ የፔትሮቪች ጉራ ሳቢያ አተካሮና ውይይት ለመክፈት አልፈለገም ። አስፈላጊውን ጉዳይ በፍጥነት ጨራርሶ ልባዊ ምስጋናውን ከገለጸ በኋላ ፣ በአዲሱ ካፖርቱ ተሸትሮ ወደ ሥራው ለመሔድ ተነሣ ።

ከቤት ወጥተው ጎዳናው ላይ ሲለያዩ ፣ ፔትሮቪች ለረጅም ጊዜ ቆሞ ያን ድንቅ ካፖርት ከበስተኋላው ተመለከተው። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ፣ በአቋራጭ መንገድ እያሳበረ በመሮጥ በሌላ ጠርዝ ላይ ቀድሞ ጠበቀውና የእጁ ጥበብ ያፈራውን ያን ካፖርት ከበስተፊት በኩል ይቃኘው ጀመር። አካኪይ አካኪየቪች አንዳንድ ርምጃ በጨመረ ቁጥር ፣ የአዲስ ካፖርት ጌታ መሆኑ ይታወሰውና መንፈሱ ሲታደስ ይሰማዋል ። ሐሳቡ ሁሉ ስለ አዲሱ ካፖርት ብቻ ነው ። የካፖርቱ በደንብ መሰፋትና በቂ ሙቀት የሚሰጥ መሆን ከልብ አስደስቶታል ። ለዚህም ነው በመንገዱ ላይ አንድ ሁለት ጊዜ አፉን አፍኖ ለብቻው እንደ መሣቅ ከጅሎት የነበረው ።

መንገዱን ሳይታወቀው አገባዱ መሥሪያ ቤቱ ሲደርስ ካፖርቱን አወለቀና እያገላበጠ ተመለከተው ። በመጨረሻ በመተላለፊያው ክፍል ውስጥ ለነበረው ተላላኪ ሲያስረክበው በጥንቃቄ እንዲጠብቅለት ከማሳሰብ አልተቆጠበም ።

አካኪይ አካኪየቪች በቀድሞ ዝተት ካፖርቱ ምትክ አዲስ ካፖርት የማሰፋቱ ዜና ፣ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ በሚገኙት ሠራተኞች ዘንድ እንዴት ባንዳፍታ እንደ ተዳረሰ በትክክል የሚያውቅ የለም ። ወሬው እንደ ተሰማ ብቻ ድፍን ሠራተኛ እየተሯሯጠ የአካኪይ አካኪየቪችን አዲስ ካፖርት ለማየት ወደ መተላለፊያው ክፍል ተሰበሰበ ።



ሁሉም እንኳን ደስ ያለህ የሚል ስሜቱን ሲገልጹለት፣ በመጀመሪያ በፈገግታ ቢቀበለውም ቀስ በቀስ ግራ የመጋባትና የማፈር ዐይነት ስሜት ይታይበት ጀመር ። ለማስመረቂያ ያህል ትንሽ ድግስ ብጤ ማዘጋጀት እንዳለበት በመግለጽ ሁሉም ባንድ ቃል ይወተውቱት ገቡ።አካኪይ አካኪየቪች ከዚያ ሁሉ ግርግርና መዋከብ እንዴት እንደሚያመልጥ ጭንቅ አለው ። ቢቸግረው ፊቱ በኃፍረት ቲማቲም መስሎ ካፖርቱ ያው ድሮ የሚያውቁት አሮጌው እንጂ ፣ አዲስ አለመሆኑን በመግለጽ ሊያሳምናቸው ሞከረ ። ፍንክች የሚል ጠፋ ። ግርግሩና ሆያሆዬው ጨርሶ ባሰበት ። በመጨረሻው የዓቃቤ ጸሐፊው ምክትል ጣልቃ ገባና ፣

“ ግዴለም፣ በአካኪይ አካኪየቪች ፋንታ ግብዣውን እኔ አዘጋጃለሁ ። እንደ ዕድልና አጋጣሚ ሆኖ ዛሬ የልደቴን ቀን ስለማከብር፣እዚህ ያላችሁት በሙሉ በዛሬው ምሽት በማደርገው የሻይ ግብዣ ላይ እንድትገኙ ተጠርታችኋል ” በማለት አካኪይ አካኪየቪችን ገላገለው ። ይሁን እንጂ ፣ የዓቃቤ ጸሐፊው ምክትል ይህን ማድረጉ ለአካኪይ አካኪየቪች አዝኖ ሳይሆን ፣ ምናልባትም ትዕቢት ያልወጠረውና ከበታቹ ጋር አብሮ ለመዋል የሚችል ቅን ሰው መሆኑንም ለማሳየት ፈልጎ ሊሆን ይችላል ። ምንም ይሁን ምን ሠራተኞቹ ወደ ዐቃቤ ጸሐፊው ምክትል በመዞር እንኳን አደረሰህ እያሉ ግብዣውን ተቀበሉ ። አካኪይ አካኪየቪች ግን፣ አንዳንድ ምክንያቶችን በመደርደር በግብዣው ላይ ለመገኘት እንደማይችል ለመግለጽ ቢሞክርም፣ ነውር መሆኑን በመግለጽ ሠራተኞቹ በአንድ ድምፅ ያዋክቡት ጀመር። እሱም አንድ የተለየ ስሜት ሲያግባባው ተሰማው ። አዲሱን ካፖርቱን ለብሶ ለማሳየት የሻዩ ግብዣ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥርለት ተገንዝቦ ግብዣውን ተቀበለ ።

ቀኑን ሙሉ አካኪ.ይ አካኪ.የቪች በፈሽታ ላይ እንደ
ሚገኝ ሰው ፍንጥዝጥዝ ብሎ ዋለ ፡፡ የዕለቱ የሥራ ሰዓት
ተገባዶ ወደ ቤቱ ሲመለስ መንፈሱ ረጋ ቢልም ፡ ደስ እን
ዳለው ነበር ፡፡ መኖሪያ ክፍሉ እንደገባ ካፖርቱን አውልቆ
ለልብስ መስቀያ እንዲሆን ግድግዳው ላይ በተሰካ ሜንጦ
ላይ በጥንቃቄ ከአንጠለጠለው በኋላ ፡ ጨርቁንና ገበሩን
በፍቅር ዐይን እያስተዋለ ይዳብሰው ጀመር ፡፡ ያን አንድ
ያውን የለየለትን የቀድሞውን ካፖርት አንሥቶ ከአዲሱ
ጋር ማወዳደር ያዘ ፡፡ የትናየት ፡፡ ሰማይና ምድር ነበሩ ፡፡
በሁለቱ መሐከል ያለውን ታላቅ ልዩነት ሲያይ ድምፁን
ከፍ አድርጎ በሣቅ ይንከተከት ጀመር ፡፡ ራቱን ሲመገብ
እንኳን የአሮጌ ካፖርቱን የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ
ሁኔታ እያሰበ ሉብቻው ከመሣቅ ሊቆጠብ አልቻለም ፡፡
ይሥቅ ይሥቅና ዝም ይላል ፡፡ ደግሞ እንደገና ይሥቃል ፡፡

ምግቡን በደንብ ከበላ በኋላ ፡ እንደ ወትሮ ልማዱ
ጽሑፍ የመገልበጥ ሥራውን አልቀጠለም ፡፡ በዚያ ፋንታ
የምሽቱን በደንብ መጨለም እየተዝናና ለመጠበቅ ያህል
አልጋው ላይ ጋደም አለ ፡፡ የግብዣው ሰዓት ሲቃረብ ልብ
ሱን በቅልጥፍና ለባብሶ አዲሱን ካፖርት ደረበና ከቤቱ
ወጣ ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ የዓቃቤ ጸሐፊው ምክትል የሚ
ኖርበት አካባቢ የት እንደ ነበር ለይቼ ለመናገር ባለመ
ቻሌ አዝናለሁ ፡፡ ብቻ ስለ አንድ ነገር ርግጠኛ ነኝ ፡፡ የሰ
ውየው መኖሪያ ከአካኪ.ይ አካኪ.የቪች ሠፈር የራቀና
ማለፊያ በሚባለው የከተማው ክልል የሚገኝ ነበር ፡፡

አካኪ.ይ አካኪ.የቪች ከቤቱ እንደ ወጣ፡ የተጓዘባቸው
ጐዳናዎች ጭር ያሉና የፈዘዙ የመንገድ መብራቶች ግራና
ቀኝ የተተከሉባቸው ነበሩ ፡፡ ወደ ዓቃቤ ጸሐፊው ምክትል
ሠፈር እየተቃረበ ሲሔድ ግን ፡ ጠቅላላው ሁኔታ የተለየ
መልክ መያዝ ጀመረ ፡፡ ጐዳናዎቹ ከወናነት ወደ ሕያውነት



ሲለወጡ ፡ የመብራቶቹ ብርሃንም ከደብዛዛነት ወደ ደማቅ
ነት እየፈካ ሔደ ፡፡ መንገዶቹና አደባባዮቹ እንደ ቀድሞ
ዎቹ ጭር ያሉ አልነበሩም ፡፡ በርካታ እግረኞች ይተላለ
ፉባቸዋል ፡፡ ብዙ ግርግር ይታይባቸዋል ፡፡ ማለፊያ ማለ
ፊያ በሆኑ ልብሶች የተዋቡ ሴቶችና ውድ ልብሶች የለበሱ
ወንዶች በብዛት ይታያሉ ፡፡ ከሥራቸው የተጋገረውን
በረዶ እየሰባበሩ ወደ ላይና ወደ ታች የሚመላለሱት
ተንሸራታች ጋሪዎች እንኳን ፡ በሌላ አካባቢዎች ዘወ
ትር እንደሚታዩት ያሉ ርካሽና በነሐስ ምስማር የተቀ
ጠቀጡ ዐይነት አይደሉም ፡፡ አካኪ.ይ አካኪ.የቪች ድንቅ
የሆኑ ሠረገላዎችንም ማየት ጀመረ ፡፡ ቀለሞቻቸው ለዐ
ይን የማይከብድ ፡ ወንበሮቻቸው የድብ ቆዳ የለበሱ ፡
ነጂዎቻቸው ፍም ከመሰለ ቀይ ከፋይ የተሰፉ መለዮ
ዎች ያጠለቁ ነበሩ ፡፡ አካኪ.ይ አካኪ.የቪች ጀንበር ካዘቀ
ዘቀች በኋላ ፡ ወደ አደባባይ መውጣት ካቆመ አያሌ ዓመ
ታት አልፈውት ነበር ፡፡ ትርዒቱን ሁሉ በመደነቅ እያስ
ተዋለ መጓዙን ቀጠለ ፡፡

አንድ ትልቅ ሱቅ አጠገብ ሲደርስ ፡ ከመስኮቱ በስተ
ኋላ የተቀመጠ ሥዕል አየ ፡፡ ይዘቱን የማወቅ ፍላጐት ወደ
መስኮቱ እንዲጠጋ አደረገው ፡፡ ከኃይለኛ መብራት የሚ
ወጣ ብርሃን ሥዕሉ ጐልቶና ደምቆ እንዲታይ ምክንያት
ሆኖታል፡፡ከመስተዋቱ በስተጀርባ በተቀመጠው ሥዕል ላይ
መጫሚያዋን የምታወልቅ አንዲት ቆንጆ ሴት ትታያለች፡፡
ትንሽ ጉንበስ በማለቷና አንዱን እግሯን ከመሬት በጥቂቱ
ብድግ ከማድረጓ የተነሣ፡በጣም የተዋበ ቅርጽ ያላቸው ተረ
ከዞቿ ፡ ባቷና ጭኗ ከቀሚሷ ወጣ ብለው ይታያሉ ፡፡ ከበስ
ተጀርባዋ ደግሞ ግርማ ሞገስ ያለው አንድ ሰው ወደ ሌላ
ክፍል የሚያስገባ በር ከፊት አድርጎ ፡ እስከ ጉንጩ ድረስ
ብቻ የወረደ ጢም ያለበት ፊቱን ብቅ በማድረግ ሲመለ

ከታት ያሳያል፣ሥዕሉ ። አካኪይ አካኪየቪች ሥዕሉን በትልቅ ስሜትና አትኩሮት ካስተዋለ በኋላ፣ራሱን ነቅነቅ አድርጎ እንደ ልማዱ አፉን ሳይከፍት በመሣቅ መንገዱን ቀጠለ ። የሣቁን ምክንያት በትክክል ለማወቅ ባይቻልም፣ ማንም ሰው እንደዚያ ያለ ትርዒት ሲያይ፣በተፈጥሮ የሚሰማው ዐይነት ስሜት እርሱንም ዳበስ አድርጐት ሊሆን ይችላል ። ምናልባትም ያሳሰበው ነገር ይኖር ይሆናል ።

እንዲህ እያለ ሲጓዝ ቆየና፣በመጨረሻው የዓቃቤ ጸሐፊው ምክትል በኪራይ ወደሚኖርበት ሕንፃ ደረሰ ። የዓቃቤ ጸሐፊው ምክትል ኑሮ በጣም ዘመናዊ ከሚባለው ተራ የሚመደብና የወቅቱን ሁኔታዎች የተከተለ ነበር ። አካኪይ አካኪየቪች በሁለተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኘው እልፍኝ ሲገባ በርከት ያሉ ፣ በክረምት ጊዜ በጫማ ላይ የሚጠለቁ የበረዶ መከላከያዎች በወለሉ ላይ ተደርድረው አየ ። በክፍሉ እማካይ ሥፍራ በተቀመጠው ‘ ሳሞቫር ’ ውስጥ የሚፈላው ሻይ ሲንተከተክ ጢስ ተጉለል እያለ ይወጣል ። ግራና ቀኝ በየግድግዳዎቹ ላይ ብዙ ካፖርቶችና ካባዎች ተሰቅለዋል። አንዳንዶቹ በውድ ዋጋ የሚገመቱ ናቸው ። ከአንደኛው ግድግዳ በስተጀርባ እንደ ማጉረምረም ያለ የታፈነ የሰዎች ድምፅ ያስገመግማል ። ወዲያውኑ ባዶ ፍንጃሎች የተደረደሩበትና በብስኩት የተሞላ ቅርጫት ያለበት ትሪ የያዘ አንድ የቤት አሽከር ድንገት በሩን ከፍቶ ሲወጣ፣የታፈነው ድምፅ የተደበላለቀ ንግግር ሆኖ ተሰማው ። የተጋበዙት እንግዶች ከርሱ ቀደም ብለው በሥፍራው መገኘታቸውንና የመጀመሪያ ዙር ሻያቸውን በማገባደድ ላይ መሆናቸውን ተረዳ ።

አካኪይ አካኪየቪች አዲሱን ካፖርቱን አውልቆ ከሰቀለ በኋላ ፣ ግብዣው ወደሚካሔድበት ክፍል ሲገባ በሠልፍ ከተኰለኰሉት ሻማዎች የሚንጸባረቀው ብርሃን ዐይ



ኑን አጥበረበረው ። የሹማምንት ፊት ፣ የትምባሆ ማጤሻ ፒፓዎች፣የካርታ መጨዋቻ ጠረጴዛዎችና ሌሎችም ትርዒቶች በመተባበር ዐይኖቹን ተጣረሩዋቸው ። ድብልቅልቁ የወጣው ጫጫታ ፣ ቅጡ የጠፋው ልፍለፋና ውይይት ፣ የሚሳቡ ወንበሮች መንሳጠጥ፣የሆነ ያልሆነው ድምፅ በአንድነት ተደባልቆ በጆሮዎቹ ያስተጋባ ጀመር ። ማድረግ የሚገባውን ማወቅ ተሰኖትና ቅጥ አንባሩ ጠፍቶት፣መሐል ቦታ ላይ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ዙሪያውን እየቃኘ ምን ማድረግ እንደሚገባው በማሰላሰል ላይ እያለ፣ወደ ክፍሉ መግባቱን የተመለከቱት እንግዶች በታላቅ ጫጫታና ጩኸት ተቀበሉት ። ወዲያው አዲሱን ካፖርቱን ለመመልከት መግቢያው ላይ ወደሚገኘው እልፍኝ በሩጫ እየተንጋጉ ሔዱ ። አካኪይ አካኪየቪች በሁኔታው ትንሽ ቢወናበድም ቅሉ፣መቼም ገራገርና የዋህ ሰው ነውና ተጋባዦቹ ለካፖርቱ በሚያሳዩት አድናቆት የተነሣ ልቡ በደስታ ተፈነቀለ ። መንፈሱ በግብዝነት ስሜት ተበረዘ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ፣ ሁሉም ሰው እሱንም ሆነ ካፖርቱን ችላ በማለት ወደ ካርታ ጨዋታው ተመለሰ ።

በዚያ ቤት የሚካሔደውን ማናቸውንም ሁኔታ ፣ ጫጫታውን፣ልፍለፋውን፣የሰዉን መተረማመስ... ሁሉ አካኪይ አካኪየቪች በአንድ ደግና ልብወለድ መጽሐፍ ውስጥ የሚያነበው እንጂ፣በዐይኑ ሥጋ የሚያየው ገሃድ አልመሰለውም ነበር ። ምን እንደሚያደርግ ፣ ምን መፈጸም እንዳለበት ለማወቅ ተቸግሮ ፣ በጭራሽ ግራ ገብቶት ነበር ። እጅና እግሮቹን እምን ላይ እንደሚያሳርፋቸውና ምን ሥራ እንደሚያሲዛቸው ፣ ብቻ ባጠቃላይ ሰውነቱን እንዴት እንደሚያደርገው መላ ቅጡ ጠፍቶት ተማቶበታል ። በመጨረሻ እንደ ምንም ብሎ የሞት ሞቱን የካርታ ጨዋታ ከሚካሔድባቸው ጠረጴዛዎች ወደ አንደኛው ተጠጋ ። አንዴ

ካርታዎቹን ይመለከታል ። አንዴ ጠረጴዛውን ከበው በተቀመጡት ካርታ ተጫዋቾች ላይ ያፈጥጣል ። ምኑም ምኑም አልጥምህ ስላለው ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማዛጋት ጀመረ ። ሁሉም ነገር በጣም አሰልቺ ከመሆኑ በላይ የመኝታ ሰዓቱም ማለፉ ተሰማው ። ወደ ጋባዡ ጠጋ በማለት እንዲያሰናብተው ፈቃድ ለመጠየቅ ሞከረ ። እንደ ፈለገው ሊሆንለት አልቻለም ። ገና ተጋባዦቹ በሙሉ ስለ አዲሱ ካፖርቱ ክብርና ምርቃት ሲባል ፣ የሻምፓኝ ጽዋ ስለሚያነሡ ብዙ ሰዎች ጥያቄውን ተቃወሙ ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ራት ቀረበ ። የተደበላለቀ አትክልት ፣ ቀዝቃዛ የጥጃ ሥጋ ጥብስ ፣ ኬክ እየተበላ ከተከፈተው ሻምፓኝ አካኪይ አካኪየቪች በግድ ሁለት መለኪያ እንዲጠጣ ተደረገ ። ሻምፓኙን ከቀመሰ በኋላ ፣ በክፍሉ ውስጥ የሚከናወነው ሁኔታ ሁሉ እጅግ አስደሳች መሆኑ ተሰማው ። ይሁን እንጂ ፣ ሌሊቱ እየገፋ መሔዱንና ወደ ቤቱ የሚመለስበት ሰዓት በጣም ማለፉን አልዘነጋውም ። በመጨረሻ ወደ ቤቱ ለመሔድ ሲነሣ ፣ የዓቃቢ ጸሐፊው ምክትል ትንሽ ሊያቆየው ጥረት ቢያደርግም ፣ እንደ ምንም ተደብቆ ሾለከና ወደ መግቢያው እልፍኝ በመሔድ ካፖርቱን መፈለግ ጀመረ ። አዲሱ ካፖርቱ ወለሉ ላይ ወድቆ ነበር ። በጣም እያዘነ ከወደቀበት በማንሣት አቧራውን አረጋግፎ ለበሰውና ከቤቱ ወጣ ።

የጕዳናው መብራቶች እንደበሩ ናቸው ። የቤት አሽከሮችና ጓደኞቻቸው እንደ ክበብ ከሚጠቀሙባቸው ሱቆች አንዳንዶቹ ገና አልተዘጉም ። የተዘጉትም አገልግሎት መስጠታቸውን ያቆሙ አይመስልም ። በየበሮቻቸው ላይ በሚገኙት ስንጥቆችና ቀዳዳዎች እየሠረቀ መንገዱ ላይ የሚያርፈው ብርማ ቀለም ያለው ብርሃን በቂ ምስክር ነው ። ምናልባት ከነዚህ የተዘጉ በሮች በስተጀርባ የእልፍኝ አሽከ



ሮችና ገረዶች ተሰባስበው ሐሜታቸውንና ትችታቸውን ያቀልጡት ይሆናል ። አካኪይ አካኪየቪች ግን ፣ በዓለም ቁንጮ ላይ እንደ ቆመ ዐይነት ስሜት እየተሰማው የደስታና የታላቅነት ስሜት እያፍነከነከው መንገዱን ቀጠለ ። አንድ ቦታ ላይ ሲደርስ አንዲት ሴት መላ አካሏን በተለይም መቀመጫዋን እያውረገረገች ፣ እየሰበቀችና እያሽከረከረች ከኋላው እንደ ንፋስ ሽው ብላ ስታልፍ ፣ ምክንያቱን ሳያውቀው ከመቅጽበት ተከትሏት መሮጥ ጀመረ ። ትንሽ ከሮጠ በኋላ ደግሞ የታዘዘ ይመስል ቀጥ ብሎ ቆመ ። እንደገና ርምጃውን በዝግታ ቀጠለ ። ባልታወቀ ሁኔታ ድንገት ፍጥነቱን መጨመሩ አስደነቀው ። ወዲያው ወደነዚያ ጭር ያሉ ጕዳናዎች ደረሰ ። እንኳንስ በደረቅ ሌሊት በጠራራ ቀትር ባዷቸውን የሚውሉት እነዚያ ጕዳናዎች ቀፋፊና አስፈሪም ነበሩ ። ፈዛዛዎቹ የመንገድ መብራቶች ጨርሶ ተባብሶባቸው ጭል-ጭል ከማለታቸው ሌላ አንዳንዶቹ ከናካቴው ጠፍተው ነበር። በዚያ አካባቢ የነዳጅ እጥረት መኖሩ በግልጽ ያስታውቃል ። ቀስ በቀስ ከጡብና ከብረት በተሠሩ ቤቶችና አጥሮች ቦታ የዕንጨት ቤቶችና አጥሮች እየተተኩ ሔዱ ። ከአካኪይ አካኪየቪች በቀር አንድም የሚላወስ ነገር አይታይም ። ዙሪያ ገባው እርጭ ብሏል ። ግራና ቀኝ ያሉት ትንንሽ ጐጆዎች እንደ መተከዝ ብለው ያንቀላፋሉ ። መሬቱ ላይ የተነጠፈው በረዶ ከመብራቶቹ የሚፈነጠቀውን ደካማ ብርሃን መልሶ ያንጸባርቃል ። አካኪይ አካኪየቪች ሲጓዝ ቆየና ወደ አንድ አውላላ አደባባይ ደረሰ። ዝር የሚል ባለመኖሩና ሌላ ሌላውም ሁኔታ ተባብሮ በብቸኛ ልብ ፍርሃትን ያጭራል ። ከአደባባዩ ጠርዝ ላይ ትልልቅ ሕንፃዎች ተገትረዋል ።

ራቅ ብላ በቆመች አንዲት የዘበኛ ቤት ውስጥ የምትስለመለም ብርሃን ትታያለች ። በዓለም ዳርቻ ላይ የተተ

ሂለች መቅረዝ መሰለችው ። አካኪይ አካኪየቪችን አጥ
ለቅልቆት የነበረው የደስታ ስሜት እየቀነሰ ሔደ ። አደባ
ባዩን ማቋረጡን ሲያያዘው ፤ ይህ ነው የማይባል ኃይለኛ
ፍርሃት ልቡን ያባጥለው ጀመር ። በዚያ ደረቅ ውድቅት
አንዳች ክፉ ነገር እንደሚደርስበት አስቀድሞ ያወቀ ይመ
ስል ሆዱ ክፉኛ ተሸበረ ። አሁንም አሁንም መገላመጥ ፤
ዐሥር ጊዜ አካባቢውን መቃኘት ብቻ ሆነ ። በዚያ ሰፊ አደ
ባባይ ሲራመድ ብቻውን በውቅያኖስ ውስጥ እንደሚንሳ
ፈፍ ሆኖ ተሰማው ። “ የሌም ወዲያ ወዲህ መመልከት አያ
ስፈልግም ” የሚል ውሳኔ በሐሳቡ አሳለፈና ዐይኖቹን
ጨፍኖ ወደፊት መግፋት ቀጠለ ። ጥቂት ርምጃዎች
ነጠቅ ነጠቅ አደረገና ወደ አደባባዩ ዳርቻ ለመድረስ ምን
ያህል ርቀት እንደ ቀረው ለማየት ፤ የተከደኑ ዐይኖቹን ሲገ
ልጥ ሪዝ ያላቸው ሰዎች በአጠገቡ ተገትረዋል ። ማንነ
ታቸውን መለየት አዳገተው ። ጉም የመሰለ ነገር ዐይኖቹን
ጋረዳቸው ። ልቡ ካለበት ሥፍራ ተመንጥቆ ለመውጣት
እንደሚታገል ሁሉ ደረቱን እንደ አታሞ ይደልቀው ጀመር ።

“ ሰማህ ሰውዬ ! ይሄ የለበስከው ካፖርት የኔ ነው ! ”
በማለት ከሰዎቹ አንደኛው የካፖርቱን ክሳድ በእጆቹ ጨም
ድዶ በማስፈራራት ዐይነት ድምፅ ጮኸበት ። አካኪይ
አካኪየቪች ፎዳታ ለመጥራት አፉን ሲከፍት ፤ አንደኛዉ
ሰው የአራስ ጭንቅላት በሚያክል ቡጢው አቆጋውና ፤
“ እስቲ ጩኸና ሞክረኝ ” በማለት አንባረቀበት ። ወዲ
ያው ካፖርቱን ከላዩ ላይ ገፍፈው ወሰዱበት ። ቀጥሎም
ከሰዎቹ አንደኛው በጉልበቱ ከአንበረከከው በኋላ ፤ ጀር
ባው አከርካሪ ላይ በመቆም መሬቱ ላይ ከተጋገረው በረዶ
ጋር አዋሐደው ። ከዚያ በኋላ ስለሆነው አካኪይ አካኪ
የቪች ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረውም ። ሩሁን
ስቶ ተጋደመ ። ጥቂት ደቂቃዎች ቆይቶ ሕሊናውን ሲያ



ውቅ እንደ ምንም ተግተርትሮ ለመቆም ሞከረና ዙሪያውን
ተመለከተ ። አንድም ሰው አልነበረም ። በዚያ ቅልጥጥ ያለ
ሰፊ አደባባይ የሌሊቱ ብርድ ክፉኛ ይሸነቁጠው ጀመር ።
ኤዲሱ ካፖርቱ በነዚያ ጃውሳዎች መወሰዱን ሲገነዘብ
ድምፁን ከፍ አድርጎ መጮህ ቃጣው ። ግን ድምፁ ስልል
በማለቱ እንኳንስ በአደባባዩ ሊያስተጋባና ከዳር ሊደርስ
ቀርቶ ወደ ራሱም ጆሮ መቅረብ ተሳነው ። ተስፋው በው
ስጡ ሲያከትም ተሰማው ። በአካሉ ውስጥ የቀረችውን ጥን
ካሬ እንደ ምንም አሰባስቦ እንደ እብድ እየለፈለፈና እያላ
ን ማዶ ለማዶ ወደምትታየው የዘበኛ ቤት በሩጫ ከነፈ ።
ከትንሿ የዘበኛ ቤት አጠገብ የጦር መሣሪያውን ደገፍ ብሎ
የቆመው ዘበኛ ፤ የሌሊቱን ቀዝቃዛና ጸጥ ያለ አየር በአ
ሪታ እያሸበረ ወደርሱ የሚበረውን ሰው ማንነት ለማወቅ
በመጓጓት በጨለማው ውስጥ አፍጥጦ ይመለከት ጀመር።

አካኪይ አካኪየቪች ትንፋሽ አጥሮት እያለከለከ ወደ
ዘበኛው ዘንድ ደረሰ ። በመንግሥት አደባባይ ቀማኛ ካፖ
ርቱን ሲገፈው እያየ ሊረዳው በመሞከር ፈንታ ፤ በግዴለ
ሽነት እንቅልፉን እየለጠጠ ስላስጠቃው ፤ ዐቅሙ በፈቀደ
ለት መጠን በዘበኛው ላይ ሊደነፋበት ሞከረ ። ዘበኛው
ግን ፤ አንዳችም የንጥቂያ ወንጀል ሲፈጸም አለማየቱንና
በአደባባዩ መሐል አብረውት ቆመው የነበሩ ሁለት
ሰዎችም ጓደኞቹ እንጂ ፤ ማጅራት መቺዎች እንዳልመሰ
ሉት ረጋ ባለ አኳኋን ነገረው ። በመጨረሻውም በውድ
ቅት ሌሊት እየጮኸ ጊዜውን ከሚያባክንና አገር ከሚ
ጠብጥ በማለዳ ተነሥቶ ለጣቢያው የሃምሳ አለቃ ማመ
ልከቻ ቢያስገባ የሚበጀው መሆኑን በጥሞና አስረዳው ።
የመመለጥ ተራውን የሚጠብቀው ከጭንቅላቱ በስተኋላ
ኩል በጆሮዎቹ ዙሪያ የሚገኘው ጸጉሩ ተመነጫጭሮ ፤
ሪው ፤ ደረቱና ጉኖቹ በበረዶ ተለውሰው ፤ በቃላት ለመ

ግለጽ በሚያዳግት ሁኔታ ሁለመናው ተንሳቁሉ አካኪይ
አካኪየቪች ወደ መኖሪያው በረረ ።

ዋናው የመግቢያ በር በኃይል ሲመታ የሰሙት ቤቱን
ያከራዩት አሮጊት ከተኙበት በፍጥነት ዘለው ተነሡ ። ከመ
ቻኮላቸው የተነሣ ፣ አንዱን ነጠላ ጫማቸውን ብቻ እግ
ራቸው ላይ ሰክተውና በጥድፊያ ብዛት ለመልበስ ያስቸ
ገራቸውን የሌሊት ሸሚዛቸውን በደረታቸው ላይ ደግፈው
በመውጣት በሩን ከፈቱለት ። አካኪይ አካኪየቪች ወደ
ውስጥ ሲገባ፥ በሁኔታው በመደናገጣቸው ወደ ኋላቸው አፈ
ገፈጉ ። በመንገድ ላይ ስላጋጠመው አደጋ በዝርዝር ከተ
ረዱ በኋላ ግን እያጨበጨቡና ፣ ‘ጉድ’ እያሉ በማዳነቅ
በማለዳ ተነሥቶ ለተቆጣጣሪው እንዲያመለክት ምክራ
ቸውን ለገሡት ። የሃምሳ አለቃውን ጉዳይ ግን እምብ
ዛም ነገሬ አላሉትም ። የሃምሳ አለቃው ስለማይፈጽመው
ነገር ቃል ከመግባትና ጉራ ከመንዛት በቀር ርባና ያለው
ሥራ መሥራት የማይሳካለት ሰው መሆኑን አስረዱት ፡
ተቆጣጣሪውን ግን ፣ በቅርብ የሚያውቁት ከመሆኑም በላይ
ቀደም ሲል እርሳቸው ዘንድ በወጥ ቤትነት ትሠራ የነበ
ረችው የፊንላንዷ ተወላጅ አና እርሱ ዘንድ በሞግዚትነት
ተቀጥራ በማገልገል ላይ እንደምትገኝ ገለጡለት ። ይህም
ብቻ ሳይሆን ፣ ተቆጣጣሪው ሠርክ በቤታቸው በኩል ሲያ
ልፍ የሚያዩት መሆኑንና በሰንበትም ቀን ወደ ቤተ ክር
ስቲያን ሔዶ ጸሎት ሲያደርስ አካባቢውን በፈገግታና በደ
ስታ መንፈስ የመቃኘት ፀመል ስላለው ፣ ደግ ሰው መሆ
ኑን እንደሚያምኑበት ግልጽ አድርገው ነገሩት ።

አካኪይ አካኪየቪች የአሮጊቷን ምክር በአንክሮ
ከአዳመጠ በኋላ ፣ ወደ መኖሪያ ክፍሉ እየቆዘመ ገባ ። ቀሪ
ውን ሌሊት በምን አኳኋን እንዳሳለፈው በጽሑፍ ለመ
ግለጽ ከመሞከር ይልቅ ፣ ራሱን በሌላ ሰው ሥፍራ ተክቶ



ሁኔታዎችን ለማየት ለሚችል አንባቢ ምናብ ብንተወው
ይቻላል ።

በማግሥቱ፥አካኪይ አካኪየቪች በማለዳ ተነሥቶ ወደ
ተቆጣጣሪው ቤት ሔደ ። ግን ተቆጣጣሪው ገና ከመኝ
ታው አለ መነሣቱ ተገለጸለትና በሔደበት እግሩ ተመለሰ።
እረፋፈደና በአራት ሰዓት ላይ ዳግመኛ ሞከረ ፤ አሁንም
ከእንቅልፉ አለ መንቃቱ ተነገረው። በአምስት ሰዓት ላይ
ተመልሶ ሲጠይቅ ከቤት ወጥቷል ተባለ ። የምሳ ሰዓ
ትን ጠብቆ ደጅ ጥናቱን ቀጠለ ። ነገር ግን ፣ በቤቱ መግ
ቢያ ላይ በሚገኘው ክፍል ውስጥ ተቀምጠው የሚሠሩ
ጸሐፊዎች የመጣበትን ጉዳይ አስቀድሞ ካልገለጸላቸው
በቀር ሊያስገቡት እንደማይችሉ አስረዱት ። አካኪይ አካ
ኪየቪች በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ኰስተር በማለት ፣
ከመንግሥት መሥሪያ ቤት በሥራ ምክንያት መምጣቱ
ንና ፣ ተቆጣጣሪው ዘንድ በግንባር ቀርቦ ጉዳዩን ለማስ
ረዳት የሚሻ መሆኑን ገለጸላቸው ። ጸሐፊዎቹ ጥያቄውን
የማይቀበሉ ከሆነ ግን ፣ ክስ እንደሚቀርብባቸው በመ
ጠቆም እቅጩን ነገራቸው ። በሐሳባቸው ለመጽናት
ስላልደፈሩ ፣ ከመካከላቸው አንዱ ለተቆጣጣሪው ለመንገር
ወደ ውስጥ ገባ ።

ተቆጣጣሪው ፣ ስለ ዘረፋው የቀረበለትን ታሪክ ሲሰማ
ታየው ሁኔታ በፍጹም እንግዳ የሆነና ያልተጠበቀም ነበር።
አቤቱታው ፍሬ ነገር ላይ በማተኮር ፋንታ፥አካኪይ አካኪ
የቪች እንደዚያ እስኪመሽ ድረስ ከቤቱ ውጭ ስለቆየበት
ምክንያት ይጠይቀው ጀመር ። ምናልባትም ያ ሁሉ ጣጣ
ያጋጠመው ወራዳ በሆኑ ቦታዎች ሲልከሰከስ በማምሸቱ
ቢሆን እንደሚችል ይነግረው ጀመር ። አካኪይ አካኪየ
ቪች ነገሩ ሁሉ ግራ ሆኖበት ፣ ትዕግሥቱም በመሟጠጡ
ከተቆጣጣሪው ቤት ወጥቶ ሔደ ። የተነጠቀ ካፖርቱን

ለማግኘት ክትትል እንዲደረግ ትእዛዝ መስጠት አለመስጠቱን እንኳን አያውቅም ነበር ። አካኪይ አካኪየቪች በሕይወቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያን ዕለት ወደ ሥራው ሳይገባ ዋለ ።

በተከታዩ ቀን እንደ አስከሬን ገርጥቶና ከበፊቱ የባሰ የተንኮሳቆለውን ያንኑ የቀድሞ ዝተት ካፖርቱን ለብሶ ወደ መሥሪያ ቤቱ ሔደ ። የሥራ ጓደኞቹና ኃላፊዎቹ ጭምር የካፖርቱን መዘረፍ ሲሰሙ ፤ ከንፈራቸውን በመምጠጥ ኃዘናቸውን ገለጡለት ። አንዳንድ ባለጌዎች ግን ፤ በአካኪይ አካኪየቪች ላይ ለመሣለቅና ለማፌዝ መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸው ። በመሥሪያ ቤቱ አካባቢ እንደ ተመለደው ሁሉ ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ ፤ ስለ ዘረፋው የሚገልጽ ጽሑፍ የሠፈረበት የዕርዳታ መዋጮ መሰብሰቢያ ወረቀት ከቢሮ ቢሮ ማዞር ተጀመረ ። እዚህ ግባ የማይባል ጥቂት ገንዘብ ተገኘ። ለመዋጮው ገንዘብ ማነስ ብዙ ምክንያቶች ነበሩ ። ቀደም ብሎ ሠራተኞቹ ልዩ ልዩ መዋጮዎችን በማድረጋቸው ኪሣቸው ተራቁቷል ። በመጀመሪያ የሥራ አስኪያጁን ምስል በሠዓሊ ለማስነደፍ ሲባል መዋጮ ተጠየቀ።አዋጡ። ከዚያ ቀጥሎ የክፍል ኃላፊያቸው ጓደኛ የሆነ አንድ ደራሲ፣ አዲስ ያሳተመውን መጽሐፍ እንዲገዙ ተጠየቀ ። ዋጋውን ከፍለው ገዙ ። እና ለአካኪይ አካኪየቪች ችግር የሚሆን ትራፊ ገንዘብ አልነበራቸውም ።

ልባዊ ኀዘን ከተሰማቸው ሠራተኞች መካከል አንደኛው የመዋጮው ነገር አልቋጭ ቢልም እንኳን ፤ አካኪይ አካኪየቪችን በምክር ሊረዳው ወሰነ ። በምንም ዐይነት ሁኔታ ወደ ፖሊሱ የሃምሳ አለቃ እንዳይሔድ ሐሳብ አቀረበለት ። ምክንያቱም ምንም እንኳን የሃምሳ አለቃው በአለቆቹ ዘንድ ለመመስገን ሲል ሰማይ ወጥቶ ፤ መሬት ገብቶ ካፖርቱን የሚያገኝለት መሆኑ ባያጠራጥርም ፤ አካኪይ



አካኪየቪች ሕጋዊ የባለቤትነት ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር፥ ካፖርቱ በፖሊስ ጣቢያው ተይዞ እንዲቆይ የሚደረግ መሆኑን ገለጠለት ። ስለዚህ ወደ ጣቢያ በመሔዱ ፋንታ ወደ አንድ ትልቅ ሰው ፊት ቀርቦ እንዲያመለክት መከረው ። ይህን ካደረገ ያ ፤ ትልቅ ሰው ማስታወሻዎችንና ማሳሰቢያዎችን ጉዳዩ ወደሚመለከታቸው ሰዎች እያስተላለፈ ባጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ትክክለኛ ፈር ሊያሲዝለት እንደሚችል አስረዳው ።

እውነትም አካኪይ አካኪየቪች ወደ ትልቁ ሰው ከመሔድ በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም ። የዚያ ትልቅ ሰው ማዕረግና ሥራ ምን እንደ ነበረ በትክክል ባለመታወቁ እስከ ዛሬ ድረስ ምስጢር ሆኖ ቆይቷል ። እኛም ስለ ትልቁ ሰው መናገር የምንችለው አንድ ነገር ብቻ ነው ። ይኸውም ያ ፤ ትልቁ ሰው ትልቅ እንዲሆን የተደረገው ከቅርብ ጊዜ በፊት መሆኑንና ከዚያ ቀደም ግን ትልቅ ሰው ያልነበረ መሆኑን ብቻ ነው። በርግጥ ያ ፤ ትልቁ ሰው የተመደበበት አዲሱ ሥራ ከሌሎች ትልልቅ ሰዎች የሥራ ደረጃ ጋር ሲወዳደር ፤ ይህን ያህልም ከፍተኛ ወይም ትልቅ የሚባል ዐይነት አልነበረም ። ሆኖም ትልቅነቱን ለማጋነን ሲል፥ የማይጠቀምበት ዘዴና ብልሃት አልነበረም ። ለምሳሌ ወደ ቢሮው በሚገባበት ጊዜ ፤ ከበታቹ የሚገኙ ኃላፊዎች ወደ ፎቅ በሚያስወጣው ደረጃ ላይ ቆመው እንዲቀበሉት መመሪያ ይሰጣል ። ማንም ባለጉዳይ ሊያነጋግረው ሲፈልግ ፤ በቀጥታ ሳይሆን በጠምዛዛ መንገዶች እንዲቀርብ የሚያደርጉ አስቸጋሪ ሕግጋት አውጥቷል።ስለሆነም ባለጉዳይ በቅድሚያ ወደ ክፍለ ሀገሩ ጸሐፊ ዘንድ ይቀርባል ። ጸሐፊው የሥልጣን ተዋረድን ተከትሎ ለሚቀጥለው የበላይ ኃላፊ ያስተላልፈዋል ።እንዲህ እያለ በመጨረሻ ትልቁ ሰው ፊት ለመቆም ይበቃል ። ምክን

ያቱም በተቀደሰችው ሩሲያ ምድር የሌላውን አስመስ
ሎና ገልብጦ ለመሥራት እንጂ፡ራሱን ሆኖ ለመኖር የሚ
ፈልገው ሰው ቁጥር እየቀነሰ ሔዷል ፡፡ የበላዩን ፋና ለመከ
ተልና ፍጹም ግልባጩን ሆኖ ለመገኘት የሚጣጣረው
ቁጥር እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ፡፡ አንዳንዴ
የሚደረገውማ በጣም ያስደንቃል ፡፡ ይህንን በሚመለከት
በየጊዜው የሰማሁዋቸው አያሌ ታሪኮች ትዝ ይሉኛል ፡፡
ለምሳሌ አንድ ተራ ብጤ ሠራተኛ የአንዲት ንዑስ ክፍል
ኃላፊ ሆኖ እንዲሠራ ዕድገት ሲሰጠው፡ በመጀመሪያ የሚ
ወስደው ርምጃ ከሌሎች ሠራተኞች የሚለየውን የማካፈያ
ግድግዳ ማሠራትና በመግቢያው በር ላይ ‘ ዋና ክፍል ’
የሚል ጽሑፍ መለጠፍ ይሆናል ፡፡ ወዲያው ደግሞ ፡ ቀይ
ኩሊታ ያለውና ወርቀ ዘቦ ጉንጉን የተጠለፈበት ጌጠኛ
የደንብ ልብስ የለበሱ ተላላኪዎችን ደጃፉ ላይ ያቆማል ፡፡
ከዚያ በኋላ እንግዳና ባለጉዳይ በመጣ ቁጥር ወደዚያች ቁም
ሳጥን መሳይ ቢሮው የሚያስገባውን በር ቀልጠፍ ብለው
እንዲከፍቱ መመሪያ ይሰጣል ፡፡

ታዲያ ፡ የዚያ የትልቁ ሰው ልምዶችና የአሠራር
ዘዴዎች ታላቅና የተከበሩ ዐይነት ቢሆኑም ፡ የውስብስብ
ነት ባሕርይ ግን አልነበራቸውም ፡፡ ትልቁ ሰው ለሚመ
ራበት መርሕ መሠረቱ ‘ ጥብቅነት ’ ነው ይባላል ፡፡ በን
ግግሮቹም መሐል ‘ ጥብቅ መሆን ያስፈልጋል ’ የሚሉ
ትን ቃላት ማዘውተር ይወዳል ፡፡ የመሥሪያ ቤቱን አስተ
ዳደር የሚያንቀሳቅሱት ቁጥራቸው ወደ አንድ ደርዘን የሚ
ጠጋ የተለያዩ ኃላፊዎች ሕጎቹን አክብረው እንደሚሠሩ
ባያጠያይቅም ፡ ትልቁ ሰው ገና ከሩቅ ብቅ ሲል ሁሉም
የጀመሩትን ሥራ እርግፍ አድርገው ከቅምጣቸው በመነ
ሣት ፡ በአጠገባቸው ዐልፎ ከዐይናቸው እስኪሠወር ድረስ
በተጠንቀቅ ቆመው ማሳለፍ የተለመደ ተግባራቸው



ነበር ፡፡ ከበታቹ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ኩስታራነት አይ
ለየውም ፡፡ በዘወትር ንግግሮቹ መሐል ፡ ‘ እንዴት ብትደ
ፍር ነው ? ... ለመሆኑ ከማን ጋር እንደምትነጋገር አውቀ
ሃል ? ... ከፊትህ የቆመው ሰው ማን መሆኑን በሚገባ ተረ
ድተሃል ? ’ የሚሉ የዕብሪት ሐረጎች አይጠፉም ፡፡ ትልቁ
ሰው በተፈጥሮው የዋህና ገራገር ልብ ያለውና ለማንም
ሰው ወዳጅ ሊሆን የሚችል ዐይነት ቢሆንም ፡ ከቅርብ ጊዜ
በፊት ያገኘው የማዕረግ ዕድገት በፍጹም እንዲለዋወጥ አድ
ርጎታል ፡፡ የጄኔራልነቱን ማዕረግ እንዳገኘ ሁለመናው
ተቀያይሮ ማሳየት የሚገባው መልካም ጠባይ ከመጥ
ፎው ጋር ተሳከረበት ፡፡ ይሁን እንጂ ፡ ከእኩዮቹ ጋር
በሚቀላቀልበት ጊዜ ባንዴ ተለውጦ ትሑት ፡ ብልህና
ትጨዋች መስሎ ለመታዬት ይሞክራል ፡፡ በአንድ ደረጃ
እንኳን ከሚበልጣቸው ሰዎች ጋር ሲሆን ፡ ወዲያው ይለዋ
ወጥና ልዩ ፍጡር ይሆናል ፡፡ እንደ ግዑዝ ድንጋይ በጸ
ጥታ ይዋጣል ፡፡

ዐልፎ ዐልፎ በተጋጋለ ሁኔታ የሚካሔድ ውይይትና
ክርክር በሚያጋጥመው ጊዜ ፡ ልቡ በተመስጦ ሲማረክና
ተሳታፊ ለመሆን ሲከጅል ከዐይኖቹ ይነበባል ፡፡ ነገር ግን
እንዲህ ቢደረግ ክብሩ ዝቅ እንደሚልበት ወዲያውኑ ይሰ
ማውና ፍላጎቱን ለመግታት ሲታገል ይታያል ፡፡ የክብ
ሩን ከፍና ዝቅ ማለት ፡ ለበታቹ ፊት መስጠት ሊያስከት
ልበት የሚችለውን ንቀት ያወጣ ያወርድና በጭንቀት ፡
በጥበት ያሰላስልና ወደዚያ የግዑዝ ጸጥታው ይመለሳል ፡፡

አካኪይ አካኪየቪች የካፖርቱን ጉዳይ ሊያቀርብ
ለት የመረጠው ትልቅ ሰው ይህን የመሰለ ሲሆን ፡ አቤቱ
ታውን ለማሰማት የመረጠው ጊዜ ደግሞ በጭራሽ ተስ
ማሚና አመቺ አልነበረም ፡፡

ትልቁ ሰው ለብዙ ዘመናት ሳያየው ከቆየ የልጅነት
ጓደኛው ጋር ቢሮው ውስጥ የደራ ጨዋታ ይዟል ። ደስታ ፣
የሚይዝ የሚጨብጠውን እሳጥቶት ከአብሮ አደጉ ጋር
ሲያወጋ ፣ ባሽማችኪን የተባለ ሰው ሊያነጋግረው እንደ
ሚፈልግ ተነገረው ። ቀልጠፍ ባለ ሁኔታ ፣ ‘ ማነው እሱ ? ’
ሲል ጠየቀ ። “ ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የመጣ
ነው ” የሚል መልስ ተሰጠው ። “ እንደዚያ ከሆን ትንሽ
ይጠብቅ ። አሁን ጊዜ የለኝም ” በማለት ዘጋ ። እንደ
እውነቱ ከሆነ ግን ፣ ትልቁ ሰው ጊዜ የለኝም ሲል በጣም
ዋሽቷል ። አቤት ባዩን ለማነጋገር የሚበቃ በጣም ብዙ
ጊዜ ነበረው ። እንዲያውም ባይገርማችሁ ፣ ከአብሮ አደግ
ጓደኛው ጋር የሚጫወቱት ወሬ ሁሉ ተሟጦ በጸጥታ እየተ
ያዩ የሚያሳልፏቸው ደቂቃዎች እየበዙ ከመሔዳቸው የተ
ነሣ መሰለቻቸትም ጀምረው ነበር ። የሚወራ በመጥፋቱ
አንዱ የሌላውን ጭን መታ ያደርግና፣ “ ታዲያስ ጃል!ኢቫን
አብራሞቪች ”ሲል . . . “ይሸውልህ እንዲህ ነው ስቴፓን
ባርላሞቪች ” በመባባል ብቻ ተወስነው ነበር ። ይሁን
እንጂ ፣ ሁኔታው እንዲህ ያለ መልክ ቢኖረውም ፣ ከውጭ
የሚጠባበቀውን የመንግሥት ሠራተኛ ለማነጋገር ጊዜ የሌ
ለው መሆኑን ከመግለጥ ትልቁ ሰው ወደ ኋላ አላለም ።
ዋናው ዓላማና ቁም ነገር ግን ሌላ ነበር ። የትልቁ ሰው
ዓላማ ማንንም ባለጉዳይ ቢሆን በእንግዳ ክፍል ተቀምጦ
እንዲጠብቀው የማድረግ ሥልጣን እንዳለው ለጡረተኛ ጓደ
ኛው ማሳየት ብቻ ነበር ።

በመጨረሻው የሚጨዋወቱት ሁሉ ተንጠፍጥፎ በማ
ለቁና ከሚያወሩበት ይልቅ በጸጥታ ተለጉመው የሚፋ
ጠጡበት ጊዜ እየበዛ በመሔዱ ፣ ተለጣጭ ድጋፍ ባላቸው
ወንበሮቻቸው ላይ እየተዝናኑ ሲጋሮቻቸውን ሊያጨሱ
ሲዘገጃጁ ፣ እንዳጋጣሚ ጸሐፊው ሪፖርት ለመውሰድ ብቅ



አለ ። ትልቁ ሰው ረስቶት የነበረ አንዳች ነገር ድንገት
ያስታወሰ በማስመሰል ፣ “ እም - ም አንድ የሆን የመንግ
ሥት ሠራተኛ ሊያነጋግረኝ ፈልጎ ይጠብቃል መሰ
ለኝ . . . . አሁንም ውጭ አለ አይደለም ? . . . . በላ እንዲ
ገባ ንገረው ” አለና ትእዛዝ ሰጠ ።

የቢሮውን ደፍ የረገጠው አካኪይ አካኪየቪች አን
ገቱን ወደ መሬት መቀለሱንና የለበሰውም የደንብ ልብስ
ከማርጀት ዐልፎ መሻገት የጀመረ መሆኑን ሲመለከት
ትልቁ ሰው ፣ ‘ ምንድነው እሱ ? ’ የሚል ጥያቄውን በአ
ስፈሪ ድምፁ በመወርወር ፣ ደጅ ጠኝውን ባለበት አቆ
መው ። በዚያ ዐይነት ድምፅ የመናገር ችሎታውን ለማዳ
በር ሲል ፣ የብዙ ጊዜያት ጥናትና ልምምድ አድርጓል ።
አሁን የያዘው ሥልጣንና ማዕረግ ሊሰጠው አንድ ሳምንት
ያህል ሲቀረው ፣ ቢሮውን ይቆልፍና ለብቻው ከመስተዋት
ፊት ለፊት ተገትሮ የዚያን ዐይነት ድምፅ ከአንደበቱ
ለማውጣት ሲታገልና ሲለማመድ ነበር የከረመው ።

ገና ከውጭ ሆኖ ለመግባት በመጠባበቅ ላይ ሳለ ፣ ጀም
ሮት በነበረው ፍርሃትና ሽብር ቅስሙ የተሰበረው አካኪይ
አካኪየቪች በትልቁ ሰው ሁኔታና ጥያቄ ክናካቴው በረገ
ገና ዕጡ ዱብ አለ ። የተሣሠረ ምላሱን ለማፍታታት እየታ
ገለና የሞት ሞቱን እየተንተባተበ ፣ በደኅናውም ጊዜ እን
ኳን ሲናገር በመደጋገም የሚያሰማቸውን ‘ ኧ - ኧ ’ የሚሉ
የመንቀጥቀጥ ድምፆች በብዙ እጥፍ በንግግሩ መሐል እየ
ጨመረ ችግሩን ለማስረዳት ይፍገመገም ጀመር ። ገና ውሃ
ያልነካው አዲስ ካፖርቱን ፍጹም አረመኔአዊ በሆነና ጭካኔ
በተመላው ሁኔታ መዘረፉንና አሁንም ከቡርነታቸው በጭ
ዳዩ ጣልቃ ገብተው ፣ የተከበሩ የፖሊስ ዋና ተቆጣጣሪው
ወይም ሌላ ሰው አንጡራ ንብረቱን እንዲያስመልሱለት

ትእዛዝ እንዲሰጡለት ለመማጠን መምጣቱን ለመግለጥ ሞከረ ።

አካኪይ አካኪየቪች በጣም የተቀናጣ መሆኑ ለትልቁ ሰው ወዲያው ተሰማው ። “ ታዲያ ወዳጄ አሁን አንተ የምትፈልገው .... ” በማለት በዚያ ስለታም ድምፁ ፡ የትዕቢት ንግግሩን ጀመረ ። “ የሆነውስ ሆነና ሥነ ሥርዓቱን በጭራሽ አታውቀውም ማለት ነው ? ለመሆኑ በአሁኑ ቅጽበት የት ቦታ እንዳለህና ማን ፊት እንደ ቆምክ በትክክል ታውቃለህ ? ጉዳይህንስ በምን መልክ ማቅረብ እንደ ነበረብህ አልተረዳህም ኖሯል ? ... እየህ ወዳጄ አቤቱታህን በመጀመሪያ ለጽሕፈት ቤቱ ማቅረብ ነበረብህ ። ከዚያ በኋላ ወደ ዓቃቤ ጸሐፊዉ ይመራል ። ቀጥሎ ደግሞ ለክፍል ኃላፊው ይተላለፍና ደረጃውን ጠብቆ ለዋና ጸሐፊዉ ይቀርባል ። እንደዚህ እያለ በመጨረሻ ዋና ጸሐፊዉ ለኔ ለራሴ ያቀርብልኛል ። ”

“ ግን እኮ ክቡር ሆይ ” አለ አካኪይ አካኪየቪች ፡ ከፍርሃቱ የተነሣ በላብ እየተጠመቀና በአካሉ ውስጥ የሚገኘውን የመጨረሻ ድፍረት ለማሰባሰብ እየታገለ ። “ መቼም ክቡርነትዎን ለማስቸገር የደፈርኩት .... ያው ኧ .. ኧ ... እርስዎም እንደሚያውቁት ሁሉ ... የርስዎ ጸሐፊዎች ... ኧ-ኧ ... በሙሉ እምነት የማይጣልባቸው ... ”

“ ምን ! ምን ? ምናልክ ? እስቲ ያሁኑን ንግግርክን እንደገና ድገመው !!! ” አላና ትልቁ ሰው ፡ “ ለመሆኑ እንዲህ ለመናገር የበቃኸው እንዴት ብትደፍር ነው በል ? እንዲህ ያለውንስ ሐሳብ ከወዴት አመጣኸው ። ይህ ለበላዮችና ለአለቆች ያለመታዘዝ አዝማሚያ ፡ በዛሬ ዘመን በወጣት የበታች ሠራተኞች ዘንድ ክፉኛ እየተስፋፋ በመ



ሔድ ላይ መሆኑን ደርሰንበታል ። እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ነው ! ” በማለት ይደነፋ ጀመር ።

አካኪይ አካኪየቪች በሃምሳኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው መሆኑን ትልቁ ሰው በፍጹም የተገነዘበ አይመስልም ። አካኪይ አካኪየቪች በዚያን ጊዜ ወጣት ሊባል የሚችለው ፡ ምናልባት ከሰባ ዓመት አዛውውንት ጋር ቢወዳደር ብቻ ነበር ።

“ ለመሆኑ ከማን ጋር እንደምትነጋገር ተረድተሃል ? ... ከፊትህ የቆመው ሰው ማን እንደሆነ ዐውቀሃል ? ... ጥያቄ እኮ ነው የምጠይቅህ ! ትሰማኛለህ ? ” አለ ትልቁ ሰው ፡ አካኪይ አካኪየቪችን ብቻ ሳይሆን ማንንም ሰው ብርክ ሊያሲይዝ በሚችል ጣሪያ የሚሰነጥቅ ድምፅ እየጮኸና ወለሉን በእግሩ እየደበደበ ። አካኪይ አካኪየቪች ሰውነቱ ራደ ። እንጥፍጣፊ ወኔው ከድቶት ሸሸ ። ቀፎው ብቻ ቀረ ። እንድያውን አለቀለት ። በፍርሃትና በሽብር የሥራ ጅስሙ በድን ሆኖ፡ወባ እንደ ያዘው ሁሉ፡ከግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጠጉሩ እየተንዘፈዘፈ ወደ ኋላው ለማፈግፈግ ሞከረ ። ከድንጋጤው ማየል የተነሣ ፡ ወለሉን በእግሩ መቆንጠጥ ተስኖት እንደ ሕፃን ተውተርትሮ በአፍ ጢሙ ሊደፋ ሲል ፡ ሁለት ተላላኪዎች ተሯሩጠው ድጋፍ ሰጡት። ከዚያ በኋላ ሕሊናውን ስቶ ተዘረረ ። ሁለቱ ሰዎች የወሳንሳ ተሸክመው ከቢሮው አወጡት ።

ትልቁ ፡ ሰው በዘዴና በጥበብ የሰነዘራቸው ኃይለቃላት በአካኪይ አካኪየቪች ላይ ከጠበቀው በላይ የሆነ ውጤት በማስከተላቸው በጣም ተደሰተ ። ሌላ ነገር ሳይታከልባቸው ነጐድጓዳዊ ቃላቶቹ ብቻ አንድን ሰው ነፍስና ሥጋውን ለያይተው ከሕሊናው ውጪ ሊያደርጉት እንደሚችሉ በማሰብ ፡ ፍንጥዝጥዝ ብሎ የልጅነት ጓደኛው፡ስለ ሁኔ

ታው ምን አስተያየት እንዳለው ለመረዳት ያህል ዞር ብሎ ተመለከተው ። ይሁን እንጂ ፥ ባወረደው የቂጣ ግልምጫ ሳቢያ አብሮ አደግ ጓደኛውም ፍርሃት እየከጀለው በአጠራጣሪ ሁኔታ ውስጥ ስለ ነበር ፥ ትልቁ ሰው ይህን ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደበትም ።

አካኪይ አካኪየቪች የፎቁን ደረጃዎች እንዴት እንደ ወረደና ወደ ውጭ ወጥቶ በጐዳናው ላይ ጉዞ እንደ ጀመረ በጭራሽ ትዝ አይለውም ። ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በመደንዘዙ ፥ በአካሉ ላይ እጅና እግር ያለው መሆኑ እንኳን ተዘንግቶት ነበር ። በሕይወቱ ሙሉ እንዲህ ያለ ውቃቢ የሚያሥርቅ ዘለፋ ከአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ተሰንዝሮበት አያውቅም፤ያውም በሌላ መሥሪያ ቤት የሚገኝ። የዐይኖቹ ብሌኖች በአንድ አቅጣጫ ላይ ተሰክተው አፉን ገጥሞ አሁንም አሁንም እንቅፋት እያነገለው ፥ የሚያፏጭ የበረዶ ውሽንፍር ጆሮ ጆሮውን እያለው ወደፊት ጉዞውን ቀጠለ።ብዙም ሳይቆይ በደረቱ አካባቢ የሕመም ስሜት እየተፈጠረ ሲሔድ ታወቀው ። ቤቱ ሲደርስ ድምፁ ተዘግቶና ጉሮሮውም ልቅልቅ ብሎ አብጦ ነበር ። ጊዜ ሳያባክን አልጋው ውስጥ ገብቶ ጥቅልል ብሎ ተኛ ። የከባድ ውረፋና ግልምጫ ውጤት እንዲህ ሆነ ።

በማግሥቱ ጠዋት ፥ ሰውነቱ በሙሉ በኃይለኛ ትኩሳት ይቃጠል ጀመር ። የፒተርስበርግ አየር ጠባይ ተጨማሪ ምክንያት በመሆኑ ፥ ሕመሙ ከታሰበው ይበልጥ ተፋጥኖ ጠናበት ። በመጨረሻም እየደከመ ሔደ ። ሐኪም ተጠርቶ እጁን በመያዝ የደሙን ትርታ አዳመጠው ። እንዲያው መድኃኒት የመውሰዱ ወግ እንዳይቀርበት ያህል ብቻ፥ ሰናፍጭና ተልባ ተቀቅሎ በጨርቅ እየተነከረ ሰውነቱ ላይ እንዲደረግለት አዘዘ ። ከክፍሉ ሲወጣ ቤቱን ያከራዩትን ባልቴት ለብቻቸው ገለል አድርጎ ፥ “እሜትዬ የሰ



ውዬው ሁኔታ ብዙም ተስፋ የሚጣልበት ስላልሆነ ፥ በጊዜ የሬሣ ሣጥን ቢያሠሩለት ደኅና ይመስለኛል” የሚል ምክሩን ወርወር አደረገላቸው—ሐኪሙ ።

አካኪይ አካኪየቪች እንዚያን ሐኪሙ የሰነዘራቸውን የሚዘገንኑ ቃላት ይስማ አይስማ ፥ በእውነቱ የምናውቀው ነገር የለም ። የሐኪሙን አስተያየት አዳምጦ፥ያን ጉስቋላና የቁም ስቅል ሕይወቱን ጥሎ የሚሔድበት ወቅት መቃረቡን እያሰላሰለ፥ ልቡናው በኀዘን ተጨንቆ እንደሆንም አናውቅም ። በዚያ ሰዓት በኃይለኛ ትኩሳት እየተሠቃየ ሰመመን ባሰመጠው ቅዠት ይወራጭ ነበር ። በየደቂቃው አዳዲስ ትርዒቶች እየተፈራረቁ ይታዩታል። ወደ ፔትሮቪች ዘንድ ሔዶ፥ ሌቦችን ማጥመድ የሚችል ልዩ ኰት እንዲሰፋለት ትእዛዝ ሲሰጥ ይታየዋል ። ማጅራት መቺዎችና ቀማኞች ቅዠት ከጀመረው ጊዜ አንሥቶ ከአልጋው ሥር ጠፍተው አያውቁም። አንዳንድ ጊዜ፥ ዙሪያውን ከበው ካሉት ሌቦች መካከል አንደኛዉ ፥ አልጋው ላይ በመውጣት ፥ አንሶላና ብርድ ልብሱን ገልጦ አጠገቡ የተኛ ይመስለዋል ። ትርዒቱ እንዲያ ሲሆንበት ፥ ቤቱን ያከራዩትን ባልቴት እየደጋገመ በመጣራት እንዲያስወጡለት ይጠይቃል ። አንዳንዴ ደግሞ ያ አሮጌው ካፖርቱ፥ ፊት ለፊቱ ባለው ግድግዳ ላይ ለምን እንደ ተሰቀለ ጥያቄውን ያቀርብና፥ወዲያው አዲስ ካፖርት አለኝ እያለ ይለፈልፋል ። በሌላ ቅዠት ደግሞ፥ከትልቁ ሰው ፊት ቆሞ የስድብና የቂጣ ውርጅብኝ ሲቀበልና ፥ ‘ክቡር ሆይ በጣም አዝናለሁ’ እያለ ሲያጉተመትም ይታየዋል ። በመጨረሻው አስፈሪ የሆኑ ርግማኖችንና አስቀያሚ ስድቡን እንደ አንዳች ነገር ያወርደዋል ። ቤቱን ያከራዩት መልካም ሴት ይህን ስድቡንና ርግማኑን ሲሰሙ ለብቻቸው ያማትባሉ ። አካኪይ አካኪየቪችን ካወቁት ዕለት አንሥቶ እስከዚያ ጊዜ ድረስ

ያን መሳይ ክፉ ነገር ከአፉ ሲወጣ ሰምተው አያውቁም፡፡
በይበልጥ የሚጨነቁት ደግሞ በሽተኛው እነዚያን አስከፊ
ቃላት ማጉረፉን የሚጀምረው ‘ ክቡር ሆይ ’ የሚል ቃል
ከአስቀደመ በኋላ በመሆኑ ነው ፡፡ የኋላ ኋላ መዘላበድ
ጀመረ ፡፡ ሆኖም ዝብርቅርቅ ቢልና መጨበጫ ባይኖ
ረውም ቅሉ ፣ ልፍለፋውና ቅብጥርጥሩ ሁሉ ስለዚያው
ጦሰኛ ካፖርቱ ብቻ ነበር ፡፡

ሲያራዝሙና ሲያቀባዥረው ከረመና ፣ በመጨረሻው
አካኪይ አካኪየቪች የሕይወቱ መደምደሚያ የሆነውን
ሕቅታ ተንፍሶ ዐረፈ ፡፡ ሞተ ፡፡ ይኖርበት የነበረውን ክፍል
ማሸግ አስፈላጊ አልሆነም ፡፡ ሁለት ምክንያቶች ነበሩ ፡፡
አንደኛ ፣ ንብረቱን የሚጠይቅ ወራሽ የለውም ፡፡ ሁለተኛ ፣
በክፍሉ ውስጥ የተገኘውም ንብረት ትርኪ ምርኪ
እንጂ ፣ ይህን ያህል ከቁም ነገር የሚጣፍ አልነበረም ፡፡ አንድ
እስር የዳክዬ ላባዎች ፣ አንድ ደስጣ ነጭ ሉክ ወረቀት ፣
ሦስት ጥንድ ካልሲዎችና አንባቢ ጥሩ አድርጎ የሚያው
ቀው ያ አሮጌ ካፖርት ነበር የተገኘው ፡፡ በነገራችን ላይ
አሮጌው ካፖርት ወደ ማን እጅ እንደ ገባ እግዜር ብቻ ነው
የሚያውቀው ፡፡ ይህን ታሪክ የተረከልኝም ሰው ሁኔታ
ውን ለመከታተልና ካፖርቱን ማን እንደ ወሰደው ለማ
ወቅ አንዳችም ጥረት ያላደረገ መሆኑን መግለጽ ይኖ
ርብኛል ፡፡

አካኪይ አካኪየቪች ከተቀበረ በኋላ ሁሉም ነገር
ተረሣ ፡፡ የቅዱስ ፒተርቡርግ ከተማ የቀድሞ ሕይወት እንደ
ነበር ቀጠለ ፡፡ በዚያች ከተማ ውስጥ አካኪይ አካኪየቪች
የሚባል ምስኪን ጽሑፍ ገልባጭ በአንድ ወቅት ይኖር
እንደ ነበር የሚያስታውስ አንዳችም ምልክትና ትዝታ
አልቀረም ፡፡ ማንም አይዞህ ባይና ደጋፊ ያልነበረው ፣ አን
ድም አፍቃሪና ታዳጊ የማያውቀው ፣ ይህ ነው የማይባል



ግራኪና አስደናቂ ባሕርይ ያልነበረው አካኪይ አካኪየ
ቪች ሳያምርበት ኖሮ ፣ ሳያምርበት ሞተ ፡፡ ሌላው ቀርቶ በወ
ንፊት ተይዛ በወረቀት መርፌ ምናምን ላይ የተጣበቀች
አንዲት ተራ የቤት ውስጥ ዝንብ ፣ በሚያጉላ መነጥር
ሊመረምራት የሚቻኮልን አንድ የሥነ ፍጥረት ሊቅ የምት
ማርከውን ያህል እንኳን ፣ የሰዎችን ስሜት ለመሳብ ያልታደ
ለው ቀለም ገልባጭ ነገር ቢቃ ፣ ተከተተ ፡፡ የሥራ ባልደረ
ቦቹን ሬዝና ማንጓጠጥ በታላቅ ትሕትና ሲቀበል የኖረ
ውና ስሙን የሚያስጠራ አንዳችም ቁም ነገር ማከናወን
ያልተቋጨለት አካኪይ አካኪየቪች አልባሌ ሆኖ ኖሮ ፣
በማይረባ ምክንያት ወደ መቃብሩ ወረደ ፡፡ በሕይወት
ዘመኑ ውስጥ በጣም አጭር ለሆነ ጊዜ ብቻ ጐስቋላ ኑሮው
የመታደስ አዝማሚያ ታይቶበት ነበር፡፡ በአዲሱ ካፖርት
አምሳያ ደስታና የተስፋ ማገገም የቤቱን ደጃፍ ዘል
ቀው ነበር ፡፡ ይሁንና ደስታውም ሆነ የማንሰራራት አዝ
ማሚያ ማሳየት ጀምሮ የነበረው ሕይወቱ ብዙም ጊዜ
ሳይቆይ እንደገና ተዳፈነ ፡፡ ኃያልና ታላቅ የሚባሉ የዓለ
ማችንን ሰዎች እንደሚያጋጥመው ሁሉ ፣ በርሱም ላይ በደ
ረሰው ከዐቅም በላይ የሆነ ውርጅብኝና መርገምት ሕይ
ወቱ ተንኮታኰተ ፡፡

አካኪይ አካኪየቪች ከሞተ ጥቂት ቀናት ቆይቶ ፣
አንድ የመሥሪያ ቤቱ ዘበኛ ወደ ቀለም ገልባጩ
መኖሪያ መጣ ፡፡ አካኪይ አካኪየቪችን ወደ ሥራ
ቦታው እንዲያቀርበው በዋናዉ ሥራ አስኪያጅ የተላከ
ነበር ፡፡ ብቻውን ወደ መሥሪያ ቤቱ የተመለሰው ዘበኛ
አካኪይ አካኪየቪች እስከ ወዲያኛውም ሥራ ገበታው
ላይ የማይገኝ መሆኑን አስረዳ ፡፡ ‘ ለምን ? ’ የሚል ጥያቄ
ቀረበለት፡፡ ‘ አይ ፣ እሱ እንደሆን ሞቷል፡፡ ቀብሩም ከሦስት
ቀናት በፊት ተፈጽሟል ’ የሚል መልስ ሰጥቶ ደመደመ ፡፡

ለብዙ ዓመታት ያገለገለበት መሥሪያ ቤት የአካኪይ አካኪ
የቪችን ሞት ከተረዳ በኋላ፥በተከታዩ ቀን ሌላ ጸሐፊ በቦ
ታው እንዲቀጠር አደረገ ። አዲሱ ተቀጣሪ ከአካኪይ አካ
ኪየቪች በቁመት ዘለግ ከማለቱ ሌላ፥ጽሑፍ በሚገለብጥ
በትም ጊዜ የብዕር አያያዙና የፊደል አጣጣሉ ለየት ይል
ነበር ።

ነገር ግን ፥ ከሁሉም ከሁሉም በጣም የሚያስገርመው
ነገር፥የአካኪይ አካኪየቪች ታሪክ በዚህ አለማብቃቱ ነው።
ያሳለፈውን ከንቱና አጓጉል ኑሮ እንዲያካክስለት ሆን ተብሎ
የተደረገ ይመስል፥ቀለም ገልባጩ ከሞተ በኋላ ፥ ለጥቂት
ተጨማሪ ቀናት በፒተርስበርግ ከተማ የመኖር ዕድል አግ
ኝቶ ነበር ። የኛም ደረቅ ታሪክ ልዩና የሚያስደንቅ መደ
ምደሚያ እንዲያገኝ መልካም አጋጣሚ ሆነ ።

በካሊንኪን ድልድይና በአካባቢው አንድ ኤኬራ
( መንፈስ ) ሌሊት ሌሊት መታየት የጀመረው አካኪይ
አካኪየቪች ከሞተ በኋላ፥ብዙም ቀን ሳይቆይ ነበር ።ወሬው
ተጋኖ መናፈስ ቀጠለ ። ታዲያ እንደ ወሬው ከሆነ በየም
ሽቱ የሚታየው ኤኬራ የመሥሪያ ቤት ጸሐፊ የሚመስል
ከመሆኑ ሌላ፥ የተሰረቀ ካፖርት እንደሚፈልግ ሁሉ ማዕ
ረግና የሥራ ደረጃ ሳይለይ ፥ እገሌ ከእገሌ ሳይል ፥ በመን
ገድ ሲተላለፍ ያገኘውን ማናቸውንም ሰው ካፖርት የመ
ግፈፍ ጠባይ ነበረው ። በተለይ ባለ ጐፈር ኰሌታ ፥ በቀ
በሮና በድብ ቆዳ የተከፈፈ ወይም በወፍራሙ የተሰፋ ካፖ
ርት በይበልጥ ይፈልጋል የሚል ወሬ ባንድ ሁለት ገርም
በር አገሩን አዳረሰው ። አንድ ምሽት ፥ አካኪይ አካኪ
የቪች በሕይወቱ ሳለ ይሠራበት በነበረው መሥሪያ
ቤት የሚሠራ አንድ ጸሐፊ ፥ ከዚሁ በሰፊው ከሚወራ
ለት ኤኬራ ጋር ተፋጠጠ ። ጸሐፊው ማንነቱን ወዲ
ያው ለይቶ ዐወቀው ። የአካኪይ አካኪየቪች ኤኬራ መሆ



ኑን ለማወቅ ብዙም አላዳገተውም ። ነገር ግን ፥ ደጋ
ግሞና ረጋ ብሎ ለማስተዋል በቂ ድፍረት ስላልነበረው ፥
ከአካባቢው ሽምጥ ጋልቦ ጠፋ ። ከብዙ ቀናት በኋላም ፥
“ ኤኬራው በርቀት ቆሞ ጣቱን በማወዛወዝ ይዝትብኝ
ነበር ” እያለ ሲናገር ተሰምቷል ።

ይህ የሌሊቱ ቀበኛ ኤኬራ ፥ በተከታታይ በፈጸመው
የካፖርት ዘረፋ የተነሣ ብዙ ሰዎች ለብርድ መጋለጣቸ
ውን መነሻ በማድረግ የሚያቀርቡት አቤቱታ ይጐርፍ
ጀመር ። ስለዚህ መንፈሱ ከተቻለ እጅ ከፍንጅ እንዲያዝ ፥
እለያም ደግሞ ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን በተገኘበት
ቦታ ላይ ከባድ ቅጣት እንዲፈጸምበት የሚል ትእዛዝ
ከፖሊስ ተላለፈ ። በትእዛዙ መሠረት ጠንካራ ጥበቃና
ክትትል ይካሔድ ጀመር ። እንዲያውም በአንድ አጋጣሚ
ኤኬራውን ሊይዙት ለጥቂት አመለጣቸው ። ሁኔታው እን
ዲህ ነበር ። በኪርዩሽኪን ድልድይ አካባቢ አንድ የፖ
ሊስ ተራ ወታደር በጥበቃ ሥራው ላይ እንዳለ ወዲያ
ወዲህ ይንጐራደዳል ። ድንገት ያ ፥ መክረሚያውን ብዙ
ሲወራለት የሰነበተ ኤኬራ፥ በጡረታ ላይ ከሚገኙ አንድ
የሸንት ተጫዋች አሮጌ ካፖርት ለመግፈፍ ሲተናነቅ
ወታደሩ ይመለከታል ። በፍጥነት ወደ ትንቅንቁ ይሔ
ድና፥የኤኬራውን ማንቁርት ፈጥርቆ በመያዝ በአቅራቢ
ያው የሚገኙ ሌሎች ፖሊሶች እንዲደርሱለት በጩኸት
ይጣራል ። የሥራ ባልደረቦቹ ተሯሩጠው እንደ ደረሱለት፥
ኤኬራውን አጥብቀው እንዲይዙ ያስረክባቸውና እሱ በቀ
ቀዘ አፍንጫው ላይ ሕይወት ለመዝራት ያህል ቦት
ጫማው ውስጥ የወሸቃትን ትንሿ የሱረት ማጥን አውጥቶ
የአፍንጫውን የቀኝ ቀዳዳ በጣቱ በማፈን በሌላው በኩል
ሱረቱን በሙሉ ኃይሉ ይስባል ። ሱረቱ ፥ እንኳን ሕይ
ወት ላለው ቀርቶ ለበድንም ቢሆን ዋዛ ስላልነበረ፥ኤኬ

ራውን በኃይል ሲያስነጥሰው አንዳች ቀዝቃዛ ነገር በሦስ
ቱም ፖሊሶች ዐይኖች ላይ ይረጫል ። ፖሊሶቹ ዐይና
ቸውን በእጃቸው እያበሱ ሲደነባበሩ ፥ ኤኬራው ከመ
ቅጽበት አፈትልኮ ከአጠገባቸው ጠፋ ።

የሟቹ ቀለም ገልባጭ ኤኬራ በካሊንኪን ድልድይ
ዙሪያ ብቻ ሳይወሰን ፥ እያደር ራቅ ያሉ አካባቢዎችንም
እየጐበኘ ፍርሃት መንዛቱን ቀጠለ—በተለይ በቀላሉ
በሚሸበሩት ልቦች ።

በነገራችን ላይ ፥ ለዚህ እውነተኛ ታሪክ መነሻ ምክ
ንያት የሆነውን ትልቁን ሰው፥እስከ አሁን ረስተነው ቆይ
ተናል። ነገር ግን፥እውነቱን የመናገር ኃላፊነት ያለብን በመ
ሆኑ ፥ አካኪይ አካኪየቪች እንደዚያ ተዋርዶና እንደ ምና
ምን ተቆጥሮ ከቢሮው እንዲባረር ካደረገ በኋላ ፥ በትልቁ
ሰው ልብ ውስጥ እንደ ጸጸት ያለ ስሜት ሳይመላለስበት
እንዳልቀረ መግለጽ ይገባናል ። መቼም ርኅራኄ የሚሉ
ነገር ሙሉ በሙሉ በርሱ ዘንድ የለም ለማለት አይ
ቻልም ። የተሰጠው ሥልጣንና ማዕረግ አፍኖ ያዛቸው
እንጂ ፥ ያስመሳይነት ባሕሪው ገናና ሆኖ ተጫናቸው እንጂ
ልቡስ በሰብአዊ መልካም ስሜቶች የተሞላ ነበር ።
በዚያን ዕለት አብሮ አደግ ጓደኛው ተሰናብቶት ከቢሮው
እንደ ወጣ ፥ ሐሳቡ ሁሉ ወደ ምስኪኑ አካኪይ አካኪየቪች
ተመልሶ ነበር ። መሰንበቻውንም የአካኪይ አካኪየቪች
የገረጣ ፊት ባለማሰለስ በዐይነ ሕሊናው ሲታየው ከረመ ።
በስድብና በቁጣው መዓት ተብረክርኮ ፍርክርኩ ሲወጣና
እንደ ግንብ ተንዶ እግሩ ሥር የዶግ ዐመድ ሲሆን ይታ
የዋል ። የዚያ ምስኪን ሰው ገጽታ ጧት ማታ በአእም
ሮው ሰሌዳ በጉልህ ቅርፅ እየተገለጠ ሕሊናውን ዕረፍት
ስለ ነሣው ፥ ሊረዳው የሚችልበትን መንገድ አጣርቶ እን



ዲያቀርብለት ከጸሐፊዎቹ አንደኛውን ወደ አካኪይ አካኪ
የቪች መኖሪያ ልኮት ነበር ። ይሁን እንጂ ፥ ምስኪኑ ቀለም
ገልባጭ በደረሰበት ኃይለኛ ሕመም የተነሣ ፥ ከዓለም
በሞት መለየቱን ሲሰማ የድንጋጤ ላብ አሰመጠው ።
ጸጸት ልቦናውን ሰተረው ። ሕሊናው የሚያኽርጐደጉደውን
የቫከረ ወቀሳ መቋቋም ከዐቅሙ በላይ ሆነበት ። ቀኑን
ሙሉ መንፈሱ ተሸብሮና ቅዝዝ ብሎ ዋለ ።

ወደ ማታ ገደማ ፥ ደስታና ሰላም የነሣው የአካኪይ
አካኪየቪችን የሞት ዜና ከአእምሮው ለማስወገድና ሌላ
ሌላውንም ነገር ለመርሳት ሲል ፥ አቻዎቹ የሆኑ መኳንንት
ዘወትር ወደሚያመሹበት አንድ ጓደኛው መኖሪያ ቤት
ሔደ ። እንዳሰበውም በጣም ቀለል ብሎትና የተረበሸ መን
ፈሱ ተረጋግቶ ሲያወራ ፥ ሲሥቅ ሲዝናና አመሸ ። እንዲያ
ውም ከእራት ጋር አንድ ሁለት መለኪያ ሻምፓኝ ወርወር
አደረገ ።

ከንደኛው ቤት ተሰናብቶ ከወጣ በኋላ ፥ የሻምፓኙ
ሞቅታና የመንፈሱ መንጠልጠል እንደ መዳራት ፥ እንደ
መጫዎወት ... ያለ ስሜቱን ስለ ቀሰቀሰበት ፥ በቀጥታ ወደ
ቤቱ በመሔድ ፋንታ ካሮላይና አይቫኖቭና ትዝ አለችው ።
ጀርመናዊ ደም ካላት ወዳጁ ጋር ትንሽ የፍቅር ሰዓ
ቶችን ማሳለፍ አማረው ። ትልቁ ሰው ከወጣትነት ዕድሜ
ብዙ የራቀና በልጆች የበለጸገ ትዳር አባወራ ነበር ። ከሁ
ለቱ ወንዶች ልጆች አንደኛዉ በመንግሥት መሥሪያ ቤት
ተቀጥሮ ያገለግላል ። ትንሽ ደፍጠጥ ቢልም ደስ የሚል
አፍንጫ ያላትና በየማለዳው እጁን እየሳመች ፥ ‘ ቦንዡር
ፓፓ ’ በሚል የፈረንሣይ ልሳን ሰላምታ ያስለመደችው
የዐሥራ ስድስት ዓመት ኮረዳም አባት ነው ። ባለቤ
ቱም ብትሆን እስከዚህ ለማጋነን አያመች እንደሆን ነው
እንጂ ፥ ጐኑ ሻጥ ሲያደርጋት በቂ የሆነ መልክ አላጣችም

ነበር ። የትልቁ ሰው ቤተሰብ እንዲህ የተሟላና አስደሳች ቢሆንም ፤ በከተማው ሌላ ክፍል ከምትኖረውና በዕድሜም ሆነ በውበት ከሚስቱ ከማታንሰው ዕቁባቱ ጋር የሚጋራውን ልዩ ፍቅር ከመንከባከብ አልቦዘነም ነበር ። እናም ታዲያ በዚያን ምሽት ፤ ትልቁ ሰው በበረዶ በሚንሸራተት ጋሪው ተደላድሎ ከተቀመጠ በኋላ ‘ በቀጥታ ወደ ካሮላይና አይቫኖቭና መኖሪያ ቤት ! ’ ሲል ለነጂው ትእዛዝ ሰጠ ። በሚሞቀው ምቹ ካፖርቱ ተጠቅልሎ ፤ ሳይፈልጋቸውና ሳይጠራቸው በአእምሮው ዙሪያ ያሰፈሰፉ ደስ ደስ የሚሉ ሐሳቦችን ማሰላሰል ያዘ ። በራት ግብዣው ላይ ያሳለፋቸው አስደሳች ሰዓቶች ትውስ አሉት ። በጭውውት ጣልቃ ጣል ተደርገው ፤ እንባውን እስኪጨርስ ያሣቁት ቀልዶች ትዝታ እንደገና ሊያሥቀው ቃጣው ። ብቻ ምን ያደርጋል ! ደስ ደስ ቢለውም ያን ልዩ የሆነ ስሜቱን በምን ምክንያት ፤ ከየት አቅጣጫ እንደ መጣ የማይታወቅ ንፋስ አሁንም አሁንም ጣልቃ እየገባ ደፍረስ ያደርግበታል ። ፊቱ ላይ የበረዶ ፍንጣቂዎችን ያሳርፍና የካፖርቱን ክሳድ ወደ ላይ ይቀለብስበታል ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ድንገት አንዳች ነገር አንገትጌውን በኃይል ጭምድድ አድርጎ ሲይዘው ታወቀው ። አንገቱን በፍጥነት ወደ ኋላ ጠምዘዞ ሲመለከት ፤ አሮጌ የደንብ ልብስ ያጠለቀ አንድ ትንሽ ሰው አለ ። አካኪይ አካኪየቪች መሆኑን ሲረዳ ይህ ነው የማይባል ድንጋጤ ፤ መሐል አናቱን ሲበረቅሰው ተሰማው ። የሽማግሌው ጸሐፊ ገጽ እንደ በረዶ ነጭ ሆኖ አስከሬን ይመስላል ። መንፈሱ በበቀል ስሜት አፉን ማጣመምና ማጨማደድ ሲጀምር፣ትልቁ ሰው ገደብ በሌለው የሽብርና የፍርሃት ማጥ ውስጥ ዘቀጠ። የአካኪይ አካኪየቪች ኤኬራ ከመቃብር ሽታ ጋር የሚመሳሰል ትንፋሽ እየተነፈሰ ፤ “ ታዲያስ ፤ ጌታው ! በመጨ



ረሻ ተገናኘን አይደለም ? አንገትህ በመዳፌ ውስጥ ገባ ! አሁን ካንተ የምፈልገው ካፖርትህን ብቻ ነው ! በችግር ጊዜ ልትረዳኝ ሲገባህ ፤ በስድብና በውርደት አሠቃይተህ እንደ ተኰነነች ነፍስ ከቢሮህ አባረርከኝ ። ስለዚህ አሁን የበቀል ተራዬን የምወጣበት ሰዓት ነውና ካፖርትህን በቶሎ አስረክበኝ ! ” ሲል ጮኸበት ።

አይደነግጡ ዐይነት ድንጋጤ የደነገጠው ትልቁ ሰው ፤ ነፍሱ ምንጥቅ ብላ ከሰውነቱ እንደ ወጣች ሁሉ ወዲያው በድን ሆነ ። ያ ፤ በምቾት የደለበ ግዙፍ አካል፣ እሳት እንዳየው ጅማት ኩምትርትር ብሎ ጭብጦ አከለ ። የሚመካበት ጥንካሬውና ለምንዝሮቹ የሚያሳየው ኃያልነት ሁሉ ከመቅጽበት ገደል ገባ ። በፍርሃት የሚርበተበቱት እጆቹ ለማድረግ በሚችሉት ፍጥነት ካፖርቱን አውልቆ ወረወረና የርሱ ባልሆነ ባዕድ ድምፅ ፤ “ አዙርና በቀጥታ ወደ ቤቴ ውሰደኝ ! ” አለው ጋሪ ነጂውን ። ያን የተለየ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙት ጊዜ ብቻ የሚፈጠር ልዩ ዐይነት ድምፅ የሰማው ጋሪ ነጂ ጅራፉን በኃይል አጣቀሰና ጋሪውን አስፈተለከው ። ከስድስት ደቂቃዎች በኋላ ፤ ወደ ካሮላይና ኢይቫኖቭና ቤት የመሔድ ዕቅዱ ተሰርዞ፣ፊቱን ዐመድ የነፋበት መስሎና ካፖርቱ ከላዩ ተገፍፎ ትልቁ ሰው ቤቱ ደጃፍ ደረሰ ። ወደ መኝታ ክፍሉ እንደ ምንም እየተንገዳገደ ገብቶ ቢተኛም ፤ እንቅልፍ የሚሉ ባይኑ ሳይዞር አደረ ። ጧት ሲነሣ ውቃቢ ርቆት ፤ ምጌው ወጥቶ ያየችው ሴት ልጁ፣ “ ውይ አባባ ፊትህ ክፉኛ ገርጥቷል ! ” የሚል አስተያየቷን ከመሰንዘር አልተቆጠበችም ። አባባ ትልቁ ሰው ግን ፤ በዚያ ጉደኛ ምሽት ስለ ደረሰበት ነገር አንዲት ቃል እንኳን ትንፍሽ ሳይል ቀረ ። የዚያ ገጠመኝ ውጤት ኃይለኛ ነበር ። በአካሉና በመንፈሱ ፤ በጠቅላላ በእሱነቱ ላይ ክፍተኛ ለውጥ አስከተለበት ። ከዚያ ቀን በኋላ ፤ “ እን

ዴት ብትደፍር ነው ? ጃል ! . . . ለመሆኑ ከማን ፊት እንደ ቆምክ ታውቃለህ ? ” በሚል ድንፋታ የበታቾቹን ቀልብ መግፈፉን እርግፍ አድርጎ ተወው ። እንዳጋጣሚ ሆኖ እነዚህን ቃላት ቢሰነዝርም እንኳን ፣ በቅድሚያ ሌላው ሰው የሚናገረውን በአንክሮ ከአዳመጠ በኋላ ብቻ ነበር ።

ያ ፣ ኤኬራ የሚፈልገው ነገር የትልቁን ሰው ካፖርት ስለ ነበር ፣ ከዚያ ታሪከኛ ምሽት በኋላ በቅዱስ ፒተር ስቡርግ ከተማ መታየቱን አቆመ ። ለየፖሊስ ጣቢያው ይቀርብ የነበረው የካፖርት ዘረፋ ክስ ወዲያውኑ ተቋረጠ።



# ቪላድሚር ግላክቲዮኖቪች ኮሮሌንኮ

(1853—1921)



በ1852 ሰኔ 27 ቀን ብኡክሬይን ግዛት ፣ ዥቶሚር በምትባል ሥፍራ ተወለደ ። ኮሮሌንኮ ገና የዐሥራ አምስት ዓመት ወጣት ሳለ አባቱ በመሞቱ የተነሣ ፣ በትውልድ አካባቢው ለመኖር አዳጋች ስለ ሆነበት ፣ ትምህርቱን ለመቀጠልና የኑሮውን መሠረት ለመጣል ፣ ወደ ቅዱስ ፒተር ስቡርግ ከተማ አመራ ። ግን በዚያም ሁኔታዎች አመቺና ቀላል አልሆኑለትም ። ከባድ የሕይወት ትግልና ውጣ ውረድ አፋጠጠው ። በተለይም በነጻ አመለካከቱና ለቄሣራዊው የዘውድ አገዛዝ በነበረው የከረረ ጥላቻ ሳቢያ ፣ ከሚማርበት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የመባረርና በኋላም የመጋዝ ዕጣ ገጠመው ። በዚህም መንስኤ በፖለቲካ ፖሊሶች ትኩረትና ጥቋር መዝገብ ውስጥ ገባ ።

በየዳር አገሩ ብዙ የግዞትና የሥቃይ ዘመናትን ካሳለፈ በኋላ ፣ ነጻ ኑሮ ሲጀምር የሥነ ጽሑፍ ሥራውን ተያያዘው። ከአፍላ የወጣትነት ዕድሜው እንሥቶ መጋዝና መንከራተት ከገበሬውና በጠቅላላውም ለጉልተኛው ሥርዓት ከተ

ዶት ብትደፍር ነው ? ጃል ! . . . ለመሆኑ ከማን ፊት እንደ ቆምክ ታውቃለህ ?” በሚል ድንፋታ የበታቾቹን ቀልብ መግፈፉን እርግፍ አድርጐ ተወው ። እንዳጋጣሚ ሆኖ እነ ዚህን ቃላት ቢሰነዝርም እንኳን ፣ በቅድሚያ ሌላው ሰው የሚናገረውን በአንክሮ ከአዳመጠ በኋላ ብቻ ነበር ።

ያ ፣ ኤኬራ የሚፈልገው ነገር የትልቁን ሰው ካፖ ርት ስለ ነበር ፣ ከዚያ ታሪከኛ ምሽት በኋላ በቅዱስ ፒተር ስቡርግ ከተማ መታየቱን አቆመ ። ለየፖሊስ ጣቢያው ይቀርብ የነበረው የካፖርት ዘረፋ ክስ ወዲያውኑ ተቋረጠ።



# ቪላድሚር ግላክቲየኖቪች ኰሮሌንኰ

(1853—1921)



በ1852 ሰኔ 27 ቀን በኡክሬይን ግዛት ፣ ዥቶሚር በምትባል ሥፍራ ተወለደ ። ኰሮሌንኮ ገና የዐሥራ አም ስት ዓመት ወጣት ሳለ አባቱ በመሞቱ የተነሣ ፣ በትውልድ አካባቢው ለመኖር አዳጋች ስለ ሆነበት ፣ ትምህርቱን ለመ ቀጠልና የኑሮውን መሠረት ለመጣል ፣ ወደ ቅዱስ ፒተር ስቡርግ ከተማ አመራ ። ግን በዚያም ሁኔታዎች አመቺና ቀላል አልሆኑለትም ። ከባድ የሕይወት ትግልና ውጣ ውረድ አፋጠጠው ። በተለይም በነጻ አመለካከቱና ለቄ ሣራዊው የዘውድ አገዛዝ በነበረው የከረረ ጥላቻ ሳቢያ ፣ ከሚማርበት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የመባረርና በኋ ላም የመጋዝ ዕጣ ገጠመው ። በዚህም መንስኤ በፖለቲካ ፖሊሶች ትኩረትና ጥቁር መዝገብ ውስጥ ገባ ።

በየዳር አገሩ ብዙ የግዞትና የሥቃይ ዘመናትን ካሳለፈ በኋላ ፣ ነጻ ኑሮ ሲጀምር የሥነ ጽሑፍ ሥራውን ተያያዘው። ከአፍላ የወጣትነት ዕድሜው አንሥቶ መጋዝና መንከራ ተት ከገበሬውና በጠቅላላውም ለጉልተኛው ሥርዓት ከተ

ጋልጠው የኅብረተሰቡ ክፍል ጋር በመቀራረብ ፣ ከችግራቸ
ውና ከጉስቋላ ሕይወታቸው ለመጋራት አመቺ ሁኔታን
ስለ ፈጠረለት ፣ የሕዝቡን እስከሬ የኑሮ ገጽታ ባልተበረዘ
እውነታና በጠንካራ ሐቅ በሥነ ጽሑፍ ሥራዎቹ ውስጥ
ለማቅረብ ችሏል ። ሰፊው ሕዝብ ሠርቶ የሚጠቀምበትን
የጠራ ቋንቋ ፣ ዘይቤና ፈሊጥ እንዳለ በድርሰቶቹ ውስጥ
ሊገለገልበት የቻለውም ከዚሁ ተጨባጭ ልምዱ የተነሣ
ከመሆኑ ሌላ ፣ የፈጠራ ሥራዎቹ የተዋቡ ሆነው አድ
ናቆትንና ሕያውነትን እንዲያገኙ ምክንያት ሆኗቸዋል ።
ለዚህም ነው ሊዎ ቶልስቶይ አንድ ጊዜ የኰሮሌንኮን
ሥራዎች ሲገመግም ፣ "በመላው የሩሲያ ሥነ ጽሑፍ
ውስጥ የኰሮሌንኮን የቋንቋ ችሎታና አስደናቂ የአ
ጻጻፍ ውበት የሚወዳደር ሥራ አላየሁም" በማለት የተ
ናገረው ።

ኰሮሌንኮ ከሥነ ጽሑፍ ሥራውጉን የሕዝቡን ችግርና
ብሶት ለማቃለል ፣ ዐቅሙ የፈቀደውን ጥረት ከማድረጉ
ሌላ ፣ ብዕሩ የሩሲያን ድሃ ገበሬ ሕይወት ትክክለኛ ሥዕል
ከመንደፍና የጭቆናና የግፍ ተግባሮችን ከማጋለጥ ቶቆ
ጥባ አታውቅም ነበር ። ሕዝቡ ፣ 'የሩሲያ ሕሊና' የሚል
ቅጽል ስም እስከ መስጠት የደረሰው በዚሁ የተነሣ መሆኑ
ይነገራል ። በሌላ በኩል ደግሞ ወጣት ደራሲያንን በማበ
ረታታትና በመምከር ረገድ ፣ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው
በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመምህርነት ተግባር ይፈ
ጽም ስለ ነበር ፣ ከደቀ መዛሙርቱ መሐል እንደ ማክ
ሲም ጐርኪ ያለ ታላቅ የብዕር ሰው ለማፍራት በቅቷል ።

የኰሮሌንኮ የሥነ ጽሑፍ ችሎታ እያደገና እየዳበረ
በሔደ ቁጥር ' ዐይነ ሥውር ሙዚቀኛ ' እንደ ተሰኘው
ዐቢይ ልብወለድ ያሉ ዘለዓለማዊ ሥራዎችን ለማበርከት
ችሏል ። ኰሮሌንኮ በላቀ የፈጠራ ችሎታውና ባለገኞች



ውም የጥበብ ውጤቶች የተነሣ ፣ የሩሲያ የሥነ ጥበብ አካ
ዳሚ አባል ለመሆንም በቅቶ ነበር ። ይሁን እንጂ ፣ ማክሲም
ጐርኪ የዚሁ አካዳሚ የክብር አባል እንዲሆን በተመረጠ
ጊዜ የወቅቱ ንጉሥ ፣ ኒኮላይ ዛር ምርጫውን በማገዱ ፣ ኰሮ
ሌንኮ ይህን አምባገነናዊ ርምጃ የሚቃወም መሆኑን ለማ
ሳየት ሲል ፣ የራሱን አባልነት በፈቃዱ ሠርዞ ከአካዳሚው
ተሰናብቷል ።

ኰሮሌንኮ በረጃጅም ልቦለዶች ብቻ ሳይሆን ፣ በአጫ
ጭር ድርሰቶች አጻጻፍም ረገድ ልዩ የሆነ ሥልትና ተሰ
ጥኦ ነበረው ። በመሆኑም በዚህ የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ በር
ከት ያሉ ሥራዎችን ትቶልን ያለፈ ሲሆን ፣ በዚህ መጽሐፍ
ውስጥ የሚገኘው ' የማልረሳት ልዩ ወጣት ' በሚል
ርዕስ ተተርጉሞ የቀረበው አጭር ልቦለድ ተደናቂ ከሚ
ባሉት ተራ የሚመደብ ነው ።

ከሩሲያ የሥነ ጽሑፍ አውራዎች አንዱ የሆነው
ይህ ሰው ፣ በ69 ዓመት ዕድሜው በ1921 ከዚህ ዓለም
በሞት ሲለይ ፣ አስቸጋሪና ውስብስብ የነበረውን ረጅም
የትግልና የሥነ ጽሑፍ ሕይወቱን ፣ "እሾሃማ የጀግና
መንገድ" በማለት ሰይሞታል ፣ ማክሲም ጐርኪ ።

# የማልረሳት ልዩ ወጣት

“ የማረፊያ ጣቢያ ወዳለበት ለመድረስ ገና ብዙ ያስኬደናል ? ” ጥያቄው የቀረበው ለሠረገላ ነጂው ነው ።

“ እሱስ እምብዛም ሩቅ አይደለም ። ግን ከማዶ የመጣው የበረዶ ውሽንፍር ሳይጠምደን ወደ ጣቢያው የምንደርስ አይመስለኝም . . . . ”

እውነትም የበረዶው ዶፍ በፍጥነት እየተቃረበ መጣ። ከምሽቱ ጋር አብሮ የሰፈነው ቀዝቃዛ አየር ሥጋን ዐልፎ አጥንትን ይሸነቁጣል ። መሬቱ ላይ የተጋገረው በረዶ ከሠረገላዋ ተንሸራታች እግሮች ሥር እየተሰነጣጠቀ ሲሰባበር ይሰማል ። ኃይለኛው የክረምት ነፋስ በመንገዱ ግራና ቀኝ በተገጠገጡት ዛፎች መሐል እየተውዘገዘገ ሲያፏጭ ፤ ቅርንጫፎቻቸው ወደ መንገዱ ዝቅ ብለው የተንጠለጠሉት የጽድ ዛፎች ደግሞ ፤ እየተጫጫኑ በሔደው ጽልመት ውስጥ በኩርፊያ መልክ ይወዛወዛሉ ።

ሠረገላዋ ጠባብ ስለ ሆነች ምቾት የላትም ። ከመንገዱ ማንገላታት ይበልጥ የሚያበሳጨው ደግሞ ብርዱ ነው ። ትንሿ ሠረገላ በተበላሸው መንገድ ላይ በተንገጫገጨች ቁጥር ጐንና ጐኔ እንደ ብረት ሲቀጠቀጥ ከአጥንቶቼ አንዱ የተሰነጠረ ይመስለኛል ። በጉዞው ንቅናቄ የተነሣ ፤ በሠረገላዋ ላይ የተንጠለጠሉት ትንንሽ ቃጭሎች ወደ ፊትና ወደ ኋላ ፤ ወደ ግራና ወደ ቀኝ እየተወዛወዙ በየደቂቃው ኃይሉን ከሚጨምረው የውሽንፍሩ



ድምፅ ጋር የሚስማማ ረኸምና የማላዘን ዐይነት [illegible] ሰሙ ፤ አጠገቤ የተቀመጡት ፖሊሶች የታጠቋቸው [illegible] ጦችና ሰይፎች ደግሞ ወዲያና ወዲህ ይወናጨፋሉ ።

በላያችን ላይ ውሽንፍሩ መውረድ ከጀመረ በኋላ ጉዟችን እምብዛም አልተራዘመም ። ከበረዶው ጋር [illegible] ከሚያጉረመርመው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ጠርዝ ላይ ፤ የማረፊያው ጣቢያ መብራቶች ብቅ ሲሉ ጮቤ የሚያስረግጥ ደስታ ተሰማን ።

ሠረገላዋ ከጣቢያው ደርሳ ስትቆም ፤ አጅበውኝ የሚጓዙት ፖሊሶች የጦር መሣሪያዎቻቸውን እያንኳኩ ወርደው በረዶውን ከልብሳቸው ላይ ማራገፍ ጀመሩ ። የማረፊያ ጣቢያ የምትባለው አንዲት ትንሽ ጐጆ ናት ። ወደዚያች የደከመ ብርሃን ጭል ጭል የሚልባትና በጢስ የታፈነች ሞቃት ጐጆ ስንገባ ፤ አንዲት ሴት የተፈለጡ ዕንጨቶችን በምድጃው ላይ እየደረደሩ እሳት ለማያያዝ ይዘጋጃሉ ። የጐጆዋ ባለቤት ናቸው ።

“ እሜቴ የሚበላ ነገር ይኖርዎታል ? ” ከእኛ በኩል የቀረበ ጥያቄ ነበር ።

“ ኧረ በቤቱም የሚላስ የሚቀመስ የለ . . . . ” አሉ ሴትዮዋ ።

“ዓሣ እንኳን የላችሁም ? . . . ወንዙ እንደሁ በደጃፋችሁ ነው የሚያልፍ ። ”

“ ነገሩስ ነው ። ግን በዚያ ሰሞን አንዳች የባሕር አውሬ መጥቶ ዓሣውን ሁሉ ሙልጭ አድርጎ በልቶት ከሔደ በኋላ ምን አለ ብላችሁ ! ”

“ ታዲያ ድንች እንኳን አያገኙልንም ? ”

# የማልረሳት ልዩ ወጣት

“የማረፊያ ጣቢያ ወዳለበት ለመድረስ ገና ብዙ ያስኬደናል ?” ጥያቄው የቀረበው ለሠረገላ ነጂው ነው ።

“እሱስ እምብዛም ሩቅ አይደለም ። ግን ከማዶ የመጣው የበረዶ ውሽንፍር ሳይጠምደን ወደ ጣቢያው የምንደርስ አይመስለኝም . . . .”

እውነትም የበረዶው ዶፍ በፍጥነት እየተቃረበ መጣ። ከምሽቱ ጋር አብሮ የሰፈነው ቀዝቃዛ አየር ሥጋን ዐልፎ አጥንትን ይሸነቁጣል ። መሬቱ ላይ የተጋገረው በረዶ ከሠረገላዋ ተንሸራታች እግሮች ሥር እየተሰነጣጠቀ ሲሰባበር ይሰማል ። ኃይለኛው የክረምት ነፋስ በመንገዱ ግራና ቀኝ በተገጠገጡት ዛፎች መሐል እየተውዘገዘገ ሲያፏጭ ፣ ቅርንጫፎቻቸው ወደ መንገዱ ዝቅ ብለው የተንጠለጠሉት የጽድ ዛፎች ደግሞ ፣ እየተጫጫነ በሔደው ጽልመት ውስጥ በኩርፊያ መልክ ይወዛወዛሉ ።

ሠረገላዋ ጠባብ ስለ ሆነች ምቾት የላትም ። ከመንገዱ ማንገላታት ይበልጥ የሚያበሳጨው ደግሞ ብርዱ ነው ። ትንሿ ሠረገላ በተበላሸው መንገድ ላይ በተንገጫገጨች ቁጥር ጕንና ጐኔ እንደ ብረት ሲቀጠቀጥ ከአጥንቶቼ አንዱ የተሰነጠረ ይመስለኛል ። በጉዞው ንቅናቄ የተነሣ ፣ በሠረገላዋ ላይ የተንጠለጠሉት ትንንሽ ቃጭሎች ወደ ፊትና ወደ ኋላ ፣ ወደ ግራና ወደ ቀኝ እየተወዛወዙ በየደቂቃው ኃይሉን ከሚጨምረው የውሽንፍሩ



ድምፅ ጋር የሚስማማ ረኸርምና የማላዘን ዐይነት [illegible] ሰሙ ፣ አጠገቤ የተቀመጡት ፖሊሶች የታጠቁትም [illegible] ጦችና ሰይፎች ደግሞ ወዲያና ወዲህ ይወናጨፋሉ ።

ቡላያችን ላይ ውሽንፍሩ መውረድ ከጀመረ በኋላ ጉዟችን እምብዛም አልተራዘመም ። ከበረዶው ጋር [illegible] ከሚያጉረመርመው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ጠርዝ ላይ ፣ የማረፊያው ጣቢያ መብራቶች ብቅ ሲሉ ጮቤ የሚያስረግጥ ደስታ ተሰማን ።

ሠረገላዋ ከጣቢያው ደርሳ ስትቆም ፣ አጅበውኝ የሚጓዙት ፖሊሶች የጦር መሣሪያዎቻቸውን እያንኳኩ ወርደው በረዶውን ከልብሳቸው ላይ ማራገፍ ጀመሩ ። የማረፊያ ጣቢያ የምትባለው አንዲት ትንሽ ጐጆ ናት ። ወደዚያች የደከመ ብርሃን ጭል ጭል የሚልባትና በጢስ የታፈነች ሞቃት ጐጆ ስንገባ ፣ አንዲት ሴት የተፈለጡ ዕንጨቶችን በምድጃው ላይ እየደረደሩ እሳት ለማያያዝ ይዘጋጃሉ ። የጐጆዋ ባለቤት ናቸው ።

“እሜቴ የሚበላ ነገር ይኖርዎታል ?” ከእኛ በኩል የቀረበ ጥያቄ ነበር ።

“እረ በቤቱም የሚላስ የሚቀመስ የለ . . . .” አሉ ሴትዮዋ ።

“ዓሣ እንኳን የላችሁም ? . . . ወንዙ እንደሁ በደጃፋችሁ ነው የሚያልፍ ።”

“ነገሩስ ነው ። ግን በዚያ ሰሞን አንዳች የባሕር አውሬ መጥቶ ዓሣውን ሁሉ ሙልጭ አድርጎ በልቶት ከሔደ በኋላ ምን አለ ብላችሁ !”

“ታዲያ ድንች እንኳን አያገኙልንም !”

“ አይ ጌቶቼ! የዘንድሮ ውርጭ እንዲህ ዋዛ! ድንቼን ሁሉ ድምጥማጡን አጥፍቶት ምን አገኘን መሰላችሁ ።”

ጥያቄና መልሱ ሲያበቃ የሻይ ማፍያው ‘ ሳሞቫር ’ * ተጣደና ትኩስ ሻይ ጠጣን ። አካላችን በመጠኑም ቢሆን ሞቅ አለ ። ሁኔታችን አሳዝኖአቸውም እንደሆን እንጃ ፣ ሴትዮዋ ቁራሽ ዳቦና ጥቂት ራስ ቀይ ሽንኩርት አቅርበውልን ወስፋታችንን በዚያ ለመሸንገል ሞከርን ። ከውጭ ንፋሱ አይሎ አንዴ ያጉረመርማል ፤ አንዴም ያፏጫል ። እንደ ዱቄት የላመ በረዶ በንፋሱ ኃይል እየተነነ በመስኮቱ መስተዋትና በማገሩ ላይ ይመረጋል ። ለክፍሉ ብርሃን እንዲሰጥ እማካይ ሥፍራ ላይ በተቀመጠው ፋኖስ ክር የተለኮሰችው ትንሽ ነበልባል በመጥፋትና በመልማት መካከል እየተርገበገበች ትስለመለማለች ።

“ በንዲህ ያለው በረዶና ንፋስ ጉዞ መቀጠሉ ደግ አይደለም ። እዚሁ አድራችሁ ጧት ብትሔዱ ነው የሚበጅ ” አሉ ሴትዮዋ ።

“እዎ!እውነት ብለዋል።አድረን መሔዱ ይሻለናል።” ከፖሊሶቹ አንደኛዉ የሴትዮዋ አስተሳሰብ የሚደገፍ መሆኑን አረጋገጠ ።

ድንገት በክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ። የማረፊያው ቤት ባለቤት የሥራ ዕቃዎቻቸውን አነሣሡና መብራቱን አጥፍተው ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ ። ጨለማና ጸጥታ ዋጠን ። ዐልፎ ዐልፎ ከሚሰማው የንፋሱ ድምፅ በስተቀር አካባቢው እርጭ አለ ።

---

* ሳሞቫር ፣ ሩሲያውያን ሻይ ለማፍላት የሚጠቀሙበት ልዩ ዐይነት መግሪያ ፣ በከሰል እሳትና በኤሌክትሪክ የሚሠራበት ነው ።



ብለው ብሠራው እንቅልፍ እምቢ አለኝ ። ከቤቱ ውጪ እያስገመገመ የሚውዘገዘገው ንፋስ የሚያሳድዳቸው ይመስል ፣ የተለያዩ ሐሳቦች እየተከታተሉ በአእምሮዬ ሜዳ ያቋርጡ ጀመር ። አንዱ ሲያልፍ ሌላው ይተካል ፤ አንዱ ሲመጣ የቀደመው ሥፍራ ይለቃል ።

በማረፊያው ጣቢያ አድረን መሔዱ እንደሚሻል ልሴትዮዋ የገለጠው ፖሊስ ድንገት በጨለማው ውስጥ፣ “ አልተኛህም እንዴ ? ” ሲል ጠየቀኝ። በአነጋገሩ ትሑት ፣ የደስደስ ያለውና የሚወደድ ዐይነት ሰው ነው ። የሌሎቹ ሁለት አጃቢ ፖሊሶች አለቃ መሆኑን ያወቅሁት ፣ በጉዟችን መጀመሪያ ላይ ነበር ። ነገረ ሥራው ቀልጣፋ ከመሆኑ በላይ በሥራውም ታታሪ ይመስላል ። አንዳንድ የማያስፈልጉና የተንዛዙ ደንቦችና ትእዛዞች እንዲከበሩ የማስገደድ ችኩነት አያሳይም ።

“ በጭራሽ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም ” አልኩት ፣ ለጥያቄው ምላሽ እንዲሆነው ።

ለጥቂት ጊዜ ሁለታችንም ሳንነጋገር በጨለማው ውስጥ በጸጥታ ቆየን ። እርሱም እንደ እኔ እንቅልፍ እምቢ ብሎት ከሐሳቦቹ ጋር እንደሚታገል ተሰማኝ ። በጸጥታው መሐል የሚሰማ ድምፅ ቢኖር ፣ እንቅልፍ ከጣላቸው ሁለቱ ፖሊሶች አንደኛዉ በእንቅልፍ ልቡ የሚያሰማው ማጉተምተም ብቻ ነበር ። ንፋሱ ተማ እያለ ሔዷል ።

“እናንተ የተማራችሁና በጥሩ እንክብካቤ ያደጋችሁ ወጣቶች ፣ ሕይወታችሁን የሚጎዳ እንዲህ ያለ ተግባር ለምን እንደምትፈጽሙ ሊገባኝ አልቻለም ” አለኝ እንቅልፍ እምቢ ብሎት የሚቸገረው የፖሊሶቹ አለቃ ፣ ጎርናና ድምፁ በጨለማውና በጸጥታው ውስጥ እያስገመገመ ።

“ እንዴት ያለ ተግባር? ” አልኩት ።

" ለምን የማያውቅ ለመምሰል ትሞክራለህ ፤ ከልጅ ነትህ ጀምሮ በእንዲህ ያለ ሁኔታ እንዳልኖርክ መቼም ግልጽ ነው " አለ ።

" ታዲያ ምን አለበት ? አንዳንድ ጊዜ የማያውቁት ንና ያልለመዱትን መሞከር . . . "

"እና በአሁኑ ሁኔታህ ተደስተሃል ማለት ነው ? " አለኝ ፣ ጥያቄው የመጠራጠር ዐይነት ነበር ።

" አንተስ ? . . . . . በራስህ ሁኔታ ደስተኛ ነህ ? " አልኩት መልሼ ።

ወታደሩ ጋቭሪሎቭ ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብሎ ቆየ ። በሐሳብ የተዋጠ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል ።

" ምኑ ደስተኛ ነው ብለህ ። ምንም ደስታ የለኝም " አለና በማያያዝ ፣ " በተለይ አንዳንዴ ቁጭ ብዬ ሳስበው ለምን ቁም ነገር እንደምውል ፣ መኖሬ ምን ጥቅም እን ደሚሰጥ አልገባህ እያለኝ እቸገራለሁ ። "

" ሥራህ ይከብድሃል ? "

" ሥራውማ እንደምታየው ሥራ ነው . . . መቼም እንዳንተ ያሉ ግዞተኞችን አጅቦ ከቦታ ቦታ ማድረስ ፣ ሽርሽር መውጣት ማለት አይደለም ። አለቆቻችን ደግሞ የዋዛ እንዳይመስሉህ ፤ በጣም ኃይለኞች ናቸው ። ቢሆንም ግን ዋናው ቁም ነገር ያ ሳይሆን . . . " ንግግሩን አንጠ ልጥሎ ተወው ።

" ታዲያ ምንድነው " አልኩት ፣ ንግግሩን እንዲ ቀጥል ለመገፋፋት ያህል ።

" ማን ያውቃል ብለህ . . . " አለና እንደገና ወደ ጸጥታው ተመለሰ ። እኔም በዝምታው ተባበርኩት ። ትንሽ ቆይቶ ፣



" የኛ ሥራ " ሲል ጀመረ ። " የኛ ሥራ ዘወትር ንቁና ቀልጣፋ መሆንን ይጠይቃል ። ያ ነው ዋናው ቁም ነገር ። እኔ ግን የአገልግሎት ጊዜዬ በቅርቡ ስለሚፈጸም ፣ ወደ ትውልድ ሥፍራዬ ለመመለስ እያሰብኩ ነው ። እንደ ዕድል ሆኖ በሠራዊቱ ውስጥ ጥሩ ስም ስላለኝ ፣ አዛዦችን በሥራው ላይ እንድቆይ ጠይቆኛል ። ይሁን እንጂ ፣ ወደ ገጠር ተመልሼ ምን እንደምሠራ ግን ለራሴም ቢሆን ገና አላወቅሁትም " አለ ቅዝዝ ባለ አንደበት ።

"ታዲያ በሥራህ ላይ ትቆያለህ ማለት ነው ? " አልኩት ።

" መቆየትስ አልቆይም ። ነገር ግን ወደ ትውልድ ሥፍራዬ ተመልሼ ከረሳሁት የገጠር ኑሮና የግብርና ሥራ ጋር ፣ እንዴት አድርጌ እንደምላመድ ጨርሶ አልታይህ ብሎኛል " አለ ።

" ታዲያ የራስህን ቆራጥ ውሳኔ መስጠት እንጂ ማመ ንታቱ ምን ይጠቅማል " አልኩት ።

ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብሎ አሰበና ፣

" አንድ ታሪክ ልነግርህ እፈልጋለሁ ። የማትሰለች ከሆነ አንድ ጊዜ ስላጋጠመኝ ሁኔታ ባጫውትህ ደስ ይለ ኛል " አለ ይበልጥ ትሑት በሆነ አነጋገር ።

" ግድየለም አጫውተኝ " በማለት ፣ ለመስማት ያለ ኝን ፈቃደኝነት ገለጽሁለት ።

ወዲያው ወደ ግዞት ቦታዬ እኔን ለማድረስ በአጃቢ ነት አብሮኝ የሚጓዘው ፖሊስ ጋቭሪሎቭ ፣ ታሪኩን እንዲህ ሲል መጀረ ።

2

"አሁን በምገኝበት ሠራዊት ውስጥ ሥራ የጀመር ኩት በ1874 ዓ.ም. ነው ። አዲስ ተመልምለን ከተቀጠር

ነው ወታደሮች መሐል ተመርጬ በቀጥታ በፈረሰኛ ክፍሃ ውስጥ እንድመደብ ተደረገ ። በሚገባ ማገልገል ጀመርሁ ። የዐቅሜን ያህል ማለት ነው ። መቼም የኛ አገር የውትድርና ሕይወት ምን እንደሚመስል ታውቀዋለህ ! አንዴ ሠልፍ እንወጣለን ። አንዴ በቲያትር ቤት ደጃፍ ዘብ እንድንቆም እንመደባለን ። ስንቱ ተቆጥሮ ! ሥራው ብዙ ነው ። ታዲያ ይመስገነውና ያኔም ቢሆን በቅጡ ማንበብና መጻፍ እችል ስለ ነበር ፥ ቀስ በቀስ በአለቆቼ ዘንድ ታዋቂነት ማግኘት ጀመርሁ ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ደግሞ ፥ እኔ የተመደብሁበትን ክፍል የሚያዘው ሻለቃ ያገሬ ሰው ነበር ። የማሳየውን ጥረትና ትጋት በመመልከት ይመስለኛል ፥ አንድ ቀን ሻለቃዉ ወደ ቢሮው አስጠርቶኝ ፥ ‘ ጋቭሪሎቭ የሃምሳ አለቅነት ማዕረግ እንድታገኝ ለማድረግ አስቤአለሁ . . . ለመሆኑ ከተቀጠርክ ጀምሮ የፖለቲካ እስረኞችን ወደ ግዞት ቦታቸው አጅቦ በማጓጓዝ ግዳጅ ላይ ተሠማርተህ ታውቃለህ ? ’ ሲል ይጠይቀኛል ። ‘ ፀጭራሽ ጌታዬ ’ የሚል መልስ ሰጠሁት ። ‘ እንግዲያስ በሚቀጥለው ጊዜ እስረኞች ወደ ግዞት ቦታቸው ሲጓጓዙ በአጃቢነት ተመድበህ ትሔዳለህ። ሥራው ቀላል ነው። እምብዛም አያስቸግር’’ በማለት ሲያሰናብተኝ ፥ እኔም ግዳጄን በሚገባ ለመወጣት ዝግጁ መሆኔን ከሰላምታ ጋር አረጋግጬ ከቢሮው ወጣሁ። እውነትም ከዚያ ጊዜ በፊት እንዲህ እንዳንት ያሉ እስረኞችን አጅቦ ወደሚጋዙበት ሥፍራ በመውሰዱ ሥራ ተሳታፊ ሆኜ አላውቅም ነበር ።

‘‘ከአንድ ሳምንት በኋላ ፥ እንደገና ወደ ሻለቃችን ቢሮ ተጠራሁ ። ከእኔ ጋር አንድ የሃምሳ አለቃም አብሮ ቀረበ ።

‘እንግዲህ በቀደም እንደ ነገርኩህ ግዞተኛ ፀማጀብ ግዳጅ ላይ ተመድሃበል ’ አለኝ ሻለቃው ፥ ፈርጠም ብሎ ። ወዲያው ወደ ሃምሳ አለቃው ዞር አለና ፥ ‘ ከሥራው ላይ



የተመደበልህ ረዳት እርሱ ነው ። ግና ለሥራዉ አዲስ ይሁን እንጂ ምንም አይል ’ ሲል አስተዋወቀኝ ። አከታትሎም ሥራችንን ስናከናውን ጠንቀቅ እንድንልና ፥ ንቁ ሆነን ሁኔታዎችን እንድንቆጣጠር በምክር መልክ ከአሳሰበን በኋላ ፥ ሥራው እንደማይከብደን የሚያምን መሆኑን ገለጸልን ። በመጨረሻም ፥

‘ ከዋናው ወህኒ ቤት ወደ ግዞት ቦታ የምትወስዷት እስረኛ ወይዘሪት ሞሮዞቫ ትባላለች ። የትእዛዝ ወረቀቶቹ እነዚህ ናቸው ። የጉዞ አበላችሁን ተቀብላችሁ አሁኑኑ እንድትንቀሳቀሱ ’ የሚል መመሪያውን ተቀብለን ከቢሮው ወጣን ።

‘በዚያን ጊዜ ፥ እኔ የቡድኑ የበታች አባል ስሆን ፥ አብሮኝ የሚጓዘው የሃምሳ አለቃ ኢቫኖቭ ደግሞ ፥ የቡድኑ መሪና አለቃየም ነበር ። ከሻለቃችን ቢሮ እንደ ወጣን የጉዞውን መሰናዶ ጀመርን ። በንዲህ ያለው ጉዞ ላይ የቡድን መሪ የሚሆነው ሰው የትእዛዝ ወረቀቶችን ፥ ሰነዶችንና አበሉን በኃላፊነት ተረክቦ ይይዛል ። ለማንኛውም ነገር ቡድኑን ወክሎ የሚፈርመው ፥ ገንዘብ ወጪ የሚያደርገው በጉዞ ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፈው እርሱ ነው ። የቡድኑ የበታች አባል ሆኖ የሚመደበው ወታደር ደግሞ፥ በረዳትነት ልዩ ልዩ ተግባሮችን ያከናውናል ። ይላላካል ፤ ለጉዞው የተያዙትን የግልና የመንግሥት ንብረቶች ይጠብቃል ፤ ደግሞ አንዳንድ ጥቃቅን ሥራዎችን መፈጸም የእርሱ ድርሻ ይሆናል ።

‘ በተከታዩ ቀን ከጠቅላይ መምሪያው ግቢ ጉዞ ስንጀምር ፥ የማለዳ ብርሃን ገና መሬት መውጋቱ ነበር ። የሃምሳ አለቃ ኢቫኖቭ ትንፋሽ ድንገት ሽው ሲልብኝ፥በጧት አንድ ሁለት ብርጭቆ አረቄ የቀመሰ መሆኑን ተገነዘብሁ ። እውነቱን ለመናገር ከሆነ ኢቫኖቭ ለተሠማራንበት

ዐይነት ግዳጅ የሚስማማ ሰው አልነበረም ። አለቆቹ ፊት ሲቀርብ ፣ ጥንቁቅና ቆፍጣና ወታደር መስሎ ለመታየት ይሞክራል ። እንዲያውም እንደሚወራለት ከሆነማ ፣ በበላዮቹ ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን ሲል የሥራ ጓዶቹን በውሸት ይወነጅላል ይባላል ። ተራ አሉባልታና የሐሰት ስሞታም ከማቅረብ እንደማይመለስ ይነገራል ። ከአለቆቹ ፊት ዞር ሲል ግን ፣ የመጀመሪያ ተግባሩ የሚሆነው መጠጣትና መስከር ብቻ ነው ።

"ወደ ትልቁ ወህኒ ቤት እንደ ደረስን፣ በደንቡ መሠረት የቀረበልንን ቅጽ ሞልተን እስረኛዋን መጠባበቅ ጀመርን። ወደ ሩቅ ሥፍራ አጅበን ስለምንወስዳት ወጣት እስረኛ ማሰላሰል ያዝኩ ። ሐሳቤ ሁሉ ወደማላውቃት ልጃገረድ እስረኛ ተጓዘ ። አብረናት ረጅም መንገድ እንደምንሔድና ለብዙ ቀናት በአንድነት እንደምንቆይ ዐውቃለሁ ። የጉዟችን አቅጣጫ በዚሁ ዛሬ እኛ በመጣንበትና ነገም በምንቀጥልበት መንገድ ነበር ። ብቻ ልዩነቱ አሁን አንተ የምትሔድባት የግዞት ቦታ መንደር ስትሆን ፣ የርሷ አነስተኛ ከተማ ብጤ ነበረች ። በትልቁ ወህኒ ቤት ቁጭ እንዳልኩ ስለ ልጅቷ ማሰብና መደነቄን ቀጠልኩ ። የልጃገረድ የፖለቲካ እስረኛ ምን ዐይነት ትሆን ? . . . ከወንዶቹ ትለያለች ወይስ . . . የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች ተፈራረቁብኝ ።

"ለአንድ ሰዓት ያህል በወህኒ ቤቱ ቁጭ ብለን የወይዘሪቷን መውጣት ስንጠባበቅ ቆየን ። ወጣቷ ከእኛ ጋር ከመቀላቀል የዘገየችው ዕቃዎቿን ስታሰናዳ መሆኑን የተረዳሁት ከጊዜ በኋላ ነበር ። ጓዟ ከአንድ አነስተኛ ጥቅል ያላለፈ ነበር ። አንዲት ቀሚስና ሁለት ሦስት ምናምን ነገሮች ፣ ጥቂት መጻሕፍትም አብረው ተጠቅልለዋል ።



በቃ ፣ ሌላ የለም ። ጠቅላላ ንብረቷ ይኸው ነበር ። ምናልባት ቤተሰቦቿ ችግረኞች ይሆናሉ አልኩ — በልቤ ።

"እስረኛዋ እኛ ወዳለንበት ስትመጣ ወጣትነቷ በጣም አስደነገጠኝ ። ገና አንድ ፍሬ ልጅ ናት ። የሚያምረው ዘንፋላ ጠጉሯ በነጠላ ጉንጉን ተሠርቷል ። ጉንጮቿ ቀላ ቀላ ብለዋል ። ገና እንዳየሁዋት መላ ሁኔታዋ ክፉኛ አሳዘነኝ። ይሁን እንጂ ፣ የታሰረችው በጥፋቷ እንደሆነ ገመትሁ ። አንዳች የፖለቲካ ወንጀል እንደ ፈጸመች ተሰማኝ ። ያም ቢሆን ግን ሁኔታዋ አንጀቴን በላው ። እውነቴን ነው የምልህ ፣ ከልቤ አዘንኩላት ።

"ኰቷን እስክትደርብና የክረምት ጫማዎቿን እስክታጠልቅ እኛ ዕቃዎቿን መፈተሽ ጀመርን ። ደንብ ነበር። ግዞተኛው በጉዞው ወቅት የሚይዘው ንብረት በጥንቃቄ መፈተሽ አለበት ። ከፍተሻው በኋላ ገንዘብ ይዛ እንደሆነ ጠየቅናት ። አንድ ሩብል ከሃያ ኰፔክ* አውጥታ ስታሳየን የሃምሳ አለቃ ኢቫኖቭ ተቀብሎ ኪሱ ከተተና ፣ 'ወይዘሪት ፣ አንቺም መፈተሽ አለብሽ ' አላት ።

የኢቫኖቭን ንግግር ስትሰማ ፣ ወጣቷ ከመ ቅጽበት ብው አለች ። ዐይኖቿ እሳት እንደ ነደደባቸው ያህል ይንተገተጉ ጀመር። ቀላ ቀላ ያሉት ጉንጮቿ የበለጠ ፍም መሰሉ። ከንፈሮቿን በኃይል አጣብቃ በንዴት ጨመቀቻቸው ። እንደ ወላፈን በሚገረምም የጥላቻ አስተያየት ገላመጠችን። ያ አስተያየቷ እስከ ዛሬ ፊቴ ድቅን እያለ ይታየኛል ። ሰውነቴ ኩምትር ፣ ሽምቅቅ አለ ። ወደ አጠገቧ ለመቅረብም ድፍረት አጣሁ ። ኢቫኖቭ ግን ከማለዳው ሞቅ ብሎት

---

* ኰፒክ በሶቪየት ኅብረት የሚሠራበት የሽርፍራፊ ገንዘብ (ሣንቲም) ስም ነው ። አንድ መቶ ኰፒክ አንድ ሩብል ይሆናል ።

ነበርና፣የወጣቷ ሁኔታ በስሜቱ ላይ ቅንጣት ለውጥ አላስከተለበትም ። እንዲያውም ይበልጥ ተጠጋትና፣ ‘ መፈተሽ አለብሽ ወይዘሪት ። ትእዛዝ ትእዛዝ ነው ’ አላት ፈርጠም ብሎ ።

“ወጣቷ ንዴቷ ተባብሶ በኃይል መጮሁዋን በመቀጠሏ፣ ኢቫኖቭ ወደኋላ እንደማፈግፈግ ቃጣው ። በውስጡ ያለው ደም በአንዳፍታ እንደ ተመጠጠ ሁሉ የወጣቷ ፊት እንደ በረዶ ነጭ ሆነ ። ዐይኖቿ በቁጣ ነደዱ ። ብቻ ምን አለፋህ ፣ በደፈናው እንደ አራስ ነብር ቱግ አለች ። መሬቱን በእግሯ እየመታች፣ኃይለ ቃሉን በፍጥነት ታወርደው ጀመር ። እውነቱን ለመናገር ከሆነ፣ በበኩሌ አንዱንም አልሰማሁትም ። የወህኒ ቤቱ ዘበኛ ፍርሃቱ በግልጽ እያስታወቀበት፣አንድ ብርጭቆ ውሃ አመጣና እንድትጠጣው እየጋበዛት፣ ‘ረጋ በይ እባክሽ ፤ ራስሽን እኮ ነው የምትጎጂው’ አላት፣እንደ ማጽናናት ባለ ድምፅ ። እሷ ግን፣ወይ ፍንክች! ከናካቴው እሱንም ዞረችበት ። ‘ ሁላችሁም እንከፍ ፣ አጋሰስ ፣ ጋጠወጥ ናችሁ ። ሁላችሁም አጭበርባሪዎች ናችሁ፤ ሌላ ምንም አይደላችሁም ። ደደቦች ፣ አጭበርባሪዎች ናችሁ ’ ስትል አንባረቀች ። የስድቡ ውርጅብኝ ቀጠለ ። ‘አየህ ባንተ ላይ ላይ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች እንዲህ ባለ ሁኔታ መናገር ተገቢ አይደለም ። ‘ይቺ ክፉ መርዘኛ ነች’ አልኩ — በሐሳቤ . . . . . ጥጋበኛ !

“በመጨረሻ የወህኒ ቤቱ ዘበኛ እንደ ምንም ብሎ ወደ ሌላ ክፍል ወሰዳትና፣ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአንዲት ሴት ዘበኛ ጋር ተመለሱ ። ‘ ምንም ነገር አላገኘንባትም ’ አለ የወህኒው ዘበኛ ። ወጣቷ እስረኛ በማፌዝ ዐይነት አስተያየት ዘበኛውን ገረመመችው ። ልትሥቅበት የቃጣች ትመስል ነበር ። ኢቫኖቭ በፍተሻው ባለመርካቱ ‘ ትክክል አይደለም ። አሠራሩ ከሕግ ውጭ ነው ። የተቀበልኩትን ትእዛዝ የማ



ውቅ እኔ ነኝ ’ እያለ፣ዝቅ ባለ ድምፅ ያጉመተምት ጀመር ። የዘብጥያው ዘበኛ ከቁም ነገር አልጣፈውም ። እርሱም እንደኔ የኢቫኖቭን ሞቅታ ተረድቶታል ።

“ከወህኒ ቤቱ ወጥተን ጉዟችንን ቀጠልን ። የተሣፈርንበት ሠረገላ በከተማይቱ መንገዶች ሲሽከረከር፣ወጣቷ እስረኛ በመስኮቱ በኩል ወደ ውጭ መመልከት ጀመረች ። የምታውቃቸውን ሰዎች በጐዳናው ላይ ወዲያ ወዲህ ቢሉ ለማየት የምትፈልግ ትመስላለች ። አልያም ከተማውን ለመሰናበት የምትሻ ። ኢቫኖቭ ወዲያው መጋረጃውን ሳብ አድርጎ መስኮቱን ከለለባት ። ወደ ኋላ ተመልሳ በመቀመጫዋ ጥጋት ላይ ኩርምት ብላ ተቀመጠች ። እኛን ላለማየት ዐይኖቿን ወደ ሌላ አቅጣጫ ወረወረቻቸው ። አሁንም ልቤ ስለርሷ በኀዘን ተወረረ ። ልደብቅህ አልሻም ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የውጪውን ትርዒት ለራሴ ለመመልከት እንደ ፈለግሁ አስመስየ የመጋረጃውን አንዱን ጫፍ በመያዝ በመጠኑ ገለጥሁትና እርሷም እንድታይ ለማድረግ ሞከርሁ ። እሷ ግን በዕድሉ ለመጠቀም አልፈለገችም ። በወንበሯ ጥጋት በኩርፊያ እንደ ተቀመጠች ከንፈሮቿን በቁጭት መልክ ትነካከሳቸው ጀመር ።

“ሠረገላው ወደ ባቡር ጣቢያው ካደረሰን በኋላ ጉዟችንን በባቡር ቀጠልን ። ደስ የሚል የበልግ ቀን ነበር ። የጠራው የመስከረም ሰማይ ላይ ደመና የሚባል ላመል ያህል እንኳን አይታይም ። በገረረችው ፀሐይ ሙቀት መሐል ቀዝቃዛ አየር አካልን ዳሰስ እያደረገ ያልፋል ። ወጣቷእስረኛችን በየጊዜው መስኮቱን እየከፈተች ንፋሱን ይበልጥ ለማግኘት ወደ መስኮቱ ጠጋ ትላለች ። ሁኔታዋን ስመለከት፣ እስረኞች በሚጓጓዙበት ጊዜ መስኮቶቹን ሁሉ እንድንዘጋ የተሰጠን ትእዛዝ ትዝ አለኝ ። ኢቫኖቭ በባ

[illegible]ሩ አልጋ ላይ ተኝቶ ማንኮራፋት ከጀመረ ጥቂት ጊዜያት አልፈዋል ፡፡ መስኮቶቹን መክፈት ክልክል መሆኑን ልነግራት ብፈልግም ድፍረቱ እምቢ አለኝ ፡፡ በመጨረሻ የሞት ሞቴን ትእዛዙን ተነፈስኩት ፡፡ እንዳልሰማ ሰው ጭጭ አለች ፡፡ ጥቂት ጠበቅሁና ፡

" ወይዘሪት ብርዱ ደግ አይደለም እኮ' አልኳት ፡፡ አንዳች የሚያስደንቅ ነገር የተናገርኩ ይመስል ፡ ፊቷን ወደኔ [illegible]ዞር ዐይኖቿን በሰፊው ብልጥጥ አድርጋ በመደነቅ መልከ አተኮረችብኝ ፡፡ ትንሽ ቆይታ ፡ 'ግድየለም ይሁን' የሚል አጭር መልስ ብቻ ሰጥታኝ ወደ ዝምታዋ ተመለሰች ፡፡ እንደገናም ባቡሩ እያቋረጠ የሚያልፈውን አካባቢ ትርዒት መመልከቷን ቀጠለች ፡፡ ደስ እንዳላት ታድርግ ብዬ እኔም ነገሩን ተውኩት ፡፡

"ከፊት ለፊቷ ቁጭ ብዬ ሁናቴዋን ሳስተውል ፡ ከቀድሞው ትንሽ የተረጋጋች መሰለች ፡፡ ዐልፎ ዐልፎ መስኮቱን ትዘጋና ሙቀት ለማግኘት የፈለገች ይመስል ፡ ስስ ኮቷን ትከሻዋ ላይ አስተካክላ ቁጭ ትላለች ፡፡ ትንሽ ቆይታ ደግሞ ፡ ወደ መስኮቱ በመጠጋት በባቡሩ ፍጥነት ልክ እየተፈተለከ ወደ ኋላ የሚያልፈውን የውጭ ትርዒት መመልከት ትቀጥላለች ፡፡

"ነፋሱ ክፉኛ እየቀዘቀዘ ሔደ ፡፡ ወጣቷ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተዘግቶባት ከቆየች በኋላ ፡ ወደ ውጭ ለመውጣት በመብቃቷ በምታየው ትርዒት ሁሉ የተደሰተች ትመስላለች ፡፡ አንዳንዴም በገጽታዋ ላይ የደስታ ፈገግታ ይሠርቃል ፡፡ እንደዚያ በምትሆንበት ጊዜ ሲያዩዋት ደስ ትላለች ፡፡

"ጋቭሪሎቭ ትንሽ ለማሰብ ያህል ንግግሩን ቆም አደረገና ማውጋቱን ሲቀጥል ፡ ስሜቱ ከመጀመሪያው ሞቅ ብሎ ነበር ፡፡



"ኮስትሮማ ስንደርስ ከባቡሩ ወርደን ቀሪውን ጉዟችንን ለመቀጠል ፡ ፖስታ በሚያመላልስ ጋሪ ላይ ተሣፈርን ፡፡ ኢቫኖቭ አብዛኛውን መንገድ የተጓዘው ፡ ጥንብዝ ብሎ እየሰከረ በማንቀላፋት ነበር ፡፡ አንዳንዴ ቢነቃም እንደገና ጠርሙሱ አረቄውን ይጨልጥና ተመልሶ ይገነደሳል ፡፡ ከስካር የተለየበት ጊዜ በፍጹም አይታወሰኝም ፡፡ በተለይ ከባቡሩ ስንወርድ በአፍ ጢሙ ሊደፋ የነበረው ሁኔታ ምንጊዜም ከአእምሮዬ የማይጠፋ ትርዒት ነው ፡፡ መጠጡ ከመጠን በላይ በመብዛቱ ከመንግሥት የተሰጠንን ገንዘብ በስካር ብቻ ያወድመዋል የሚል ሥጋት ሳያድርብኝም አልቀረም ፡፡ ያም ሆኖ ፡ ኮስትሮማ ላይ ከባቡሩ ወርደን ወደ ፖስታ ማመላለሻው ጋሪ ስንጋባ ፡ ኢቫኖቭም እንደ ምንም ተደነባብሮ ቦታውን ያዘና ወዲያው ማንኮራፋቱን ቀጠለ ፡፡ ወጣቷ እስረኛ የደረሳት ቦታ ከአይቫኖቭ አጠገብ በመሆኑ ፡ ቅፍፍ ብሏት ዐሥር ጊዜ በጥላቻ አስተያየት ስትገላምጠውና ወንበሯ ላይ ጭብጥ ብላ በመቀመጥ ፡ በተቻላት መጠን ከእርሱ ለመራቅ መሞከሯን ከመታዘብ አልተቆጠብሁም ፡፡ ለጊዜው ምንም ማድረግ ስላልተቻለ ፡ እኔም ከጋሪ ነጂው አጠገብ ሥፍራየን ያዝኩና መንገዳችንን ቀጠልን ፡፡ ከወደ ሰሜን በኩል የሚነፍሰው ቀዝቃዛ ነፋስ አንጀቴ ውስጥ ገብቶ ሲያንዘፈዝፈኝ ፡ ወጣቷን እስረኛ ደግሞ በማከታተል ያስላት ጀመር ፡፡ ትንሽ እንደ ተጓዝን ሳሏን ለማፈን አፏ ላይ አድርጋው የነበረውን ነጭ መሐረብ ስታነሣው ትንንሽ የደም ነጠብጣቦችን ተመለከትሁ ፡፡ ልቤ በድንጋጤ ክፍል ሲል ተሰማኝ ፡፡

" ወይዘሪት ያምሻል መሰለኝ ፡፡ በእንዲህ ያለ ብርድ ይህን መሳይ ረዥምና አስቸጋሪ መንገድ መጓዝ አልነበረብሽም ፡፡ በጣም ተሳስተሻል ' አልኳት ፡፡

ዐይኖቿን ወደኔ ስታቀና የወህኒ ቤቱ ቁጣዋ እንደ ገና እንደ ተቀሰቀሰባት ገባኝ ።

“ ለመሆኑ አንተ ፥ ደደብ ወይስ ምን የሚሉት ዐይነት ሰው ነህ ? ይህን ቁዞ የማደርገው በራሴ ፈቃድና ፍላጎት እንዳልሆነ አይገባህም ! ደግሞ ያሰርከኝ አንተው ሆነህ ልታዝንልኝም ትሞክራለህ ? ’ አለች ።

“ ሌላው ቢቀር ሆስፒታል እንዲያስገቡሽ እንኳን እዬት ማለት ትችይ ነበር ማለቴ ነው ። መቼም በዚህ ብርድ ከመጓዝ ሳይሻልሽ አይቀርም ነበር ። ከጉዟችን ደግሞ ገና ምንም አልተነካ ’ አልኳት ፥ ይበልጥ እንዳትከፋ በማሰብ ፥ ንግግሬን ትሕትናና ትዕግሥት ያልጐደለው ለማድረግ እየታገልኩ ።

“ ለመሆኑ የጉዟችን መጨረሻ የት ነው ? ’ ስትል ጠየቀችኝ ። እስረኞች የሚላኩበትን የግዞት ሥፍራ በግልጥ ለይተን እንዳንነግር ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቶናል ። መልስ ለመስጠት ተቸግሬ ሳመነታ አየችና ፊቷን ከኔ አዞረች ። ነገሩ ገብቷታል ።

“ ግድየለም ። ለመጠየቅ ፈልጌ አልነበረም ። አንተም በኔ ጉዳይ ጣልቃ መግባትህን አቁም ’ አለችኝ ።

“እኔ ግን ዝም ማለት ስላላስቻለኝ ንግግሬን ቀጠልኩ። ‘ ምን ያህል ሩቅ ቦታ እንደሆነ ይታይሻል ? ’ አልኳት ። እርሷ ግን ፊቷን ኩስትርትር አድርጋ ከንፈሯን በኃይል ጨመቀችና ጸጥ አለች ። ጭንቅላቴን ነቀነቅሁና ፥ ‘ ወይ ዘረት ፥ አንቺ ገና ወጣት ነሽ ። ምን እንደምትሠሪ ፥ ለምን ዓላማ እንደ ቆምሽ አታውቂም ’ አልኳት ። በጣም ንድድ ብሎኝ ስለ ነበር ፥ ከመናገሬ በፊት ለማሰብ እምብዛም አልተጨነቅሁም ።



“ በተለመደው ጦር ግልምጫዋ አንዴ ቆጋችኝና ፥ ‘ በጣም ተሳስተሃል ’ አለች ። ‘ ምን እንደምሠራ ፥ ለምን ዓላማ እንደ ቆምሁ ደኅና አድርጌ ዐውቃለሁ ። ለጤንነቴ በማሰብ ስለ ሆስፒታል ሐሳብ በመሰንዘርህ ሳላመሰግንህ አላልፍም ። ይሁን እንጂ አንድ ነገር እንድትረዳልኝ እፈልጋለሁ ። አየህ ! ብሞትም እንኳን በእስር ቤት ውስጥ ሳይሆን እኔን ከመሰሉ ጓዶቼ ጋር ተቀላቅዬ ፥ ከወገኖቼ ፥ ከኔዎቹ ጋር ሆኜ ብሞት እመርጣለሁ ። ብድንም ደግሞ ጤንነቴ ከነዚያ አስከፊ የወህኒ ቤት ግድግዳዎች ውጪ ቢሆን ደስ ይለኛል ። የበሽታዬ መንሻ ቀዝቃዛው አየርና ብርዱ ይመስልሃል ? . . . . አይደለም ። በሽታዬ ሌላ ነው ’ አለችኝ ።

“በወገኖቿ መሐል ሆና ለመዳን ስላላት ምኞት ስትናገር በሰማሁዋት ጊዜ ነገሩ ግራ አጋባኝ ። ነገሩን በግልጽ ለመረዳት እንድችል ጥያቄ ለማቅረብ ፈለግሁ ። ‘ ለመሆኑ አሁን በምትሔጅበት ቦታ የሚኖሩ ዘመዶች አሉሽ ? ’ አልኳት ።

“ አንድም ዘመድ የለኝም ። እንኳንስ ዘመድ ፥ የምጋዝበትን አካባቢ እንኳን አላውቀውም ። ግን ቀደም ሲል ወደዚያ አካባቢ የተላኩ እንደኔ ያሉ ግዞተኛ ጓዶችን አገኛለሁ ’ አለች ። ፈጽሞ አይታቸው እንኳን የማታውቃቸውን ሰዎች ‘ የኔዎቹ ’ . . . ‘ ወገኖቼ ’ እያለች መጥራቷ በጣም አስደነቀኝ ። ቀደም ሲል የማታውቃቸውና የማያውቋት ባይተዋር ሰዎች ሊረዷትና ሊንከባከቧት ይፈቅዱ ይሆን ? እንደ እርሷው የተጋዙ የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ዋጋና ክፍያ ቁራሽ ዳቦ ሊሰጧት ይጨነቁ ይሆን ? አንዱን ከሌላው እያፈራረቅሁ በሐሳቤ ከማውጠንጠን በቀር ተጨማሪ ጥያቄ ከመሰንዘር ተቆጠብሁ ።

“ከዚያ በኋላ የመደሰት ስሜት ከገጿ ፈጽሞ ጠፋ ። እኔም
ይበልጥ እንዳላስከፋት በማሰብ ጸጥ ብዬ ተቀመጥሁ ።

“ሐሳቤ ግን አላረፈም ። ስለ ወጣቷ ይመራመራል - ወደ
ፊት ስለሚያጋጥማት ሁኔታ ። ‘ ደኅና ነው ’ አልኩ ለብ
ቻዬ ። ይሁን እንጂ ። ገና ስላልቀመሰችው ነው የዓለ
ምን ነገር ። በማታውቀው ዳር አገር መኖር የሚያስከት
ልባትን ችግርና ውጣ ውረድ ስትቀምሰው ነው ክብደትና
ምሬቱን የምትረዳው ።

“በጉዟችን ብዙ ገፋን ። ለዐይን መያዝ ሲጀምር ፤ ሰማዩ
ጠቋቆረና እንደ ስለት የሚቀረደድ ቀዝቃዛ ነፋስ ተከተለ ።
ትንሽ ቆይቶ መዝነብ ጀመረ ። አስቀድሞም በደንብ ያልደ
ረቀው መሬት ይበልጥ ጨቀየ ። የፈረሶቹና የጋሪው እግ
ሮች የሚያፈናጥቁት ጭቃ ጀርባየን አለበሰው ። የአየሩ
መበላሸት በተለይ ለወጣቷ መጥፎ መሆኑ ሳይሰማኝ አል
ቀረም ። የምንጓዝበት ጋሪ ሽፋን ብጤ ያለው ቢሆንም
ወጨፎው ፊት ፊቷን ይመታት ጀመር ። በጣሪያው ላይ
ምናምኑን በመደራረብ ከለላውን ለማጠናከር ሞከርኩ ።
በአንዳንድ ክፍት ቦታዎች እየሾለከ የሚገባውን ጠፈጠ
ፍና ውሽንፍር ለመከላከል ግን አልተቻለም ።

“ብርዱ እየባሰበት ሲሔድ ፤ ሞሮዞቫ ዐይኖቿን ከድና
የሠራ አካላቷ በኃይል የሚንቀጠቀጥ መሆኑን ተመለከ
ትሁ ። የዝናቡ ጠብታዎች በፊቷ ላይ ኰለል እያሉ ይወ
ርዳሉ ። ገጿ እንደ በረዶ ነጭ ሆኖ ፤ ነፍሷን የሳተች ያህል
ያለ እንቅስቃሴ ወንበሯ ላይ ተቀምጣ ጋሪው በተንገጫገጨ
ቁጥር ብቻ እሷም አብራ ትወዛወዛለች ። ሁኔታዋ በጣም
አሸበረኝ ። ሁሉም ነገር ያደመባትም መሰለኝ ። ግድየለሹ
ኢቫኖቭ ግን ፤ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ በተኛበት እያንኰራፋ
የቁም በድኑ ይጓዛል ።



ያሮስላቭ ከተማ ስንደርስ ጨልሞ ነበር ። ኢቫኖቭን
ቀስቀስኩና ወደ ሙንገደኞች ማረፊያው ጣቢያ አመራን ።
እንደ ደረስን የሻይ ማፍያው ፤ ‘ሳሞቫር’ እንዲሞቅልን
ጠየቅሁ ።

“ ከያሮስላቭ ከተማ እየተነሡ እኛ ወደምንሔድበት
ሥፍራ የሚቀዝፉ ጀልባዎች ነበሩ ። ነገር ግን ፤ ልንጠቀ
ምባቸው እንደማንችል ዐውቃለሁ ። ምንም ዐይነት
ሁኔታ ቢገጥሙን እስረኞችን በጀልባ እንዳናጓጉዝ ጥብቅ
ትእዛዝ ተሰጥቶናል ። እርግጥ በጀልባ ሙጓጓዙ ለእኛም
ለአጃቢዎቹ ቢሆን ወጪን ስለሚቀንስ ፤ ትንሽ ገንዘብ ለማ
ዳን ያስችለን ነበር ። ግን በወንዙ ዳርቻ ላይ እየተንጐራ
ደዱ የሚጠብቁ ዘበኞችና እንደ እኛ ያሉ የአካባቢው
የፖሊቲካ ፖሊሶች በብዛት ስለ ነበሩ ፤ በጀልባ ለመጠቀም
መቃጣቱ አደገኛና የማያዋጣ ነበር ። እስረኛ በጀልባ ሲጓ
ጓዝ ከተመለከቱ ፤ የአካባቢው ፖሊሶች ጉዳዩን ለበላይ ከማ
ሳወቅ የማይቦዝኑ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን ። ይሁን
እንጂ ፤ ይህን ምስጢር ያልተረዳችው ወጣት እስረኞችን
ቀሪውን ጉዞ በጀልባ ካልሆነ ፤ በጋሪ ለመቀጠል ፈቃደኛ
እንዳልሆነች ከመግለጽ አልተቆጠበችም ።

“ ከአሁን በኋላ በጋሪም ሆነ በሠረገላ የማልጓዝ
መሆኑን እንድታውቁት . . . ምንም ይሁን ምን ፤ ከዚህ
ወዲያ ያለውን መንገድ በጀልባ እንድትወስዱኝ እፈል
ጋለሁ ’ አለችኝ ።

“ከመጠጡ ብዛት የተነሣ ዐይኖቹን እንኳን መግለጥ
የተሳነው ኢቫኖቭ ፤ የወጣቷን ንግግር ሲሰማ ድንገት ቱግ
አለ ። ‘ በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የምትሰጪው አንቺ አይ
ደለሽም ። እኛ በምናዘጋጀው መጓጓዣ ወደምንወስድሽ
ቦታ ቀጥ ብሎ ከመሔድ በቀር ፤ በሌላ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ

መግባት አትችይም’ አላት ። እሷ ግን አንዳችም ቃል
ሳትመልስለት ወደ እኔ ዞር ብላ ፥

“ አልሔድም ! ጉዞውንም አልቀጥልም ብያለሁ ። ገብ
ቶሃል’ አለችኝ ። በዚህ ጊዜ በዝግታ የኢቫኖቭን ክንድ
በመያዝ ከወጣቷ ራቅ አድርጌ ወሰድሁትና ፥ ‘ ለምን
በጀልባ አንሔድም ’ የሚል ጥያቄ በማቅረብ የማግባባት
ሙከራየን ጀመርኩ ። ‘ በጀልባ ብንሔድ ከመጓጓዣው
ወጪ ላይ ትንሽ ገንዘብ ለማዳን ስለምንችል ጥቅሙ በይ
በልጥ ለኛ ነው ’ አልኩት ። ኢቫኖቭ በነገሩ ቢደሰትና
ቢስማማም መፍራቱ ግን አልቀረም ።

“ የዚህ አካባቢ የበላይ ሹም አንድ ኮሎኔል ነው ።
ስለዚህ በምናደርገው ሁሉ መጠንቀቅ አለብን ። ቢሆንም
ወደ ኮሎኔሉ ዘንድ ሔደህ ስለ ልጅቷ ሁኔታ ልታስረዳውና
ስምምነቱን ልትጠይቀው ትችላለህ ። እኔ ግን ብዙም ደኅና
ስላይደለሁ እዚሁ እቆያለሁ ። እናም ባንተ ያምራል’
አለኝ ።

“የኮሎኔሉ ቤት እኛ ካለንበት ጥቂት ራቅ ይላል ።

“ ከሆነስ ሦስታችንም አብረን ብንሔድ ነው ደጉ’
የሚል ሐሳብ አቀረብሁ ። ልጅቷንና ኢቫኖቭን ለብ
ቻቸው ትቼ መሔዱን አልወደድኩትም ። እኔ በሌለሁበት
ኢቫኖቭ እንደ ልማዱ ቢያንቀላፋ፥ወጣቷ እስረኛ ልታመ
ልጥ ወይም በራሷ ላይ አንዳች ጉዳት ልታደርስ ትችላለች ።
ይህ ዐይነቱ ሁኔታ የሚያስከትለው መዘዝ ደግሞ ቀላል
አይሆንም ።

በመጨረሻ ወደ ኮሎኔሉ ዘንድ ቀረብን ። ምን እንደ
ፈለግን ስንጠየቅ መልስ የሰጠችው ልጅቷ ነበረች። ወጣቷ
ወይዘሪት ጉዳዩን ስታስረዳ ረጋ ለማለትና ሥነ ሥርዓትን
ለመጠበቅ አልተጨነቀችም ። ‘ እባክዎ ፥ የክቡርነትዎ



መልካም ፈቃድ ቢሆንና . . . ’ በሚሉ ሐረጎች ጀምራ
ጥያቄያችንን በማቅረብና ስለ ሁኔታው በትሕትናና በል
ምምጥ መንፈስ በማስረዳት ፋንታ ፥ የተለመደ የኩራት ንግ
ግሯን አመጣችው ። ‘ ለመሆኑ በየትኛው መብታችሁ
ነው. . . . ’ ብላ ንግግሯን ጀመረች ። በማከታተልም እንደ
ነበልባል የሚገርፉ ቃላቷን አዥጎደጎደቻቸው ። እናንተ
የፖለቲካ ሰዎች ፥ መቼም እንዲያ ያለውን አነጋገር ትወዱ
ታላችሁ ። የነዚያን ከላይ ያሉ ሰዎች ደንዳና ቆዳ ሠርስሮ
የሚገባው እንዲያ ያለው ንግግር ቢሆንም ፥ ነፍሳቸውን
የሚያረካው ግን ልምምጥና ልመና ብቻ ነው ። ታዲያ ኮሎ
ኔሉም የወጣቷን ድንፋታና እንደ አለንጋ የሚሸነቁጥ ንግ
ግር በጸጥታ ካዳመጠ በኋላ ፥

‘ ሕጉ ስለማይፈቅድ ምንም ላደርግላችሁ አልች
ልም ’ ሲል መለሰልን ።

‘ ሕጉ ! ’ አለች ወጣቷ ፥ በማንጓጠጥ ዐይነት ሁኔታ።

“ አዎ ! ሕጉ አይፈቅድም ’ አለ ኮሎኔሉ ። አነጋገሩ
የመጨረሻና የማያዳግም መልስ መሆኑን የሚገልጽ ድም
ፀት ነበረው ።

“ብልጭ አለብኝ ። እውነቱን ለመናገር ከሆነ ፥ በዚያች
ቅጽበት ራሴን መቆጣጠር እንኳን ተስኖኝ ነበር ።

‘ እርግጥ ሕጉ አይፈቅድ ይሆናል ፥ ክቡር ሆይ ’ አል
ኩት ለኮሎኔሉ ። ‘ ይሁን እንጂ ይህች ወጣት ክፉኛ በሕ
መም እየተሠቃየች ነው ። ’

ፊቱን ቅጭም አድርጎ ተመለከተኝና ‘ ስምህ ማነው? ’
ሲል ጠየቀ ። መልሱን ሳይጠብቅ በፍጥነት ወደ እስረኛ
ችን ዞር በማለት ‘ ስማሽ ወይዘሪት ! በእርግጥ የሚያምሽ
ከሆነ በከተማችን ወደሚገኘው የወህኒ ቤት ሆስፒታል

ሔደሽ ዕረፍት ማድረግና የሕክምና ርዳታ ማግኘት ትች ያለሽ ’ አላት ። ሞሮዞቫ ግን መልስ ሳትሰጠው ወደ መጣ ንበት አቅጣጫ ዞራ ርምጃዋን ቀጠለች ። እኛም በጸጥታ ተከተልናት ።

“ሌላ ምርጫ አልነበረንም ። ምንም ለማድረግ እንደ ማንችል አረጋግጠናል ። ኢቫኖቭ በነገሩ ስለ ተበሳጨ በኔ ላይ ዞረብኝ ። ‘ አንተ ደደብ ፤ ደኅና አድርገህ ነው ማጥ ውስጥ የዘፈቅሽን ። ብቻ ግድየለም ፤ አንድ ጊዜ ሥራችንን ጨርሰን እንመለስ እንጂ ፤ ሁለታችንም መልስ እንሰጥበ ታለን ’ አለኝ ።

‘ከዚያ በኋላ ትዕግሥት አልነበረውም ። ፈረሶቹ እንዲ ለጐሙ ትእዛዝ ሰጠ ። ሌሊቱን በከተማው ውስጥ ለማሳ ለፍ የነበረንም ዕቅድ ተሰረዘ ። መሽ ፤ አልመሽ የለም ፤ ጉዟ ችንን እንድንቀጥል ተወሰነ ። በጣቢያዉ ወደሚገኘው የማ ረፊያ ቤት ስንገባ ፤ ወጣቷ አንድ አግዳሚ መቀመጫ ላይ ጋደም ብላ ፤ ብርድ ያኰማተረው አካሏን ለማሞቅ ስትሞክር አገኘናት ። ጉዟችንን እንድንቀጥል መወሰኑን ስንነግራት ከተቀመጠችበት ተፈናጥራ በመነሣት ፤ ሁለታችንንም ትክ ብላ ታስታውለን ጀመር ። አስተያየቷ አስፈራኝ ። ‘ እና ንተ አውሬዎች ’ በማለት የተለመደውን ስድብ አወረደ ችብን ። ንግግሯ የንዴትና የማዘን ቃና ነበረበት ። የምታ ነጋግርበት ቋንቋ ሩሲያኛዊ ቢሆንም ፤ አብዛኞቹን ቃላት ልንረዳቸው አልቻልንም ። ከባድና የበሰሉ ነበሩ ። በመ ጨረሻው ፤

‘ በኔ ላይ የፈለጋችሁትን ለማድረግ ኃይልና ሥልጣን አላችሁ ። የሞቴን ጊዜ ለማፋጠንም ትችላላችሁ ። ያሻች ሁትን ፈጽሙ ፤ ወዳሻችሁም ውሰዱኝ ። እኔም ለመከተል ዝግጁ ነኝ ’ አለችን ።



“ቀደም ብሎ በተዘጋጀው ‘ ሳሞቫር ’ የራሳችንን ሻይ አፈላሁና ለእሷም ቀዳሁላት ። ለስንቅ ከያዝኩት ዳቦ ትንሽ ቆረስ አድርጌ ፤ ‘ እስቲ ሞክሪው ፤ ሻዩ ደግሞ ሞቅ ያደርግሻል ’ በማለት ልጋብዛት ሞከርኩ ። ጫማዎቿን ማለጥለቅ ከተጐነበሰችበት ቀና አለችና ፤

“ አንተ በጣም ቀልደኛ ሰው ነህ ። ያንተን ሻይ ተካ ፍዬ እንደምጠጣ አስበህ በመጋበዝህ እብድ ትመስለኛ ለህ ’ አለችኝ ። ንግግሯ ከፉኛ መታኝ፤እስከ ዛሬ ድረስ ሳስ በው ደሜ ይፈላል ። አሁን ለምሳሌ አንተ በትንሽ ነገር አትቆጣም ፤ አንድ ሩባኖቭ የሚባል ሌላ ግዞተኛም ትዝ ይለኛል ። ልክ እንዳንተው የረጋ ነበር ። የዚያች ወይዘሪት ግን የተለየ ነው።ታዲያ የሚገርመው ደግሞ ፤ ወዲያውኑ ለብ ቻዋ ሻይ እንዲዘጋጅላት አዝዛ ጠጣች ። ሒሳቡን ስትጠ የቅም ከዚያው ከነበራት አንድ ሩብል ከሐያ ኰፔክ ገንዘብ ላይ ፤ ለሻይና ለስኳሩ ከተለመደው እጥፍ ዋጋ ከፍላ መን ገዷን ለመቀጠል ከማረፊያው ቤት ወጣች ። እኛም ተከተ ልናት ። ”

3

ጋቭሪሎቭ ትረካውን አቋረጠና ጭጭ አለ ። እልፍ ብሎ ከተኛው ወጣት ፖሊስ ከሚወጣው ኃይለኛ ትንፋ ሽና፤ከንፋሱ ፉጨት በስተቀር ለጥቂት ጊዜ በቤቱ ውስጥ የሚሰማ ድምፅ ጠፋ ።

“ እንቅልፍ ከጀለህ እንዴ ” ? ጋቭሪሎቭ ትንሽ ቆይቶ ጠየቀ ።

“ኧረ በፍጹም። በሚገባ እያዳመጥሁ ነኝ ” አልኩት።

እንደገና ዝም ብሎ ቆየና ጋቭሪሎቭ ታሪኩን ቀጠለ።

“መቼም በወጣቷ ሁኔታ የተነሣ የገጠመኝ ሥቃይ ቀላል አልነበረም።በጊዜ የጀመረው ዝናብ ሌሊቱን በሙሉ

ያለማቋረጥ ሲጥል አደረ ። በዚያ ላይ ብርዱ አይጣል ነው ።
በጫካው መሐል ስናልፍ የሚያጉረመርመውም ነፋስ የብ
ቸኝነትን ስሜት እየፈጠረ ልብ ያሸብራል ። ጨለማው
ጥቅጥቅ ያለ በመሆኑ ፣ ዐይን ቢጓጉጡ እንኳን ማየት አይ
ቻልም ነበር ። በዚያን ወቅት ወጣቷን መመልከት ቢሳ
ነኝም ፣ ያእስከ ዛሬ የማይረሳኝ ገጽታዋ ግን ፣ ለዐይን ሕሊ
ናዬ ወለል ብሎ ይታየኝ ነበር ። ትልልቅ ዐይኖቿ ፣ ደስታ
የራቀውና ቁጣ የተላበሰው ፊቷ ፣ በብርድ የተኮራመተው
እንኳ ፣ አእምሮዋ አንዳች ረቂቅ ሐሳብ ሲያውጠነጥን ፣ ምናቧ
በራቀ ነጥብ ላይ ተተክሎ ፣ በምርምር የተመሰጠች የሚ
ያስመስላት የትኩረት አመለካከቷ ሁሉ ፣ አንድም ሳይቀር
ይታየኛል ።

“ገና ከያሮስላቭ ከተማ ስንነሣ ፣ ከበግ ጸጉር የተሠራ
ኮት አውጥቼ ‘ ትንሽ ያሞቅሽ ይሆናል ’ በማለት በትከ
ሻዋ ላይ ላደርግላት ስሞክር ፣ ‘ ያንተ ኮት ስለሆነ ራስህ
ተጠቀምበት ’ በማለት ከላይዋ ላይ አሽቀንጥራ መጣሏ ትዝ
ይለኛል ። እርግጥ እንዳለችው ኮቱ የእኔ መሆኑን ዐው
ቃለሁ ። ግን በግትርነትና በእልህ የተነሣ በብርድ ክምት
ጉዳ ፣ በኮቱ እንድትጠቀም ማድረግ የምችልበትን መን
ገድ ስፈልግ አንድ ሐሳብ መጣልኝ ። ወዲያው ፣ ‘ ኮቱ ለእስ
ረኞች መጠቀሚያ እንዲሆን የያዝነው እንጂ የኔ ንብ
ረት አይደለም ’ አልኳት ። ብዙም ሳትቆይ ከቁጣዋ መለስ
አለችና ኮቱን ተቀብላኝ እላይዋ ላይ ደረብ አደረገችው ።

“ጧት ሲነጋ እንዳየሁት ግን ፣ ኮቱ እምብዛም አልረዳ
ትም ። ብርዱ ክፉኛ አጉሳቁሏት ነበር ። ወደ አንድ ጣቢያ
ስንደርስ ኢቫኖቭ ከጋሪው ወጥቶ ከነጂው ጐን እንዲቀመ
ጥና እኔ በተራዬ ከርሷ ጋር በጋሪው ውስጥ እንድሆን ጥያቄ
አቀረበች ። ኢቫኖቭ ትንሽ ቢነጫነጭም ስካሩ በመጠኑ



ቀለል ብሎለት ስለ ነበር ወጣቷን ላለማስቆጣት ሲል ጥያ
ቄዋን ተቀበለው ። እኔም ጋሪው ውስጥ ገብቼ አጠገቧ ተቀ
መጥሁ ።

“ለሦስት ቀንና ሌሊት ያለማቋረጥ ከተጓዝን በኋላ ፣ ወጣቷ
በግዞት እንድትኖርበት ወደ ተወሰነው ከተማ ደረስን ።
ከደረቴ ላይ ትልቅ ሸክም የተነሣ ያህል ቀለለኝ ። በጉዟችን
መጨረሻ አካባቢ ወይዘሪቷ በጣም እየተዳከመች ሔደች ።
ከሕመሟ ብርታት የተነሣ ደጋግማ በመዝለፍለፏ ፣ በእጆቼ
ማቀፍ ግድ ሆኖብኝ ነበር ። ስርጉጥጉጡ መንገድ ባንገጫ
ገጨን ቁጥር ከጋሪው ግድግዳ ጋር እንዳትጋጭ በይበልጥ
መጠንቀቅም ነበረብኝ ። በድካም ጭነት የተነሣ ክንዶቼ
ላይ ያንቀላፋችውን ወይዘሪት ቁልቁል ስመለከታት ፣ በዐ
ይኖቿ ሽፋሽፍት ላይ ጥላ አረብቧል ። ቢሆንም ገጽታዋ
የደስ ደስ ለዛውን አላጣም ። በተለመደው ቁጣ ፋንታ ደስታ
የሰፈነበት ይመስላል ። በሕልሟ የሚያሥቅ ትርዒት እን
ደሚታያት ሁሉ ዐልፎ ዐልፎ ፈገግታ ይታይባታል ።
‘ ምስኪን ለጋ አበባ ! ምናልባት ጥሩ ጥሩ ነገሮች እንደ
ራዕይ ይታይዋት ይሆናል ’ አልኩ በሆዴ ።

“ወደ ከተማው ስንደርስ ከእንቅልፏ ነቃች ፤ ሰማዩ ጥርት
ብሎ ፀሐይም ጨረሮቿን ፈንጥቃለች ። ወጣቷ ትንሽ
ቀለል ብሏት መንፈሷም ዘና ብሏል ። ከተማው ውስጥ ገብ
ተን እስረኛችንን በፖሊስ ጣቢያ እንድትቆይ ካደረግን
በኋላ ፣ ጉዳዩ ወደሚመለከተው ክፍል በመሔድ ሪፖርት
ስናደርግ ያልጠበቅነው ጉዳይ አጋጠመን ። ከተማው የክ
ፍለ ሀገሩ ርዕሰ ከተማ በመሆኑ ፣ ወጣቷ በግዞት ልትቀመጥ
በት ፣ እንደማትችል ትእዛዝ ስለ ተላለፈ ፣ ጉዟችንን ወደ ሌላ
ሥፍራ መቀጠል እንደሚኖርብን ተነገረን ። እንዳጋጣሚ
ሆኖ ፣ የአካባቢው የፖለቲካ ፖሊሶች በግዳጅ ምክንያት ወደ

ሌላ ሥፍራ በመሔዳቸው፣ ወጣቷን እስረኛ እኛው አጅበን
መጓዝ እንዳለብንም ተገለጸልን ።
አዲሱን ትእዛዝ ልንግራት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ስደርስ፣
ግቢው ሰው ብቻ ሆኖ አገኘሁት ። ወጣት ሴቶች፣ ተማሪዎች፣
ሙሉ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወንዶች በብዛት እስረኛችንን
ከበዋታል ። ከአካባቢው እየተያዙ የተፈረደባቸው ግዞተ
ኞች ናቸው ። እርስ በርስ ከሚለዋወጡት ሞቅ ያለ ሰላ
ምታ ሌላ፣ ጫወታቸው ሁሉ ለረጅም ጊዜ እንደሚተዋወቅ
ባልንጀራ ነበር ። ስለ ተለዋጩ ትእዛዝ ለወጣቷ አስረድ
ቻት ጉዟችንን ለመቀጠል ስንነሣ ግዞተኞቹ ፣ ያዋጡትን
ጥቂት ገንዘብና ለብርዱ መከላከያ የሚሆን ከሱፍ የተሠራ
መደረቢያ አበረከቱላት በፍቅር ተሰናበቷት ።
በቀሪው ጉዟችን ላይ ዐልፎ ዐልፎ ቢያስላትም እንኳን፣
ከበፊቱ ይልቅ በጣም ደስ ብሏት ትታይ ነበር ።
በመጨረሻም ፣ ለግዞት ወደ ተወሰነላት አነስተኛ ከተማ
ስንደርስ፣ በቀጥታ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመሔድ ለተረኞቹ
ፖሊሶች አስረከብናት ። የመጀመሪያ ጥያቄዋ በከተማይቱ
ውስጥ ሪያዛንትሴቭ የሚባል ሰው የሚኖር ስለመሆኑ ነበር።
የአዎንታ መልስ ተሰጣት ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ የወረዳው
ፖሊስ አዛዥ መጥቶ ስለምታርፍበት ቦታ ያላትን ሐሳብ
ጠየቃት ። ምንም እንደሌላትና የምታውቀው ነገር አለመ
ኖሩን ገለጠችለት ። ወዲያው አከታትላም ፡ ‘ ሪያዛንትሴ
ቭን ለማግኘት እፈልጋለሁ ’ አለችው ። በሐሳቧ መስማ
ማቱን ለመግለጥ ፣ ቅከሻውን ነቅነቅ አደረገ ። በፍጥነት
ትንሿን ጥቅሏን አንጠለጠለችና ተለየችን ። የስንብት ሰላ
ምታ እንኳን አልሰጠችንም ። ”

4

ታሪኩን ማዳመጥ አለማዳመጤን ለማረጋገጥ ይመ
ስለኛል ፣ ጋቭሪሎቭ ንግግሩን ላንድ አፍታ ቆም አደረገ።



እኔም የተከታተልኩ መሆኑን ለማረጋገጥና፣እግረ መንገ
ዴን ጥያቄም ለማቅረብ ፈልጌ ፣

“ ታዲያ ከዚያን ጊዜ በኋላ ወጣቷን አይተሃት ታውቃለህ ? ” አልኩት ።

“አዎ አንድ ጊዜ አይቻታለሁ ። ብቻ በቀረብኝ ይሻል
ነበር ” አለና ጋቭሪሎቭ ያቋረጠውን የወጣቷን ታሪክ
ቀጠለ ።

“ወይዘሪት ሞሮዞቫን በግዞት ከተማዋ ትተናት ከተመ
ለስን በኋላ ፣ ብዙም ሳይቆይ እንደገና ወደዚያው አካ
ባቢ ተላክን። አንድ ፣ ዛግሪያዥስኪ የሚባል ተማሪ እስ
ረኛ አጅበን በሔድንበት ጊዜ ነበር ። ዛግሪያዥስኪ ተጫ
ዋች ፣ የደስ ደስ ያለው ፣ ዘፈን መዝፈንና አንዳንዴም
ፉት ማድረግ የሚወድ ማለፊያ ወጣት ነበር ። ታዲያ የወ
ጣቱ የግዞት ቦታ ወይዘሪት ሞሮዞቫ በግዞት ከምትኖርበት
ከተማ ዐለፍ ብሎ የሚገኝ በመሆኑ ፣ በጉዟችን ወቅት
በወጣቷ የግዞት ከተማ ውስጥ የማረፍ አጋጣሚ አግኝተን
ነበር ። ትዝ አለችኝ ። ስለ ጤንነቷና ኑሮን እንዴት እንደ
ምትገፋው ለማወቅ ጓጓሁ ።

‘ ባለፈው ጊዜ ያመጣናት ወይዘሪት ትኖር ይሆን ? ’
ብዬ ጠየቅሁ ።

‘ አዎ ! አለች ። ደኅና ናት ። እዚህ ከደረሰችበት ጊዜ
ጀምሮ ከአንድ ግዞተኛ ጋር ነው የምትኖረው ። ከቤቷ ውጪ
በየትም አካባቢ ታይታ አታውቅም ። ከግዞተኞቹ ሁሉ የተ
ለየች ናት ። አንዳንድ ሰዎች ከቤት የማትወጣው በጣም
ታማሚ ስለ ሆነች ነው ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ መጋባታቸ
ውን ያወራሉ ። ብቻ ሁሉም ወሬ ነው ። የተረጋገጠ ነገር
የለም ’ የሚል መልስ አገኘሁ ።

«ወደ ግዞቱ ሥፍራ አጅበን ስናጓጉዛት ወጣቷ የተና
ገረችው ትዝ አለኝ ። ‘ ብሞትም በወገኖቼ መሐል ቢሆን
እመርጣለሁ ’ ያለችንን አስታወስኩ ። ወገኖቿ እነማን
እንደሆኑና እሷም ያለችበትን ሁኔታ ለማወቅ ከቀድሞው
የበለጠ ጉጉት አደረብኝ ። ቤቷ ሔጄ ልጠይቃት ወሰንኩ።
ያኔ በጉዟችን ወቅት ያቅሜን ያህል ልንከባከባት ከመሞ
ከር ሌላ ፣ እንድትከፋ ያደረግሁበት አጋጣሚ ትዝ ስለማይ
ለኝ ፣ ብጎበኛት በደስታ ትቀበለኛለች የሚል እምነት ነበ
ረኝ ።

«ያካባቢው ሰዎች የመኖሪያዋን አቅጣጫ እየጠቆሙኝ
ወደዚያው አመራሁ ። ከከተማው ዳርቻ ላይ የምትገኝ አነ
ስተኛ ቤት ነች ። የፊት ለፊቱ በር ዝቅ ብሎ ስለ ተሠራ ፣
ሲገቡ ጐንበስ ማለትን ይጠይቃል ። ወደ ዋናዉ ክፍል
ገባሁ ። በቂ ብርሃን ያላትና በሥርዓት የተያዘች ንጹሕ ክፍል
ናት ። በአንደኛዉ ጥጋት አነስተኛ የሸራ አልጋ ተዘርግ
ታለች ። በመጽሐፍ መደርደሪያውና በጠረጴዛውም ጭምር
በርከት ያሉ መጽሐፍ ተቆልለዋል ። በአንደኛዉ ማዕዘን
ደግሞ እንደ አልጋም የሚያገለግል አግዳሚ ወንበር ተቀ
ምጧል ።

«ወደ ክፍሏ በገባሁ ጊዜ ፣ ወጣቷ በሸራው አልጋ ላይ
እግሮቿን አጣጥፋ በመቀመጥ ጨርቅ ብጤ ትሰፋለች ።
ለሙቀት እንዲሆናት ወፍራሙን ነጠላዋን ፣ ደረብ አድርጋ
ለች ። ሪያዛንትሴቭ የሚባለው አብሯት የሚኖር ግዞተኛ
በአጠገቧ ከሚገኝ አንድ ሌላ አግዳሚ ወንበር ላይ ቁጭ
ብሎ ድምፁን ከፍ በማድረግ ከአንድ መጽሐፍ ውስጥ ያነ
ብላታል ። መነጽር ዐይኖቹ ላይ አድርጓል ። ሲያዩት ኮስታ
ራና ጥንቁቅ ይመስላል ። እሷም በእጅዋ የያዘችውን
ጨርቅ እየሰፋች ታዳምጣለች ።



«በሩን ከፍቼ ስገባ ከልጅቱ ጋር ዐይን ለዐይን ግጥም
አልን ። ወዲያው ብድግ እንደ ማለት ቃጣትና የመደናገጥ
ድምፅ በማሰማት ፣ የሪያዛንትሴቭን እጅ ጥብቅ አድርጋ
ያዘችው ። ዐይኖቿ ትልልቅ ሆነው ፍርሃት ይነበብባቸዋል።
ፊቷ ከቀድሞው ይበልጥ ገርጥቷል ። የሰውዬውን እጅ
በጣም ማጥበቋን በመቀጠሏ ፣ ‘ምን ሆንሽ ?. . . አይዞሽ !
ረጋ በይ ! ’ አላት ። በመጀመሪያ አላየኝም ነበር ። ወጣቷ
ቀስ ብላ እጁን እየለቀቀች ከመቀመጫዋ በመነሣት ‘ ደኅና
ሁን ። እነዚህ ሰዎች ሞቴን እንኳን በጸጥታ እንዳልሞት
የሚፈልጉ ይመስለኛል ’ አለችው ። በዚህ ጊዜ ነበር ወደ
ቤታቸው ውስጥ መግባቴን የተረዳው ። ዞር ብሎ ተመ
ለከተኝና ከተቀመጠበት በፍጥነት ተነሣ ። ተንደርድሮ
ሊያንቀኝና ሊገድለኝም የፈለገ መስሎ ታየኝ ። ቁመቱ
ረጅም ነው ። ጠቅላላ ሁኔታውን ሲያዩት ሙሉ ጤና ያለው
ይመስላል ።

«ወደ ቤታቸው የሔድኩት ለሰላምታ ሳይሆን ወጣቷን
ወደ ሌላ ሥፍራ ለመውሰድ እንደ ተላከሁ አድርገው መገ
መታቸው ገባኝ ። ነገር ግን ፣ ብቻየን መሆኔንና በድንጋጤ
ከው ብዬ መቆሜን ሰውየው ሲመለከት ቀስ ብሎ እጅዋን
ያዘና ፣ ‘ረጋ በይ ! ራስሽን ጠንከር አድርጊው’ አላት ።
ወደኔ መለስ በማለት ፣ ‘ወንድሜ ከእኛ የምትፈልገው ጉዳይ
አለህ ? ’ የሚል ጥያቄውን አቀረበልኝ ።

«ወደ ግዞት ቦታ እስረኛ አጅበን ስናልፍ እግረ መንገ
ዳችንን በከተማው ስላረፍን ፣ በራሴ ፍላጎት ወጣቷን ልጠ
ይቅ መምጣቴንና ፣ በመጀመሪያ ወደ ግዞት ቦታዋ አጅቤ
ባደረስኩዋት ጊዜ በሕመም ትሠቃይ እንደ ነበር ስለማውቅ፣
ስለ ጤንነቷና ስለ ኑሮዋ ለመጠየቅ እንጂ፣ሌላ የተለየ ተል
ዕኮ እንደሌለኝ ገለጽሁለት ። ንግግሬን ሲሰማ ጋብ አለ ።
እሷ ግን ከንዴቷ ልትመለስ አልቻለችም ። ቁጣ መላ አካ

ቷን ሲያምሰው ያስታውቃል ። ‘ በመንገዳችን ላይ ምን በደል አድርሼባት ነበር ’ አልኩ በልቤ ። ‘ባይሆን እንኳን አይቫኖቭ እንጂ ፡ እኔ መቼም የተቻለኝን ያህል ለማድረግ ከመሞከር አልተቆጠብሁም ’ የሚል ሐሳብ ይመላለስብኝ ጀመር ።

«ሪያዛንትሴቭ ስለ ዓላማዬ በደንብ ከተረዳ በኋላ ፡ ወደ ወጣቷ ዞር ብሎ እየሣቀ ይቀልድባት ጀመር ። ‘እየሽ ይህን ነበር ፡ ብዙ ጊዜ ደጋግሜ የነገርኩሽ ’ አላት ። ከዚያ በፊት ስለ እኔና በጉዞው ወቅት ስላጋጠማት ሁኔታ ተነጋግረው እንደ ነበር ገባኝ ።

‘ አስደንግጫችሁ እንደሆነ በጣም አዝናለሁ ። ይቅርታ አድርጉልኝ ። ለጉብኝት የመረጥኩትም ጊዜ አጉል ሊሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ ከመሔዴ በፊት መጥፎ ሰው እንዳልሆንኩና ለተንኮል እንዳልመጣሁ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ ። ብቻ ለማንኛውም ይቅርታ አድርጉልኝ’ አልኩ በመደጋገም ።

«ሪያዛንትሴቭ ብድግ ብሎ በትኩረት ከተመለከተኝ በኋላ ፡ እጁን ለሰላምታ ዘረጋልኝ ።

‘ በመልስ ጉዞህ ወቅት ብትጠይቀን ደስ ይለናል ። ጊዜ ካገኘህ ’ አለኝ ።

«ወጣቷ የተለመደውን የማፌዝ ዐይነት ፈገግታዋን አሳየችኝና ወደ ሪያዛንትሴቭ መለስ ብላ ፡

‘ተመልሶ እንዲጠይቀን የሚያስፈልግበት ምክንያት አይታየኝም ። አንተም ለምን እንደምትጋብዘው አይገባኝም ’ አለችው ።

‘ ምንም አይደለም ፤ ደስ ካለው መጥቶ ቢጠይቀን ክፋት የለውም ’ አለ ሪያዛንትሴቭ ። በኋላም ወደኔ ዞር



ብሎ ፡ ‘እና እንዳልኩህ ብቅ ለማለት ሞክር ። ምንም አይደለም ደስ ይለናል ’ ሲል ጨመረበት ። ከዚያ በኋላ የተናገሩት ብዙም አልገባኝም ። መቼም የናንተ ቋንቋ በተለይ እርስ በርሳችሁ ስትወያዩ የምትጠቀሙበት ለእኔ ዐይነቱ ከበድ ይላል ። ታዲያ ምን እንደሚሉ ለመረዳት ያህል ትንሽ መቆየት ቢያምረኝም ፡ አነጋገራቸውና ጠቅላላ ሁኔታቸው እንድሰናበታቸው መፈለጋቸውን ግልጽ ስላደረገልኝ ሳልወድ ወጥቼ ሔድኩ ።

«ዛግሪያዥስኪን አጅበን ወደ ግዞት ቦታው ካደረስን በኋላ ፡ በጥቂት ቀናት ውስጥ ልጅቷ ወደምትኖርበት ከተማ ተመለስን ። እንደ ደረስን የከተማዉ ፖሊስ አዛዥ ጠርቶን ሌላ ትእዛዝ እስከ ተሰጠ ድረስ በሥፍራው መቆየት እንዳለብን ነገረን ። ‘ ተለዋጭ ትእዛዝ እስከ መጣ ድረስ ከዚህ እንዳትንቀሳቀሱ ሰሞኑን በደረሰኝ ቴሌግራም ተገልጾልኛል ። ’ መመሪያው ቁርጥ ባለ አነጋገር ነበር ። ምንም ምርጫ አልነበረንምና እዚያው ቆየን ።

«ወጣቷን በድጋሚ ለመጠየቅ አሰብሁ ። እንደ በፊቱ የጠቋሚ ርዳታ ሳያስፈልገኝ ወደ መኖሪያ ቤቷ ስሔድ ፡ በቅድሚያ ያገኘሁት ቤቱን በከፊል እየተጠቀመበት ከፊሉን ያከራያቸውን የቤቱን ባለንብረት ነበር ። በአጋጣሚው በመጠቀም ስለ ወጣቷ አንዳንድ ነገሮችን እንዲነግረኝ ጠየቅሁት ። ‘ ጤናም የላት ፡ በጣም አሥጊ ደረጃ ላይ ያለች ትመስላለች ። ምናልባትም ብዙ ዕድሜ ላይኖራት ይችላል ’ በማለት አስረዳኝ ። በንግግራችን መካከል ፡ ሪያዛንትሴቭ ከሚኖርበት ክፍል በኩል ብቅ አለ ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ‘ እና ተመልሰህ መጣህ ማለት ነው ? ታዲያ ለምን ወደ ውስጥ አትዘልቅም ? ’ የሚል ጥያቄውንና ግብዣውን በአንድነት አቀረበልኝ ። ዝግ ባለ ርምጃ ወደ ውስጥ ስገባ እሱም ከኋላ ተከተለኝ ።

«‘ ያ ግራ የገባው ሰውየ ዛሬም ተመልሶ መጣ?’ አለች፣ ወጣቷ ገና ስታየኝ ። ‘ አንተ ነህ መጥቶ እንዲጠይቀን የጋበዝከው ’ ሪያዛንትሴቭን አከታትላ ጠየቀችው ።

‘እኔ በበኩሌ እንዲጐብኘን የተለየ መልዕክት አልሰደድሁለትም ። በራሱ ፈቃድ ነው ሊጠይቀን የመጣው’ አላት ። በበኩሌ ከፋኝ ። ዝም ለማለትና ለመታገሥ አልቻልኩም ።

« ‘ለመሆኑ ምንድነው ያደረግሁሽ ወይዘሪት ! እስከዚህ የጠላሽኝ ምን በድየሽ ነው ? ጠላትሽ እንኳን አይደለሁ ’ አልኳት ። አነጋገሬ የብስጭት ነበር ።

« ‘ነህ ! ጠላቴ መሆንክን ማወቅ አለብህ !’ ለማንባረቅ ሞከረች ። ግን ድምጿ ከቀድሞው ይልቅ ደካማና ቀሰስተኛ ሆኖ ተሰማኝ ። ጉንጮቿ እንደ ፍም ቀይ ሆኑ ። ሁኔታዋ አሳዘነኝ ። ከዚያ ጊዜ በኋላ ለረዥም ጊዜ በሕይወት እንደማትቆይም ገመትሁ ። ሳላውቀው ይቅርታ የመጠየቅ ፍላጐት ተናነቀኝ ። ‘ ይቅር ሳትለኝ ብትሞትስ ?’ ራሴን ጠየቅሁ ። ወደዚያው ጊዜ ሳላባክን ፣

« ‘ወይዘሪት ሆይ ፣ በድየሽ ከሆነ ይቅርታ አድርጊልኝ ’ አልኳት ፣ ትሕትና ባልጐደለው አንደበት ። እሷ ግን በንግግሬ ይበልጥ ጤሰች ።

« ‘ይቅርታ አልከኝ ። በጭራሽ አይታሰብም ። ከኔ አንዳችም ይቅርታ አትጠብቅ ። ምናልባት ብዙም አልቆይ ይሆናል ። በቅርቡ እንደምገላገል ይሰማኛል ። ግን ላንተ የሚሆን ቅንጣት ይቅርታ በልቤ ውስጥ የማይገኝ መሆኑን እንድታውቀው እፈልጋለሁ ’ አለች ።»

ጋቭሪሎቭ ድንገት ንግግሩን አቋረጠና ጸጥ አለ ። ለትንሽ ጊዜ ሲያስብ ቆይቶ ፣ ለስለስ ባለ አንደበትና በቆዘመ ሁኔታ ንግግሩን ቀጠለ ።



እንደ ተለመደው ለኔ በማይገባ ቋንቋ ሁለቱ ውይይታቸውን ቀጠሉ ። ትርጉማቸው ባይገባኝም ከቃላቶቻቸው አብዛኞቹ እስከ ዛሬ በትዝታዬ ተመዝግበው ስለሚኖሩ ፣ ብነግርህ ምናልባት አንተ ትረዳቸው ይሆናል ። ለኔ ግን ያኔም ሆነ ዛሬ ትርጉም አልባ ናቸው ።

‘አየሽ አሁን ቤትሽ ድረስ የመጣው እንደ ማንኛውም ጠያቂ እንጂ ፣ እንደ ፖለቲካ ፖሊስ ሆኖ አይደለም ። ያን ጊዜ እዚህ ድረስ አጅቦ ሲያመጣሽ የሚያደርገውና የሚፈጽመው ሁሉ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ነበር ። ዛሬ ግን ሁኔታው የተለየ ነው ። ዛሬ ሊጠይቀን የመጣው በራሱ ፈቃድና ፍላጐት እንጂ በትእዛዝ አይደለም ’ አላትና ወደኔ ዞር ብሎ ’ አንተስ ምን ይመስልሃል ? ለመሆኑ ስምህ ማነው ? ’ ሲል ጠየቀኝ ።

‘ ስቴፓን ፔትሮቪች ጋቭሪሎቭ ’ መለስኩለት ።

‘እንግዲህ ባልሳሳት ስቴፓን አንተ እዚህ ድረስ የመጣኸው በግል ፍላጐትህና ሰብአዊ ስሜትህ ገፋፍቶህ መሰለኝ ። ትክክል ነኝ ? ’ አለ ።

‘ትክክል ነህ ። አመጣጤ በግል ፍላጐቴ ነው ። እንዲያውም እንደ እውነቱ ከሆነማ ግዞተኞችን ወደ መኖሪያቸው ሔዶ መጠየቅ በደንባችን በፍጹም የተከለከለ ነው። የበላዮቼ ይህን ድርጊቴን ቢረዱ ፣ ብዙ ጣጣ እንደሚደርስብኝ የማውቀው እኔ ነኝ ’ አልኩት ።

‘አየሽ ምን እንደሆን ጉዳዩ ? ’ አላት ፣ እጅዋን እየጨበጠ ። እሷ ግን በብሽቀት መንፈስ እጅዋን ከእጁ ምንጭቅ አድርጋ አላቀቀችው ።

‘ጉዳዩ ሁሉ ለኔ ምንም ትርጉም የለውም ። አንተ የምትለው ሁሉ በፍጹም ሊገባኝ አይችልም ። ያልሆኑና የሌሉ ነገሮችን እንደሆኑና እንዳሉ አድርገህ መገመት ዐመ

ልህ ነው ’ አለችው ወጣቷ ። ‘ እኔና ፖሊሱ ፡ እንደ ማንኛውም ሰው ተራ አእምሮ ያለን በመሆናችን፡አካፋን አካፋ ብለን ከመጥራት በስተቀር፡ያልሆነውን ነው የሚል ትርጉም የምንሰጥ አይደለንም ። አንዳችን ለሌላው ጠላት ነን ። የርሱና የመሰሎቹ ሥራ እኔን ፡ አንተንና መሰሎቻችንን በዐይነ ቁራኛ መጠበቅ ነው ። የኛ አንዱ ተግባር ደግሞ እነርሱን መፈታተን ፡ ከተቻለንም ከነሱ በልጠን ቆቅ ለመሆን መሞከር ነው ። እየው እስቲ እንዴት አስልቶ እንደሚያዳምጠኝ ። የምናገረው ሁሉ የሚገባው ከሆነ ወደ አለቆቹ ዘንድ ሔዶ ቃል በቃል ሪፖርት እንደሚያደርግ እርግጠኛ ነኝ ’ አለች ወጣቷ ። ሪያዛንትሴቭ ወደኔ ዞር ብሎ በመነጽሩ ውስጥ እያነጣጠረ በጥሞና ያስተውለኝ ጀመር ። እንደ ስለት የሚወጉ በሚመስሉት ዐይኖቹ ብልህነትና ደግነት ይነበባሉ ።

‘ ለዚህ ዐይነቱ ንግግር ምን መልስ አለህ ? ’ አለና ለጥያቄው መልስ ሳይጠብቅ ፡ ‘ግን ተወው ፤ ምንም እንድታስረዳኝ አያስፈልግም ። እንዳስቀየምንህ ይገባኛል ’ በማለት ደመደመ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ፡ ወጣቷ የተናገረችው በአብዛኛው ትክክል መሆኑ ሳይሰማኝ አልቀረም ። የማገለግለውን ሥርዓት የሚጻረር የተቃውሞ ንግግርም ሆነ ድርጊት በሚያጋጥመኝ ጊዜ ፡ ለሚመለከተው ክፍል ሁኔታውን ማሳወቅ ግዴታዬ መሆኑ ግልጽ ነው ። አባቴ እንኳን ቢሆን በዝምታ ማለፍ አይገባኝም ። ግን ወደዚያ ቤት የሔድኩት ይህን መሳይ ተግባር ለመፈጸም ባለመሆኑ የሆዴን ለመረዳት ባልቻለችው ወጣት አነጋገር ቅር መሰኘቴ አልቀረም ። ከቤቱ ለመውጣት ፊቴን ወደ በሩ ሳዞር ሪያዛንትሴቭ እንድቆይ ጠየቀኝ ።



« ‘ ለምን ትሔዳለህ ስቴፓን ፔትሮቪች ? ትንሽ ብትቆይ ምናለ ’ አለኝ ። ወደ ሞርዞቫ ዞር ብሎ ታረቅሽው አልታረቅሽው ለሱ ምንም ፋይዳ የለውም ። እንዲያውም የተበደለውና ይቅርታ ሊጠየቅ የሚገባው እሱ ነው ። ጠላትም እንኳን ቢሆን እንደ ማንኛውም ሰው ሰብአዊ ስሜቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ ለመረዳትና ለመቀበል ያልቻልሺው አንቺ ነሽ ’» አላት ።

«‘እኔ እንደዚህ ከሆንኩ አንተ ደግሞ ባለጌ ፡ ልዝብ ጋኔን ነህ ! አንተ የምታስበው ለመጻሕፍትህ ብቻ ነው ።’ አነጋገሯ በጩኸት ነበር ።

« ሪያዛንትሴቭ ከመቀመጫው ተፈናጥሮ ተነሣ ።

«‘ ባለጌ ጋኔል አልሽ። ትክክል አለ መሆንሽን ፡ የተናገርሽው ሁሉ እውነት አለ መሆኑን ልቦናሽ እንደሚያውቀው አልጠራጠርም ’ አላት ።

«‘ እኔስ የምናገረውንም የምሠራውንም በሚገባ ዐውቃለሁ ። አንተ ግን እውነቱን ተናግሬአለሁ ብለህ ታምናለህ ? ’ አለች ።

«‘ በሚገባ። አንቺ ከራስ ጠጉርሽ እስከ እግር ጥፍርሽ ገና ያልተለወጥሽ የከበርቴ ዘመዶችሽ አምሳያ ነሽ. . . . ’ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው ። ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብላ ስታስብ ከቆየች በኋላ እጅዋን ዘረጋችለት ። ጨበጠው ። ፊቱን ትክ ብላ ከአስተዋለች በኋላ ፡ ‘ ትክክለኛ ነህ ብዬ አምናለሁ ’ አለችው ።

በኔ በኩል የሁለቱን ንትርክ ከዳር ሆኜ መመልከቱን አልወደድኩትም ። ራሴን ሞኝ አድርጌ ገመትሁት ። ጉሮሮዬ ውስጥ አንዳች ነገር ተሰንቅሮ ተናነቀኝ ። ወጣቷ ፊቷን ወደኔ አዞራ ፡ ቁጣና ብስጭት በማይታይበት የረጋ አመለካከት እያስተዋለችኝ እጅዋን ዘረጋችልኝ ።

«‘ልነግርህ የምፈልገው ሁለታችን ምንጊዜም ጠላቶች እንደ ሆንን ነው ። ግን፤እንድንጨባበጥ ፈቃደኛ ነኝ ። እና ደግሞ፡ዘወትር ትእዛዝ ፈጻሚ ብቻ ሆነህ ከመኖር ዐልፋህ አንድ ቀን ሰው እንድትሆን ፤ ሰብአዊ ፍጡር ለመሆን እንድትበቃ እመኝልሃለሁ’ አለችኝና ወደ ሪያዛንትሴቭ ዞር ብላ ‘በጣም ደክሞኛል’ አለችው ።

ተሰናብቻቸው ወጣሁ ። ሪያዛንትሴቭ እስከ ደጅ ድረስ ሸኘኝ ። ውጭ ቆመን ስንሰነባበት በዐይኖቹ እንባ ግጥም ሲል ያየሁ መሰለኝ ።

«‘እስከ መቼ ነው በከተማው ውስጥ የምትቆየው ስቴፓን ፔትሮቪች ?’ ጥያቄዉ በለሰለሰ አነጋገር ነበር ።

«‘ሁለት ፤ ግፋ ቢል ሦስት ቀናት . . . ብቻ ማንኛውንም የሚወስነው የሚቀጥለው ፤ ፖስተኛ መምጣት ነው’ አልኩት ።

‘ደስ ካለህ ከመሔድህ በፊት መጥተህ ልትጠይቀን ትችላለህ ። ቤታችን ቤትህ ነው ። ነገሩን ሁሉ ከሥራህ ጠባይ አንጻር ሳየው ጥሩ ሰው ትመስለኛለህ’ አለ ።

‘ብቻ አስደነገጥኳት መሰለኝ ። በጣም አዝናለሁ ።’

‘መቼስ መደንገጧማ የት ይቀራል ። ግን ሌላ ጊዜ ልትጐበኘን ፈቃድህ ከሆነ ፤ ቤቱን ያከራዩን ሰው መምጣትህን በቅድሚያ እንዲያሳውቁን ብታደርግ መልካም ነው’ አለኝ ።

‘አንድ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ ። ቀደም ሲል ስትነጋገሩ በደንብ ገብቶኝ ከሆነ ፤ ወይዘሪቷ የአንድ ትልቅና ከበርቴ ቤተሰብ ወገን ትመስለኛለች ። ትክክል ነኝ ?’ ስል ጠየቅሁት ።

‘ምንም ትሁን ምን ዓላማዋ ሌላ ነበር ። ምን ያደርጋል ። አሁንማ አንድ ጊዜ ሰብራችሁዋታል ። ግን ልታ



ጐብጧት አትችሉም ። ያን አንተም ራስህ ሳትረዳው የቀረህ አይመስለኝም ። እንደሷ ዐይነት ሰዎችን አንደኛውን ለመስበር ይቻል እንደሆነ እንጂ ፤ ለማጉበጥና ለማጠፍ ግን በፍጹም ዘበት ነው ። እንዲያጐበድዱ ማድረግም በጭራሽ አይሞከርም’ ሲል መለሰልኝ ።

“ሰላምታ ተለዋውጠን ተለያየን ።

“ከዚያ ቀን በኋላ ወጣቷ ብዙም ሳትቆይ ሞተች ። ምንም እንኳን በጊዜው እኔም በከተማው ውስጥ የነበርኩ ቢሆንም ፤ በፖሊስ ጣቢያው የያዝኳቸው አንዳንድ ሥራዎች ፋታ ሊሰጡኝ ስላልቻሉ በቀብሯ ሥነ ሥርዓት ላይ ሳልገኝ ቀረሁ ። በተቀበረች ማግሥት ድንገት ሪያዛንትሴቭን በመንገድ አገኘሁት ። በጣም ተለዋውጧል ። ሁኔታው ሁሉ ያሳዝን ነበር ።

“በሌላ ጊዜ በደግ ዐይኖቹ ያስተውለኝ የነበረው ረጅሙና ኩስታራ ፊት ያለው ሪያዛንትሴቭ፡በዚያን ዕለት ግን በጥላቻ ዐይነት ፊቱን ቅጭም ፤ ቅንድቦቹን ከስክስ አድርጎ ነበር የተቀበለኝ ። ፊቱን በፍጥነት አዞረና ፤ ‘ሰውየው አንተን ማየት በጣም ነው ያስጠላኝ ። ከአጠገቤ ብትሔድልኝ እወዳለሁ’ አለኝ ። ወዲያው አንገቱን በኀዘን ሰበር አድርጎ በማቀርቀር በዝግታ ርምጃ መንገዱን ቀጠለ። ወደ ማረፊያዬ ስመለስ በጣም ከብዶኝ ነበር። ነገሩ ሁሉ ተማትቶብኝ ውዥንብር ውስጥ ወድቄና ብስጭትጭት ብዬ ለሁለት ቀናት ያህል፡እህል የሚሉ ባፌ ሳይዞር ቆየሁ። ከዚያ ቀን አንሥቶ ለረጅም ጊዜ ሊለቀኝ ያልቻለ ኀዘንና ትካዜ ወረረኝ ።

“በማግሥቱ ፤ የፖሊሱ አዛዥ የሚጠብቀው ደብዳቤ የደረሰው መሆኑን በመግለጽ ፤ ወደ መጣንበት እንድንመለስ አሰናበተን ። ደብዳቤዉ፡ወጣቷ ሞሮዞቫ ይበልጥ ራቅ ወዳለ ሥፍራ እንድትጋዝ የሚገልጽ ተጨማሪ ትእዛዝ

የያዘ እንደ ነበርም ተረዳን ። በጣም ዘግይቷል ። የኔ ኀዘን ይፀልጥ በረታ ። እሷ ግን ተገላግላለች ።

“የመልስ ጉዟችንን ቀጠልንና በመንገዳችን ላይ ወደ ምትገኝ አንዲት አነስተኛ ጣቢያ ስንደርስ ፤ እንደ ተለመደው ጥቂት ዕረፍት ለማድረግ ቆም አልን ። በጣቢያው የማረፊያ ቤት ውስጥ በአንድ ጠረጴዛ ላይ የሻይ ማፍያው ‘ ሳሞቫር ’ ተቀምጧል ። ቀላል ምግቦችና መጠጦች ተደርድረው አንዲት ፀዓዳ ልብሶች የለበሱና የደስ ደስ ያላቸው መንገደኛ አዛውንት ሴት ፤ ከማረፊያው ቤት ባለንብረት ጋር ይገባበዛሉ ። ምግብና መጠጡ አዛውንቷ ሴት ለመንገዳቸው የያዙት ስንቅ ነው ። ከምግቡ እየቀማመሱ ባለማቋረጥ ያወራሉ ። ስለ ግል ኑሮዋቸውና ጉዳያቸው ነበር አብዛኛው ወሬ ።

« ‘ እዩ በውርስ ደርሶኝ የነበረውን ቤት ሸጥኩና አስፈላጊ የመሰሉኝን ዕቃዎች ብቻ ቀርቅቤ ተነሣሁ ። ይኸው እንደሚያዩኝ ወደዚያች ምስኪን ልጄ ዘንድ እየተጓዝሁ ነው ። መቼም ሳታስበው ብቅ ስልባት ምን ያህል እንደምትገረም ይታየኛል ። መምጣቴን አስቀድሜ ሳላስታውቃት ድንገት ዱብ ስልባት መደናገጧ ባይቀርም፤ ደስ እንደሚላት ግን አምናለሁ ። መቼም ዐመሏ ነውና መጀመሪያ ብትቆጣም በኋላ ግን ደስ ብሏትም አታባራ ። ግዙት ቅሔደች ወዲህ ደጋግማ በጻፈችልኝ ደብዳቤዎቿ በምንም ዐይነት እሷ ወደምትኖርበት ሥፍራ ለመሔድ እግሬን እንዳላነሣ አስጠንቅቃኝ ነበር ። ታዲያ የወለደ ሆድ አልችል ሲለኝ ምን ላድርግ ? ብትቆጣም እንዳሻት ። ብቻ ፀይኖቿን አይቼው እንደ ፈለገው ይሁን ’ ይላሉ አሮጊቷ ያለማቋረጥ ።

“ንግግራቸው የዱላ ያህል ነበር የመታኝ ። ከመቀመጫዬ ተነሣሁና በቀጥታ ወደ ማዕድ ቤቱ ገባሁ ። የወጥ ቤት ሠራተኛዋን ስለ አሮጊቷ ማንነት ጠየቅሁዋት ።



« ‘ በዚያ ሰሞን አጅባችሁ የወሰዳችሁዋት ወጣት ግዞተኛ እናት ናቸው ’ ስትል መለሰችልኝ ።

«አንዳች ነገር አናቴ ላይ እንደ ተከሰከሰ ሁሉ ፤ ላንዳፍታ ጭው ብሎብኝ ያለሁበት ተረሳኝ ። የፊቴንና የጠቅላላ ሁኔታየን መለዋወጥ የተገነዘበችው የወጥ ቤት ሠራተኛ፤ ‘ ምን ሆንክ ? ’ አለችኝ፤ በጩኸት ።

“ ረጋ በይ እንዳትጮሂ እባክሽ ። ወጣቷ ልጃገረድ በቀደም ዕለት ሞታለች ’ አልኳት ፤ ሁለመናዬ ድንዝዝ ብሎ የምናገረውንም ሳላውቅ ።

«የወጥ ቤት ሠራተኛዋ ፋታም ሳትሰጠኝ እየጮኸች ከማዕድ ቤቱ ስትወጣ፡እኔም መለዮዬን ካስቀመጥኩበት አንሥቼ ተከተልኳት ። እኒያ የደስ ደስ ያላቸው አሮጊት ለማረፊያው ቤት ባለቤት የጀመሩትን ጨዋታ እንደ ቀጠሉ ናቸው ። ስለ ርሳቸው የተሰማኝ ኀዘን ምን ያህል እንደ ነበር ልገልጽልህ ቃላት ያጥሩኛል ። ብቻ ምንም ቃል ሳልተነፍስ የዕውር ድንብሬን ከቤቱ ወጥቼ ወደ ዋናው መንገድ ገባሁ ። ኢቫኖቭን የያዘው ጋሪ ከወደ ኋላዬ መጥቶ አጠገቤ ሲደርስ ተሣፈርኩና መንገዳችንን ቀጠልን ።

« ለዚያች ወጣት ባሳየሁት ርኅራኄና የተለየ ስሜት ለበላዮቼ ሪፖርት ቀርቦ ስለ ነበር ፤ ለብዙ ጊዜ ዕድገት እየታለፈኝ እንድቆይ ተደረገ ። ያቺ እንደ ተከፋች ኖራ ፤ እንደ ተከፋች የሞተች ወጣት ግዞተኛ ትዝታ ግን ፤ እስከ ዛሬም ከአእምሮዬ ሊጠፋ አልቻለም ። አሁን ታሪኩን ሳወጋህ እንኳን ያቺ መቼም መች የማትረሳኝ ልዩ ወጣት ልዐይኔ ሕሊናዬ ቁልጭ ብላ ትታየኛለች ። »

1880 ዓ.ም. 1974ዓ.ም

# ማክሲም ጎርኪይ

(1868—1936)



በሩሲያ ሶቪዬት ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ውስጥ ዛሬ ጎርኪይ ተብላ በምትጠራው፣ የቀድሞዋ ኒዥኒኖቭጎሮድ ከተማ በ1868 ተወለደ ። እውነተኛ ስሙ አሌክሴይ ማክሲሞቪች ፔሽኮቭ ሲሆን፣ ዛሬ በመላው ዓለም የሚታወቀው ግን፥ጎርኪይ በሚለው የብዕር ስሙ ነው ።

የሶቪዬት ሥነ ጽሑፍ መሥራች፣ የሶሻሊስት እውነታነት ሥልት አባት ተብሎ የሚጠራው ማክሲም ጎርኪ፥የሥነ ጽሑፍ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ፥ኀይለኛና የተባች ብዕሩ፥እያሌ ሕያው የኪነት ሥራዎችን አፍልቃለች ። በብዙ ደራሲያን ሥራ የበለጸገውን፥ የሩሲያን ክላሲክ የሥነ ጽሑፍ ባህል እንዲቀጥል በማድረግ፣ አድሶና አሻሽሎ ለተተኪው አዲስ ሶሻሊስት ትውልድ ለማስተላለፍ የድልድይነት ሚና ተጫውቷል ። ዝነኛው የሶቪዬት ኅብረት ደራሲ አሌክሴይ ቶልስቶይም፥ "ሕያው ድልድይ" የሚል ቅጽል የሰጠውም በዚሁ የተንጣ



ነው።ማክሲም ጎርኪ ታላቁ የጥቅምት አብዮት ከፈነዳ በኋላ፥ አዲስና ተራማጅ ሥነ ጽሑፍ ለመመሥረት የታገለውን ያህል፣ ከአብዮቱም በፊት ለወዛደሩ ትግል በድል ማበብና ለጭቁን መደቦች ነጻነት ያደረገው ትግል በቀላሉ የሚታይና የሚዘነጋ አይደለም ። ለዚህ እንጸባራቂ ታሪኩም ምስክር ከሚሆኑ ሥራዎቹ መካከል፣እጅግ ታዋቂ የሆነውና በሞስኮ ፕሮግሬስ ማተሚያ ቤት ወደ አማርኛ የተመለሰው 'እናት ' የተሰኘው ዐቢይ ልቦለድ ይገኝበታል ። ሌኒን " የጊዜው አስፈላጊ መጽሐፍ " ሲል የሠየመው ይህ የጎርኪይ ልቦለድ፥የሩሲያ የኢንዱስትሪ ወዝ አደሮችን ቅድመ አብዮት ሥቃይ የሚያሳይ መስተዋትና፣የዓለም ሠርቶ አደሮችን ለዐመፅ፣ ለአርነት ትግል፣ ለሶሻሊዝም ምሥረታ የሚቀሰቅስ ብርቱ ጥሪ ነው ።

የጎርኪይ ሥነ ጽሑፋዊ አስተዋጽኦ፣በቄሣራዊው መንግሥት እንዲጠመድ ስላደረገው፣ በ1905 ተካሒዶ በነበረው የመጀመሪያው ሕዝባዊ ዐመፅ ሙከራ ወቅት ተይዞ ታሰረ ። ከተለቀቀም በኋላ፣የዘውዱን አገዛዝ የሚቃወሙና ሰፊውን ሕዝብ ለፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያነሣሡ ድርሰቶችንና ድራማዎችን ለሕዝብ አቅርቧል ። ይሁን እንጂ፣የ1905ቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከከሸፈ በኋላ፥ የነበረው ሁኔታ አመቺና አስተማማኝ ባለመሆኑ፣ጎርኪይ አገሩን ለቅቆ ለመሔድ ተገደደ ። መኖሪያውን ካፕሪ ፀተባለችው የኢጣልያ ደሴት አድርጎ በስደት ከቆየ በኋላ፣ በ1913 ዓ. ም. በተደረገው የምሕረት ዐዋጅ ሳቢያ ወደ አገሩ ተመልሶ ለቦልሼቪክ ፕሬስ ጽሑፎችን ማበርከት ጀመረ ። የራሱንም መጽሔት አቋቋመ ።

ጎርኪይ በ1905 እና በ1917 አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች መካከል ስላለው ታሪካዊ ሒደት፥በግልጥ ባለመረዳቱ፣በወሰዳቸው የተሳሳቱ አቋሞች ሌኒን ሒስ የሰነዘረ

በት ሲሆን፡በኋላ ግን ራሱን አስተካክሎ በሐቀኛ ታጋይነት ሊዘልቅ በቅቷል ።

የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት በድል አድራጊነት ከወጣና፡የመጀመሪያዉ የሠራተኛዉ መደብ መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ ፡ ጐርኪይ በጤንነቱ መታወክ የተነሣ ለሕክምናው ሲባል በውጪ አገሮች እንጂ ፡ እምብዛም በሩሲያ ለመቀመጥ ባይችልም፡በርከት ያሉ ልቦለዶችን ፡ አጫጭር ታሪኮችን፡ሒሳዊ መጣጥፎችንና ድራማዎችን በማዘጋጀት፡ ለአዲሱ የሶሻሊስት ሥነ ጽሑፍና ለመላው ዓለም የኪነት ቅርስ መዳበር ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ከዚህም ሌላ፡ ውዝግብና ውዥንብር በሰፈነበት የጥቅምቱ አብዮት የመጀመሪያ ቀውጢ ዓመታት ወቅት ፡ የሶቪዬት ኅብረትን ተራማጅ የደራስያን ማኅበር በመመሥረት ረገድ ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫውቷል ።

ይህ ፡ በጥቂት ሐረጐች ፡ በተወሰኑ ገጾችና በኃያል ውብ ቃላት የዘመናትን የጭቆና ታሪክና የእልፍ አእላፍ ምዝብሮችን ጐስቋላ ሕይወት ቁልጭ አድርጎ የመንደፍ ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ የነበረው ፡ ጽኑ የማይታክተው የወዛደሩ መደብ የብዕር ሰው ፡ ከዕድሜው ዐርባ አራቱን ዓመታት ለሥነ ጽሑፍ ሥራና ለሶሻሊዝም ማበብ መሥዋዕት በማድረግ ከኖረ በኋላ ፡ በ1936 የፖለቲካ ተቀናቃኞቹ በሰጡት መርዝ ልክ በ68 ዓመት ዕድሜው ለዘለዓለሙ አንቀላፋ ። ብዕሩም አብራው ዝም አለች ።



# ሴማጋ ፡ እንዴት እንደ ተያዘ

ትንሽ ሆቴል ናት ። ሴማጋ አንድ ጠረጴዛ ለብቻው ይዞ ተቀምጧል ። በማህን ከቀረበለት ዐሥራ አምስት ኰፔክ የሚያወጣ የተቆራረጠ ቅቅል ሥጋ ሌላ ፡ አንድ ሊትር በሚይዝ ጠርሙስ የተሞላ ቮድካ ፡ ከፊት ለፊቱ ተቀምጧል።

በአንድ ፎቅ ሥር በሚገኝ የምድር ቤት ውስጥ ያለችው የሆቴሏ አነስተኛ ክፍል፡እምብዛም መተናፈሻ የላትም ። ጢስ ጠግቦ በጠቆረው የግንብ ጣርያዋ ላይ ከሦስት አቅጣጫዎች የተፈነጠቀ ብርሃን ዐርፎበታል ። አንደኛው ብርሃን የሚመጣው ባንኮኒው አጠገብ ከተቀመጠ መብራት ሲሆን ፡ ሌሎች ሁለት መብራቶች ደግሞ አማካይ ቦታ ላይ ሆነው ብርሃናቸውን ይፈነጥቃሉ ። የክፍሏን አየር በበረዘው ጢስ ውስጥ የብዙ ሰዎች የደበዘዘ ቅርፅ ይታያል ። ገሚሱ ያወራል ፤ ያወካል ። ሌላዉ ይዘፍናል ፤ ያቅራራል ። አንዳንዱ ይሳደባል ። በዚያች ክፍል እስካለ ድረስ ሁሉም ከዘመኑ መንግሥት ሕግ የተሸሸገ፡ሕጉ እንደ ማይፈጸምበት፡ራሱን በራሱ አሳምኖ የተደላደለ ይመስላል።

በጣም ብርዳም ምሽት ነው ። ከውጭ የበረዶ ውሽንፍር በኃይል ሲወርድ ፡ የተለመደው የበልግ ነፋስ በከፍተኛ ፍጥነት እየተውዘገዘገ ያፏጫል ። በሆቴሏ ክፍል ውስጥ ግን፡ጫጫታውም፡ጭሱም፡የሰው ትንፋሽም፡ምኑም ምኑም ተጋግዞ በቂ ሙቀት አለ ። አንድ የተለመደ ዐይነት ደስ የሚል ጥሩ ሽታ ዐልፎ ዐልፎ አፍንጫን ዳሰስ እያደረገ ያልፋል ።

ሴማጋ ፣ ክፍሏን አፍኖ በሚርመሰመሰው ጢስ ውስጥ ትክ ብሎ የሚያስተውለው በር በሩን ብቻ ነው ። በተለይ ከውጭ የመጣ አንድ ደንበኛ በሩን ከፍቶ በሚገባበት ጊዜ፣ ይበልጥ ይነቃና አስተያየቱም የቆቅ ይሆናል ። ከውጭ የመጣው ሰው አካሉን ሙሉ በሙሉ ወደ ክፍሏ ካስገባ በኋላ ደግሞ ፣ ሴማጋ ወደ ፊት ትንሽ ዘንበል ይልና ፊቱን በእጆቹ በመከለል እሱ ሳይታይ፣ የገባውን ሰው ማንነት ደኅና አድርጎ ያስተውላል ። ሴማጋ ይህን የሚያደርግበት ምክንያት አለው ።

ወደ ክፍሏ የገባውን ሰው ማንነት ፣ ከራሱ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ሲያበቃና ችግርእንደ ሌለ ሲያረጋግጥ፣በብርጭቆ የተሞላውን ቮድካ አንሥቶ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ ያደርገዋል ። ከተቆራረጠው ቅቅል ሥጋ ደግሞ ፣ ጥቂቱን በሹካ ወግቶ በማንሣት ይጎርሳል ። በዝግታ አላምጦ ሲጨርስ ፣ ከንፈሩንና ጢሙን የነካካውን ምግብና ቮድካ *እያጣጣመ እንደገና ወደ በሩ ማተኮሩን ይቀጥላል ።

ሴማጋ ፣ ፊቱ ሰፋ ያለ ሆኖ ፣ ሪዝ የሚባል የለውም ። ትልልቅና ግራጫ መሳይ ዐይኖቹን የማጉረጥረጥ ዐመል አለበት ። ችምችም ያሉት ጥቋቁር ቅንድቦቹ ዐይኖቹ ላይ አጥልተዋል ። በግንባሩ አዘቅዝቆ የወረደው የተጠቀለለ ጸጉር በስተግራ ቅንድቡ ላይ እንደ መረፍረፍ ቃጥቶታል። ብቻ በአጠቃላይ ፊቱን ሲያስተውሉት ፣ የሴማጋ ገጽ ታማኝነት የሸሸው ይመስላል ። በተለይ በዚያ ምሽት ሰፍኖ የሚታየው ስሜት ፣ እጅግ የተዝናኑ ሰዎች ባሉበት የመዝናኛ ሥፍራ መምጣት የማይገባው ዐይነት ነው ። በቁርጠኛ ውሳኔ ማስወገድ ያልቻለው ግራ የሚያጋባ የጭንቀት መልክ ጉልቶ ይነበብበታል ።

---

* ቮድካ ፣ ከስንዴ ፣ ስኳር ድንች ወዘተ ተቀምሞ የሚሠራ ኃይለኛ አልኮል ነው



ወገቡ ላይ በገመድ ታብቶ የለበሰው አሮጌ የሱፍ ኮት ነትቧል ። ከብርድ የሚከላከልበትን ጓንቲ መሳይ የእጅ ልባስና፣ኰፍያውን ጠረጴዛ ላይ ወርወር አድርጓቸዋል ። አንዱን ባዶ ወንበር ደገፍ ብሎ የቆመው፣ ጫፉ ድብልብል ያለ ዱላ ፣ እህል ውሃ አያሰኝም ።

ሴማጋ ፣ የጐረሰውን ምግብ የሚያወራርድበት ቮድካ በማለቁ ፣ ተጨማሪ እንዲቀርብለት ለማዘዝ ቀና ሲል፣ የሆቴሏ በር ድንገት በኃይል ተበረገደና አንድ ድንቡሼ ብላቴና ጥልቅ አለ ። ልብሱ ጭርንቁስ ነው ።

"ይገርማል ጉበዝ ! አሰሳው ቀልጦላችኋል !" አለና ከመግባቱ ፣ በስሜት የተወጠረው ሲቃ መለስ ሳይልለት ። ድምፁ የሕፃን ቢሆንም ኃይለኛ ብጤ ነው ። ክፍሉን የመላው ሁካታ ባንዴ ተግ አለ ። አብዛኛው ሰው በወንበር ላይ አቀማመጡን እያስተካከለ እርስ በርሱ በውይይት ሲያጉተመትምና ሲንሾካሾክ ፣ አንዳንዶች ደግሞ ለልጁ ጥያቄዎችን መወርወር ጀመሩ ።

"ትቀልዳለህ ወይስ የምርህን ነው ?"

"ምኑ ነው ቀልዱ ! . . . . . ነፍሴ ምንጥቅ ልትል ነበር ። ከግራ ከቀኝ እኮ ነው ያዋከቡን ። የእግረኛዉ ፣ የፈረሰኛዉ ፣ ምኑ ቅጡ !"

"እንዴት እኮ ! . . ብዙ ናቸው ለማለት ነው ?"

"እንግዲህ ገምቱት ! በሁለት መኮንኖች አዛማችነት ፣ ጉልቆ መሣፍርት የሌለው ሠራዊት "

" አሰሳው ማንን ፍለጋ እንደሁ ሰምተሃል ? "

" ሴማጋ የሚሉትን ሰው መሰለኝ። ኢኪፎሪችን ከያዙት በኋላ ስለ ሴማጋ ሲጠይቁት ሰምቻለሁ ። " ልጁ ንግግሩን ሲያበቃ ልክ ባንኮኒው አጠገብ ደርሶ ነበር ። ይህን ሰዓት

ነው ፤ ሴማጋ ከመቀመጫው ቀስ እያለ በመነሣት ፤ “ እ-እ-ለምን ? ኒኮፎሪችን ለምን ያዙት ? ” በማለት ድምድም ባለው ጠጉሩ ላይ ኮፍያውን እያስተካከለ ልጁን ጠየቀው።

“ ምክንያቱን እንጃ፡መያዙን ብቻ ነው የማውቀው፤” ልጁ እንደ ዘበት መለሰ ።

“ ቦታው የት ነው ? ”

“ ስቴንካ ጉዳና — እትዬ ማርያ ቤት ። ” ክፍሏን የሞላው ሰው ሁሉ ያተኮረው በልጁ ላይ ነው ።

“ አንተ አሁን ከዚያ ነው የምትመጣው ? ” የሴማጋ ጥያቄ ቀጠለ ። ልጁ ግን ፤ ለዚህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ሰጠና በሦስት እርምጃ ተንደርድሮ ከክፍሉ ወጣ ። እፍታም አልቆየ።የሆቴሏ ባለቤት አዬና ፔትሮቪች ልጁን ተከትለው ወደ በሩ ወጡና ፤ “ አንተ የዛር ውላጅ ፤ አጋንንት! አንድ ሣህን ሙሉ ትመንትፈኝ !” እያሉ ደጃፍ ላይ ቆመው ይጮሁ ጀመር ።

ከሆቴሏ ለመውጣት በሩ ላይ ደርሶ የነበረው ሴማጋ ቀበል አደረገና ፤ “ ሣህን ሙሉ ምን ? ” ሲል ጠየቃቸው ። “ ጉበት ነዋ ! አንድ ሣህን ሙሉ ጉበት ! አንዲት ቁራጭ ሳያስትርፍ እኮ ነው የጠረገው ። ደሞ አፈጣጠኑ በሉ ! ... ሞሽላቃ ! ...እንዲህ አድርጎ ጉድ ይሥራኝ ! ” የሆቴሏ ባለቤት አዬና ፔትሮቪች መንጨርጨራቸውን ቀጠሉ ። አዬና ፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው ፤ ፀይናቸው በመድከሙ የዐይን መነጽር የማይለያቸው ፤ ድርቅ ያሉ ከሲታ አዛውንት ናቸው ። “ አቤት ! እውነትም እንዴት ጉድ ሆኑ ! አሁን አንድ ሣህን ጉበት ተሰረቁና ልመና ሊገቡ ነዋ!” ደረቅ ሬዙን ጣል አደረገና ሴማጋ ፤ ከሆቴሉ ውልቅ አለ ።



በጉዳናው ላይ የሚውዘገዘገው ቀዝቃዛ ንፋስ ድምፁ ከቀድሞው ተለውጦ ለስለስ ያለ ዐይነት ሆኗል ።የሚዘንበው ሳሳ ያለ በረዶ ግን ፤ አሁንም አልተቀነሰም ። ሴማጋ ከትንሹ ሆቴል እንደ ወጣ ወዲያውኑ ጉዞውን አልተያያዘውም ። ደጃፉ ላይ ቆም አለና ጆሮውን አቅንቶ ማዳመጥ ጀመረ ። በየቤቱ ጣርያና ግድግዳ ላይ የሚያርፈው በረዶ ከሚፈጥረው ድምፅና ከነፋሱ የለሆሳስ ሹክሹክታ በስተቀር ኮሽታ እንኳን አይሰማም ። ሰሜን ፤ ምዕራብ ምሥራቅ.... ዙርያውን በደንብ አጢኖ ሲያበቃ ፤ በአንደኛው አቅጣጫ ጉዞ ጀመረ ። ፀሥር ያህል እርምጃዎች ነጠቅ ነጠቅ እንዳደረገ ፤ በአንድ አጥር ላይ ዘልለና ከሰው ጓሮ ዘው አለ ። የውሻ ጩኸትና የፈረስ ማስካካት ተቀበለው ። ደነበረና በመጣበት ተመልሶ ወጣ ። ወደ ከተማዉ እምብርት የሚወስደውን ጉዳና ተከትሎ ከቀድሞው በፈጠነ እርምጃ እንደ ገና ጉዞውን ቀጠለ ።

ለጥቂት ደቂቃዎች ከተጓዘ በኋላ ፤ ከወደፊት ለፊቱ የሆነ ድምፅ ሰማ ። ቀልጠፍ አለና ቀረብ ባለው ሌላ አጥር እናት ዘሎ ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ሰው ጓሮ ገባ ። አሁን ግን ፤ ወደ ኋላ የሚመልሰው ዕንቅፋት ስላልገጠመው ፤ በአንድ የተከፈተ በር በኩል አድርጎ ዐለፈ ። ከፊት ለፊቱ ወዳለው ግቢ ሲገባ ፤ ዙርያውን በአትክልት መከበቡን አስተዋለ ። ሌሎች ሁለት ሦስት አጥሮችን በቅልጥፍና አከታትሎ እየዘለለ ተሻገረና ሌላ ጉዳና ላይ ብቅ አለ ። አሁንም ጉዞውን ቀጠለ ።

እየተጓዘ ማሰብ ጀመረ ። የመጣው አሰላ እስኪ.የልፍ ለመደበቅ የሚችልበትን ደኅና ሰዋራ ቦታ በሐሳቡ ያማትራል ። ግን አንድም አመቺ ቦታ አልታይህ አለው ። አሰሳው አንዴ ከተጀመረ ጓዳ ጐድጓዳውን ሁሉ ሳያዳርስ አይገታም ። ስለዚህ ...ቦታዎቹ ሁሉ አደገኛ ናቸው ።

ደግሞ በዚያ ላይ ውጪ ሲታደር በረዶው ፥ ብርዱ ፥ ውርጩ
ምኑም ደስ አይል ። ይቀፋል ፤ ያሠቃያል ፤ ያበሳጫል ።
ዝም ብሎ ወደ ፊት መግፋቱን ቀጠለ ።

ወደፊት እየሔደ ደሞ ፥ ትክ ብሎ ባሻገር ያስተውላል።
ሰማይና ምድሩ መኻል የተዘረጋ ነጭ ሸማ በሚመስለው
የበረዶ ዶፍ ውስጥ ቤቶች ፥ ምሰሶዎች ፥ የመንገድ መብ
ራቶች ፥ ዛፎች ድንገት ብቅ እያሉ ሲገተሩ እንደ ጥላ ይታ
የዋል ። ግን ሁሉም በረዶ ለብሰው ፥ የተባዘቱ የጥጥ ክምር
መስለዋል ። ለማያውቃቸው ያሳስታሉ ።

ድንገት የበረዶው ዶፍ ሲወርድ ከሚፈጥረው ፥ የተለየ
ድምፅ ሰማ ። ድምፁ የመጣው ከፊት ለፊቱ እንደሆነ ርግ
ጠኛ ነው ። ራቅ ቢልም እንኳን ፥ የሕፃን ልቅሶ ይመስላል ።
አዶጋ እንዶ ሽተተው አውሬ ሴማጋ አንገቱን አሰግጎ ቆመ፤
ድምፁ ግን ድጋሚ አልተሰማም ። ጸጥ እርጭ አለ ።

ሴማጋ በመደነቅ ዐይነት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። በረ
ዶና ብርዱን ለመከላከል እንዲረዳው ፥ ኮፍያውን ዐይኑ
ድረስ ጐተተና የግራና ቀኝ ትከሻውን ወደ ላይ ሽምቅቅ
አድርቶ መንገዱን ቀጠለ ።

ብዙም አልተራመደም ! ያ ድምፅ እንደገና ደግሞ
ጥርት ብሎ ተሰማው ። አሁን ግን ሩቅ አልነበረም ። ከአ
ጠገቡ ነው ። ከው አለ ። ዕጢው ዱብ ። ቀጥ ብሎ በጸጥታ
ቆመ ። ትንሽ ቆይቶ አጎነበሰና መሬቱን ይዳብስ ገባ ።
ዳበስ ዳበስና ድንገት እጁ አንድ ነገርን ነካ ። ሲያነሣው
በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር ነው ። የበረዶውን ክምር ከጥ
ቅሉ ላይ ማራገፍ ጀመረ ። ጨርቁን ሲገላልጥ በደከመ
ሁኔታ የሚንፈራገጥ ፥ በቀለጠው በረዶ የቀዘቀዘ ጨቅላ
ሕፃን ብቅ አለ ። ከሴማጋ ቡጢ የማትበልጠው የሕፃኑ ፊት
ከመጨማደዱ በላይ ጃኖ መስላ ቀልታለች ። ዐይኖቹ ተክ



ድነዋል ። ከተጠቀለለበት ጨርቅ የሚንጠባጠበው ውሃ
ከናፍሮቹ ላይ ዐርፎ ድዱን እያራሰ ወደ ውስጥ ሲገባ ፥
ጡት እንደሚጠባ ዐይነት አፉ ይንቀሳቀሳል ።

በድንጋጤ ፈዝዞ የቆመው ሴማጋ ፥ ከቆሻሻው ጨርቅ
የሚንጠባጠበው ውሃ ወደ ሕፃኑ መግባቱ ደግ ላይሆን
ይችላል የሚል ሐሳብ ተሰማው ። በረዶና ውሃውን ለማ
ራገፍ ሕፃኑን ዘቅዝቆ ይነቀንቀው ጀመር ። ይህ ድርጊት
ያልተስማማው ሕፃን ግን እሪ ብሎ ጩኸቱን ለቀቀው ።

"እሽ. . . .እሽ. . . .ማሙሽ ! . ." ሴማጋ ማባበሉን
አላወቀበትም ። " እሽ . . . . ዝም በል ብያለሁ ! . . .
አለዚያ ዋጋህን ታገኛለህ ! . ." እንደ መቆጣትም ቃጣው ።

" ምንህ መሰልኩህ እዚህ አንተን የማንቆላብሰው ?
ላንተ ስሜት ያለኝ . . . . የምፈልግህ መሰለህ ? ሲኔ ብለህ
እንዲሁ ቀጥል ! አልቅስ ! ሞኝ ! . ." ይለው ጀመር ።
ነገሩ ልቅሶውን ለማቆም ነው ።

ግን አልሆነም ። የሴማጋ ቁጣም ሆነ ማባበል ውጤት
አልሰጠም ። ሕፃኑ ድክም ባለ ድምፅ እምርሮ ማልቀሱን
ቀጠለ ።

. . . . የሕፃኑ ልቅሶ አላቋረጠም ። ሴማጋ ፥ ትንሽ
ቆየና አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰ ። "እንግዲህ በምንም ሁኔታ
ልረዳህ አልችልም ። የማደርግልህ አንድ ነገር ብቻ ነው"
አለና ፥ ሕፃኑን በጨርቁ ጥቅልል አድርጎ እዚያው አገ
ኘበት ቦታ ላይ መልሶ አስቀመጠው ።

" አዎ ፤ ምንም ላደርግልህ አልችልም ። " ሴማጋ
ማጉተምተሙን ቀጠለ ። " እኔም ራሴ ያንተው ብጤ
ነኝ ። ከእጅ አይሻል ዶማ . . . . ! ' ምን ለምን ዉደጋገፍ
ተያይዞ ዘፍ ' አሉ . . . እና እንግዲህ . . . ደኅና . . . ሁን

ልኝ ! . . . በቃ ይኸው ነው ። ሌላማ ምን ማድረግ ይቻላል ።” እጇን በሰላምታ አወዛውዞ ጉዞውን ቀጠለ ።

“ ግን እኮ . . . ይኽ አሰሳ ባይኖር እኮ አንዲት ቦታ ፈልጌ ሕይወቱን ላድናት እሞክር ነበር ” እያለ በመንገዱ ላይ ለብቻው ይነጋገር ጀመር ። “ አዎ አሰሳው ባይኖር ደግ ነበር ። ግን ምን ማድረግ እችላለሁ ? . . . ምንም ፤ ለራሴም ያሠጋኛል ። ብቻ ይቅርታ እንደማትነፍገኝ አምናለሁ ። ማሙሽ ጓዴ ። አንተማ ምን ታደርግ ፡ ለራስህ ንጹሕ ነፍስ ነህ ። ያቺ እናትህ ናት ርኩስ ።” ሴማጋ በሐሳቡ ከሕፃኑ እናት ጋር የተገናኘ መስሎት ፡ ድንገት መደንፋት ጀመረ ።

“ እህ ! የኛ እናት ተብዬዋ ! ዋ ! ባገኘሽ እንቺን አያድርገኝ ። ጧት ማታ እየቀፈቀፍሽ ፡ በየሜዳው እየጣልሽ የምትኖሪ ይመስልሻል . . . . በዚህ ዐይነት የምትዘልቂው ? . . . . . ደግሞ በደረቅ አየር ቢሆን በተሻለ ። እስቲ የግፍ ግፍ ይህን መሳይ የበረዶ ዶፍ እየጣለ ።” እንዲህ ሲለፈልፍ ቆይቶ ድንገት ከሐሳቡ ተመስጦ መለስ ሲል ፡ በጨርቅ የተጠቀለለው ሕፃን ካለበት ቦታ የቆመ መሆኑን ተገነዘበ ። ወደፊት በመጓዝ ፋንታ ወደ ኋላ መመለሱን ልብ አላለም ነበር ። በልፍለፋው ወቅት የትኛው ነጥብ ላይ ሲደርስ እንደ ተመለሰ ወይንም እንዴት እንደ ተመለሰ በፍጹም አያውቅም ።

ብቻ ፡ አሁን ምንም ሳያመነታ ሕፃኑን በፍጥነት አነሣና ፡ ኮቱ ውስጥ ውሽቅ አደረገው ። በዐይን ሕሊናው በሚያየው የሕፃኑ እናት ላይ ለመጨረሻ ጊዜ አንዴ አንባረቀና የተቋረጠ ጉዞውን ቀጠለ ። አሁን ግን ፡ እንደ በፊቱ ቀለል አላለውም ። ስለ ሕፃኑ የተሰማው ኀዘን ልቡን ክፉኛ ተጭኖታል ። በዚያን ወቅት ለተመለከተው ደግሞ እርሱም ራሱ የሕፃኑን ያህል የሚያሳዝን ነበር ።



ሕፃኑ በዚያ የነተበ ኮት ተጀቡኖ በመታፈኑና የሴማጋ መዳፍ ስለ ተጫነው ፡ ባለበት ሆኖ ይወራጫል ። ትንሽ እንደ ተጓዘ ሴማጋ አንዳች ነገር ተሰማው ። እየተሻለው ከሔደው ሕፃን አካል የሚመጣው ሙቀት ፡ ከሱፍ ኮቱ ሥር በለበሳት የተቀዳደደች ሸሚዝ ዘልቆ አካሉን ሲያተኩሰው ፡ ሴማጋ የግድ ፈገግ አለ ።

ጉዞውን ቀጠለ ። ገና መወራጨቱን ያላቆመው ሕፃን እያለቀሰ አካባቢውን እንዳያነቃበት ፡ ሴማጋ አሁንም አሁንም ያባብለዋል ። ለጊዜው ካልሆነ ዘላቂ ዕርዳታ ሊያደርግለት የማይቻል መሆኑንም እየደጋገመ ያወራለታል ። “ አንተ ሞገደኛ ” ይለዋል ። “ ዕድለ ቢስ ነህ ። ምን እንደማደርግህ . . . . የት እንደምወስድህ ሊገባኝ አልቻለም ። . . . ብቻ ያቺን እናትክን ባገኛት እሷን አያርገኝ . . . እሽ . . . እኮ አትንፈራገጥ ፤ ትወድቃለህ ” ይለዋል ፡ ወደፊቱ እየተጓዘ ።

ትንሽ ሔድ እንዳለ ፡ መሞቅ የጀመረችው የሕፃኑ ፊት ከሸሚዙ ቀዳዳዎች በአንደኛዉ በኩል ሾልካ ፡ ደረቱን ስታሸው ተሰማው ። ሴማጋ ድንግጥ አለ ። እርምጃው ተቋረጠ ። ቀጥ ብሎ ቆመና ለዘብ ባለ ድምፅ ፡ “ አቤት ያንተ ያለህ ! ጡት እኮ ነው የሚፈልገው ። የናቱ ጡት መስሎት ” ሲል አጉተመተመ ። ምክንያቱን ሳያውቀው ከእግር እስከ አናቱ ይንቀጠቀጥ ጀመር ። ምናልባት ከኃፍረት ወይም ከፍርሃት የተነሣ ይሆናል ። ምናልባትም አንድ የተለየ ኃይለኛ ፡ በሥቃይ የተመላና ልብ ሰብር አንጀት የሚበላ ስሜት በሠራ አካላቱ ተሠራጭቶ ይሆናል ።

“ ማሙሽዬ ፡ እናትህን መሰልኩህ እንዴ ? የኔ ምስኪን ! ምንም ላደርግልህ አልችልም ፣ ብታሠቃየኝ ምናለ ! . . . አንዳች ነገር ላደርግልህ የምችል ዐይነት ሰው አይደለሁም . . . ለመሆኑ እኔ ምን እንደ ሆንኩ ታውቃለህ?

. . . ቀድሞ ወታደር ነበርኩ ጓዴ ! ዛሬ ደግሞ ሌባ ተብዬ የምፈለግ ሰው ነኝ ። ” ሴማጋ የኀዘን ቃና በተቀላቀለበት ድምፅ ሕፃኑን ማነጋገር ቀጠለ ። የሚሸነቁጠው ነፋስም በመኻል እያቋረጠ ያፏጫል ።

“ ተኛ ማሙሽዬ . . . . እንቅልፍ ይውሰድህ እስቲ ! አሁን ከኔ ምን ጠብ ይላል ብለህ ነው፤ ቤሳ የሌለኝ መናጢ ! ይልቅስ ዐርፈህ ብተተኛ ይሻላል ። የሞግዚቶችን ያህል ባላውቅበትም እሹሩሩ እልሃለሁ ። እሺ ማሙሽዬ . . . ” እያለ ቆይቶ ጭንቅላቱን ዝቅ በማድረግ ፡ ሕፃኑን እንገቱ ሥር ወሸቀና በተለመደው የእሹሩሩ ዜማ እያዜመ የሚያውቀውን ያህል ግጥም በመደርደር ያባብለው ጀመር ።

“ እሹሩሩ - ሩሩሩ . . . እሹሩሩ . . ሩ ሩ
የማሙዬ እናት ቆሎ ነይለት ፤
ዳቦውን ባህያ ፥
ወተቱን በጉያ ነይ ይዘሽለት ፤
የማሙዬ እናት ።
እሹ - ሩሩ - ሩሩ . . . . እሹሩሩ ሩሩ ”

ሴማጋ እንዲህ እየዘመረ ፥ ሕፃኑ እያለቀሰ ፡ ነፋሱ እያፍጨ፥ጉዞውን ቀጠለ ። በሕፃኑ ሰበብ ብዙ ጊዜ ማባከኑን ግን አልታወቀውም ነበር ።

ድንገት ሳያስበው እንደ ቀልጠ በረዶ ያለ ነገር በጉንጮቹ ላይ ኮለል ብሎ ሲወርድ ተሰማው ። ዐልፎ ዐልፎ መንቀጥቀጡንም አላቆመም ። ጉሮሮው ውስጥ አንዳች ነገር እንደ ተወተፈ ሆኖ ይሰማዋል ። ልቡን የተጫነው ክብደትም ከፋኛ ተሰማው ። ብቸኝነት ወረረው ። በሕይወቱ ውስጥ በዚያች ምሽት እንደ ከበበው ያለ ብቸኝነት ተሰምቶት አያውቅም ። የበረዶ ዶፍ በሚወርድበት ድቅ



ድቅ ጨለማ ፥ በዚያ ጭር ያለ ጐዳና የፖሊስ ጥላ እያንዣበበበት፥አዲሱ ጓደኛዉ ከኮቱ በታች ብብቱ ሥር ተወትፎ እሪ እያለ ፥ከዚህ ቀደም ያልለመደው ዐይነት ብቸኝነት ነፍሱን ወረራት ። ቢሆንም ግን ፥ ወደፊት ከመንዝ አልተቆጠበም ።

ጥቂት እንደ ሔዱ ከወደ ኋላው የኮቴ ድምፅ ሰማ ። ዞር ብሎ በፈረስ ላይ የተቀመጡ ሰዎች ቅርፅ በጨለማው ውስጥ ሲታየውና ፥ ወዲያው ፈረሰኛ ፖሊሶች ሲደርሱ አንድ ሆነ ።

“ ቁም ማነህ !? ” የሁለት ሰዎች ድምፅ፥ በአንድ ጊዜ አስተጋባ ።

“ ማነው ስምህ? ” ሦስተኛው ሰው ጠየቀ ።

“ ምንድነው የተሸከምከው . . . አውጣና አሳይ ! ”

ፖሊሱ ትእዛዙን ሲሰጥ፡ ፈረሱን ይበልጥ ወደ ሴማጋ አስጠጋው ።

“ ይሄ ? ይሄማ ሕፃን ነው ። ’ ሴማጋ እየተደናገጠ መልስ ሰጠ ።

“ ስምህ ማን ነው ? . . . አትናገርም ! ”

“ ሴማጋ ! . . . ሴ . . . ሴማጋ እባላለሁ ። ”

“ አሃ ! አንተው ነሃ ! . . . . እንኳን ተገናኘን ፤ አንቱ ነበር የምንፈልገው ። ወለም ዘለም ሳትል፥ ከፈረሱ ፊት ለፊት ሆነህ ወደ ጣቢያ ቀጥል ! ” ፖሊሱ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጠ ።

“ ብርዱ ለራሱ አይቻል ፤ በቤቶች ጥግ ጥግ እንኳን እንድሔድ ብትፈቅዱልኝ እስቲ ምን ነበረበት ። መቼም ከመንገድ መኻል ይልቅ የቤቶቹ ክለላ ትንሽ ይሻላል ። ”

ሴማጋ ፣ የተናገረውን ከሚከተሉት ፖሊሶች መኻል አንድም የሰማው አልነበረም ። በራሱ ፈቃድ በቤቶቹ ጥግ ጥግ መሔድ ሲጀምር ግን ተቃውሞ አልገጠመውም ። ሆኖም ዐይናቸው ይጠብቀዋል ። እንዲህ ባለ አጀብ ሴማጋ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ደረሰ ።

" ያዛችሁት ? . . . በጣም ግሩም ! " አለ የፖሊሱ አዛዥ ፣ ቢሮው ውስጥ ሲቀበላቸው ።

" ሕፃኑስ ? . . . ሕፃኑን ምን ላድርገው ? " ሴማጋ በቀዘቀዘ አንደበት ጠየቀ ። " ምን ? . . . . የምን ሕፃን ? . . . ስለ ምንድነው የሚያወራው እሱ ! "

" ይህን ሕፃን ማለቴ ነው ። ጐዳናው መኻል ተጥሎ ነው ያገኘሁት ። " ሴማጋ ንግግሩን ሳይጨርስ ፣ ከኮቱ ሥር የወሸቀውን ጸጥ ያለ ጥቅል ዝግ ብሎ አወጣው። ሕፃኑ በሴማጋ እጆች ላይ ዝልፍልፍ ብሏል ።

" እንዴ ! ሞቷል እኮ ! " የፖሊሱ አዛዥ ጮኸ ።

" ሞቷል !? " የሴማጋ ግራጫ መሳይ ዐይኖች በትንሹ ጥቅል ላይ አተኮሩ ። በከባዱ ተንፍሶ ፣ " ጉድ ነው " አለና ለብቻው ያጉተመትም ጀመር ።

" ምንድነው የምታጕረመርመው ? " የፖሊሱ አዛዥ በጐላ ድምፅ ጠየቀው። ሴማጋ መልስ ሳይሰጥ ዞርያውን፣ በተከፋ መልክ ያስተውላል ። በዐይኖቹ እንባ እንደ መንቆርዘዝ ብሏል ።

ሴማጋ በጐዳናው ሲጓዝ በነበረበት ወቅት ፣ ይሰማው የነበረው ስሜት ሁሉ ከሕፃኑ ጋር አብሮ ሞተ ። አሁን ቀዝቀዝ ያለ አስፈሪ ሥልጣን ዞርያውን ከቦታል ። በሐሳቡ ፍንትው ብሎ የሚታየው ነገር ቢኖር፡የወደፊቱ መራር ፍርድና አስከፊ ወህኒ ቤት ብቻ ነው ። ዞር ብሎ ሕይወት አልባ የተጋደመውን የሕፃኑን በድን አካል ተመለከተ ።



ጿአስተያየቱ በጣም ያዘነ ይመስላል ። አሁንም በከባዱ ተነፈሰ ።

" አንተስ ጥሩ ሕፃን ነበርክ ፤ ብቻ መጨረሻው እንዲህ ሆነ ። ላመልጥ ስችል ላንተ ብዬ ደኅና ዕድሌን በሞትህ ለወጥኩና ከንቱ ጣልኳት ። እኔ ሳስብ የነበረው ሌላ ፣ አንተ ግን ትንፋሽህን እላየ ላይ አፈንካት ። " . . . ሴማጋ እንደገና ጫን ተነፈሰና ማጅራቱን በኃይል አከከው ።

" ውሰዱት ! " አለ የፖሊሱ አዛዥ ፣ ወደ ሴማጋ ዞሮ ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ። ፖሊሶቹም ይዘውት ሔዱ ፤ ወሰዱት ።

1973 ዓ.ም.

# ሌቭ ኒኮላየቪች ቶልስቶይ

## (1828 - 1910)



ከቄማራዊው የሩሲያ ቤተ
መንግሥት ጋር ግንኙነት
ከነበረው ቤተሰብ በ1828
በማዕከላዊ ሩሲያ በምትገኝ፣
ቱላ የተባለች ሥፍራ የቤተ
ሰቡ ጉልት በነበረው ያስናያ
ፖሊያና እየተባለ በሚጠራ
አካባቢ ተወለደ። አባቱ ካው
ንት ኒኮላይ ቶልስቶይና እናቱ
ልዕልት ማርያ ቮልኮንስካያ
አራት ልጆቻቸውን ትተው፣በሰባት ዓመት ልዩነት በመ
ሞታቸው ፣ ቶልስቶይ በግል መምህር እየተኮተኮተ አከ
ስቱ ዘንድ አደገ። ዕድሜው ከፍ ሲል፣ በ1844 ዓ.ም. ወደ
ካዛን ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በመጀመሪያ የምሥራቅ ቋንቋዎ
ችን ፣ በኋላ ደግሞ ሕግ ማጥናት ጀመረ ።

ከዩኒቨርስቲው የተመደበለትን ትምህርት ሳይጨርስ
በግል ፈቃዱ ከወጣ በኋላ ፣ እስከ 1851 ዓ.ም. ድረስ የጭ
ፈራና የፈንጠዝያ ሕይወት ኖረ ። ከዚያም በሩሲያ ጦር
ሠራዊት ውስጥ በመኮንንነት ተመልምሎ ኮውካሰስ ወደ
ሚባለው ቀበሌ ተላከ ። በክራይሚያ ጦርነትም በመድ



ፈኛነት ለመዋጋት በቃ ። በዚያም እያለ በሥነ ጽሑፍ
ተሰጥኦው በመጠቀም እያዘጋጀ ለጋዜጦች በሚልካቸው ፣
" የሴቫስቶፖል ታሪኮች " የተሠኙ ተከታታይ አጫጭር
ድርሰቶች፣በሕዝብ ዘንድ ስሙን ለማስተዋወቅ ቻለ ።

ቶልስቶይ ፣ ከውትድርና ተሰናብቶ ወደ ሩሲያ ከተ
መለሰ በኋላ ፣ ሶፊያ አንድሬያቭና በህር ከተባለች ሴት ጋር
ተጋብቶ በጠቅላላው ዐሥራ ሦስት ልጆችን ያፈሩ ሲሆን፣
በሥነ ጽሑፍ ረገድም በርካታ ረጃጅም ልቦለዶችን ፣ አጫ
ጭር ታሪኮችን ፣ የፍልስፍና ድርሳኖችንና በሃይማኖታዊ
እምነቶቹ ላይ የተመሠረቱ የጥናት ጽሑፎችን አበርክ
ቷል ። በዚህም መሠረት የእያንዳንዳቸው ዝግጅት አም
ስት አምስት ዓመታት ፈጅቦት ፣ "አናካሬኒና" እና
"ጦርነትና ሰላም" የተሠኙ ዐበይት ልቦለዶች ሌላ ፣ "የኢ
ቫን ኢሊች ሞት" እና "ጌታና ሎሌ" የሚባሉት አጫ
ጭር ልቦለዶች እንዲሁም በሕይወቱና በሙያው ፍጻሜ አካ
ባቢ ያሳተመው ፣ " ትንሣኤ " የሚባለው ልቦለድ በሰው
ልጅ የፈጠራ ጽሑፍ ቅርስ ውስጥ፣ግንባር ቀደም ከሚባሉት
መካከል የሚመደቡ ናቸው ።

በሥነ ጽሑፍ ረገድ ፣ ቶልስቶይ ወደ ከፍተኛ ደረጃ
ከመድረሱ ሌላ፣ በቅድመ አብዮት ሩሲያ በገበሬዎችና ምዝ
ብር መደቦች ላይ የሚፈጸመውን በደል ይቃወም ነበር።በተ
ለይም መኖሪያውን በያስናያ ፖሊያና ካደረገ በኋላ ፣ ከገጠሩ
ሕይወት ጋር በቅርብ ለመተዋሠር በመብቃቱና የሕዝቡ
ጥቃት እየተሰማው በመሔዱ ፣ የ " ካውንትነት" ማዕረ
ጉን በፈቃዱ ሠርዞ ፣ በውርስ ያገኘውን ሰፊ ርስት በላዩ
ላይ ሠፍረው ለሚገኙት ገባሮች በማከፋፈል ከጭሰኝነት
አውጥቶ ባለመሬት አደረጋቸው ። ቶልስቶይ ከገበሬዎች
ኑሮ ጋር እየተዋሐደና ተራ ኑሮን እየተከተለ መኳዝ
ጀመረ ። ይህ ድርጊቱ ግን ፣ ቅንጦት ከሚወደው ቤተሰቡ ፣

በተለይም ከሚስቱ ፍላጎት ጋር የሚቃረን በመሆኑ ፣ የቤቱ ሰላም እየደፈረሰ ፍቅሩም እየጠወለገ መሔድ ጀመረ ።

የቶልስቶይ እምነትና ፍልስፍናም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠና የራሱን መንገድ እየተከተለ በመምጣቱ ፍጹም ሞራሊስትና ምክኑያዊ ሆነ ። የቤተ ክርስቲያንን አሠራር ተቃወመ ። የግል ሀብት ይዞታ መኖር እንደ ሌለበት ፣ አቋሙን ገለጠ ። በሃይማኖታዊ አስተሳሰቡ ልዩነት የተነሣ ፣ ከሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በውግዘት ተባረረ ። ይሁን እንጂ ፣ ቶልስቶይ መሠረታዊውን የክርስትና ሃይማኖት ዶክትሪን ፈር ሳይለቅ የነደፈውን እምነት የሚከተሉ ፣ "ቶልስቶያውያን" የሚባሉ ሰዎች የመሠረቱት የአማንያን ቡድን እስከ ዛሬ ይገኛል ።

ቶልስቶይ ፣ በመላው ዓለም የሚገኙ መጽሐፍ አንባቢዎችን ፍቅርና ፣ የአያሌ ጠቢባንን አድናቆት ለማትረፍ የበቃ ፣ በልዩ ተሰጥኦ የበለጸገ ፣ በጠለቀ አስተሳሰብ የዳበረ ፣ ብሩህ አእምሮ የነበረው ፈላስፋ ፣ ደራሲ ፣ የጭቁኖች ወዳጅ ሲሆን ፣ ቭ ፡ ኢ. ሌኒንም የሌቭ ቶልስቶይን መርሕ ፣ ርዕዮትና ኪነታዊ ሥራዎች በሚመለከት በርካታ የሒስ መጣጥፎችን አዘጋጅቷል ። በተለይም "ቶልስቶይ እንደ ሩሲያ አብዮት መስተዋትነቱ" ፣ "ቶልስቶይና ዘመናዊው የሠራተኛው መደብ ንቅናቄ" በተባሉት ጽሑፎች ፣ ቶልስቶይ የሩሲያን ገበሬዎችና የተገፋውን ኅብረተሰብ ወክሎ ይናገር እንደ ነበር ፣ ለአስመሳይነትና ለሽፋፋኝነት የማይበለጥ ፣ ጥፋትን ለማጋለጥ ወደ ኋላ የማይል ደፋርና ኃይለኛ የእውነታ ጸሐፊ እንደ ነበር ከመመስከሩ ሌላ ፣ ደካማ ጐኖቹንና ቅራኔዎቹንም እያነጻጸረ በመተንተን አሳይቷል።

የቶልስቶይ የሕይወቱ ምሽት በጣም ለየት ያለ ነው ። ጥቅምት 28 ቀን 1910 ዓ.ም. ለምን እንደሆን ተለይቶ ባል



ታወቀ ምክንያት ፣ ዝናብ በሚዘንብበት በአንድ ምሽት ትልቁ ደራሲ ከቤቱ ወጥቶ ወዳልታወቀ አቅጣጫ ከግል ሐኪሙ ጋር ጉዞ ጀመረ ። ከአራት ቀናት ጉዞ በኋላ ፣ አስታፖቮ ወደ ተባለች የባቡር ጣቢያ ሲደርስ በከፍተኛ ሕመም ተይዞ ወደቀ ። በባቡር ጣቢያው ሹም ቤት ተኝቶ ሰፊ ሕክምና ተደረገለት ። በጣም ብዙ መድኃኒቶች በአጣዳፊ ከሞስኮ ወደ አስታፖቮ ተላኩ ። ወሬውን ሰምተው የመጡት ሚስቱ ፣ ልጆቹና ወዳጆቹ ፣ በርካታ ጋዜጠኞች ፣ አያሌ ድኃ ገበሬዎች ፣ የፖለቲካ ፖሊሶች ፣ የመንግሥት ሠራተኞችና ካህናት እንኳን ሳይቀሩ ፣ በጣቢያው ተሰብስበው ታላቁ ሰው የተኛበትን ቤት በመከበብ ውጤቱን መጠባበቅ ጀመሩ። ይሁን እንጂ ፣ በዕድሜ የገፋውን አዛውንት ሕይወት የጥበብ ሰው ለማትረፍ ባለመቻሉ ኅዳር 7 ቀን 1910 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት ከ5 ደቂቃ ሲሆን ፣ ሌቭ ኒኮላየቪች ቶልስቶይ በ82 ዓመት ዕድሜው ዐረፈ ።

## ኰርኔይ ቫሲሊየቭ

ኰርኔይ ቫሲሊየቭ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ገጠር በመጣበት ወቅት ፥ ዕድሜው ሃምሳ አራት ዓመት ሞልቶ ነበር። እየተጠቀለለና እርከን እየሠራ በሚወርደው ወፍራም ጠጉሩ መኻል ሽበት የሚባል ላመል ያህል እንኳን አይታይም ። በጥቁር ሪዞ ውስጥ ብቻ—ለዚያውም ወደ ዐይኖቹ ጠጋ ብሎ በበቀለው አካባቢ—በመጠኑ ፈንጠቅጠቅ ማድረግ ጀምሯል ። ለስላሳና ፍም የመሰለ ፊቱን ፥ ደልዳላና የፈረጠመ ደንደሱን ፥ ወዙ ግጥም ያለበትን ሞንዳላ ሰውነቱን ሲያዩት ፥ በምቹ የከተማ ኑሮ የሚንደላቀቅ ሰው መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም ።

ከሐያ ዓመት በፊት ከውትድርና አገልግሎት ተሰናብቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ፥ ለመቋቋሚያ ያህል የሚያበቃው ገንዘብ አጠራቅሞ ስለ ነበር ፥ በመጀመሪያ ሱቅ ከፈተ ። ብዙም ሳይቆይ ሱቁን ዘግቶ ወደ ከብት ንግድ ተዛወረና ፥ ከቸርቻሪዎች በርካሽ የሚገዛቸውን ቁም ከብቶች ወደ ሞስኮ እየነዳ በብዙ ትርፍ መሸጥ ጀመረ ።

ጋይ በምትባል መንደር ውስጥ፥ ከግንብ የተሠራ የቆርቆሮ ቤት አለው ። አሮጊት እናቱ ፥ ሚስቱ ፥ ሁለት ሕፃናት ልጆቹ ፥ (አንድ ወንድና አንዲት ሴት) ዐሥራ አምስት ዓመት የሞላው እናትና አባቱ የሞቱበት፥ ድዳ የወንድሙ ልጅ እና አንድ ሠራተኛቸው በዚሁ ቤት ይኖራሉ ።

አሁን ቤት ውስጥ ያለችው ሁለተኛ ሚስቱ ናት ። ምን ጊዜም በሽታ ተለይቷት የማታውቀው የመጀመሪያ ሚስቱ



አንድም ልጅ ሳትወልድለት ከሞተች በኋላ ፥ ለብዙ ዓመታት በብቸኝነት ሲኖር ቆይቶ ፥ በመጨረሻ አንዲት ልጅ አገባ ። ሁለተኛዋ ሚስቱ አባቷን ያጣች ፥ መልከ መልካምና ጠንካራ ልጃገረድ ነበረች ።

አንድ ጊዜ ፥ ኰርኔይ የመጨረሻ ከብቶቹን በጥሩ ዋጋ ሻሸጠ፥ሦስት ሺህ ሩብል ያህል በእጁ እንደ ያዘ ጠቃሚ መስይ ወሬ ይሰማል ፤ ምንም ነገር አልሳካልህ ያለው አንድ ባለርስት ለጣውላ የሚሆን ዕንጨት ያለበት መሬቱን በርካሽ ዋጋ ለመሸጥ በማስማማት ላይ እንደሚገኝ የመንደሩ ነዋሪ የሆነ ሰው ይነግረዋል ። ኰርኔይ ወደ ውትድርና ከመግባቱ በፊት ለአንድ የጣውላ ነጋዴ ጸሐፊ ረዳት ሆኖ ያገለግል ስለ ነበር ፥ ሥራው የቱን ያህል እንደሚያዋጣ ጠንቅቆ ያውቃል ። ስለዚህ የተባለውን መሬት ገዝቶ የጣውላ ንግድ ለመጀመር ወሰነ ።

በጋይ መንደሩ አቋርጦ የሚያልፍ የባቡር መሥመር ባለመኖሩ ፥ የባቡሩ ጣቢያ የሚገኘው ከመንደሩ ራቅ ባለ ሥፍራ ላይ ነበር ። አንድ ቀን ኰርኔይ ከባቡር እንደ ወረደ የመንደሩ ነዋሪ የሆነውን ኩዝማ የሚባል ሰው ጣቢያው ላይ ያገኘዋል። ባቡር በሚያልፍባቸው ቀኖች ሁሉ ፥ ኩዝማ ከጣቢያው ይለያል ማለት ሐሰት ነው ። ከባቡር ከወረዱ በኋላ ፥ ወደየመንደራቸው ለመድረስ ሁለት ጌኛ ፈረሶች የሚጐትቱትን አርጌ ጋሪዎቹን የሚከራዩ መንገደኞች ቢያጋጥሙ ፥ ከነርሱ ትንሽ ገንዘብ ለመለቃቀም እያለ ነበር ኩዝማ ጣቢያውን የሚያዘወትረው ። ኩዝማ ያጣ የነጣ ድኃ ነው ። በዚሁ ሳቢያ ሀብታሞችን አይወድም ። በተለይ ደግሞ ኰርኔይን አይወደውም ። ሲጠራውም ፥ ኰርኑሽካ እያለ ነው ።

ከውስጥ በለበሰው ሌጦር ኮት ላይ ፥ ከበግ ቆዳ የተሠራ ሌላ ረጅም ኮት ደርቦ ፥ በእጁ የመንገድ ቦርሳ ያን

ሰጠለው ኰርኔይ ቫሲሊየቭ ከባቡሩ ወርዶ ደረጃዎቹ ላይ ቆም አለ ። እንደ ነፍስ ጡር ሆድ የተንጠረዘዘው ቦርጩ ከሌላው አካሉ ቀድሞ ወደፊት አሞጥሙጧል ። ካለበት ሳይንቀሳቀስ ጉንጮቹን ዳበስ ዳበስ አደረገና ዙሪያውን ተመለከተ ። ገና ማለዳ ነው ። አየሩን እፍን አድርጎ ከተን ጠረበበው ደመና ሌላ ፣ በመጠኑም ቢሆን አመዳይ እንደ መጣል ብሏል ።

" ምነው ዛሬስ . . . አንድም መንገደኛ አላገኘህም እንዴ አብዬ ኩዝማ ? " አለ ኰርኔይ ። " ታዲያ ምናለ እኔን ወደ ቤቴ ብታደርሰኝ-እ ? "

" የምትፈልግ ከሆነ ምናለ . . . ያው ዋጋውን አንድ ሩብል ትከፍላለህ ።"

" ሰባ ኰፔክ ይበቃሃል ። አይበቃም -እ ? "

" ያንድ ምስኪን ሰው ሠላሳ ኰፔክ ለማስቀረት የሚሻ ሆዱ የሞላ ሰው " አለ ኩዝማ ።

" እንዳልከው ይሁና እንግዲህ " አለ ኰርኔይ ቦርሳውንና የተጠቀለለ ጓዙን በጋሪው ላይ እየጫነ ። ቀጠለና ራሱም ጋሪው ላይ ወጥቶ ከኋላ በኩል በሚገኘው ወንበር ላይ ዘርፈጥ ብሎ ተደላድሎ ተቀመጠ ።

ኩዝማም የተለመደ ቦታውን ያዘ ።

" መቀጠል ትችላለህ" አለ ኰርኔይ ።

በጣቢያዉ አካባቢ ያለውን ስርጉጥጉጥና የተቦረቦረ መንገድ ዐልፈው፣በምቹው ጐዳና ላይ ሽምጡን ተያያዙት።

" ታዲያስ እንዴት ናችሁ ጃል ? ኑሮ እንዴት ነው ! እኛን ሳይሆን —እናንተ እዚህ ገጠር ያላችሁትን ኑሮ እንዴት ይዟችሁዋል ? " ኰርኔይ ነበር ጠያቂው ።

"እውነቱን ለመናገር ከሆነ ይሄን ያህልም አይደል።"



"እንዴት?ምን ማለትህ ነው ? . . . የኔዋስ አሮጊት እንደምን ናት ? ለመሆኑ በሕይወት አለች ?"

" እንዴታ ፤ አሉ እንጂ ! ትናንት እንኳን ቤተ ክርስቲያን አይቻቸዋለሁ ። አሮጊቷስ ምንም አይሉ . . . ወጣቷ ሚስትህም ደኅና ናት ። ምናለ አሁንማ ተመችቷታል ። ተስማምቷታል ። አዲስ ሠራተኛም ቀጥራለች " አለና ኩዝማ እንደ መሣቅ ሞካከረው ። አሣሣቁ ግን ልዩና የለበጣ ዐይነት መሰለው—ለኰርኔይ ።

" ሠራተኛ ? ጴጥሮስ ምን ሆነና? "

" አዬ ጴጥሮስማ ታሞ ከተኛ ሰንት ጊዜው ። ሚስትህ የቀጠረችው አዲሱ ሠራተኛ ኢቭስቲግኒ ቤሊ ይባላል ። የካሜንካ ሰው ነው ። የትውልድ መንደሯ ልጅ " አለ ኩዝማ ።

" እውነት ! " አለ ኰርኔይ ።

ኰርኔይ የአሁኗን ሚስቱን ማርፋን ባገባ ጊዜ፣ ስለርሷና ስለ ኢቭስቲግኒ ቤሊ ግንኙነት በአካባቢው ሴቶች ዘንድ አንዳንድ ሹክሹክታ ነበር ።

" እና ይሄውልህ እንዲህ ነው ነገሩ፣ኰርኔይ ቫሲሊየቪች ። በዛሬ ጊዜ የሴቶች ነጻነት በዝቷል ። አለቅጥ መረን ተለቋል " አለ ኩዝማ ።

" ይባላል ! " አለና ኰርኔይ አያይዞ ፡ " በነገርህ ላይ ሽበቱ እኮ ባዛብህ ጃል ! አረጀህ ማለት ነው ?" ሲል አከለበት—የጀመሩትን አርዕስት ለመለወጥ ፈልጎ ።

" እንግዲህ ወጣት መሆን የታለ ! አከትሞ ። ፈረሱም ቁይቀር እንደኔው እያረጀ ነው ። " ኩዝማ መልሱን እየሰጠ ፣ እግረ ወርኃውን መጋጃ በአለንጋው አንዴ ሸጥ አደረገው ።

ግማሽ መንገድ ያህል እንዳገባደዱ ወደ አንዲት ማረፊያ ሆቴል ደረሱ ። እንዳፍታ እንዲያቆምለት ትእዛዝ ሰጠና ኩርኔይ ወደ ሆቴሏ ገባ ። ኩዝማም ባዶውን ወደ ተጋደመው የውሃ ገንዳ ፈረሶቹን እየሳበ በመሔድ ልጓሙን ያስተካክል ጀመር ። ኩርኔይ ዞር ብሎ ባያየውም እንኳን ፤ ከአሁን አሁን ለመጠጥ ግብዣ ይጠራኝ ይሆናል በሚል ተስፋ ጆሮውን ቀስሮ ጥሪውን ይጠባበቃል ።

“ ወዲህ መጥተህ አንድ ነገር አትቀምስም አብዬ ኩዝማ ! ” አለ ኩርኔይ ተመልሶ ወደ ደጃፉ እየወጣ ።

“ አመሰግናለሁ ” አለ ኩዝማ ፤ ለመጠጡ የተቻኮለ ላለመምሰል እየታገለ ።

ኩርኔይ አንድ ጠርሙስ ቮድካ አዘዘና ኩዝማ ወዳለበት ይዞ ሔደ ። ከነጋ እህል የሚሉ ያልቀመሰው ባለጋሪ ገና የመጀመሪያዋን ብርጭቆ ሲጨልጥ ለብ አለው ። ወደ ኩርኔይ ተጠግቶ ፤ በመንደራቸው ውስጥ ስለሚናፈሰው ወሬ በሹክሹክታ ይነግረው ጀመር ። ሚስቱ ማርፋ የዱር ወዳጅዋን በሠራተኛ ስም ቀጥራ አብረው የሚኖሩ ስለ መሆናቸው ፤ መንደሩ የሚያመነዥከውን ሐሜት ይዘከዝክለት ጀመር ።

“ እኔስ ላንተ በጣም ነው የማዝነው ” አለ መጠጡ እየተጫጫነው የሔደው ኩዝማ ። “ ደግ አይደለም ፤ ደግ አይመስለኝም ። ድፍን መንደረተኛው እየተሣለቀብህ ነው ። እኔማ ሁልጊዜ ቆዩ እስቲ እላቸዋለሁ ። ግዴላችሁም ፤ እሱ ባለቤቱ እስኪመጣ ታገሡ እስቲ እላቸዋለሁ ፤ . . . . እና እንዲህ ነው ነገሩ ሁሉ ፤ ኩርኔይ ቫሲሊየቪች ” አለ ።



ኩርኔይ ፤ የኩዝማን ንግግር ፀጥታ ሲያዳምጥ ቆየ ፤ ችምችም ብለው የበቀሉ ቅንድቦቹን፤ብርሃን በሚፈነጥቁ ዐይኖቹ ላይ ስብስብ አድርጎ ።

“ ፈረሶቹን ውሃ ማጠጣት ትፈልጋለህ ? ” አለ ኩርኔይ ። ኩዝማ ማነብነብ ከጀመረ ጊዜ አንሥቶ የተነፈሰው ቃል ቢኖር ይሄን ብቻ ነበር ። “ ውሃ የማታጠጣቸው ከሆነ መንገዳችንን እንቀጥል ” አለ ።

ወዲያው ለባለ ሆቴሉ የመጠጡን ዋጋ ከፈለና ተመልሶ ወደ ጐዳናው ወጣ ።

ቤቱ ሲደርስ ደንገዝገዝ ብሏል ። ጋሪው ወደ ግቢው ገብቶ ቆም ሲል ፤ መጀመሪያ ያገኘው ሰው ያው መንገዱን በሙሉ ሲያስበው የመጣው ኢቫስቲግኒ ቤሊ ነበር ። ኩርኔይ ወደርሱ እየተጣደፈ መምጣት ለጀመረው፤ ኢቫስቲግኒ ሰላምታ ካቀረበለት በኋላ፤ከሲታ ፊቱንና ነጭ ሽፋሎቹን አይቶ ግራ በመጋባት ዐይነት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ። “ ይሄ አሮጌ ውሻ ሳይዋሽ አልቀረም ” አለ በሐሳቡ ፤ የኩዝማን ቃላት አንድ በአንድ ለማስታወስ እየሞከረ ። “ ግን ደግሞ ምን ይታወቃል . . . ለማንኛውም ሁሉንም ነገር ማጣራት አለብኝ ” አለ አሁንም ለብቻው ።

ኩዝማ ፤ ፈረሶቹ አጠገብ እንደ ቆመ ፤ ኢቫስቲግኒን በዐይኑ ጠቀሰው ። “ እኛ ዘንድ መኖር ጀምረሃል መሰለኝ ? ” አለና ጠየቀ ኩርኔይ ።

“ መቼም ሰው ቦዝኖ አይቀመጥ ። አንዱ ዘንድ ሥራ መያዝ አለበት ። ” የኢቫስቲግኒ መልስ ነበር ።

“ ለመሆኑ ክፍሉን አሙቃችሁታል ? ”

“ በሚገባ ማትቤቫም እውስጥ ነች ” አለ ኢቫስቲግኔ ።

ኰርኔይ በደረጃዎቹ ወጣ ። ድምፁን የሰማችው ሚስቱ ወደ መተላለፊያው በመምጣት ፣ ከዚያ በፊት አይቶት በማያውቀው ያልተለመደ ዐይነት የፍቅር ስሜት ባሏን ተቀበለችው ። ገና ስታየው ፊቷ ፍም መሰለ ።

“ እናትህና እኔ ተስፋ ቆርጠን ፣ የማትመጣ መስሎን መጠበቁን እርግፍ አድርገን ትተነው ነበር ” አለችው ኰርኔይን ፣ ተከትላዉ ወደ ውስጥ እየገባች ።

“ ታዲያስ ፣ ለመሆኑ እኔ በሌለሁበት ጊዜ የብቸኛ ኑሮዋችሁ እንዴት ነበር? ”

“ ያው ድሮ እንደምንኖረው ነዋ ! ” አለች ማርፋ፣ የሁለት ዓመት ሴት ልጅዋን ብድግ አድርጋ እየታቀፈች ። ሕፃኗ ጡት ፍለጋ የእናቷን ቀሚስ መጎተት ስትጀምር፣ ማርፋ በረጅሙ እየተራመደች ወደ መተላለፊያው ወጣች ።

ጥቋቁር ዐይኖች ያሏቸው የኰርኔይ እናት፣ ወደ ክፍሉ ገቡ ። አጭር ቦት ጫማ አድርገዋል ።

“ አስበህ ልትጠይቀኝ ስለ መጣህ እግዜር ይስጥህ ልጄ ! ” አሉ ፣ ዕድሜ ባስከተለው ድካም የተነሣ የሚንቀጠቀጥ ራሳቸውን እያንቃነቁ ።

ኰርኔይ ፣ ወደ ቤቱ ስለ መጣበት የሥራ ጉዳይ ለእናቱ ከነገራቸው በኋላ ፣ ኩዝማ ውጭ ሆኖ እየጠበቀ መሆኑን ትዝ ስላለው፣ ሒሳቡን ሊከፍለው ከቤት ወጣ ። ወደ መተላለፊያው የሚወስደውን በር ከፈት ሲያደርግ፣ ማርፋና ኢቭስቲግኒ ወደ ጓሮ በሚያስወጣው በር ላይ ቆመው አያቸው። በጣም ተቀራርበው ያወራሉ ። ኰርኔይ ብቅ ማለቱን ሲመለከቱ፣ ኢቭስቲግኒ አፈር ብሎ ወደ ጓሮ ወጣ። ማርፋ ደግሞ ወደሚንሰረሰረው ሻይ ማፍያ ‘ሳሞቫር’ ቀረብ ብላ የጢስ መውጫውን ታስተካክል ጀመር ።



ኰርኔይ ምንም ሳይናገር ዐልፏት ወጣ ። የተጠቀለለ ጓዙን ከጋሪው ላይ አንሣና፣ ኩዝማ ወደ ትልቁ ክፍል ገብቶ ሻይ እንዲጠጣ ጋበዘው ። ሻዩ እስኪቀርብ ድረስ ኰርኔይ ከሞስኮ ገዝቶ ያመጣቸውን ስጦታዎች ለቤተሰቡ ያከፋፍል ጀመር ። ከጥጥ የተሠራ ያንገት ልብስ ለእናቱ፣ የሥዕል መጽሐፍ ለፌድካ፣ ለድዳ የወንድሙ ልጅ ሰደሪያ፣ ለሚስቱ ደግሞ ቀሚስ ።

ሻዩ ቀርቦ በሚጠጡ ጊዜ፣ ኰርኔይ ቃል ትንፍሽ አላለም ። ፊቱን ኩስትር አድርጎ በጸጥታ ተቀምጦ ቆየ ። ብቻ አዲስ በተገዛለት ሰደርያ ፍንጥዝጥዝ ብሎ፣ የቤቱን ሰው ሁሉ የሚያጫውተውን ዱዳ ልጅ እያየ፣ አሁንም አሁንም ሳያውቀው ፈገግ ይላል ። ልጁ የሚሠራውን አሳጥቶታል ። አንዴ ልብሱን ዝርግት ያደርግና ወዲያው ደግሞ መልሶ ያጥፈዋል ። አንዴ ይለብስና ተስማምቶት እንደሆነ ያየዋል ። ወዲያው ደግሞ ይንደረደርና የኰርኔይን እጅ እየሳመ ፣ በሚሥቁ ዐይኖቹ ትክ ብሎ ያስተውለዋል ። ልጁ እንዲህ በሆነ ቁጥር ደግሞ ኰርኔይ ሳይታወቀው ፈገግ ይላል ።

ሻያቸውን ጠጥተው አበቁ ። በማከታተል ቀርቦ የነበረውም ማዕድ ከፍ አለ ። ኰርኔይ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ከሚስቱና ከትንሿ ልጁ ጋር ወደሚተኛበት ክፍልገባ፤ ማርፋ ምግብ የተበላባቸውን ሳህኖች ስታነሣሣ ትልቁ ክፍል ውስጥ ቆየች ። ኰርኔይ ጠረጴዛው ላይ ክንዶቹን አስደግፎ ለብቻው ቁጭ ብሎ ይጠባበቅ ጀመር ። በሚስቱ ላይ ያደረበት ቁጣ እየከረረ፣ እየመረረ ሲሔድ ይታወቀዋል ። ሒሳቡን ለመክፈል ያህል ግድግዳው ላይ በተሰካ ምስማር ላይ የተንጠለጠሉ ፋክቱሮችን አውርዶ ፣ ከኪሱ የማስታወሻ ደብተር በማውጣት ሒሳብ ማስላት ጀመረ ። ዐሥር ጊዜ ቀና እያለ ወደ በሩ ያስተውላል ። ደግሞ ጆሮ

ዎቹን ያቆምና በትልቁ ክፍል ውስጥ የሚያስገመግመው
የሰዎች ድምፅ ምን እንደሚል ለማዳመጥ ይሞክራል ።

ብዙ ጊዜ የትልቁ ክፍል በር እየተከፈተ ፥ የሆነ ሰው
ወደ መተላለፊያው ሲወጣ ቢሰማም፥ሚስቱ ግን ብቅ ሳትል
ብዙ ቆየች ። በመጨረሻ የሚያውቀው እረማመዷን ሰማ ።
በሩ ተከፈተ ። ባለቤቱ ጸጉሯን በቀይ ሻሽ ሸብ አድርጋ
ትንሿን ልጅዋን አቅፋ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባች ። የፊቷ
ቀለም ወደ ሮዝ የሚያደላው ሚስቱ በዚያ ምሽት ከመ
ቼውም ጊዜ ይበልጥ ቆንጆ ሆና ታየችው ።

" መቼም ጉዞው ሳያደክምህ አልቀረም " አለች
ከፈገግታ ጋር ፥ ስሜቱን የኩርፊያ ጥላ ያደበበው መሆ
ኑን ያላወቀች በመምሰል ።

ኩርኔይ ቀና ብሎ አይቷት አንዳችም መልስ ሳይሰጥ
ወደ ሒሳቡ አቀረቀረ ። ስሌቱን ከጨረሰ ግን ቆይቶ ነበር።

" በጣም እየመሸ እኮ ነው " አለችና ሕፃኗን አስ
ቀምጣ ከመጋረጃው ጀርባ ተሰወረች ።

አልጋ ስታስተካክልና ልጅቱን ስታስተኛ ይሰማ
ዋል ።

' ሰዎች እየተሣለቁ ነው ! ' የኩዝማ ንግግር ትዝ
አለው ።

' ቆይ እስቲ ብቻ ! ' አለ በሐሳቡ ፥ የግዱን በከባዱ
እየተነፈሰ ። ወዲያው ከመቀመጫው በዝግታ በመነሣት
ያለቀች እርሳሱን ሰደሪያው ኪስ ውስጥ ከተተና ፥ ፋክቱ
ሮቹን ደግሞ መልሶ ምስማሩ ላይ አንጠለጠላቸው ። ወደ
መጋረጃው ጠጋ አለ ። ሚስቱ ወደ ቅዱሳኑ ምስል ፊቷን
አዙራ ትጸልያለች ። ባለበት ቆሞ እስክትጨርስ ይጠባ
በቅ ጀመር ። አቀርቅራ ስታማትብና በታፈነ ድምፅ ጸሎ



ቷን ስታደርስ ብዙ ጊዜ ወሰደች ። ጸሎቷን ከጨረሰች
በኋላ ፥ ጊዜ ለማራዘምና ለማዘናጋት ያህል ሆን ብላ የምታ
ደርገው መስሎ ተሰማው ። በመጨረሻ ፥ ለጥቂት ጊዜ
ወለሉ ላይ ተንበርክካ ቆየችና እንደገና ተነሣች ። ወዲያው
በማከታተል ጥቂት የጸሎት ቃላትን በፍጥነት አጉተመ
ተመችና ወደ ባሏ ዞረች ።

" አጋሻን እንቅልፍ እየወሰዳት ነው " አለችው ፥
ወደ ትንሿ ልጅ እያመለከተች ። በሚንቋቋው አልጋ ላይ
ቁጭ ስትል በፊቷ ላይ ፈገግታ የሚሉ ነገር አይታይም ።

" ኢቫስቲግኒ እዚህ ከመጣ ቆይቷል ? " ኩርኔይ
ወደ ውስጥ እየገባ ጠየቃት ። ረጋ ባለ ሁኔታ አንደኛውን
ወፍራም የጠጉሯን ጉንጉን መፍታት ጀመረች ። እየፈታች
ደግሞ ትክ ብላ ፥ ፊት ፊቱን ትመለከተዋለች። ዐይኖቿ
የሚሥቁ ይመስላሉ ።

" ኢቫስቲግኒ ? . . . እንጃ ልጄ በደንብ አላስታው
ሰውም ! . . . ብቻ ሁለት ወይም ሦስት ሳምንታት ያህል
ይመስለኛል ። "

" ከሱ ጋር ነው የምታድሪው ? " አለ ኩርኔይ ። ጉን
ጉኑን ከእጅዋ ለቀቀችው ። ወዲያው ደግሞ መልሳ ያዘች
ውና ያን ወፍራም ሻካራ ጠጉሯን መፍታት ቀጠለች ።

" ሀ . . . ከኢቫስቲግኒ ጋር ነው የምታድሪው
አልክ ! ምን ዐይነት አነጋገር ነው በሉ " አለች ፤ 'ኢቫስ
ትግኒ' የሚለውን ስም ልዩ በሆነ የሚያቃጭል ድምፅ
እየጠራች ። " የዛሬ ሰዎች እንዴት እንዴት ያለውን ውሸት
ነው የሚያወሩት እናንተ ! ለመሆኑ ማነው እንዲህ ያለህ?"

" እውነት ነው ? አይደለም ነው የምልሽ ? " ኩርኔይ
ጥያቄውን ሲያቀርብላት ፥ ጠንካራ መዳፎቹን ቡጢ ጨብጦ
ኪሱ ውስጥ አመቃቸው ።

“ የማይረባ ነገር መናገሩን ትተውና ፣ ይልቅስ ጫማህን ላውልቅልህ ?”

“ ነው አይደለም ? ነው የምልሽ ” ኩርኄይ ጥያቄውን ደገመው ።

“ እንዲያው ግን ለመሆኑ ማነው እንዲህ ያለውን ውሸት ያነፋልህ ? ”

“ ቅድም መተላለፊያው ላይ ቆማችሁ ምን ነበር የምትነግሪው ? ”

“ ምን አልኩት ? በርሜሉ ላይ አዲስ ጉማ እንዲያስገባለት እንጂ የነገርኩት፣ሌላ ምን አልኩት ? ለምን እንዲህ ታስጨንቀኛለህ ! ”

“ እውነቱን ብትነግረኝ ይሻላል ! አለበለዚያ እገድልሻለሁ ! መጥፎ አመንዝራ ! ”

ድንገት የተጐነጐነ ጠጉሯን ጨምድዶ ያዘው ። ፊቷን በሥቃይ ስሜት ኩምትርትር አድርጋ ከእጅዋ መነጨቀችው ።

“ አንተ እምትፈልገው አምባገሮ ብቻ ነው ። ኧረ ለመሆኑ ምን ቀን ካንተ ደግ ነገር አግኝቼ ዐውቃለሁ ? . . . መጥኔ እቴ ከእንዲህ ያለው ኑሮስ ቢቀር ይሻላል ። ”

“ ምን ለመሆን ትፈልጊያለሽ ? ” ቃላቱን እየደጋገመ ተጠጋት ።

“ ለምን ጠጉሬን ትነጨኛለህ ? ለምን ትሰድበኛለህ? ለምን ታስጨንቀኛለህ ? እውነት ከሆነ . . . . . ”

የጀመረችውን ለመጨረስ ጊዜ አልነበራትም ። እጅዋን ለቀም አድርጎ ፣ ከአልጋው ላይ በመጐተት የዱላ መዓት



ያወርድባት ጀመር ። ራሷን ፣ ወገቧን ፣ ደረቷን . . . . . ምኗም ምኗ አልተረፈው ። በነረታት ቁጥር ደግሞ ቁጣውና ንዴቱ እየባሰበት መሔዱን ቀጠለ።ማርፋ እየጮኸች ራሷን ለመከላከል፣ ከዱላው ለማምለጥ ሞከረች፤ግን አልቻለችም ። ትንሿ ልጅ ከእንቅልፏ በመንቃቷ ወደ እናቷ ሮጣ ተጠመጠመችባት ።

“ እማምዬ ! ” አለች ሕፃኗ በጩኸት ።

ኩርኄይ የሕፃኗን እጅ ይዞ ከእናትየዋ አላቀቀና እንደ ድመት ግልገል አሽቀንጥሮ ወደ ሥርቻ ወረወራት ። ትንሿ ልጅ ለአንድ ወይም ለሁለት አፍታ ያህል ጮኸችና ጸጥ አለች ። ዳግመኛ ሌላ ድምፅ አላሰማችም ።

“ ነፍሰ ገዳይ ! ልጅቱን ገደልካት እኮ! ” ማርፋ እራታዋን እያደባለቀችው ወደ ልጅዋ ለመሔድ ተነሣች ። ኩርኄይ ግን እንደገና ያዛትና ደረቷን በኃይል ደቆሰው ። የኋሊት ተግተርትራ በጀርባዋ ተዘረረች ። ጩኸትና ልቅሶዋም ቀጥ አለ ።

ሕፃኗ ልቅሶውን ቀጠለች ። ትንፋሿን መሰብሰብ እስኪሳናት ድረስ ስቅስቅ፣እርር ብላ ማልቀሱን ተያያዘችው ።

አሮጊቷ የኩርኄይ እናት፣ያንገት ልብሳቸውን ሳያደርጉ ፣ ሽበቶ ጠጉራቸው ተመሰቃቅሎ ፣ ራሳቸው እየተንቀጠቀጠና ሲራመዱ ወዲህ ወዲያ እየተወዛወዙ ወደ መኝታ ክፍሉ ገቡ ። በቀጥታ ወደ ሕፃኗ ሔዱና ትኩስ እንባዋ ጉንጮቿን እየገመሰ የሚወርደውን የልጅ ልጃቸውን እንሥተው ታቀፏት ።

ኩርኄይ ከእንቅልፉ ባንኖ እንደ ተነሣ ሰው ፣ ዙሪያውን እየቃኘና ቁና ቁና እየተነፈሰ ባለበት ደርቆ ቆመ ።

ምን እንዳጋጠመውና የት ቦታ እንዳለ የሚያውቅ አይመስልም ።

ማርፋ እያቃሰተችና እየቃተተች ራሷን ቀና በማድረግ ፊቷን ያለበሰውን ደም በልብሷ እጅጌ ትጠርግ ጀመር።

“ አንተ አስቀያሚ ወንበዴ ! . . . እንግዲያስ ከፈለግኸው ይውጣልህ ። አሁንም ፡ ድሮም ፡ መቼም መቼም ከኢቭስቲግኒ ጋር ነው የምኖረው ! እንካ ይኸውልህ ከፈለግህ ግደለኝ ! አጋሽካም የሱ እንጂ ፡ ያንተ ልጅ አይደለችም ” አለች ፡ ቃላቶቹን በፍጥነት እያንበለበለች ። ምናልባት ዱላው የቀጠለ እንደሆነ በማለት ለመከላከል ፊቷን በእጅዋ ሸፈነችው ።

ኩርኔይ ግን ፡ አሁንም ምንም ነገር የገባው አይመስልም ። ዝም ብሎ ግራ ቀኙን ባዶ በሆነ አስተያየት ይመለከታል ።

“ ልጅቱን ምን እንዳደረግሃት ታያለህ ! እጅዋን ሰብረኸዋል ኮ ! ” አሉ አሮጊቷ በጩኸት ፡ በመሰበሩ የተነሣ ዝልፍልፍ ብሎ በጉኗ በኩል ቁልቁል ወደ ተንጠለጠለው የሕፃኗ ቀኝ እጅ እያመለከቱ ። ኩርኔይ ወደ ኋላው ዞሮ በጸጥታ ወደ መተላለፊያው ተራመደና ፡ ገልመጥ እንኳን ሳይል በበሩ በኩል ወደ ደጅ ወጣ ።

ደመናውና ውርጩ እንዳለ ነው ። በብዛት የሚወርዱት ለስላሳ የበረዶ ብናኞች በሞቀው ጉንጩና ግንባሩ ላይ በዝግታ ያርፉሉ ። ደረጃዎቹ ላይ ቁጭ ብሎ ከደረጃው ድጋፍ ላይ በእጁ ሙሉ ያፈሰውን በረዶ መብላት ጀመረ ። የማርፋ የማቃሰት ድምፅና የሕፃኗ የሚያሳዝን የሥቃይ ልቅሶ ከበሩ በስተጀርባ ይሰማል ። በሩ ተከፍቶ እናቱ ትንሿን ልጅ ይዘው ወደ ትልቁ ክፍል ሲያልፉ ተሰማው ። ተነሥቶ ወደ ክፍሉ ገባ ። መብራቱ ዝቅ በመደረጉ የተዳ



ከመ ብርሃኑ በጠረጴዛው ላይ ይስለመለማል ። ወደ ውስጥ መግባቱን ስትረዳ የማርፋ የሥቃይ ድምፅ ጉላ አለ ። ኩርኔይ በጸጥታ ልብሱን ለባበሰና ከአግዳሚው ወንበር ሥር የመንገድ ቦርሳ አውጥቶ ልብሶቹን ይከታትት ጀመር ። ከታቶ ሲጨርስ ቦርሳውን በቁራጭ ሲባጎ አሰረው ።

“ ለጥቂት ነው የተረፍኩት ! ገድለኸኝ ነበር ። ለመሆኑ እስከዚህ ምን አደረግሁህ ? ” አለች ማርፋ ፡ በሚያሳዝን ድምፅ ።

መልስ ሳይሰጣት ኩርኔይ ቦርሳውን ብድግ አድርጎ ወደ በሩ አመራ ።

“ አውዚን ትወርዳታለህ ! ነፍሰ ገዳይ ! ቆይ ግድየለም ! ለእንዳንተ ዐይነቶቹ የሚስማማ ሕግ መኖሩን አሳይሃለሁ ! ” የልቅሶዋን ድምፅ ለውጣ ፡ ቂም ያረገዘ እንባዋን ታወርደው ጀመር ።

ኩርኔይ ፡ ጸጥ እንዳለ በሩን ከፍቶ ከወጣ በኋላ፡ መልሶ በኃይል ወርውሮ ሲዘጋው የቤቱ ግድግዳዎች ተንቀጠቀጡ።

ወደ ትልቁ ክፍል ገብቶ፡ዱዳውን ልጅ ከተኛበት አስነሣና ፈረሶቹን እንዲጭንለት አዘዘው ። እንቅልፉ በሚገባ ያልለቀቀው ልጅ ራሱን በሁለት እጆቹ እያከከ፡አንገቱን በመደነቅና በመገረም ያስተውለው ጀመር ። በመጨረሻ ከርሱ የሚጠበቀው ምን እንደሆነ ሲገባው፡ ቦት ጫማዎቹን አጥልቆ ከበግ ቆዳ የተሠራ አሮጌ ኮቱን ደረበና ፉኖስ አንጠልጥሎ ወደ ጓሮ ወጣ ።

ኩርኔይና ዱዳው ልጅ ፡ በበረዶ ላይ በምትንሸራተተው ትንሽ ጋሪ ሆነው የግቢውን በር ሲያልፉ ፡ ምድርና ሰማዩ ወገግ ማለት ጀምሮ ነበር ። በትናንትናው ቀን ከኩዝማ ጋር በመጡበት መንገድ ጉዟቸውን ቀጠሉ ።

ባቡሩ ከሚነሣበት ሰዓት አምስት ደቂቃ ቀደም ብለው ወደ ጣቢያው ደረሱ ። ኩርኜይ ቲኬት ቆርጦ ፣ ቦርሳውን እንዳንጠለጠለ ወደ ፉርጎው እስኪገባ ዱዳው ልጅ ቆሞ ሲመለከት ቆየ ። ባቡሩ ተንቀሳቅሶ ከእይታው ለመጥፋት ጉዞ ሲጀምርም እጁን በማወዛወዝ ተሰናበተው ......

ፊቷ ላይ ከደረሰባት ጉዳት ሌላ ፣ ማርፉ ሁለት የጎድን አጥንቶቿ ተሰብረው ጭንቅላቷንም ተፈንክታ ነበር ። ግን ጠንካራና ጤናማ ሴት በመሆኗ ፣ ለመዳን ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም ። በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥም ጨርሳ ዳነች። ትንሿ ልጅ ግን ፣ ቀሪውን ሕይወቷን እጀ-ሽባ ሆና አሳለፈችው ። የእጅዋ ሁለት አጥንቶች ተሰብረው ስለ ነበር ፣ እስከ መጨረሻው እጅዋ ቆልማማ ሆና ቀረ ።

ስለ ኩርኜይ ግን ፣ ከዚያ ምሽት በኋላ የተሰማ ነገር አልነበረም።እምጥ ይግባ ስምጥ ፣ እልም ብሎ ጠፋ ። የውሃ ሽታ ሆነ ። ይሙት ይኑር የሚያውቅ አንድም ሰው አልተገኘም ።

—2—

ዐሥራ ሰባት ዓመታት ዐለፉ ። ወቅቱ የበልግ መገባደጃ አካባቢ ነው ። ፀሐይዋ በማዘቅዘቅ ላይ በመሆንዋ ገና በዐሥር ሰዓት መጨላለም ጀምሯል ። የአንድሬየቭ መንደር ከብቶች ወደ ቤታቸው እየተመለሱ ናቸው ። የአገልግሎቱን ጊዜ የፈጸመ አንድ የመንደሩ እረኛ ፣ ለዓመት በዓል ወደ አገር ቤት በመግባቱ ፣ ከብቶቹን የሚያግዱት ሴቶችና ሕፃናት በየተራ እየተፈራረቁ ነበር ።

ከብቶቹ ፣ እህሉ ከታጨደበት የእርሻ ቦታ ወጥተው ወደ ቆሻሻው ድንጋያማ መንገድ ገብተዋል ። የጨቀየው



መሬት በከብቶች ሰኮና ተጠቅጥቋል ። ያለማቋረጥ እየተጯጯሁና እያገሱ ወደ መንደሩ አቅጣጫ ይርመሰመሳሉ ። ትልቅ ኮፍያ ጭንቅላቱ ላይ አድርጎ በኃይለኛ ነፋስና ፣ ጠባይ መለዋወጥ የተነሣ የጠቆረና በማርጀቱ የተጣጣፈ ኮት የለበሰ አንድ ሽማግሌ ፣ ከመንጋው ፊት ለፊት መንገዱን ይዞ ወንተፍ ወንተፍ ይላል ። ሪዙና ጠቅለል ጠቅለል ያለው ጸጉሩ ሽበት ብቻ ቢሆንም ፣ ችምችም ያሉ ቅንድቦቹ ግን ጥቁር ናቸው ። አርጅተው የተበጣጠሱና በውሃ የሾቁ ከባድ ቦት ጫማዎች እግሩ ላይ ደንቅሮ በጭቃማው መንገድ ላይ ሲራመድ በመከራ ነው ። በያንዳንዱ ርምጃው ደግሞ የዕንጨት ዱላውን ይመረኩዘዋል ። ከብቶቹ ከኋላው መጥተው አጠገቡ ሲደርሱ ምርኩዙን ተደግፎ ቆመ ። ከመንጋው በስተመጨረሻ ላይ ቀሚሷን ከፊት ለፊት ሰብስባ መቀነቷ ውስጥ የሸጎጠች ወጣት ሴት መጣች ። ራሷ ላይ አልባሌ የአንገት ልብስ ጠምጥማለች ። የወንድ ቦት ጫማዎች አድርጋ ፣ ከአንዱ የመንገድ ጠርዝ ወደ ሌላው ዳርቻ በፍጥነት እየተራመደች ወደ ኋላ የሚጎተቱትንና ወደ ጎን የሚያፈነግጡትን በጎችና ዓሣማዎች ወደ ሰልፉ ትመልሳለች ። ሽማግሌዉ መንገደኛ አጠገብ ስትደርስ ቆም አለችና ከእግር እስከ ራሳቸው ቃኘቻቸው ።

“ እንዴት አመሹ አያት ! ” አለች በሚያከላላ ለስላሳ የወጣት ድምፅ ።

“ እንዴት አመሸሽ የኔ ቆንጆ ! ” ሽማግሌው አጸፋውን መለሱ ።

“ ሌሊቱን የሚያሳልፉበት ሥፍራ ነው የሚፈልጉት?”

“ መቼስ ፣ ሳይሆን ይቀራል ብለሽ ልጄ ! በጣም ነው የደከመኝ ” አሉ ሽማግሌዉ ።

" እንግዲያውስ ወደ መንደሩ እንጋፉ አዛውንት
ዘንድ ቢሔዱ ይሻላል ፥ አባቴ " አለች ወጣቷ ሴት ፥ የርጎ
ራጌ ቃና ባዘለ አነጋገር ። " በቀጥታ ወደኛ ቤት ይሔዱ፥
ከመጨረሻ ሦስተኛዉ ጎጆ ነው ። የባለቤቴ እናት እንደርሶ
ያሉ ካገር አገር ዘዋሪዎችን ማስጠጋት ይወዳሉ ። "

" ሦስተኛው ቤት አልሺኝ ? . . . እ . . . ያማ . . . .
የዚኖቪያቭ ቤተሰብ መኖሪያ መሆኑ አይደለም ? " አሉ
ሽማግሌዉ ፥ ቅንድባቸውን ሽብሽብ እያደረጉ ።

"ልክ ነው . . . . ግን በምን ዐወቁት ? "

" አይ ፥ በፊት ጊዜ እዚያ ስለ ነበርኩ ነው ። "

" ፊዱሽካ ለምን እንዲህ ግዴለሽ ትሆናለህ ! ያች
አንካሳዋ እኮ ወደ ኋላ ቀርታለች ! " አለች ፥ ወጣቷ ሴት
በጩኸት ። ከመንጋው ተነጥላ ወደ ኋላ ወደ ቀረች አንድ
እግሯ የተሰነከለ በግ እየጠቆመች ። ወዲያው በግራ እጅዋ
የያዘችውን በትር ልዩ በሆነ መንገድ እያወዛወዘችና ፥ በጠማ
ማው ቀኝ እጅዋ ደግሞ፥ራሷ ላይ የጠመጠመችውን ጨርቅ
አስተካክላ ፥ አንካሳዋን በግ ለመመለስ ወደ ኋላ በሩጫ
ተመለሰች ።

ሽማግሌዉ ሰው ኮርኔይ ቫስሊየቭ ነው ። ወጣቷ
ሴት ደግሞ ፥ ከዐሥራ ሰባት ዓመታት በፊት ገና ጨቅላ
ሕፃን ሳለች እጅዋን የሰበራት አጋሽካ ነበረች።አጋሽካ ከጋይ
ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው የአንድሬቭካ መንደር
ውስጥ ከሚኖር ሀብታም ቤተሰብ ልጅ ጋር ተጋብታለች ።

አንድ ጊዜ ጠንካራ ፥ ሀብታም ፥ ኩሩ ፥ የነበረው ኮር
ኔይ ቫሲሊየቭ ዛሬ ሁኔታው ሁሉ ተለዋውጦ ንብረት አልባ፥
አሮጌ ለማኝ ሆኗል ። ከፀሐይ በታች የቀረው ቅርስ ቢኖር
አካሉ ላይ የደረበው ዝተት ፥ በጥቅሉ የያዛቸው የውትድ



ርና መታወቂያ ቲኬቱና ሁለት ሸሚዞች ብቻ ነበሩ ። በቃ
ሌላ ነገር የለም ።

ይህ ሁሉ ለውጥ በኮርኔይ ላይ የደረሰው በጣም በዝ
ግታ ፥ ቀስ በቀስ ስለ ነበር ፥ ለውጡ መቼና እንዴት እንደ
ጀመረው እሱ ራሱም አያውቀውም ። በርግጠኝነት በሙሉ
ልብ የሚያውቀው አንድ ነገር ቢኖር ፥ ይህ መጥፎ
ዕድል የገጠመው በዚያች የተረገመች ሚስቱ የተነሣ
መሆኑን ብቻ ነው ። ቀድሞ ምን ዐይነት ሰው እንደ ነበር ፥
ወደ ኋላ መለስ ብሎ ማስታወስ ለኮርኔይ እንግዳ ነገር
ብቻ ሳይሆን ፥ ሥቃይም ጭምር ነበር ። ስላለፈ ሕልውናው ፥
ስለ አንድ ዘመን ማንነቱ ባሰበ ቁጥር ፥ ለነዚያ ዐሥራ ሰባት
የመርገም ዓመታት ምክንያትና ጦስ ነው ብሎ የሚገ
ምተውንም ሰው አብሮ ያስታውሳል ።

ሚስቱን በደበደበበት በዚያ ምሽት ከቤቱ ከወጣ
በኋላ ፥ የጫካ መሬት ይሸጣል ወደ ተባለው ባለርስት ዘንድ
ይሔዳል ። ግን ቀደም ብሎ መሬቱ ተሽጦ ስለነበር ፥ ያሰበው
ሳይሳካለት ይቀራል ። ከዚያ በኋላ ወደ ሞስኮ ተመልሶ
በኃይል እየጠጣ መስከር ይጀምራል ። ቀድሞ መጠጥ
ቢወሳስድም ሳይበዛ በመጠኑ ነበር ። መሬቱን እንደማያገኝ
ከተረዳ በኋላ ግን ፥ ሁለት ሳምንት ሙሉ ያለ ማቋረጥ እየ
ጠጣ መስከር ብቻ ይሆናል ። በመጨረሻ ከስካሩ ጋብ ብሎ
እራሱን ሲያውቅና ቀልቡ መለስ ሲልለት ፥ የቀድሞ ሥራ
ውን ለመቀጠል ፥ ከብት ለመግዛት ይሞክራል ። ግን ንግ
ዱም ስለ ጠመመበት ብዙ ገንዘብ ይከስራል ። እጁን ላለ
መስጠት ሲል እንደገና ከብት ይገዛና ይሞክራል ። አሁ
ንም በድጋሚ ሳይቀናው ይቀራል ። እናም ፥ በአንድ ዓመት
ጊዜ ከሦስት ሺህ ሩብል ውስጥ ሐያ አምስት ሩብል ብቻ
እስኪቀረው ይንኮታኮታል ። ስለዚህ ሥራ ብጤ መፈለግ ፥

ግድ ሆነበት ። የመጠጡም ነገር ይብስበትና በኃይል መጠጣቱን ይቀጥላል ።

በመጀመሪያው ዓመት ብዙም አልተጉላላ ፤ አንድ የከብት ነጋዴ ዘንድ በጸሐፊነት ለማገልገል ይቀጠራል። ነገር ግን ፣ አንድ ጊዜ በጉዞ ላይ ሳሉ በጣም በመስከሩ የተነሣ ነጋዴው ያባርረዋል ። ለጥቂት ጊዜ ሥራ ፈቶ ከቆየ በኋላ ፣ ቀድሞ በሚያውቀው ወዳጁ ርዳታ አንድ የወይን ጠጅ ነጋዴ ዘንድ ሥራ ይገኝለታል ። እዚያም ብዙ ሊቆይ አልቻለም ። ሒሳቡን በማመሰቃቀሉ ብዙም ሳይቆይ ተባረረ ። ችግሩ እየጠናበት ይሔዳል ። ወደ ቤቱ እንዳይመለስ ደግሞ ፣ ብስጭትና ኃፍረት ሕሊናውን እየሞገቱ እንቅፋት ሆኑበት ።

"እኔ ባጠገባቸው ባልገኝም ፣ እነርሱ ጥሩ ኑሮ ይኖራሉ ። ሴቷ ብቻ ሳትሆን ምናልባትም ወንዱም ልጅ የኔ ሳይሆን ይችላል " ሲል አሰበ ።

ሁኔታዎች እየከፉ ፣ እየተባባሱ ሔዱ ። የጸሐፊነት ሥራ የማግኘቱም ነገር የሕልም እንጀራ ሆነ ። የቀረው አማራጭ በከብት እረኝነት መቀጠር ብቻ ቢሆንም ፣ የኋላ ኋላ ደግሞ ለዚህ ዐይነቱ ሥራ ሊቀጥረው የሚፈልግም ጠፋ ።

ኑሮው እያዘቀጠ ፣ የማንሠራራት ተስፋው እየተማጠጠ በሔደ ቁጥር ፣ በሚስቱ ላይ ያለው ጥላቻም እየመረረ ንዶትና ቂሙ ሥር ሰደደ ። እዚህ ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ የመጨረሻውን የከብት እረኝነት ሥራ አንድ ልዩ የሆነ ሰው ዘንድ አግኝቶ ተቀጠረ ። ግን የዕድል ነገር ሆነና ከብቶቹ በኃይለኛ በሽታ ተመቱ ። ጥፋቱ የኮርኔይ አለመሆኑን ቢያውቅም ፣ በደረሰበት ጉዳት የተበሳጨው ቀጣሪ እሱንና ጸሐፊውን ሳይቀር ከሥራ አሰና



በታቸው ። ኮርኔይ ከዚህ በኋላ ሥራ እንደማያገኝ ርግጠኛ በመሆኑ ፣ ከአገር አገር እየዞረ በልመና ለመኖር ወሰነ ። ለእግሮቹ መሸፈኛ ሁለት ቦት ጫማዎች ፣ ለኮተቱ መያዣ ደግሞ ጥሩ ቦርሳ አሰናዳ ። እናም ጥቂት ስኳርና ሻይ ቅጠል በቦርሳው ፣ ስምንት ሩብል በኪሱ ይዞ ወደ ኪየቭ ጉዞ ጀመረ ። ነገር ግን ፣ ኪየቭን ስላልወደደው ብዙ አልቆየበትም ። ጉዞውን ቀጠለና ወደ ኮካሰስ ፣ ኖቪ አፎን አመራ ። በዚህ ዙረት ወቅት ኃይለኛ የትኩሳት በሽታ ስለ ያዘው ፣ አካሉ ጭምር በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዳከመ ። የተረፈው ገንዘብ አንድ ሩብል ከሰባ ኮፔክ ብቻ ነበር ። ጓደኛም ፣ ገንዘብም ፣ ጤንነትም በማጣቱ ውሳኔውን ወደ መጨረሻ አማራጩ አዞረ ። ወደ ቤቱ ለመመለስ ወሰነ ። "ያቺ የተረገመች ፍጥረት ምናልባት እስካሁን ሞታ ይሆናል " ሲል አሰበ ። " በሕይወት ካገኘኋትም እነግራታለሁ ። ስለ ፈጸመችብኝ በደል ፣ ከመሞቷ በፊት እነግራታለሁ ። ገሃነም ትግባና ! " ይህን በሐሳብ አውጥቶ ካወረደ በኋላ ፣ ወደ ትውልድ አገሩ ፊቱን አዞረ ።

በሁለት ቀናት ውስጥ በሽታው አገርሽቶበት በትኩሳት ይሠቃይ ጀመር ። እየደከመ ፣ እየዛለ ፣ እየለተተ በመሔዱ በቀን ከዐሥርና ዐሥራ አምስት ኪሎ ሜትር በላይ መጓዝ ተሳነው ። ከቤቱ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር በሚበልጥ ርቀት ላይ ሳለ ፣ ገንዘቡ ሁሉ ተሟጦ አልቆ በሚንከራተትበት በዚያ ጊዜ የነበረው ምርጫ ፣ ምግቡን ለማግኘት የክርስቶስን ስም እየጠራ መለመን ፣ ለሌሊት መጠለያው ደግሞ ፣ ወደየመንደሩ አንጋፋ አዛውንት መጠጋት ብቻ ነበር ። " ደስ ይበልሽ ! እንዴት እንደ ሆንኩ ተመልከች ! " ይላል ለሚስቱ ፣ ዘወትር በሐሳቡ በሚፋጠጡበት ጊዜ ። እናም ደግሞ የድሮ ዐመሉ አልለቅህ ብሎት ዕድሜ ያደቀቃቸው ደካማ እጆቹን ቡጢ

ይጨብጣል ። ግን የሚመታው ማንም ምንም ዒላማ የለም። የሚመታበት ኃይሉም ከመዳፎቹ ተንጠፍጥፎ አልቋል ።

ያን ረጅም ርቀት በእግሩ ተጉዞ ለማገባደድ ሁለት ሳምንት ወሰደበት ። ከቤቱ አራት ማይል ወደሚርቀውና አጋሽካን ወዳገኘበት ሥፍራ ሲደርስ ታሞ ፥ ደክሞ ፥ ደቅቆ ጠውልጎ ነበር ። ከዐሥራ ሰባት ዓመታት በፊት እጅዋን የሰበራትን አጋሽካን ሲያገኝ አላወቃትም ፤ እሷም አላወቀችውም ።

—3—

አጋፈያ ልክ እንደ ነገረችው አደረገ ። ወደ ዚኖቭያቭ ቤተሰብ ግቢ በማምራት ሌሊቱን በቤታቸው ውስጥ እንዲያሳልፍ ጠየቀ ። ተፈቀደለት ።

ወደ ጎጆው ከገባ በኋላ ፥ ዘወትር በዚያን ዐይነት አጋጣሚ እንደሚያደርገው ወደ ቅዱሳኑ ምስል ተጠግቶ አማተበ ። ለቤቱ ባለቤቶች ሰላምታ ያቀረበው ከዚያ በኋላ ነበር ።

“ በርዶዎታል መሰለኝ አባቴ ? ወዲህ ወደ ምድጃው ቀረብ ብለው ይሙቁ ” አሉ የቤቱ እመቤት ፥ ጠረጴዛውን እያጸዳዱ ። የሰውነታቸው ቆዳ በሙሉ ተጨማዷል ።

አንድ መዘዞ ወጣት ገበሬ ፥ ጠረጴዛው አጠገብ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጦ መብራቱን ያስተካክላል ። የአጋፈያ ባል ነው ።

“ ዝናቡ ክፉኛ አርሶዎት የለም እንዴ ! ” አለ ወጣቱ ገበሬ ። “ ኧረ ወዲህ ወደ እሳቱ ጠጋ ብለው ይሙቁ ። ”



ኰርኔይ ልብሱንና ቦት ጫማዎቹን አወላልቆ ፥ እግጋቹ ላይ የጠመጠመውን ድሪቶ ምድጃው ላይ ከአሰጣ በኋላ ፥ ራሱም ምድጃው ላይ ወጥቶ ቁጭ አለ ።

አጋፈያ በእጅዋ ማድጋ እንጠልጥላ ወደ ቤት ገባች ። ከብቶቹን በየበረታቸው አስገብታ መመለሷ ነው ።

“ አንድ ሽማግሌ ወደዚህ አልመጡም ? ” አለች ። “ እዚህ ማደሪያ ጠይቁ ብያቸው ነበር ። ”

“ መጥተዋል ። እኚያው እዚያ ጋ ” አሉ የቤቱ እመቤት ፥ ኰርኔይ ቁጭ ብሎ አጥንታቸው ብቻ የቀረ እጀቹን ወደሚያሻሽበት ምድጃ እያመለከቱ ።

የሻይ ጊዜ ሲደርስ አብሮአቸው እንዲቀመጥ የቤቱ ሰዎች ጋበዙት ። ከምድጃው ላይ ወረደና አግዳሚው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ ። ቁራጭ ስኳር ከኩባያ ሻይ ጋር ተሰጠው ።

ወሬ ቀጠለና ስለ ዝናቡ ፥ ስለ መኸሩም ያወጉ ጀመር። በዝናቡ የተነሣ የባለርስቱን እህል ለመሰብሰብ አለመቻሉን ተወያዩበት ። ገበሬዎቹ የራሳቸውን ድርሻ ወደየጎትራቸው አስገብተዋል ። የከበርቴዎች ሰብል ግን ፥ እዚያው እማሳው ላይ እየበሰበሰ ነው ። በዚያ ላይ ደግሞ የዐይጡ ነገር አይጣል ነው ሲባባሉ ቆዩ ። ኰርኔይም በመንገድ ላይ ሳለ ፥ በየማሳው በርካታ የስንዴ ነዶ በየእርሻው ተከምሮ ማየቱን በመግለጽ በውይይቱ ለመሳተፍ ሞከረ ።

ወጣቷ ሴት ፥ ተጨማሪ የቀዘቀዘ ሻይ ቀድታ አቀረበችለት ። አምስተኛ ኩባያዉ መሆኑ ነው ።

“ አይዞዎት አባት፥ ይጠጡት።ለርስዎ ጥሩክ ነው ” አለችው ፥ በመጀመሪያ በቃኝ በማለቱ ።

"ለመሆኑ ምን አግኝቶሽ ነው እጅሽ እንዲህ የሆነው ? " አለ ኩባያውን በጥንቃቄ እየተቀበላት ቅንድቡን ሽብሽብ አድርጎ ።

" ገና አንድ ፍሬ ልጅ ሳለች ነው የተሰበረው ። አባቷ ነው እንዲህ ያረጋት " አሉ መለፍለፍ የሚወዱት የወጣቷ ሴት እማት ።

" ግን ለምን? " አለ ኰርኔይ ፡ ወጣቷን ሴት ትክ ብሎ እያስተዋለ ። ድንገት ኢቭስቲግኒ ቤሊ ከነሰማያዊ ዐይኖቹ ትውስ አለው ። ወዲያው ኩባያውን የያዘበት እጁ በኃይል መንቀጥቀጥ በመጀመሩ ፡ መልሶ ጠረጴዛው ላይ ለማስቀመጥ ሲሞክር ግማሹ ሻይ ተፋሰሰ ።

" ከዚህ ከኛ ራቅ ብሎ በሚገኘው ጋይ የሚባል መንደር አንድ ሰው ነበር ። አባቷ ነው ። ኰርኔይ ቫስሊየቭ ይሉታል ስሙን ። ልክ የሌለው ሀብታም ፡ በሚስቱም የሚኮራ ዘበናይ ነበር ። ታዲያ አንድ ቀን ይችኑ ሚስቱን ሲደበድብ ሕፃኗንም አብሮ መትቷት ኖሮ ፡ ይኸው እንዲህ ሽባ አድርጎ አስቀራት " አሉ ፡ አሮጊቷ የቤቱ እመቤት ።

ኰርኔይ በጸጥታ ቁጭ ብሎ ግንባሩን ኩስትር በማድረግ፣ አንዴ የቤቱን ባለቤቶች፣ አንዴ ደግሞ እጋሽካን ከሚንቀጠቀጡ ቅንድቦቹ ሥር በሚዋልሉ ዐይኖቹ ይመለከታል ።

" ግን እኮ እንዲህ ያለ ነገር መፈጸሙ ለምንድነው በሉ ? " አለ ፡ የተሰጠውን ስኳር በጥርሱ ሸረፍ እያደረገ።

" ማን ያውቃል ብለው እርስ ደግሞ ! መቼም የኛ የሴቶች ነገር . . . ከሚያሳማ ነገር አንርቅ " አሉ አሮጊቷ። "ብቻ እንደ ወሬው ከሆነ ፡ የኛ መንደር ቀወላጅ በሆነ



ሠራተኛቸው ሰበብ ነው ይባላል ። እሱም ኖሮ ኖሮ እዚያው እቤታቸው ውስጥ ሞተ ። "

" ሞተ? " አለ ኰርኔይ እየሳለ ።

"ውይ ስንት ጊዜው! ቆይቶ ።ይቺ የኛ ሸጋ እንግዲህ ከዚያ አሁን ካልኩዎት ቤተሰብ የተገኘች ናት ። እዬ ዓለም ፡ እንዴት ያለ ኑሮ ይኖሩ ነበር ። እዬ ጊዜ!እንደምን ያሉ ጥሩ ሰዎች ነበሩ ። አባወራው በሕይወት ሳለ፡ በሞላው አገር ላይ ማንም የሚስተካከላቸው አልነበረም ።"

" እንዴ አባወራውም ሞቷል ማለት ነው ? " ኰርኔይ ጠየቀ ።

"ይመስለኛል ። የዛሬ ዐሥራ አምስት ዓመት ገደማ ነው ድንገት ብድግ ብሎ የጠፋው ። "

"አዎ ከዚያ አይበልጥም ። እማምዬ እንደ ነገረችኝ ከሆነ እኔ ገና ጡት መጣሌ ነበር ። "

" ታዲያ አንቺስ እጅሽን ስለ ሰበረብሽ አዝነሽበታል ? " . . . . . ኰርኔይ ጉሮሮው ውስጥ ድምፁ ተሰንቅሮበት የጀመረውን ንግግር መጨረስ ተሳነው ።

" የውጭ ሰው አይደለ ። መቼስ ምንም ቢሆን አባቴ እኮ ነው ። ሻዩን ይጠጡት እንጂ አባት ፡ ትንሽ ሞቅ ቢያደርግዎት እንኳን ። ዐፈር ስሆን ትንሽ ልጨምርልዎት ! "

ኰርኔይ ግን ፡ መልስ በመስጠት ፋንታ ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ ።

" ምንድነው ነገሩ . . . .ምን ሆኑ? "

" ምንም አይደል . . . . እንዲያው ብቻ ... "

እናም ኰርኔይ በሚንቀጠቀጡ እጆቹ ግድግዳና ምሰሶውን እየተደገፈ በረጃጅም ከሲታ እግሮቹ እየተውተረተረ ወደ ምድጃው ወጣ ።

“ ይሄዋ ! ” አሉ አሮጊቷ ፣ ለገበሬው ልጃቸው ወደ ሽማግሌው አቅጣጫ ዐይናቸውን ጠቀስ በማድረግ ።

—4—

በማግሥቱ ኰርኔይ ከሁሉም በፊት ማልዶ ተነሣ ። ከምድጃው ወርዶ የእግር መጠቅለያውን ጨርቅ አስተካከለና ፣ በሙቀት የተነሣ የተጨረማመቱ ቦት ጫማዎቹን አጥልቆ ቦርሳውን ትከሻው ላይ አንጠለጠለው ።

“ ለምን ቁርስ በልተው አይሔዱም አባት ? ” አሉ አሮጊቷ የቤት እመቤት ።

“ የለም አልቆይም ፤ መሔድ አለብኝ ። እግዜር ከናንተ ጋር ይሁን ” አለ ኰርኔይ ።

“ እንግዲያውስ ከትናንቱ ቂጣ ጥቂት ይያዙ ። ይቆዩኝ እንዴ ፤ በቦርሳዎ ውስጥ ላድርግልዎት ፤ ስንቅ ይሆንዎታል ። “ ኰርኔይ አሮጊቷን ተሰናበተ ።

“ እንግዲህ ሲመለሱ ጐራ ይበሉ አደራ ! እስከዚያው መቼም በሕይወት እንደምንቆይ እምናለሁ ” አሉ አሮጊቷ።

ጥቅጥቅ ያለው የበልግ ጭጋግ አገር መሬቱን ሸፍኖታል ። ኰርኔይ ግን ፣ መንገዱን በሙሉ ደኅና አድርጎ ስለሚያውቀው ጉዞውን ያለ ችግር ቀጠለ ። አባባ ጐርፋጣው ፣ ቁጥቋጦና ጫካው ሁሉም ለእርሱ እንግዳ አይደለም ። እርግጥ ባለፉት ዐሥራ ሰባት ዓመታት ብዙ



ዛፎች ተቆርጠዋል ። ግን በምትካቸው የተተከሉትም ጸድቀው ፣ አድገው አርጅተዋል ።

የጋይ መንደር ምንም አልተለወጠም ። ዳር ዳሩን ብቻ ጥቂት አዳዲስ ቤቶች ተሠርተዋል ። ከአሮጌዎቹ የዕንጨት ቤቶች መካከል አንዳንዶቹ ከጡብ በተሠሩ ቤቶች ተተክተዋል ። ከድንጋይ የተሠራው የኰርኔይ ቤትም በጊዜ ብዛት ከማርጀቱ በቀር እንዳለ ነው ። የጣሪያው ቆርቆሮ ለብዙ ዓመታት ቀለም አለማግኘቱ ያስታውቃል ። ከግድግዳዎቹ ማዕዘናት ጥቂት ጡቦች ተፈነቃቅለው ወደ ዋናው በር የሚያደርሱትም ደረጃዎች ተወለቃቅመዋል ።

ኰርኔይ ቀድሞ ንብረቱ ወደ ነበረው ቤት ሲቃረብ ፣ የቅጥሩ በር ተንቋቋና አንዲት ባዝራ ዓመት ካልሞላው ግልገሏ ጋር ፣ እንዲሁም አንድ ግራጫ መጋኛ ፈረስና ሦስት ዓመት የሚሆነው ድንጉላ ተከታትለው ብቅ አሉ ። አሮጌው ግራጫ ፣ ኰርኔይ ከቤቱ ከመኰብለሉ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ገዝቷት የነበረችውን ባዝራ ይመስላል ።

“ ያኔ ባዝራዋን ስገዛት እርግዛው የነበረ ልጅዋ መሆን አለበት ። በተለይ የኋላ እግሮቹ አካባቢ ፣ ሰፊ ደረቱና የእግሮቹ በከርዳዳ ጸጉር መሸፈን ልክ እናቱን ቁርጥ ነው ” አለ በሐሳቡ ።

ፈረሶቹ ውሃ ለመጠጣት ነበር የሚሔዱት ። ከኋላቸው ጥቋቁር ዐይኖች ያሉት ፣ አዳዲስ ጫማዎች ያደረገ ትንሽ ልጅ ይከተላል ። “ ያለ ጥርጥር የልጄ ልጅ መሆን አለበት ። አባቱን ይመስላል ። ” አሁንም ኰርኔይ በሐሳቡ ያገናዝብ ጀመር ።

ልጁ እንግዳውን ሽማግሌ ትኩር ብሎ አየና ፣ ጭቃ ውስጥ ገብቶ የሚፈነጥዝ አንድ ያልተቀጠቀጠ ፈረስ

ተከትሎ ሮጠ ። ከልጁ ቀጥሎ አንድ ውሻ ብቅ አለ ። የቀድሞ ውሻቸው ቮልቾክን ይመስላል ።

" ቮልቾክ ራሱ ሊሆን ይችላል ? " አለ ኩርኔይ አሁንም በሐሳቡ ።ግን ቮልቾክ በሕይወት ከቆየ አሁን ሐያ ዓመት እንደሚሆነው አስታወሰ ። በዚያ ትዝታው መቼም መች ከአእምሮው በማይጠፉ ምሽት ፣ ከደረጃው ድጋፍ ላይ ያፈሰውን በረዶ ቁጭ ብሎ የበላባቸውን ደረጃዎች በብዙ ትግል ወጣና ወደ መተላለፊያው የሚያስገባውን በር ከፈተው ።

" መጀመሪያ ሳትጠይቅ ፤ ወይ ሳታንኳኳ እንዴት እንዲሁ ዘው ትላለህ ? " ከቤቱ ውስጥ የአንዲት ሴት ድምፅ አንባረቀበት ። የሚስቱ ድምፅ መሆኑን ወዲያው ለየው ። እዎ አልተሳሳተም ። እሷው ራሷ የድሮ ሚስቱ ናት ። ጠውልጋ ጅማቷ ወጥቶ ፤ አርጅታ ቆዳዋ ሁሉ ተሸብሽቦ ወደ በሩ ብቅ አለች ። የኩርኔይ ግምት ሌላ ነበር ። የተጫወተችበትን ፤ ቋቅ እስኪላት ሊዘልፋት ያቀደውን ከፉኛ የጠላትን ሚስቱ ማርፋን ፣ ወጣቷንና መልከ መልካሟን ማርፋን ለማየት ነበር የጠበቀው ። እንዳሰበው ሳይሆን አይቷት የማያውቅ ልዩና እንግዳ አሮጊት እፊቱ ቆማለች ። " ለልመና ከሆነ የመጣኸው እዚያው መስኮቱ አጠገብ ተቀምጠህ መብላት ትችላለህ " አለችው ፤ ጀሮን በሚቀፍ ድምፅ ቆጣ ብላ ።

" እረ እኔስ ለመለመን አይደለም የመጣሁት " አለ ኩርኔይ ።

"ታዲያ ሌላ ምንድነው የምትፈልገው ? "

ድንገት ከቆመችበት ድርቅ ፣ ቀጥ አለች ። ፊቷ ልውጥውጥ አለ ። እንዳወቀችው ተገነዘበ ።



"እዚህ ቤት ከየትም እየመጡ የሚልከሰከሱና የሚያደቡ የአንተ ዐይነቶች ብዙ ናቸው ። ስለዚህ ሒድልኝ እባክህ ! በእግዚአብሔር ይሁንብህና ከዚህ ቦታ ሒድልኝ" አለች ።

ኩርኔይ እንደ መንገዳገድ ሞከረው ። በምርኩዙ ድጋፍ እንደ ምንም ቀጥ ብሎ ቆመና ትክ ብሎ ያስተውላት ጀመር ። ለብዙ ዓመታት በልቡ ይዞት የኖረው ስለ ርሷ ያለው ጥላቻ ፣ በድንገት እልም ብሎ በመጥፋቱ ተደንቆ ይመለከታት ጀመር ።

" ማርፋ ከእንግዲህ ብዙም ዕድሜ አይቀረንም ፣ ሁላችንም በቅርቡ እንሞታለን " አለ ።

" ሒድ እባክህ ፣ በግዜር ይሁንብህና ሒድ " አለች ፣ በተጣደፈ አነጋገር ።

" ሌላ የምትይው ነገር የለሽም ? "

"ምንም የምጨምረው ነገር የለኝም ። በፈጣሪ ይሁንብህና ከዚህ ግድም ሒድ ። እዚህ ቦታ እየመጡ የሚያንዣብቡ ያንተ ዐይነት ዘዋሪዎች ብዙ ናቸው ። "

ቀልጠፍ ባሉ ርምጃዎች ወደ ቤት ውስጥ ተመልሳ በሩን በኃይል የጓሊት ዘጋችው ።

" ምን በድሎሽ ነው እንዲህ የምትሰድቢው ? " የወንድ ድምፅ ከወደ ውስጥ ተሰማ ። ወዲያው ወገቡ ላይ ፉስ ያንጠለጠለ ወጣት ገበሬ ወደ በሩ ብቅ አለ ። ከዐርባ ዓመታት በፊት የነበረውን የኩርኔይን መልክና ቁመና ቁርጥ ነው ። ብቻ ይህኛው ትንሽ አጠር ፣ ቀጠን ይላል ። ጥቁር የሚያንጸባርቁ ዐይኖቹ ግን ፍጹም የኩርኔይ ናቸው ።

ሰውየው የኩርኔይ ወንድ ልጅ ፊዮካ ነበር ። ከዐሥራ ሰባት ዓመታት በፊት ከአባቱ የሥዕል መጽሐፍ ሽልማት

ያገኘው ወጣት ነው ። ለማኙን ሽማግሌ በትሕትናና በደግ መንፈስ ባለማስተናገዱ ከእናቱ ጋር ሲጨቃጨቅ ቆየ ። ከርሱ ተከትሎ ደግሞ ዱዳው የኩርኜይ ወንድም ልጅ ብቅ አለ ። እሱም እንደ ፌዶካ ትንሽ መጥረቢያ ወገቡ ላይ አንጠልጥሏል ። ደግሞም እንደ አጎቱ ልጅ ትልቅ ገበሬ ወጥቶታል ። ሪዙን በቀጭኑ ተላጭቶታል ። ሰገግ ያለው አንገቱ ቀጭን ነው ። አስተያየቱ ሁለመናን ዘልቆ የሚሰረስር ይመስላል ። ሁለቱ ጉረምሳ ገበሬዎች እንጨት ቆረጣ ወደ ጫካ ለመሔድ፡ገና ቁርሳቸውን በልተው መውጣታቸው ነበር ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ "አባት" አለ ፌዶኮ ወደ ሽማግሌውና ወደ ቤቱ ውስጥ በየተራ እያመለከተ ። ወዲያው ዳቦ እንደ መቁረጥ ያለ ምልክት ለዱዳው አሳየው ።

ፌዶካ ወደ ዋናው መንገድ ሲያመራ ፣ ዱዳው ወደ ቤት ተመልሶ ገባ ። ኩርኜይ ግድግዳውን ተደግፎ ፣ ዱላውን በመመርኩዝ አቀርቅሮ ቆመ ። የማይቋቋመው ዐይነት ድካም መላ አካሉን ተጫጭኖታል ። ጉሮሮው ውስጥ የሚተናነቀውን መንሰቅሰቅና በዐይኖቹ ግጥም የሚለውን እንባ ለመመለስ ብዙ መታገል ነበረበት ። ዱዳው የወንድሙ ልጅ ትኩስ የጥቁር ዳቦ ቁራሽ አምጥቶ ሰጠው። ኩርኜይ እያማተበ ዳቦውን ተቀበለ ። ዱዳው አንዳች ነገር እንደ ወረደበት ሁሉ ድንገት በድን ሆኖ ቆመ ። ማንነቱን ለይቶ በማወቁ ፣ አፉን ከፍቶ ኩርኜይን ይመለከተው ጀመር ። ኩርኜይ ሲታገለው የቆየው እንባውን ከዚያ በኋላ መቆጣጠር አልቻለም ። ዐይኖቹን ፣ አፍንጫውንና ሽበቶ ሪዙን በኩቱ ጠርዝ እየጠራረገ ከዱዳው ሰው ዞር ብሎ በደረጃዎቹ ወረደ ። ልዩ ዐይነት ኃይለኛ የመረታት ስሜት ወረረው ። በሰው ልጅ ፊት ፣ በሚስቱ ፊት ፣ በሞላው ዓለም ፊት ትሁት ሆኖ የመቅለብ ፍላጎት ሲያድርበት



ተሰማው ። አንዳች ሥቃይ ፣ ግን ደስ የሚልና የሚያረካ ሥቃይ ልቡናውን ጠቅ አደረገው ።

ሁሉንም ነገር በመስኮቱ በኩል ትመለከት የነበረችው ማርፋ ፣ የቀድሞ ባሏ በቤቱ ጥጋት ታጥፎ ከእይታዋ ሲሰወር በከባዱ ተነፈሰች ። የመገላገል ፣ የእፎይታ ትንፋሽ ነበር ። ወዲያው በሸማኔ ዕቃዋ አጠገብ ተቀምጣ ሥራዋን ለመቀጠል ሞከረች ። ግን አልቻለችም ። ዐርቡን ደጋግማ ብትመታው አልሆን አላት ። እጆቿ ለመሥራት አሻፈረን አሉ ። ሥራውን አቁማ ኩርኜይን ከጥቂት ጊዜ በፊት እንዳየችው ሆኖ በዐይነ ሕሊናዋ ለመመልከት ሞከረች ። እሱ መሆኑን ዐውቃለች ፣ አንድ ጊዜ የወደዳትና የደበደባት ሰው ለመሆኑ ርግጠኛ ነበረች ። የፈጸመችው ነገር ዘገነናት ። ማድረግ የማይገባትን ፈጽማለች ። ግን እንዴት አድርጋ ማስተናገድ ነበረባት ? እርሱም ፣ ኩርኜይ መሆኑንና በመጨረሻም ወደ ቤት መመለሱን አልገለጸላትም ። እናም እንደገና መወርወሪያውን አንሥታ ለዐይን እስኪይዝ ድረስ ስትሠራ ቆየች ።

—5—

ከብዙ ድካም በኋላ ፣ ኩርኜይ አንድሬያቭካ መንደር ሲደርስ ፣ እንድያውን ጨላልሞ ነበር ። ለአዳሩ ወደ ዚኖቪያቭ ቤተሰብ መኖሪያ ሔደ ።

" እንዴት እንዲህ በቶሎ ተመለሱ? ርቀው አልሔዱም መሰለኝ አባት "ሲሉ ተቀበሉት ።

" አልቻልኩም ። በጣም ስለ ደከመኝ ርቄ ለመሔድ አልቻልኩም ። አሁንም ወደፊት ከመቀጠል ወደ መጣ

ሁቡት መመለሱ የሚሻል ይመስለኛል ። ዛሬ ሌሊቱን እዚሁ ባሳልፍ ፈቃዳችሁ ነው? ” አለ ኵርኔይ ።

“ ምን ገዶን አባት ። ምን ያህል ሲያስቸግሩን ፤ ቦታው እንደሁ እንደሚያዩት ለሁላችንም ይበቃል ። ይልቁንስ አሁን ወዲህ ወደ እሳቱ ጠጋ ይበሉና ይሙቅዎት ። ”

ሌሊቱን በሙሉ ኵርኔይ በትኩሳት ሲቃጠል አደረ። ሊነጋጋ ሲል ትንሽ ሽለብ አደረገው ። ተመልሶ ሲነቃ የቤቱ ሰዎች በሙሉ ወደየሥራቸው ተሠማርተዋል ። አጋፊያ ብቻ ወደ ኋላ ቀርታ ጉድ ጉድ ትላለች ።

ኵርኔይ የተኛው አሮጊቷ የቤቷ እመቤት በሰጡት ኮት ላይ ነበር ።

አጋፊያ የጋገረችውን ዳቦ ከምድጃው ላይ እያነሣች ሳለ ፡

“ ወዲህ ቀረብ በይ እስቲ የኔ ልጅ ” አለ ኵርኔይ ድክም ባለ ድምፅ ።

“ እሺ መጣሁ አባት ” አለች ፡ ዳቦውን በዕቃ እያ ኖረች ። “ የሚጠጣ ነገር ይፈልጋሉ ? ትንሽ ክቫስ ምን ይልዎታል ? ”

መልስ አልሰጣትም ።

የጀመረችውን ሥራ ስትጨርስ ክቫስ ይዛ ተጠጋችው። መጠጡን ሳይቀበል ፡ ወደርሷም ዘወር ሳይል ፊቱን ወደላይ እንዳቀና ተኝቷል ። ካለበት ሳይንቀሳቀስ ያናግራት ጀመር።

“ አጋሻ ” አለ በለስላሳ ድምፅ ። “ እንግዲህ ጊዜ ተቃርቧል ። እኔም ለመሞት እፈልጋለሁ ። እና ስለ ክርስቶስ ብለሽ ይቅር በይኝ ። ”



“ እግዜር ይቅር ባይ ነው አባት ። ግን እኮ እርስዎ ያደረሱብኝ ጉዳት የለም ። ”

ጸጥ እንዳለ ቆየ ።

“ ሌላም ተጨማሪ ነገር አለ ልጄ ። ሒጂና ለእናትሽ ንገሪያት . . . እንግዳው ሰውዬ . . . ንገሪያት . . . የትናንቱ እንግዳ ሰው . . . ብለሽ ንገሪያት . . . ”

ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ ።

“ ወደኛ ቤት ሔደው ነበር ማለት ነው? ”

“ አዎ ትላንት ብቅ ብዬ ነበር ። እና ያ የትናንቱ ሰው እንግዳው ሽማግሌ ብለሽ ንገሪያት . . . እንግዳው በያት ” . . . እንደገና የልቅሶው ሣግ ጉሮሮውን ተናነቀው ። በመጨረሻ ግን ፡ እንደ ምንም ራሱን አበረታታና ቀጠለ ። “ የትናንቱ እንግዳ የመጣው ሊሰናበትሽ ነበር . . . ” ንግግሩን ሳይጨርስ እደረቱ አካባቢ ይዳብስ ጀመር ።

“ እነግራታለሁ አባት ፤ እነግራታለሁ ። ግን ምንድ ነው የሚፈልጉት ? ” አለች አጋፊያ ።

ሽማግሌው ጭጭ እንዳለ ፡ ከደረቱ አካባቢ አንዲት ቁራጭ ወረቀት አወጣና ጾጉር የለበሰውን ከሲታ እጁን ወደ ወጣቷ ሴት ዘረጋው ።

“ . . . . እነሆ ይሀን ለሚጠይቅሽ ለማንኛውም ሰው ስጪልኝ ፤ ወታደር ሳለሁ የምጠቀምበት ቲኬት ነው ። እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ከእንግዲህ የበደሌን ጭነት አራግፌአለሁ ። ” ገጹ የሐሤት ጸዳል ተላበሰ ። ቅንድቡን ሽቅብ ሰብሰብ አድርጎ ዐይኖቹን ጣሪያው ላይ ሰካና ጸጥ ፡ እርጭ ፡ ጭጭ አለ ።

“ ሻማ ” ሲል ጠየቀ ፡ ከንፈሮቹን ሳያንቀሳቅስ ፤

አጋፊያ ወዲያው ገባት ። ከቅዱሳኑ ምስል አጠገብ አንድ ከሰም የተሠራ ሻማ አንሥታ ሰጠችው ። በአውራ ጣቱ ጥብቅ አድርጎ ያዘው ።

የሰጣትን ቲኬት ሰንዱቁ ውስጥ ለመክተት ሔደች ። ስትመለስ ሻማው ከእጁ ወድቆ ፤ የዐይኖቹ ብርሃን ጨልሞ ደረቱን ከፍና ዝቅ የሚያደርገው ትንፋሽ ጸጥ ብሏል ። አጋፊያ እማተበችና የሻማውን ነበልባል እፍ ብላ አጠፋችው ። ንጹሕ ፎጣ አውጥታ ራሱን ሸፈነችለት ......

ሌሊቱን በሙሉ ማርፋ እንቅልፍ የሚሉ በዐይኗ ሳይዞር ፤ ስለ ኩርኔይ ስታስብ አደረች ። ጧት ተነሥታ ኮቷን በትከሻዋ ፤ እንገት ልብሷን ደግሞ ራሷ ላይ ጣል አደረገችና የትናንቱ እንግዳ ሰው የት እንደ ደረሰ ለማጣራት ወጣች ። ብዙም ርቃ ሳትሔድ ሽማግሌው፤ አንድሬያቭካ መንደር ማደሩን ተረዳች ። ማርፋ ለምርኩዝ የሚሆን ዱላ ብጤ ያዘችና ወደ አንድሬያቭካ አቀናች ። “ ሁለታችንም ይቅርታ እንደራረጋለን ። ወደ ቤታችን አመጣውና ከበደላችን ነጻ ሆነን እንኖራለን ። ሌላው ቢቀር በገዛ ቤቱ ውስጥ ፤ በወለደው ልጁ አጠገብ መሞትም አንድ ነገር ነው ” እያለች በሐሳቧ ፤ መንገዷን ቀጠለች ።

ማርፋ ወደ አማቶቿ ቤት ስትቃረብ፤በርከት ያሉ ሰዎች ከውጭ በኩል ተሰባስበዋል ። ገሚሶቹ መተላለፊያው ላይ፤ ሌሎች ከመስኮቱ አጠገብ ቆመዋል ። ሁሉም ሰው ስለ ሁኔታው ዐውቋል ። ከዐርባ ዓመታት በፊት በአካባቢው ተደናቂ የነበረው ሀብታሙና ዝነኛው ኩርኔይ ቫሲሊየቭ ድሃ ከርታታ ሆኖ በልጁ ቤት መሞቱን መንደርተኛው በሙሉ ተረድቷል ። እንደ ውጭው ሁሉ ውስጡም እስከ ደጃፉ በሰው ጢም ብሏል ። ሴቶቹ ለብቻቸው እያንሾካሾኩ በከባዱ ይተነፍሳሉ ። ጭንቅላታቸውን ይነቀንቃሉ ።



ማርፋ ወደ ጐጆው ስትገባ ፤ መንደርተኛው ገለል ብሎ መንገዱን ለቀቀላት ። አስከሬኑ ተጣጥቦ በፎጣ ተሸፍኖ ከቅዱሳኑ ምስል ግርጌ ተጋድሟል ። በመንደሩ ውስጥ የማንበብ ችሎታ ያለው ፊሊፕ ኩኖቪች ልክ እንደ ዲያቆን ሆኖ ከመዝሙረ ዳዊት ያነበንባል ።

ይቅር ለማለትም ሆነ ይቅርታ ለመለመን ዘግይቷል ። ኩርኔይ በበኩሉ ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ይቅር ብሎ ይሆን ወይስ ቂምና ጥፋቱን ገና በልቡናው እያስታመመ ! .... ኩራት ከሰፈነበት የኩርኔይ በድን አርጌ ገጽ የትኛውንም ለማወቅ በፍጹም አይቻልም ።

1975 ዓ.ም

# አንቷን ፓቪሎቪች ቼኾቭ

(1860—1904)



በአዞቭ ባሕር አጠገብ በምትገኝ ታጋንሮግ የምትባል ሥፍራ በ1860 ተወለደ ። አባቱ በአንዲት አነስተኛ ሱቅ ልዩ ልዩ ሸቀጦችን እየቸረቸረ ለመተዳደር የሚሞክር ቢሆንም ፣ እምብዛም የተሳካለት ነጋዴ አልነበረም።ቼኾቭ፣ ደስተኛና ንቁ በሆነ ቤተሰብ ውስጥ በማደጉ ፣ የኋላ ኋላ ለጻፋቸው ቀልድ-አዘል ድርሰቶችና ኮሜዲዎች መዋጣት ረድቶታል ይባላል ። ከዚህም ሌላ የቼኾቭ ሦስት ሠዓሊዎች ወንድሞች የነበሩት ሲሆን ፣ ይህም የኪነታዊ ምናቡን አድማስ ለማስፋትና ከልጅነት አንሥቶ ሥር የሰደደ የኪነት ፍቅር ለማዳበር እንደ ረዳው ይገመታል ።

ቼኾቭ የቅድመ ኮሌጅ ትምህርቱን አጠናቆ ወደ ሞስኮ ዩኒቨርስቲ ከገባ በኋላ ፣ ሕክምና በማጥናት በዶክተርነት ተመረቀ ። ይሁን እንጂ ፣ የልቡ ትርታ ሥነ ጽሑፍ በመሆኑ ፣ በሕክምናው ዘርፍ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ካገለገለ በኋላ ፣ ይህን የሠለጠነበትን ሙያ እርግፍ አድርጎ በመተው



ሙሉ ጊዜና ጉልበቱን ለኪነ ጥበብ መሥዋዕት ለማድረግ ብዕሩን አነሣ ። አንቷን ቼኾቭ ለሥነ ጽሑፍ የነበረው ፍቅርና አክብሮት እጅግ ከፍተኛና አብሮት ያደገ በመሆኑ ፣ ገና በትምህርት ቤት ሳለ ፣ ለወንድሞቹ ይጽፋቸው በነበሩት ደብዳቤዎች ግርጌ ፣ የሦስቱን ዕውቅ የብዕር ሰዎች ስም በማያያዝ ፣ “ ሼለር ሼክስፒሮቪች ገተ ” እያለ ይፈርም እንደ ነበር ተጽፏል ።

ቼኾቭ የሥነ ጽሑፍ ሙያውን የጀመረው ፣ ‘ ለኮሚክ ’ ጋዜጦችና መጽሔቶች አሥቂኝ ታሪኮችን እያዘጋጀ በማቅረብ ሲሆን ፣ እነዚህን ታሪኮች አጠቃልሎ የያዘው መጽሐፍ ታትሞ ከወጣ በኋላ ፣ በሕዝብ ዘንድ ለመታወቅ ከመብቃቱ ሌላ የቀልድና የጨዋታ ጽሑፎቹን ትቶ ፣ ዛሬ የምናውቃቸውን የበሰሉ ሥራዎቹን በማዘጋጀት ላይ አተኰረ ። በዚህም መሠረት፣የሕዝቡን ጉስቁልናና ትግል ፣ እንዲሁም የረጅም ዘመን ወግና ባህል ቀላል በሆኑ ዘዴዎች የሚያሳዩ በርካታ አጫጭር ታሪኮችና ድራማዎችን ለማቅረብ በቅቷል ። በይበልጥ ደግሞ በድራማ ረገድ የነበረው ቶስጥአ ፣ ታላላቅ ከሚባሉት ዘመናዊ ጸሐፌ ተውኔቶች ጐን የሚያሰልፈው ሲሆን በተለይም ፣ “ አጎት ቫንያ ” “ ሦስት እኅትማማቾች ” እና “ የባሕር አሞራ ” የተሠኙት ተውኔቶች ዛሬም በመላው ዓለም ተወዳጅ ከመሆናቸው ሌላ፡ በያገሩ ቋንቋና መድረክ በመቅረብ ላይ የሚገኙ ሕያው ሥራዎች ናቸው ።

ለዘመናዊ ድራማ ዕድገት ፣ በቀላሉ የማይገመት አስተዋጽኦ ያበረከተውና ፣ ጥልቅ መልእክት ያላቸው ጠንካራ አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍም በኩል ለሩሲያና ለዓለም ሥነ ጽሑፍ ባለውለታ የሚባለው ፣ ይህ የቀለም ሰው ጨዋታና ቀልድ የሚያዘወትር ፣ ከማንም ጋር በቀላሉ የሚግባባና ለማይረቡ ነገሮች የማይጨነቅ ፣ መብለጥለጥ

የማይወድ ተራ ሰው ነበር ። በመሆኑም ነው ጐርኪይ አንድ ጊዜ ስለርሱ ሲጽፍ ፡ “ ቼኾቭ በጣም ተራ ሰው ነበር ። ተራ ፣ ቀላል ፡ እውነትና ቀጥታ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሚወድ ቅን ሰው ነበር ። ዐልፎ ተርፎም ሰዎች ሁሉ እንደርሱ እንዲሆኑ የሚያደርግበትም የራሱ የሆነ ልዩ መንገድ ነበረው ” በማለት አስተያየት የሰነዘረው ።

አንቷን ቼኾቭ ፡ በ1901 የሩሲያ ታዋቂ ተዋናይት የነበረችውንና በድራማዎቹ ሁሉ በመሪ ሚናዎች የተሳተፈችውን አልጋ ክኒፐርን አግብቶ ትዳር ከመሠረተ ከሦስት ዓመታት በኋላ ፡ ባደረበት የሳንባ በሽታ ጠንቅ በ1904 በጀርመን አገር ዐረፈ ።



# በሽለቆው መኻል

ኡክሊየቮ በሸለቆ መኻል የተወተፈች መንደር ናት ። ራቅ ብሎ ከሚገኘው የባቡር ጣቢያና አውራ ጐዳናው ላይ ሆነው ሲመለከቱ የሚታይ ነገር ቢኖር ፣ የቤተክርስቲያኑ ጉልላትና የጥጥ ማባዘቻዎቹ ጢስ መውጫዎች ብቻ ናቸው ። ማዶ ማዶውን የሚያልፉ መንገደኞች ባሻገር የሚያዩዋት መንደር ማን እንደምትሠኝ ሲጠይቁ የሚሰጣቸው መልስ ፡ “ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሞቶ ቀብሩ እየተፈጸመ ሳለ ፡ የቤተክርስቲያኑ ገበዝ ከዓሣ ዕንቁላል የተሠራውን ‘ካቪያር’ * የተባለ የለቀስተኛ ምግብ ለብቻቸው የበሉበት ሥፍራ ነው ” የሚል ነበር ።

ታሪኩ እንደዚህ ነው ። የመንደሯ የእህል ወፍጮ ባለቤት ለሆነው ኩስትየኰቭ የሚባል ከበርቴ የሚዛመድ ሰው ይሞትና ፡ ቀብሩ በሚፈጸምበት ወቅት የሽማግሌው ገበዝ ዐይኖች ለለቀስተኛዉ ተብሎ ከተዘጋጁት የተለያዩ ጣፋጭ ምግቦች መካከል በገንቦ በተቀመጠው ካቪያር ላይ ያርፋሉ ። ያለ ምንም ማመንታት ያን ከዓሣ ዕንቁላል የተሠራ ምግብ ይያያዙታል ። በሥፍራው የተሰበሰቡት ሰዎች ቢጐሽሚቸው ፣ ቢጐንትሏቸው ፡ በልብሳቸው እጅጌ ጐትት ቢያደርጓቸው ገበዙ ግን ወይ ፍንክች ! አንዱንም ነገሬ ሳይሉ ምግቡን በመስገብገብ መብላታቸውን ይቀ

* ካቪያር ፡ ከትልልቅ ዓሣዎች በተለይም ስተርጀን ከሚባለው ዓሣ ዕንቁላል የሚሠራ ጣፋጭ ምግብ ነው ።

ጥላሉ ። እንዲያም ብለው እንስራው ውስጥ የነበረውን
አራት ነጥር የሚሆን ካቪያር ምናምኒት ሳያስተርፉ ያሚ
ጥጡታል ።

በእርግጥ ድርጊቱ ከተፈጸመ አያሌ ዓመታት ዐል
ፈዋል ። ገበዙም ከሞቱ ቆይቷል ። ግን የዚያን ዕለቱን
ሁኔታ መንደርተኛው ሊረሳው አልቻለም ። ልክ ትናንት
እንደ ተፈጸመ አድርጎ ያስታውሰዋል ። የኡክሌየቮ መን
ደር አዘውትሮ አዲስ ነገር ስለ ማይታይባት ፣ ነጋም ጠባ
ያው የተለመደ አደዳቢ ኑሮ ስለሚገፋባት ይሁን ፣ ወይም
ይህ ከዐሥር ዓመታት በፊት የተፈጸመ እዚህ ግባ የማይባል
ድርጊት ከምንም ነገር ይበልጥ የመንደርተኛውን ልብ ስለነ
ካው ፣ ተለይቶ ባይታወቅም፣ የኢክሌየቮ መንደር ስም ሲነሣ
አብሮ የሚወሳው ይኸው የገበዙና የካቪያሩ ጉዳይ ነበር ።

በመንደሯ ሰዎች ዘንድ ትኩሳት ፣ በየቦታው ደግሞ
ጭቃ ከዓመት እስከ ዓመት ጠፍቶ አያውቅም ። በበጋው
ወቅት ሳይቀር ፣ በተለይ ትልልቅ ዛፎች ጥላቸውን በሚያ
ነጥፉበት በየመኖሪያ ቤቶቹ አጥር ጥግ እንደ ረግረግ ያለ
ወልቅ ማየት የተለመደ ነው ። ከፋብሪካው የሚወጣው ቆሻሻ
ቅርናትና በጥጥ ማባዘቻዎቹ ውስጥ የሚገለገሉበት አሲ
ቲክ አሲድ ሽታ ከመንደሯ አየር ተለይቶ አያውቅም ።
ወጣ ብሎ የተተከሉት ሦስቱ የጥጥ ማባዘቻዎችና የቆዳ
ማልፊያው ፋብሪካ መጠናቸው አነስተኛ በመሆኑ ፣ ሁሉም
በአንድነት ተጣምረው ከአራት መቶ ሠራተኛ በላይ የመ
ቅጠር ዐቅም የላቸውም ። ከቆዳ ማልፊያው የሚወጣው
ቆሻሻና እጣቢ የወንዙን ውሃ እያግማማ መስኮቹንም ስለ
ሚበክላቸው ፣ የአካባቢው ከብቶች ዘወትር በቁርባ በሽታ
ይሠቃያሉ ። በዚሁ ሳቢያ የቆዳ ማልፊያው እንዲዘጋ ትእ
ዛዝ ተሰጥቶም ነበር ። ግን ውስጥ ውስጡን ከመሥራት
ያገደው የለም ። የአካባቢው ፖሊስ ሹምና የወረዳው ጤና



መኮንን በየወሩ ሊያንዳንዳቸው ዐሥር ዐሥር ሩብል ስለ
ሚከፈላቸው ፣ የፋብሪካውን ሥራ መቀጠል እያዩ እንዳ
ላየ ዝም ብለዋል ።

በኡክሌየቮ መንደር ውስጥ ከጡብ ተሠርተው የቆር
ቆሮ ክዳን ያላቸው ቤቶች ሁለት ብቻ ናቸው ። አንደኛው
የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ያለበት ሲሆን ፣ ሁለተ
ኛውና ከቤተክርስቲያኑ ባሻገር ተኰፍሶ የሚታየው ባለሁ
ለት ፎቅ ሕንፃ ደግሞ የግሪጐሪ ፔትሮቪች ፂቡኪን ንብ
ረት ነው ።

ግሪጐሪ ፔትሮቪች ፣ አንድ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ
አለው ። የምግቡ ሸቀጥ ለይስሙላና ለሽፋን ያህል እንጂ
ዋናው ንግዱ ግን ሌላ ነበር ። ቮድካ ፣ ቁም ከብት ፣ ቆዳ ፣
እህል ፣ ዓሣማ . . . ብቻ ተሽጦ ገንዘብ የሚያስገኝ ይሁን
እንጂ ፣ በዚያ ሱቅ ውስጥ ከፀሐይ በታች የማይሸጥ ፣ የማይ
ሸቀጥ ነገር የለም ለማለት ይቻላል ። ለምሳሌ “ ማግፒ”
የምትባለው ወፍ ላባ በውጭ አገር በጣም ተፈላጊ ሆኖ
በነበረበት ጊዜ ፣ ግሪጐሪ ፔትሮቪች ሁለቱን ላባዎች በሠ
ላሳ ኰፔክ ይቸረችር ነበር ። በዚህ ላይ ሳንቃ ይገዛል ፤ ገን
ዘብ በወለድ ያበድራል ። በደፈናው ግሪጐሪ ፔትሮቪች
ዕረፍት ብሎ ነገር የማያውቅ ፣ ገንዘብ የሚያገኝበትን አዲስ
ቀዳዳ ለመሽንቆርና አንዲት ኰፔክ ለማትረፍ የሚያስች
ለውን ብልሃት ለመቀየስ የማይታክት ብርቱ አዛውንት
ነበር ።

የሁለት ወንድ ልጆች አባትም ነው ። በፖሊስ ሠራ
ዊት ውስጥ የመረጃ ክፍል ባልደረባ ሆኖ የሚያገለግለው
አንጋፋው አኒሲም በሥራው የተነሣ በሌላ ሥፍራ ስለሚ
ኖር ፣ ብዙ ጊዜ በአባቱ ቤት አካባቢ አይታይም ። ትንሽየው
ስቴፋን ግን በንግዱ ሙያ ተሠማርቶ አባቱን ይረዳል ። ብቻ

ጆሮው በመደንቆሩና በሽታ ያጠቃው ለንቋሳ ብጤ በመ
ሆኑ ሥራው እምብዛም የሚያረካና የሚያስተማምን አል
ነበረም ። ከሱ ይልቅ የደስ ደስ ያላት ሚስቱ አክሲ
ኒያ ቀልጣፋና ንቁ ናት ። በየሰንበቱና የቅዱሳን መታ
ሰቢያ በዓላት በሚከበሩባቸው ቀናት የሴቶች ጌጠኛ ባር
ኔጣ ማድረግና ዣንጥላ መያዝ የምታዘወትረው አክሲኒያ
ሠርቷ የማይደክማት ብርቱ ታታሪ ነበረች ። ወፍ ሲን
ጫጫ ተነሥታ እስከ ምሽት ሽቅብ ቁልቁል ስትል ፣ የቤ
ቱን ሥራ በየመልኩ ስታከናውን ትውላለች ። ከፊት ለፊቷ
በኩል ቀሚሷን ወደ ላይ ሰብስባ መቀነቷ ውስጥ ሻጥ በማ
ድረግ ፣ ቁልፎቿን እያቅጨለጨለች ከዋናው ዕቃ ቤት
ወደ ምድር ቤቱ መጋዘን ፣ ከምድር ቤቱ መጋዘን ወደ ሱቁ
ስትመላለስ በሚያያት ጊዜ ፣ አማቷ ግሪጎሪ ፔትሮቪች
ልቡ በደስታ ይረካል ። አክሲኒያ በሥራ ተጠምዳ ወዲያ
ወዲህ ተፍ ተፍ ስትል በሚያያት ጊዜ ፣ ዐይኖቹ በደስታ
ስሜት ፈካ ይሉና የሴቶችን ውበት መረዳትና ማድነቅ
በማይችለው ደንቆሮ ልጁ ፋንታ ፣ አክሲኒያን ለትልቅየው
ባለማጋባቱ ስለፈጸመው ስሕተት በልቡ ክፉኛ ይቆጨዋል።
የአክሲኒያ ባል መሆን የሚገባው አኒሲም ሆኖ ሳለ ፣ ከስ
ቴፋን በማጋባቱ ይነደዋል ።

ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች ቤተሰባዊ ኑሮን የሚ
ወድ ሰው ነው ። በዓለም ላይ ከቤተሰቡ የሚበልጥበት ነገር
የለም ። ለአንጋፋው ልጁና ለምራቱ ደግሞ የተለየ ፍቅር
ነበረው ። አክሲኒያ ፣ ስቴፋንን ካገባች በኋላ ፣ የንግድ ሰው
መሆኗን ለማስመስከር እምብዛም ጊዜ አልፈጀባትም ።ከሱቁ
ደንበኞች መካከል ዱቤ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን
ለመለየት አዳጋች አልሆነባትም ። የቤቱን ቁልፎች በሙሉ
የምትይዘው እሷው ነበረች ። ከእጇቿ ወጥተው አያውቁም፤
ስለማታምነው ለባሏ እንኳን አትሰጠውም ። ፋታ ስታ



ገኝ የሒሳብ ማስሊያውን ዕንጨት እያንኳኳች ወጪና ገቢ
ውን ትሠራለች ። ደግሞ እንደ ማለፊያ ገበሬ የፈረሶቹ መና
መሟላቱንና በሚገባ መያዛቸውን ትከታተላለች ። አክ
ሲኒያ ፍልቅልቅ ናት ። ሣቅና ጨዋታ አይለያትም ። ሽማ
ግሌውም የምትሠራውን አይቶና የምትናገረውን ሰምቶ
ለርሷ ያለውን አድናቆት ሳይገልጥ የዋለበት ቀን አይታ
ሰብም ።

“ ምራት ይሏል ይቺ ናት እንጂ ! ጐሽ የኔ ቆንጆ ! ”
እያለ ድምፁን ዝቅ አድርጐ ያጉተመትማል ።

የመጀመሪያ ሚስቱ በመሞቷ ለጥቂት ዓመታት በብ
ቸኝነት ቢኖርም ፣ ስቴፋንና አክሲኒያ ትዳር ከመሠረቱ
በኋላ ግን ፣ ጦሴ ወንድነቱን ሊቋቋመው ባለመቻሉ ሁለተኛ
ሚስቱን አገባ ። ከኢክሊየቮ ሠላሳ ኪ. ሜ. ያህል ራቅ በሚል
ሥፍራ የምትኖር ቫርቫራ ኒኮላየቭና የምትባል ልጃገረድ
ነበረች የተመረጠችለት ። ቫርቫራ ከወጣትነት ዕድሜ
በመጠኑ የተላለፋት ትሁን እንጂ ፣ ደማምነቷ ገና ለዛውን
አላጣም ። የደስ ደስ ያላት ሸጋ ነበረች ። ጋብቻቸው ተፈ
ጽሞ ፎቁ ላይ ወደ ተዘጋጀላት ክፍል ስትገባ ፣ በመስኮቶቹ
ላይ አዲስ መስታወት እንደ ተገጠመ ሁሉ ቤቱ በብርሃን
ተመላ ። በቅዱሳንና በሰማዕታት ሥዕሎች አጠገብ ሻማ
ዎች ተለኮሱ ። በየጠረጴዛዎቹ ላይ እንደ በረዶ የነጡ ልብ
ሶች ተነጠፉባቸው በየመስኮቶቹ መቃኖች ላይ ፍም የመ
ሳሰሉ ቀያይ አበቦች ተቀመጡ ። ቫርቫራ ኒኮላየቭና በተ
ፈጥሮዋ ርኅሩኅና ቸር ከመሆኗ ሌላ ፣ ማራኪ ፈገግታም የተ
ሰጣት ነበረች ። ፈገግ ባለች ቁጥር በቤቱ ውስጥ የሚገኘው

ነገር ሁሉ አጸፋውን በፈገግታ የሚመልስላት ይመስል ጀመር ። ቫርቫራ የቤተሰቡ አካል ከሆነችበት ጊዜ አንሥቶ ነዳያንና ባሕታውያን በግሪጎሪ ፔትሮቪች ግቢ ማየት ተዘውተረ ። በጠጪነታቸው የተነሣ ከፋብሪካዎቹ የተባረሩ ፣ በሽታ አድቅቋቸው ጉንጮቻቸው የተጣበቀ ሰዎች ፣ የሳል ድምፅና የኢክሊየቮ ሴቶች አሳዛኝ ልመና በየዕለቱ በቅጥር ግቢው ይሰማ ጀመር ። ከግሪጎሪ ፔትሮቪች ጋር እንደ ተጋቡ ሰሞን ቫርቫራ የሰዎቹን ችግርና ሥቃይ ለማቃለል የምትሞክረው ፣ ገንዘብ ፣ ዳቦ ፣ ውራጅ በመስጠት ነበር ። እያደር በቤቱ ውስጥ ያላት ስፍራ በሚገባ መደላደሉንና መቆናጠጧን ስታረጋግጥ ግን፣ ልዩ ልዩ ዕቃዎች እየደበቀች ከሱቅ በማውጣት መመጽወቷን በሰፊው ቀጠለች ። አንድ ቀን ሁለት ባኮ ሻይ ቅጠል ስትወስድ ደንቆሮው ስቴፓን ይመለከታል ። በነገሩ በጣም በመበሳጨቱ ፣

“ እናት ፣ ሁለት ባኮ ሻይ ቅጠል ወሰዳለች ። ወጪውን በየትኛው ሒሳብ ነው የምይዘው ?” በማለት አባቱን ይጠይቃል ። ሽማግሌው ግን መልስ አልሰጠውም ። ለጥቂት ደቂቃዎች ቅንድቡን ከፍ ዝቅ እያደረገ በጸጥታ ከቆመ በኋላ ፣ ሚስቱን ለማነጋገር ወደ ፎቁ ወጣ ።

“ ማናቸውንም የምትፈልጊውን ዕቃ ከሱቁ እንዳሻሽ መውሰድ ትችያለሽ ። አይዞሽ አትፍሪ ! ያማረሽን ሁሉ ለማድረግ አታመንቺ ፤ ቤትሽ ነው ” አላት በፍቅር አነጋገር ። የቫርቫራ ደግነት ፣ ቸርነቷና ልጨኝነቷ አዲስና አስገራሚ የሆነ ልዩ ባሕርይ የሚታይበት ዐይነት ነው። በቅዱሳን ምስሎች አጠገብ እንደምታኖራቸው መብራቶችና መስኮቶቹ ላይ እንደምታስቀምጣቸው ቀያይ አበቦች ፣ እስደሳችና መንፈስን የሚመስጥ ነበር ።



በፔትሮቪች ቤተሰብ ዘንድ እያንዳንዱ ቀን በዋዛ ያልፋል ማለት ዘበት ነው ። ጎህ ሳይቀድ ተጀምሮ እስከ ምሽት በማያቋርጥ ሥራና ሽር ጉድ ይያዛል ። ገና ጀምበር ከመሥረቋ በፊት ስትታጠብና ከኃይለኛ ድምፅ ጋር አፍንጫዋን ስታጸዳ ይሰማል ። ማዕድ ቤት ውስጥ ደግሞ የሻይ ማፍያው ‘ ሳሞቫር ’ እሳቱ ተያይዞ እየተንተከተከ ሲያስገመግም ፣ በዚያ ቤት ላይ ወደፊት አንዳች መዓት እንደሚወርድ የሚተነብይ ይመስላል ። በማለዳ ሽማግሌዉ ግሪጎሪይ ፔትሮቪች ረጅም ጥቁር ኮቱን ደረብ አድርጎ ፣ ከጥጥ የተሠራ ሱሪውን አጥልቆና በደንብ ተወልውሎ የሚያንጸባርቅ ቦት ጫማውን ተጫምቶ ፣ በቤቱ ውስጥ ጐርደድ ጐርደድ ሲል በአገሩ ሰዎች ዘንድ ተወዳጅ በሆነ የባህል ዘፈን ውስጥ የሚጠቀሰውን አማት ይመስላል ። ወዲያው ሱቁ ይከፈታል ። ፀሐይ ብርሃኗን በደንብ ማዳረስ ስትጀምር ለግልቢያ ውድድር የሚሆን ዐይነት ጋሪ ወደ ቤቱ በረንዳ ይቀርብና ፣ ሽማግሌው ትልቁን ባርኔጣውን ጆሮው ድረስ ዝቅ አድርጎ በማጥለቅ ቀልጠፍ ብሎ ይሣፈራል ። እንዲያ ባለው ወቅት ሁኔታውን ለተመለከተ ፣ የሃምሳ ስድስት ዓመት ሰው ነው ብሎ ለመገመት ሆነ ለማመን ያስቸግራል ። ተከትለውት ከቤት የሚወጡት ሚስቱና አክሲኒያ በረንዳው ላይ ቆመው ይሸኙታል ። በሚገባ የተቦረሸውን ኮቱን ዝቅ አድርጎና ሦስት መቶ ሩብሉን ከስክሶ የገዛው አንዳች የሚያክል ጥራች ፈረሱ በሚጎተተው ጋሪው ላይ ተሰቅንና ለመጓዝ በሚነሣ ጊዜ፣ማንም የውጪ ሰው እንዲያነጋግረው አይፈልግም ። በተለይ አቤቱታና ልመና የያዙ ገበሬዎች አጠገቡ እንዲደርሱ አይሻም ። እንዳጋጣሚ ሆኖ አንድ ባለ ጉዳይ ዋናው በር ላይ ቆሞ ሲጠብቀው ከተመለከተ ፣

“ምን ፍለጋ ነው እዚህ የተገተርከው? ሒድ ከዚህ!” በማለት ይጮህበታል ፣ የብስጭት ስሜት በተቀላቀለበት አነጋገር ።

ዶጅ ጠኘው የለየለት ነዳይ ከሆነ ደግሞ ፤

“እግዜር ይስጥልኝ!” በማለት ከሩቅ ያሰናብተውና ወደ ጉዳዩ ያመራል ። እሱን ተከትሎ እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባልም የየድርሻውን ለማከናወን በየፊናው ይሠማራል ።

ቫርቫራ ፣ ጠየም ባለ ቀሚሷ ላይ ጥቁር ሽርጧን ጣል ታደርግና ቤቱን ታጸዳለች ፤ ከዚያም ወደ ማዕድ ቤት ገብታ ሠራተኞቹን ታግዛለች ። አክሲኒያም ወደ ሱቁ ትሔድና ከባንኮኒው በስተጀርባ በመቆም ደንበኞችን ማስተናገዱን ትቀጥላለች ። ጠርሙሶች ይንካካሉ ፤ ይንገጫገጫሉ ፤ ሳንቲሞች ይቅጨለጨላሉ ። የአክሲኒያ ሣቅ በረጅሙ ይሰማል ፤ ወይ ስድቧና ሽሙጧ ያስተጋባል ። ያጭበረበረቻቸው ደንበኞች የንዴት ቁጣና ልፍለፋ የምድር ግቢውን አየር ያስጨንቀዋል ። በስውር የሚካሔደው የዕለቱ የቮድካ ንግድ የተጀመረ መሆኑ በግልጥ ያስታውቃል ። ደንቆሮው ስቴፓንም ሱቁ ውስጥ ተጐልቶ ያንጐላቻል፤ወይም ኮፍያውን ሳያደርግ ወደ ውጭ ይወጣና አንዴ በአካባቢው የሚገኙትን ጐጆዎች እየቃኘ ፣ አንዴም ወደ ሰማዩ እያንጋጠጠ በመንገዱ ላይ ይንቀዋለላል ። በቤተሰቡ ዘንድ በቀን ውስጥ ስድስት ጊዜ ያህል ሻይ ይጠጣል ። ምግብ አራት ጊዜ ይበላል ። የማታ ማታ፣ የዕለቱ ሽያጭ በመዝገብ ላይ ከሠፈረ በኋላ ፣ ሁሉም ወደየመኝታው ያመራና እንቅልፉን ይያያዘዋል ።

በኡክሊየቮ መን[illegible] ያሉት ሦስቱ የጥጥ ማባዘቻዎች ህሪሚን ትልቁ ፣ ህሪሚን ትንሹ ፣ ኩስት የኩቭ ከሚባሉት



ባለንብረቶቻቸው መኖሪያ ቤቶች ጋር በስልክ መስመር የተገናኙ ናቸው ። በመጀመሪያ ጊዜ ስልክ ወደ መንደሯ እንደገባ፣ መሥመሩ ወደ ወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤትም ተዘርግቶ ነበር ። ግን አገልግሎቱ ለረጅም ዕድሜ አልታደለም ። በመሣሪያው ውስጥ በረሮዎችና ሌሎችም ጥቃቅን ነፍሳት እየተሠገሠጉበት ስላስቸገሩ ፣ ብዙም ሳይቆይ ሥራውን አቋረጠ ።

የህሪሚን ትልቁና የህሪሚን ትንሹ ቤተሰቦች ፣ ዘወትር አምባጓሮ እንደ ፈጠሩና ወደ አደባባይ እንደ ተጓተቱ የሚኖሩ ናቸው ። የህሪሚን ትንሹ ቤተሰቦች ደግሞ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ፣ እርስ በርሳቸው እየተጣሉ መካሰስም ዐመላቸው ነው ። የነዚህ ከበርቴ ቤተሰቦች ጠብና አተካሮ በሚቀሰቀስ ጊዜ ፣ የጥጥ መዳመጫዎች ሥራቸውን ያቆሙና ለወር ፣ ጫን ሲልም ለሁለት ወራት ይቦዝናሉ ። ጭቅጭቁ ጋብ ብሎ ዕርቅ እስኪወርድ ድረስ ሁኔታው ለኢክሌየቮ መንደርተኞች ሐሜታና ወሬ ያንድ ሰሞን አርዕስት ይሆንላቸዋል ። በተገናኙበት ፣ በተሰበሰቡበት ሁሉ ወሬውን ማመንዠክ ነው ። ወሬውን ደጋግሞ ማላመጡ ደግሞ ፣ እንደ መዝናኛም ነው — ለኢክሌየቮ መንደርተኞች ።

በዓላት በሚውሉባቸው ቀናት ፣ የህሪሚን ትንሹ ቤተሰቦች በጋሪና በሠረገላ እየሆኑ ሽርሽር የመውጣት ፣ በመንደሯ መኻል የመጋለብ ልምድ አላቸው ። እንዲህ ባሉት ቀናት አክሲኒያ የክት ልብሷን አጥልቃና በሚቻላት ሁሉ ተከሽና በመውጣት ሱቁ ደጃፍ ላይ መንጐራደድ በመዷ ነው ። ወዲያው የህሪሚን ትንሹ ሰዎች ይመጡና ፣ በሠረገላቸው አሣፍረዋት እብስ ይላሉ ። ሲወስዷት ግን በፈቃድና ስምምነት ሳይሆን በግድ እንዳደረጉት አስመስለው ነው ። ሽማግሌው ፔትሮቪችም አዲሱን

ፈረሱን ለማሳየት ያህል ፣ ሚስቱን ቫርቫራን ከጐኑ ሻጥ
ያደርግና በበኩሉ ሽርሽር ይወጣል ።

እምሽት ላይ ከሽርሽሩ መልስ ፣ መንደረተኛው ሁሉ
በየአልጋው ላይ ከሠፈረ በኋላ ፣ ውድ ከሆነ አኰርዲዮን
የሚመነጭ መልካም ዜማ ከሀሪሚን ትንሹ መኖሪያ በኩል
እየተንቆረቆረ በአየሩ ይናኛል ። የመንደረተኛውን በያ
ለበት የሚቆዝም ልብ በሐሤት እያደሰ ስሜቱን በመኩር
ኰር ኢክሌየሮንም ልዩ መልክ ያጐናጽፉታል ።

የግሪጐሪ ፔትሮቪች አንጋፋ ልጅ አኒሲም አንዳንዴ
ካልሆነ በስተቀር ወደ ዘመዶቹ ዘንድ አዘውትሮ ብቅ አይ
ልም ። ለያውም ትልልቅ በዓላትን አንተርሶ ነው ። ከአንድ
ገጽ የማይበልጥ ደብዳቤና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ግን ባለ
ማቋረጥ ይልካል። ቆሎ በመሰለ የእጅ ጽሑፍ ተዘጋጅተው
የሚላኩት ደብዳቤዎቹ የአቤቱታና የልመና ዐይነት ቃና
ተለይቷቸው አያውቅም ። አኒሲም በንግግር ወቅት የማይ
ገለገልባቸው አገላለጾችና ዘይቤዎችን በደብዳቤው ላይ
አብዝቶ ይጠቀምባቸዋል ። “ የተከበራችሁ ዘመዶቼ !
ፍላጐታችሁን ለማርካት ይበጃል በማለት ፣ ከዚህ ደብ
ዳቤ ጋር አንድ ባኮ ልዩ ዐይነት የሻይ ቅጠል ልኬላች
ሁዋለሁ ” ሲል ይጽፋል ። እያንዳንዱ ደብዳቤ የሚደ
መደመውም አኒሲም ፂቡኪን በሚል ፊርማ ይሆንና
ከሥሩ ደግሞ ፣ “የምስጢር ሠራተኛ ” የሚሉ ቃላትን
ያክልበታል ።

ደብዳቤዎቹ እንደ ደረሱ ፣ አንድ ሰው ድምፁን ከፍ
አድርጎ ለመላው ቤተሰብ ያነባል ። ደብዳቤዎቹ አንድ
ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ በተለያዩ ጊዜያት ይነበባሉ፤
ይደመጣሉ ። በቃላቶቹ ትርጉም ልቡ የሚነካው ሽማግሌ
አባት ፣ በተመስጦ ካዳመጠ በኋላ ፣ “ እንግዲህ ምን ያደ
ርጋል ! ቤቱ ዐርፎ ሊቀመጥ አልቻለም ። ትምህርት በል



ጦበት ከተለየን ምን ይሏል ፤ሁሉም የራሱን ምርጫና መን
ገድ ነው የሚከተል ። ይሁና መቼስ ! ” ይላል ፣ በኃይለኛ
ውስጣዊ ስሜት ፊቱ ፍም መስሎ ።

አንድ ቀን ፣ የሁዳዴ ጾም ከመግባቱ ጥቂት ቀናት
ቀደም ብሎ ነው ፣ በረዶ የቀላቀለ ኃይለኛ ዝናብ ይጥላል።
ሽማግሌውና ቫርቫራ መስኮት አጠገብ ቆመው ወደ ውጭ
ሲያስተውሉ ፣ አንድ በበረዶ ላይ የሚንሸራተት ጋሪ ከባ
ቡር ጣቢያው አቅጣጫ መጣና ወደ ግቢው ዘው አለ ።
አኒሲምን የያዘ ነበር ። በዚያን ወቅት ይመጣል ብሎ የገ
መተ አንድም ሰው አልነበረም ።እንደ ወትሮው ደስተኛና
ረጋ ያለ መስሎ ለመታየት እየሞከረ ወደ ቤት ገባ ። ግን
ለአንድ አፍታ እንኳን ጸጥ የማይል ፍርሃት በውስጡ
ተደብቆ እየተናነቀው መሆኑ ያስታውቅ ነበር ።

አኒሲም ፣ ዘመዶቹ ዘንድ በከረመበት ሰሞን ፣ ወደ
መኖሪያ አካባቢው ለመመለስ እንደ ወትሮው የመቻኮል
ምልክት ባለማሳየቱ ፣ ከሥራው ተሰናብቶ ይሆናል የሚል
ጥርጣሬ ቤተሰቡን እንደ መሞከከር ቃጥቶት ነበር ። በአ
ኒሲም ያልተጠበቀ ጉብኝት ከማናቸውም ይበልጥ የተደሰ
ተችው ቫርቫራ ፣ ብልጣ ብልጥ በሆኑ ዐይኖቿ ሠረቅ አድ
ርጋ ትመለከተውና በረጅሙ ተንፍሳ ፣ ጭንቅላቷን ከነ
ቀነቀች በኋላ ፣

“ በእግዜር ይሁንባችሁና እንዲህ ያለው ነገር እን
ዴት በዝምታ ይታያል ! ልጁ ሐያ ሰባት ዓመት መሙላቱ
ነው ፤ ግን ገና ወንደላጤ ! አበስኩ ገበርኩ ! ” ትላለች ።

አኒሲም ወደ አባቱ ቤት ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ቫርቫራ
ከሽማግሌውና ከአክሲኒያ ጋር በቆይታ ማንሾካሾክ ማዘ
ውተሯን ልብ ብሏል ። አንዳች ምስጢራዊ ሤራ በመ
ተብተብ ላይ እንደሆኑ በሁሉም ገጽ ላይ ቁልጭ ብሎ
ይታያል ። ሤራው አኒሲምን ትዳር የማስያዝ ነበር ።

ተዶልቶም አልቀረ ፤ በመጨረሻው አኒሲም ሚስት
እንዲያገባ ተወሰነ ። “ ታናሽ ወንድምህ ትዳር ከመሥረተ
ብዙ ዓመታት ዐልፈዋል ” አለች ቫርቫራ ። “ አንተ ግን
ለሽያጭ ወደ ገበያ እንደወጣ አውራ ዶሮ እስከ ዛሬ ብቸኛ
ነህ ። የብቸኝነት ኑሮ ፋይዳ እንደሌለውና መቅኖ ቢስ
እንደሚያደርግ ደግሞ አንተም ታውቀዋለህ ። እና ፡ እባ
ክህ ሚስት አግባ አኒሲም ። ከዚያ በኋላ ከፈለግህ ለብ
ቻህ ወደ ሥራህ መመለስ ትችላለህ ። ሚስትህ እኛው
ዘንድ ቆይታ በሥራ እያገዘችን ትኖራለች ። ሕይወትህ
መላ የለውም ልጄ ። ሕይወትን ሥርዓትና መልክ ማስ
ያዝ ማለት ምን እንደሆነ ዘንግተኸዋል ። የከተማ ልጆች
ስትባሉ እንዲያው ነገራችሁ ሁሉ ቅጥ የለውም ” አለ
ችው እንጀራ እናቱ ቫርቫራ ። አኒሲም አልተቃወመም ።

ከግሪጎሪ ፔትሮቪች ቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው
ለጋብቻ ቆርጦ ሲነሣ ፡ መቼም ባለጸጎች ናቸውና ከአካባ
ቢው ኮረዶች መካከል ብልጫ ያላት ቆንጆ ናት የምትፈ
ለግላት ። ለአኒሲምም ይህ ቀረሽ የማትባል ልጃገረድ ተገኘ
ችለት ። አኒሲም ግን ፡ እምብዛም ማራኪ ሰው አልነበረም ።
ቁመቱ አጭር ከመሆኑ ሌላ አካሉም ደካማ ነው ። ሁልጊዜ
ወደ ውጭ የሚገፉቸው ይመስል ፡ ጉንጮቹ ብቻ ወፍራም
ናቸው ። ጮሌና ምንም ነገር የማያመልጣቸው ዐይኖቹ
ዘወትር ፈጠጥ ብለው ስለሚታዩ ፡ ከቶውንም የሚረግቡ
አይመስሉም ። በዕድሜው ልጅነት የተነሣ ግጥም ባለ
ማለቱ ፡ እዚህም እዚያም ተበታትኖ የበቀለው ቀይ ጢሙን
በተበሳጨና በተናደደ ጊዜ ፡ ወደ አፉ ውስጥ እያስገባ በጥ
ርሶቹ የመቀነጣጠብ ዐመል አለው ። መጠጥ ይወዳል ፤
ንፍሱ ነው ። አዘውትሮ ለመጠጣቱ አቋሙና ገጹ ጉልህ
ምስክሮች ናቸው ። ይህም ሆኖ ግን ፡ ሚስት ተፈልጎ እንደ
ተገኘለትና ቆንጆ ልጅ መሆኗ ሲነገረው ፡



“ ምናለ ታዲያ ደግ ነዋ ! እኔም ብሆን እኮ አላሳፍ
ርም ። ወይም ማስፈራርቾ ዐይነት አይደለሁም ። ደግሞ
ለኛ ቤት ቁመናና መልክ ማነው እንከን የሚያወጣ ! ”
ከማለት አልተቆጠበም ።

የቱርጎየቮ መንደር አቀማመጥ ለከተማው ብዙም
የራቀ አይደለም ። የመንደሯ ግማሹ ክፍል እየተለጠጠ
ከከተማው ጋር መዋሐድ ከጀመረ ውሎ አድሯል ። ገሚሱ
ክፍል ግን ፡ ገና የመንደር ባሕርይውን እንደ ያዘ ነው ። ከከ
ተማው ጋር መቀላቀል በጀመረው ክልል ውስጥ ባሏ የሞ
ተባት አንዲት ሴት ፡ ከችግረኛ እኅቷ ጋር የራሷ ንብረት
በሆነ ቤት ውስጥ ትኖራለች ። እኅቷ በጣም ችግረኛ
በመሆኗ በቀን ሙያተኛነት ተቀጥራ ትሠራለች ። ሴት
ልጅዋ ሊፓም አብራት ተቀጥራለች ። ሊፓ ፡ በጣም
የተዋበች ወጣት ናት ፡ እዚህ ጉደለሽ የማትባል ! አን
ከን የማይወጣላት ። ሰዉ የቁንጅናዋን ዝና በአካባቢ
ውና በከተማው ውስጥ በሰፊው ማውራት ከጀመረ የቆየ
ቢሆንም ፡ የሚከጅሏት ሁሉ እሷን እንዳይጠይቁ ሲያግዳ
ቸውና ከፍላጎታቸውም ሲያርቃቸው የኖረው ምንም
ማካካሻ የሌለው ድኅነቷ ብቻ ነበር ። እንዲያውም እንደ
አካባቢው ነዋሪ ግምት ከሆነ ፡ ሊፓን ለጋብቻ የሚጠይቅ
ቢኖር ምናልባት ሚስቱ የሞተችበት ፡ ዕድሜውን ያሟ
ጠጠ አዛውንት ብቻ ነው ። ለዚያውም ሥርግና ምላሽ ብሎ
ጣጣ ሳይኖር እንደ ዕቃ ወስዶ እቤቱ ሊያስገባት እንደሚ
ችልና እሷም ሆነች እናቷ የዕለት ራታቸውን በቀላሉ በማ
ግኘታቸው እያመሰገኑ ከመኖር እንደማያልፉ ነበር በድ
ፍን መንደሩ የሚወራው ። ቫርቫራም ስለ ሊፓ ሁኔታ
ሰፊ ጥናት ስታደርግና ስታጠያይቅ ፡ ከአማጮቹ ጋር በመ
ወያየት ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ስታጣራ ከቆየች በኋላ ነበር
ወደ ቱርጎየቮ የሔደችው ።

የማጫው ሥነ ሥርዓት የተከናወነው በሊፓ አክስት ቤት ውስጥ ነበር ። ምግብና መጠጥ ተዘጋጅቶ ቀርቧል ። ሊፓ ፣ ለዚያኑ ዕለት ሲባል የተሰፋላትን ሮዝ ቀለም ያለው አዲስ ቀሚስ ለብሳ የእሳት ላንቃ የመሰለ ቀይ ጥብጣብ በዘንፋላው ጠጉሯ ላይ ሸብ አድርጋለች ። ሊፓ አጥብቀው ቢይዟት እንክሽ የምትል ዐይነትና ዘንግ የመሰለች ሎጋ ናት ። በዕለት ሥራዋ የተነሣ ለኃይለኛ ፀሐይ ተጋልጣ ስለምትውል ፣ ቆዳዋ ቯንጣት ይልቅ ወደ ቅላት ያደላል ። የፊቷ ቅርጽ የደስ ደስ ያለው ለስላሳና ረቂቅ ነው ። ሊፓ ማንንም የምታጓጓ ቀዘባ ፣ ሲያዩዋት የምታስጐመጅ ጥን ቅሽ ናት ። ከማፈር ከመጨነቅ ጋር የተዋሐደ ፈገግታ በከንፈሯ ላይ ያንዣብባል ። አስተያየቷ የሕፃን የመሰለ ፣ ሁሉን የመጠየቅና ሁሉን የማመን ዐይነት ነው ።

ሊፓ ፣ ጡቶቿ እንኳን በደንብ ያላጐጠጐጡ ወጣት ትሁን እንጂ ፣ ባካባቢው ደንብና ወግ መሠረት ግን ለጋብቻ ደርሳለች ። ሊፓ ፣ የውበት መንበር ነበረች ። ይህን አሌ የሚል አይገኝም ። በአካሏ ላይ ውበቷን ትንሽ ይቃረናል የሚባል ነገር ቢኖር፣ ትልልቅና የወንድ የሚመስሉ እጆቿ ብቻ ናቸው ። በየዕለቱ ከምታከናውነው ከባድ ሥራ የተነሣ ፣ የዳበሩትና የጠነከሩ እጆቿ በማጫው ዕለት ቦዝ ነው በግራና ቀኝ ቁልቁል ተንጠልጥለዋል ።

" ስለ ጥሎሹ አትጨነቁ ፣ ምንም አናስቸግራችሁ " አለ ግሪጐሪ ፔትሮቪች ፣ ወደ ሊፓ አክስት ዞር ብሎ ፤ " በፊት ጊዜ ለልጃችን ለስቴፋንም ሚስት ያጨንለት ያው እንዳሁኑ ከድኃ ቤተሰብ ነበር ። ታዲያ ዛሬ የቤቱንም ሆነ የሱቁን ሥራ ቀጥ አድርጋ የያዘችውና የንብረቱ ሁሉ ቁጠሪ ምራታችን ናት ። ስለሷ ምስጋና ለመግለጥ ቃላትም አይበቁን " አለ ።



ሊፓ ፣ በሩ አጠገብ ቆማ የሽማግሌውን ንግግር ስታዳምጥ ፣ በፊቷ ላይ የሚታየው ስሜት ፣ " እንደ ፈለጋችሁ ልትጠቀሙብኝ ትችላላችሁ ። አምናችሁዋለሁ " የሚል ይመስላል ።

ይህ ሁሉ በሚሆን ጊዜ ፣ ወላጅ እናቷ ከሰዎቹ መኻል የለችም ። ኃፍረት አሸንፎዋት ማዕድ ቤቱ ውስጥ ተደብቃ ነበር ። የሊፓ እናት በጣም ትፈራለች ። በወጣትነት ዕድሜዋ በቤት ጠራጊነት የቀጠራት ነጋዴ በርግጫ ስለመታት ፣ ከፍተኛ ድንጋጤ ደርሶባት እንደ ነበር ይነገራል ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ፍርሃቷን ከላይዋ ላይ ማስወገድ አልሆነላትም ። የሚያስፈራ ነገር ሲያጋጥማት ፣ እጅዋና ጉልበቷ ጉንጮቿ ሳይቀሩ ይንቀጠቀጣሉ ። የማጫው ዕለትም ማዕድ ቤት ውስጥ ተወሽቃ እንግዶቹና እኅቷ የሚሉትንና የሚያወሩትን ሁሉ ለመከታተል እየሞከረች አሁንም አሁንም ታማትባለች ። ግድግዳው ላይ በተንጠለጠለ የአንድ ቅዱስ ሥዕል ላይ ብሌኗን ሰክታ ጣቶቿን ግንባሯ ላይ በኃይል እየተጫነች ታማትባለች ። አብዝቶ በመጠጣቱ ለብታ የጀመረው አኒሲም ወደ ማዕድ ቤቱ የሚያስገባውን በር እየደጋገመ ክፊት በማድረግ ግድ የለሽ በሆነ አነጋገር፣

" የተወደዱ እናታችን ፣ ለምን ወዲህ መጥተው ከኛ ጋር አይሆኑም ? ያለርሶማ ምን ይዞ ጉዞ ! " እያለ ይጣራል ። የሊፓ እናት ፕራስኰቭያም እጆቿን በተጨማደደ ከሲታ ደረቷ ላይ ታስደግፍና ፣ " አይ ጌታዬ ፣ ምንም አይደለም ፤ እዚሁ ይሻለኛል ። ስላሰቡልኝ አመሰግናለሁ " ትላለች ፣ አኒሲም በተጣራ ቁጥር ።

የግሪጐሪ ፔትሮቪች ቤተሰብ ለአኒሲም የተመረጠችውን ወጣት አይቶ በጋብቻው በመስማማት ፍጥምጥም ከተደረገ በኋላ ፣ የሠርጉም ቀን ያኔውኑ ተቆረጠ ። አኒስም ወደ እባቱ ቤት ከተመለሰ በኋላ ፣ ከክፍል እክፍል እያፏጨ

ሲንጐራደድ ዋለ ። ደስ ደስ ብሎት ነበር ። ግን ደስታው አሁንም አሁንም ይረበሸበታል ። ድንገት የሆነ ነገር ትውስ ይለውና ጥልቅ በሆነ ሐሳብ ይመሰጣል ። ዐይኖቹን ወለሉ ላይ እንደ ጦር ተክሎ በጸጥታ ያስተውላል ። አንዳንዴ አመለካከቱ ወለሉን ዘልቆ ከሥር የሚገኘውን መሬት የሚያይ ዐይነት ይሆናል ። በመጪው ፋሲካ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ የሚፈጸም በመሆኑ ፣ የተሰማውን ደስታና ርካታ ለማንም ገልጾ አያውቅም ። ከሠርጉ ቀን በፊት እጮኛውን የማየትም ሆነ የመጐብኘት ፍላጐት አሳይቶ አያውቅም ። ብቻ ያለማቋረጥ ያፏጫል ፤ በለስላሳ ፉጨት ያዜማል ። ጋብቻውን የሚፈጽመው የአባቱንና የእንጀራ እናቱን ፈቃድ ለመሙላትና እነሱን ለማስደሰት እንጂ ፣ በበኩሉ ለነገሩ ቁብ እንደሌለው በግልጽ ያስታውቃል ። ወንድ ልጅ ሚስት አግብቶ ቤተሰቡን በሥራ የሚረዳ ተጨማሪ ኃይል ማምጣት ያለበት በመሆኑ፣ ይህንኑ ያገሩን ባህል ለማክበር ያህል እንጂ ፣ ትዳር የመመሥረት ፍላጐት እንደሌለው ከግንባሩ ይነበባል ። ከፍጥምጥሙ በኋላ ጥቂት ቀናት ቆይቶ፣ እኒሲም ወደ ሥራው ተመለሰ ። አካሔዱ ግን ፣ ወትሮ ዘመዶቹ ዘንድ ከርሞ ሲመለስ እንደሚያደርገው በመቻኮል ሳይሆን በቸልታና በርጋታ ነበር ።

—3—

በሺካሎቮ መንደር በልብስ ስፌት ሥራ የሚተዳደሩ ሁለት እኅትማማች ይኖራሉ ። ቫርቫራና አክሲኒያ የሠርጉ ዕለት የሚዋቡባቸውን ልብሶች እንዲሰፉ በመመረጣቸው ፣ እኅትማማቾቹ ወደ ግሪጐሪ ፔትሮቪች ቤት በየዕለቱ መመላለስ ጀምረዋል ። በመጡ ቁጥር ሴቶቹ የተጀመሩ ልብሶቻቸውን እንዲሞክሩ ያደርጉና የሚቀርብላቸውን ሻይ እየጠጡ ረጅም ጊዜ ከአሳለፉ በኋላ ይሔዳሉ። ለቫርቫራ የታዘዘው ልብስ ጠቆር ያለ ጥልፍና ጨሌ መሳይ ጌጥ የሚደረግበት ቡናማ ቀሚስ ሲሆን ፣ የአክሲኒያ ደግሞ ዋናው ቀለም ውሃ አረንጓዴ ሆኖ ፣ ከፊት ለፊት በኩል ወገቡ ላይ ቢጫ ጣል ያደረገበት መሬት ድረስ የሚረዝም ቀሚስ ነው ።

እኅትማማቾቹ የስፌቱን ሥራ አጠናቀው ሲያስረክቡ ፣ ግሪጐሪ ፔትሮቪች ዋጋቸውን በጥሬ ገንዘብ ፋንታ በሸቀጥ ስለ ከፈላቸው ፣ ወደ መጡበት ሲመለሱ በጣም ተከፍተው ነበር ። ምንም የማይጠቅማቸውን በቆርቆሮ የታሸጉ ሰርዲኖችና ከሞራ የተሠሩ ሻማዎች ተሸክመው ከመንደሩ ከወጡ በኋላ ፣ አንድ ዲብ ላይ ቁጭ በማለት በሽማግሌው በመማረር እንባቸውን እያፈሰሱ አለቀሱ ።

ሠርጉ ሦስት ቀናት ሲቀረው ፣ እኒሲም ወደ ኡክሊየቮ ተመልሶ መጣ ። ውሃ ባልነካቸው ልብሶች ተሸትሯል ። ጫማዎቹ ቀያይ ማሠሪያዎች ባሏቸው አዳዲስ የበረዶ መከላከያዎች ተሸፍነው አዲሱን ኮቱን ትከሻው ላይ እንደ ዋዛ ጣል አድርጎታል ።

ወደ ቅዱሳኑ ምስል ተጠግቶ ኰስተር ባለ ሁኔታ ጸሎት ካደረሰ በኋላ ፣ ለአባቱ ሰላምታ አቅርቦ ከብር የተሠሩ ዐሥር ሩብሎችን በስጦታ አበረከተለት ። ለቫርቫራም እንዲሁ አደረገ ። ለአክሲኒያ ደግሞ እያንዳንዳቸው የሩብል ሩብ የሆኑ ሐያ ሳንቲሞችን ሰጠ ። ሳንቲሞቹ አዳዲስ በመሆናቸው በፀሐይዋ ብርሃን እንደ መስተዋት ያንጸባርቁ ነበር ። ሁሉም በስጦታው ተደሰቱ ። እኒሲም ይበልጥ ኮራ ፣ ኮስተር ብሎ ለመታየት ሲል ጉንጮቹን ነፍቶ የፊቱን ጡንቻዎች ወጣጠራቸው ። ሁለመናው አረቄ አረቄ

ይሸታል ። በጉዞው ወቅት ባለፈባቸው ጣቢያዎች ከሚገኙት የመጠጥ ቤቶች መኻል ጐራ ያላለበት አይኖርም። አኒስምና አባቱ ምግብና ሻይ ቀርቦላቸው ሲቀማምሱ፣ ቫርቫራ ደግሞ፣ በስጦታ የተበረከቱላትን አዳዲስ ከብር የተሠሩ ሩብሎች በእጀቿ እያጫወተች ከትውልድ መንደሯ እየፈለሱ ከተማ በመግባት አዲስ ኑሮ ስለ ጀመሩት ጓደኞቿ ትጠይቀው ጀመር ።

“ ሁሉም ደኅና ናቸው ። እግዜር ይመስገን ” ይላል አኒሲም - ለያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ። “ ብቻ በዚያ ሰሞን የኢቫን የግሮቭ ባለቤት ሶፍያ ኒኪፎሮቭና በሳምባ በሽታ ጠንቅ በመሞታቸው ኀዘን ሆኖ ነው የሰነበተው ። ከቀብር መልስ ለለቀስተኛው የቀረበው የዕዝን ምግብ ፣ ይገርማችሁዋል ጣፋጭ ምግብ በሚሠራበት የተዘጋጀ ነበር ። በነፍስ ወከፍ ለያንዳንዱ ሰው የቀረበው ምግብ ከቪኖው ሌላ ሁለት ሩብል ተኩል ፈጅቷል ይባላል ። ከኛ አካባቢም ጥቂት ገበሬዎች ተገኝተው ነበር ” አለ አኒሲም ።

“ ሁለት ተኩል ሩብል ! ” ሽማግሌው በመደነቅ ፀይነት ተናገረና ጭንቅላቱን ነቀነቀ ።

“ እንዴታ ! እየህ አባቴ ፣ ከተማ እንደ ገጠር አይደልም ። መሸት ሲል የሚቀመስ ፍለጋ ወደ ምግብ ቤት ጐራ ትልና አንድ ፣ ወይ ሁለት ዐይነት ምግብ ታዛለህ ። ወዲያው ሌሎችም ሰዎች ይገቡና ፣ አንዳንድ እንበል በሚል ግብዣ ተጀምሮ መጠጥ ይቀርባል ። አንድ ፉት ፣ ሌላ ፉት እያስከተለ ሳይታወቅ ሰማይና መሬት ይገለባበጣል ። የጠጣኸው መጠጥ ሦስትና አራት ሩብል እንደሚያወጣ ይነገርሃል ። ቅሌን ጨርቄን የለም ፣ ከፍለህ ውልቅ ነው ። እንደ ሳሞሮዶቭ ካል ፣ ግብዣውን በቡናና በብራንዲ ማሳፈግ ከሚወድ ሰው ጋር ከሆንክ ደግሞ ወጪው የባሰ ነው።



ዛሬ ያንዱ መለኪያ ብራንዲ ዋጋ ደግሞ ስልሳ ኰፔክ ሆኗል ። ” አኒሲም ዘና ብሎ አስረዳቸው ።

“ አዬ እንጃ ! የዋጋው ነገር እንኳ አልመሰለኝም ” አለ ፣ ሽማግሌው በማዳነቅ አነጋገር ፣ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

አኒሲም ብዙ አወራላቸው ። ስለ መረጃ ሥራውና የሌባ ጠር ስለ መሆኑ፡በየጊዜው በሚያስገኛቸው ውጤቶች ተደናቂነትን ስለ ማትረፉና ሳሞሮዶቭ ስለሚባለውም ጓደኛው በሰፊው ሲያወጋቸው ቆየ ።

የሠርጉ ዕለት ደረሰ ። የሚያዝያው አየር ቢቀዘቅዝም ቀኑ ደስ የሚልና ብሩህ ነበር ። ከማለዳው አንሥቶ በሦስትም በሁለትም ፈረሶች የሚጐተቱ ጋሪዎችና ሠረገላዎች የኡክሊየቮን መንደር መኻል ለመኻል እየሰነጠቁ ወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ ፣ ፈረሶቹ አንገት ላይ የተንጠለጠሉት ትንንሽ ደወሎች ይቅጨለጨላሉ ። ፈረሶቹ ትከሻ ላይ በሚያርፉት አግዳሚ ዕንጨቶች ላይ የታበቱት በተለያየ ደማቅ ቀለሞች ያሸበረቁ ጥብጣቦች በማለዳው ንፋስ ይውለበለባሉ ። በፈረሶቹ ኮቴ በጋሪዎቹ መንኮራኩርና በቃጭሎቹ ድምፅ የተረበሹ አሞሮች በየዛፉ ላይ እንደ ሠፈሩ መጯጯህ ጀመሩ ። ወፎቹም መዝሙራቸውን ያለ ማቋረጥ ተያያዙት - በሠርጉ የተደሰቱ ይመስል ።

በግሪጎሪ ፔትሮቪች ቤት ውስጥ መሰናዶው ይቀልጣል ። ገና ከጠዋቱ ገበታዎች ሁሉ በምግብ ተሞልተዋል ። ትልልቅ ዓሣዎች ፣ በጢስ የደረቀ የዓሣማ ወርች የአራዊት ሥጋ ፣ በቆርቆሮ የታሸገ ዓሣ . . . . ቂጭሩ ከሁሉም ዐይነት በገፍ ተዘጋጅቷል ። ለቁጥር የሚያታክት ቮድካና ወይን ጠጅ በጠርሙስ በጠርሙስ እየሆነ ተሹሟል ። የቋሊማና የዓሣ ሽታ የቤቱን አየር ጠቅ አድ

ርጎታል ። ሽማግሌው ፣ በጠረጴዛዎቹ ዙሪያ መለስ ቀለስ እያለ ቢለዋ ለቢለዋ በማፋጨት ስለት ያወጣል ። ሁሉም ሰው ቫርቫራን እየጠራ ስለ ምኑም ስለ ምኑም ይጠይቃታል። እሷ ግን ፣ ቁና ቁና እየተነፈሰችና እየተደነባበረች ከማዕድ ቤት ዕልፍኝ ፣ ከዕልፍኝ ማዕድ ቤት ትመላለሳለች።ከኩስት የኮቨና ከሀሪሚን ትንሹ ቤት በውሰት የመጡት ሁለቱ ከፍተኛ ወጥ ቤቶች ጉህ ሲቀድ የጀመሩትን ሥራ ለማጠናቀቅ ማዕድ ቤቱ ውስጥ ደፋ ቀና ይላሉ ። ጸጉሯ ተጠቅልሎ የተሠራው አክስኒያ በቀሚሷ ላይ ምንም ሳትደርብ አዲሱ ቦት ጫማዋ እየተንሳጠጠ በግቢው ውስጥ እንደ ዐውሎ ነፋስ ትከንፋለች ። ከፍጥነቷ የተነሣ ባለፈች ባገደመች ቁጥር ለሰዎች የሚታያቸው ያልተሸፈኑ ጉልበቶቿና በከፊል የተጋለጡ ጡቶቿ ብቻ ናቸው ። በውካታው ጣልቃ ስድብ ፣ መሐላ ጉልቶ ይሰማል ። ከቅጥር ግቢው ውጭ የሚተላለፉ መንገደኞች ፣ ሙሉ በሙሉ ብርግድ ብሎ በተከፈተው የግቢው ዋና በር ትይዩ ቆም እያሉ ወደ ውስጥ ያስተውላሉ ።

ሙሽራይቱን ለማምጣት የሔዱት ሠርገኞች ከስምንት ሰዓት በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ተመለሱ ። ፈረሶቹ ላይ የተንጠለጠሉት ትንንሽ ቃጭሎች ድምፅ ፣ ከርቀት መሰማት ሲጀምር ፣ የውጭውም የግቢውም ተሰብስቦ አንዱ ባንዱ ላይ እየተጫነ እየታከከ ፣ እየተንጠራራ አቆብቁቦ ይጠባበቅ ጀመር ። ሥርዓተ ተክሊሉ የሚፈጸምበት ቤተ ክርስቲያን እስከ እልቅቱ ድረስ ጢም ብሎ በሰው ተሞልቷል ። ከጣሪያው ላይ ቁልቁል ከተንጠለጠሉት ቀንዲሎች ላይ የተሰኩት ሻማዎች ሁሉም በርተዋል ።የመዘምራኑ ልሳኖች ተከፍተው ጣዕመ ዜማ ያንቆረቁራሉ። ከሻማዎቹ የሚንጸባረቀው ብርሃንና የእድምተኞቹ ልብሶች የተለያዩ ቀለሞች በአንድነት ሆነው የሙሽራይቱን



የሊፓን ዐይኖች ተፃረሩዋቸው ። የመዘምራኑ የሚስረቀረቁ ድምፆች እንደ ትንንሽ መዶሻዎች የራስ ቅሏን የሚወቅሯት መስሎ ተሰማት ። በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ የለበሰችው ማለፊያ ሽንሽን ቀሚስ ጥብቅ ፣ ጭምቅ አድርጎ ይዟታል ። አዲሶቹ ቦት መጫሚያዎቿ እግሮቿን አንቀው በማስጨነቅ የሥቃይ ስሜት ሊፈጥሩባት ጀምረዋል። ነፍሷን ስታና ተዝለፍልፋ ቆይታ ፣ የዳነች መስላ ከመታየቷ በላይ ያለችበት ቦታ የት እንደሆነ ገና አልገባትም ነበር ።

ጥቁር ኮት ለብሶ በክራባት ምትክ ቀይ ገመድ በሸሚዙ ክሳድ ዙሪያ ሸብ ያደረገው ሙሽራው አኒሲም በጥልቅ ሐሳብ እንደ ተዋጠ ያስታውቃል ። ዐይኖቹ በአንድ ነጥብ ላይ አተኩረዋል ። ጎብረ ዘማሪያኑ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው መዘመር ሲጀምሩ ፣ በተፋጠነ ሁኔታ አማተበ ። ዜማው ስሜቱን በጣም ስለ ነካው ፣ ቢያለቅስ ደስ ባለው ነበር ። ያን ቤተ ክርስቲያን የሚያውቀው ገና አንድ ፍሬ ብላቴና ሳለ ነበር ። እናቱ እየታቀፈች አምጥታ የምታቆርበው እዚሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆኑ ትዝ ይለዋል ። ነፍስ ካወቀም በኋላ ፣ ከሌሎች ልጆች ጋር መንፈሳዊ ዜማ ያሰማ ነበር ። በዚያን ጊዜ የቅዱሳኑን ምስልና እያንዳንዱን ጓዳ ጎድጓዳ እንዴት ልቅም አድርጎ ያውቀው እንደ ነበር ትውስ አለው ። እና አሁን ደግሞ የጋብቻውን ሥርዓት በዚያው ሥፍራ እያከበረ ነው ።መደረግ ያለበት ትክክለኛና ጥሩ ነገር ስለሆነ ብቻ ፣ ጋብቻ እየፈጸመ ነው ። እሱ ግን ፣ በዚያ ወቅት መቅደሱ ውስጥ ቆሞ የሚያሰላስለው ስለሚመሠርተው ትዳር አልነበረም ። ይህ ጉዳይ ከአእምሮው ውስጥ ተንኖ ሔዷል ። በዐይኖቹ ዙሪያ እንባው ግጥም በማለቱ ፣ የቅዱሳኑን ምስል እንኳን አጥርቶ ማየት ተስኖታል ። አንዳች የሆነ ክብደት ልቡን ክፉኛ

ሲሜነው ይሰማዋል ። ለፈጣሪው የሕሊና ጸሎት አደረሰ ። በእናቱ ትይዩ የተንጠለጠለውንና በማናቸውም ቅጽበት ሊፈነዳ የተዘጋጀውን አንዳች ነገር ቋሳዩ ላይ እንዲያስወግድለት አምላኩን አጥብቆ ተማፀነው ። በድርቅ ወራት በየመንደሩ ሰማይ ላይ በማንዣበብ መጣሁ ፡ ደረስኩ እያለ የሚደነፋው ጥቀርሻ የመሰለ የዝናብ ደመና ፡ አንዲትም ጠብታ እንኳን ሳይቸር ድንገት ዐልፎ እንደሚሔድ ሁሉ ፡ በሱም ሕይወት እንደ አጕበር አረብቦ የሚያንዣብበው መቅሠፍት እልም ብሎ እንዲጠፋ ያደርግለት ዘንድ ፈጣሪውን በአርምሞ ለመነው ። ላለፈ ጥፋቱ ይቅርታና ሥርየት መጠየቅ ተገቢ ያልሆነ መስሎ ቢታየውም ፡ ይቅርታ ከመጠየቅ ግን አልተቆጠበም ። እንዲያውም አንድ ጊዜ ዙሪያውን የከበቡት ሁሉ ፡ ሊሰሙት እስኪችሉ ድረስ ሣቅ እየተናነቀው ተንሠቀሠቀ ። ደግነቱ ነገሬ ያለው አል ነበረም ። ቢኖርም በስካር ከመተርጐም አያልፍም ።

ድንገት የአንድ ሕፃን ጩኸት መቅደሱን አሸበረው ። “ እማምዬ እባክሽን ከዚህ ቦታ አውጪኝ ፡ እባክሽን እንሒድ !” አለ ሕፃኑ በጩኸት ። ፍርሃት ያመነጨው ልመና ነበር ።

“ ጸጥታ እዚያ ጋ ! ” የቄሱ ድምፅ አስተጋባ ፡ በተግሣፅ ዐይነት አነጋገር ።

ሙሽሮቹ ከነድምተኞቻቸው ቤተክርስቲያኑን ለቀው ሲወጡ ፡ አጀቡና የተሰበሰበው ሕዝብ አንድ ጊዜ ተንዶ ተከተላቸው ። በነቂስ የወጣ ይመስል ሠፈሩ ሰው ብቻ ሆኗል ። ሱቁ አጠገብ ፡ ዋናው በር ላይ ፡ ቅጥር ግቢው ውስጥ ሁሉም ቦታ በሰው ብዛት ተጥለቅልቋል ። አንዱ ባንዱ ላይ እየተጫነ ፡ እየተመረኰዘ ፡ እየተንጠራራ ይመለከታል ። ያዳንቃል ።ይተቻል ።



ሙሽራውና ሙሽሪት ፡ የቤቱን ደፍ ሲረግጡ ሴቶች መልካም ምኞታቸውን በመግለጥ ቀርበው ተቀበሏቸው ። የዜማ መመሪያ ወረቀቶች በእጆቻቸው ይዘው መግቢያው ላይ በመሠለፍ ይጠባበቁ የነበሩት ድምፃውያን በከፍተኛ ድምፅ መዝፈን ሲጀምሩ ፡ ከከተማ በኪራይ የመጡት ሙዚቀኞች በመሣሪያቻቸው ያጅቡ ጀመር ። ከዶን አካባቢ የመጣው ሻምፓኝ ተከፍቶ በረጃጅም ብርጭቆዎች እየተሞላ ለሠርገኞቹ ታደለ ። ወዲያው ቁመተ ረጅሙ ቀጭን ሽማግሌ የሌሳሮቭ ለሙሽሮቹ ንግግር ማድረግ ጀመረ ።

“ ኢኒሲምና አንቺም ልጄ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ፤ ጕዟችሁ ሁሉ በእግዜር ፊት ይሁን ። እሱ ይከተላችሁ ፤ ዐይኖቹ አይለዩዋችሁ ። ቅድስት ወላዲተ አምላክ እለሁ ትበላችሁ ” አለ ፡ እንደ ቁጥቋጦ ችፍርግ ብለው በበቀሉ ቅንድቦች የተደበቁ ዐይኖች ያሉት የሊሳሮቭ ።

አናፂና የቤት ሥራ ተቋራጭ የሆነው አዛውንቱ የሊሳሮቭ ይህን ተናግሮ እንዳበቃ ፡ ግሪጐሪይ ፔትሮቪች ትከሻ ላይ ድፍት ብሎ እንደ መንሠቅሠቅ ቃጣው ።

“ ወንድሜ ግሪጐሪ ፔትሮቪች ፡ የዛሬው ደስታችን ወሰን የለውምና ትንሽ እናልቅስ” አለ በሰለለ ድምፅ ፡ አፍታም ሳይቆይ ደግሞ ከት ብሎ ከሣቀ በኋላ ፡ በጕልህ ጐርናና ድምፅ “ ሆ! ሆ! ሆ! ይቺ ሙሽራህ የውበትእመቤት አይደለች እንዴ ! አዎ ሁሉም ነገር መሆን እንደሚገባው ሆኗል ። ተሳክቷል ። ሰምሯል ። አንድም ነገር አልጐደለ። ዝግጅቱ ሁሉ በሥርዓት ነው ። ምስማሮቹም በየቦታቸው በትክክል ገብተዋል ” አለና ደመደመ ።

የሊሳሮቭ ተወልዶ ያደገው የጐሮቭስክ በሚባል ወረዳ ነው ። ግን ከወጣትነት ዕድሜው አንሥቶ ኡክሌየቮ በሚገኙት የጥጥ ማባዘቻዎችና በዚያው በመንደሯ አካ

ባቢ ሲሠራ በመኖሩ ፣ ራሱን እንደ መንደሯ ተወላጅ አድ
ርጎ ነው የሚቆጥረው ። የሚያውቁት ሁሉ ዕድሜውን
በሙሉ ፣ ልክ አሁን እንደሚታየው ሽማግሌና መንማና ሆኖ
የኖረ ይመስላቸዋል ። ሁሉም ሰው የሚጠራው ጉጠት
በሚል ቅጽል እንጂ ፣ የሊሳሮቨ የሚለው ወይም በሌላ ስም
የሚጠራው አንድም አልነበረም ። ይህን ቅጽል ስሙን
ያገኘበት ምክንያት በውል ባይታወቅም ፣ ምናልባት በፋ
ብሪካ ውስጥ ለዐርባ ዓመታት ሲሠራ የእድሳትና የጥገና
ሥራ ብቻ ሲያከናውን በመኖሩ ይሆናል ። ወይም በሰው
ልጆችና በቁሳቁስ መካከል ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም
በአንድ ዐይነት መለኪያና ደረጃ ስለሚለካቸው ይሆናል ።
ጉጠት ፣ ሁሉንም ነገር የሚመዝነው ጠንካራ ነው ወይስ
ጥገና ያስፈልገዋል? በሚል መለኪያ ብቻ ነበር ። የሠር
ጉም ዕለት ፣ ጠረጴዛው አጠገብ ከመቀመጡ አስቀድሞ
ብዙ ወንበሮችን እያገላበጠ ፣ ጥንካሬያቸውን የፈተሸው
በዚሁ ልምዱ የተነሣ ነበር ። የቀረበለትን ዓሣ እንኳን
ከመመገቡ አስቀድሞ ነካ ነካ በማድረግ ፈትሾታል—
ጥንካሬውን ወይም ጥገና የሚፈልግ መሆኑን ለማየት።

ሠርገኞቹ የተቀዳላቸውን ሻምፓኝ በአንድ ትንፋሽ
በቁማቸው ከጨለጡ በኋላ ፣ ሁሉም በየወንበሮቻቸው ተቀ
መጡ ። ሌሎቹ እንግዶችም ሥፍራ ሥፍራቸውን በመ
ያዝ ውይይት ከፈቱ ። ዘፋኞቹ መተላለፊያውን ሞልተው
ዘፈኑን ሲያወርዱት ፣ ሙዚቀኞቹም እንደ ቀድሞው በመ
ሣሪያዎቻቸው ማጀባቸውን ቀጠሉ ። ቤተ ዘመድ የሆ
ኑት ሴቶች ደግሞ ፣ የባህል ዘፈኑን ባንድነት ያቀልጡት
ጀመር ። ቤቱም ደጁም በከፍተኛና ደማቅ ድምፅ ተጥ
ለቀለቀ ። ድብልቅልቁ ወጣ ።

ጉጠት ፣ ወንበሩ ላይ እንደ ተቀመጠ ይቁነጠነጥ ፣
ይቅበጠበጥ ጀመር ። አንዱ አጠገቡ ያሉትን ይጐሸማል።



ወዲያው በሌሎች ንግግር መኻል ጣልቃ ይገባል ። ከም
ድር ተነሥቶ በሣቅ ይንፈቀፈቃል ። ደግሞ ልቅሶውን ይያ
ያዘዋል ።

“ ልጆቼ ፤ ውድ ልጆቼ ! ” ጉጠት ፣ ድንገት ከተቀመ
ጠበት ተነሥቶ በተጣደፈ ሁኔታ ያጉመተምት ጀመር ።
“ሁላችንም እርስ በርስ ተፋቅረን ፣ በሰላምና በጸጥታ
እንኑር ። የተወደዳችሁ ልጆቼ ! . . . ” የጀመረውን አል
ጨረሰም ። አንጠልጥሎ ተወው ።

ጉጠት ፣ የመጠጥ ሱሰኛ አልነበረም ። በመጀመሪያ
የቀመሳት አንዲት መለኪያ ጂን ራሱ ላይ ወጣች ። ብው
ብሎ ሰከረ ። ይህ ከምን ጥንስስ እንደሚጠመቅ ተለይቶ
ያልታወቀ ፣ እንደ ሬት የመረረ አቅለሽላሽ መጠጥ የቀ
መሰውን ሰው ሁሉ ፣ እናቱ በዱላ የተበጠረቀ ያህል እያ
ደነዘዘ ቁጭ አደረገው ። ከያንዳንዱ ተጋባዥ አንደበት
የሚወጣው ንግግር ምኑም የማይጨበጥና ዝብርቅርቅ
እየሆነ ሔደ ።

በጠረጴዛው ዙሪያ ፣ የመንደሯ ቀሳውስትና በጥጥ
ማባዘቻዎቹ የሚሠሩት ካቦዎች ከነሚስቶቻቸው ተቀ
ምጠዋል ። በጐረቤት መንደሮች የሚኖሩ ነጋዴዎችና
የመጠጥ ቤቶች ባለንብረቶችም ከነሱ ቀጥለው በመደዳ
ተደርድረዋል ። ድፍን ዐሥራ አራት ዓመታት ሙሉ አብ
ረው የሠሩት የወረዳው ጽ/ቤት ሹምና ጸሐፊው በድግ
ሱም ሥፍራ አልተነጣጠሉም ። ጐን ለጐን ናቸው ። በነ
ዚያ ዓመታት ውስጥ ወደ ሁለቱ ጉዶች ቢሮ ገብቶ ሳይ
ጉላላ ፣ ሳይበደል ፣ ሳይጭበረበር የወጣ ወይም የሚፈል
ገውን ወረቀት አስፈርሞ በእጁ ያገባ ባለ ጉዳይ ማግኘት
ሳር ነው ። እንዲያ አወልውለውና እንደ ቀርበታ ተነ
ፋፍተው ሁለቱንም ሲያዩዋቸው ፣ በቅጥፈትና በሐሰት

የበሸቀጡ መሆናቸው በግልጥ ያስታውቃል ። የፊታቸው ቆዳ ሳይቀር የመልቲ ቆዳ መሆኑ ይታያል ።

አንድም ሳታስቀር ልጆቿን በሙሉ ሰብስባ የመጣችው ዐይነ ሽውራራዋ የጸሐፊው ሚስት ፣ ወደ ጠረጴዛው በጣም ተጠግታ በመቀመጥ ፣ እንደ ጆሬ አሞራ ከሣህን ሣህን በማማተር የቀረበውን ሁሉ እየሰበሰበች በራሷና በልጆቿ ኪሶች ውስጥ ታምቃለች ።

ሊፓ ፣ እንደ ዐምድ ደርቃ ተቀምጣለች ። በገጿ ላይ የሚታየው ስሜት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሳለች እንደ ነበረው ያለ ነው ። ከተዋወቁበት ዕለት አንሥቶ አንዲት ቃል እንኳን ስላልተለዋወጡ ፣ ኢኒሲም ምን መሳይ ድምፅ እንዳላትም አያውቅ ነበር ። አሁንም አጠገቧ ቁጭ ብሎ የቀረበለትን ጂን በጸጥታ ይጠጣል ። በመጨረሻ ሞቅታው እያየለበት ሲሔድ ፣ ከፊት ለፊቱ የተቀመጠችውን የሊፓን አክስት ማናገር ጀመረ ።

“ አንድ ጓደኛ አለኝ ሳሞሮዶቭ ይባላል ። እንደ ማንም ተራ ሰው አይደለም ። እንዴት መናገር ፣ ምን መናገር እንዳለበት አጣርቶ የሚያውቅ የተከበረ ዜጋ ነው ። እኔ ግን ደኅና አድርጌ ፣ ውስጡን ጠልቄ ዐውቀዋለሁ ። ይህን እሱም በደንብ ያውቀዋል ። እና ለወዳጄ ለሳሞሮዶቭ ጤንነት ጽዋችንን እናንሣ ፣ አክስቴ ! ” አለ ኢኒሲም ወደ ስካር ማሻቀብ በጀመረ የሞቅታ መንፈስ ።

ቫርቫራ በጠረጴዛው ዙሪያ እየተመላለሰች እንግዶቹ ምግቡን እንዲሞካክሩት ትጋብዛለች ። የሥራ ውጥረት በዝቶ ውልቅልቅ ብላ ብትደክምም እንኳን ፣ ምግቡ ሞልቶ በመትረፍረፉና ሁሉም ነገር ወደር በሌለው ሁኔታ ተሟልቶ በመዘጋጀቱ መንፈሷ በደስታ ረክቷል ። አሁን ማንም ይህ ጐደለ ብሎ ለመናገር እንደማይችል ርግጠኛ ነች ።



ጀንበር እያዘቀዘቀች ብትሔድም ፣ ፈንጠዝያና ድግሱ ግን ቀጠለ ። እንግዶቹ እጃቸውና ጥርሳቸው ሥራ አልመፍታቱን እንጂ የሚያዩት ፣ ወደ አፋቸው የሚያስገቡት ምን እንደሆነ መለየትና ማወቅ ወደ ተሳናቸው ደረጃ ደርሰዋል ። ምን እንደሚወራ ፣ ምን እንደሚባል የሚያዳምጥ የለም ። አንዱ ሌላውን አይሰማውም ። ትርምስ ፣ ድብልቅልቅ ፣ ውካታ ፣ መለፍለፍ ብቻ ነው ። ዐልፎ ዐልፎ ዘፈንና ሙዚቃው ላንዳፍታ ቆም ሲል ብቻ ፣

“ ደም መጣጭ አረመኔ ሁሉ ! መዓት ይውረድባችሁ !” እያለች የምትጮህ ሴት ድምፅ ከውጭ በኩል ጥርት ብሎ ይሰማል ።

ምሽቱ እየገፋ ሲሔድ ዳንስ ተጀመረ ። ሙዚቃው ተፋፋመ ። የራሳቸውን የወይን ጠጅ ይዘው ከመጡት የህሪሚን ትንሹ ሰዎች መካከል አንደኛው ብድግ ብሎ በሁለት እጆቹ ጠርሙሶች ይዞ ፣ በጥርሶቹ ደግሞ ብር ጭቆ ነክሶ ‘ ኳድሪል ’* የሚባለውን ዳንስ አሳየ ። ተጋባዡ በሙሉ ደስታውን ገለጠ ። ከዚያ በኋላ የዳንሱ ዐይነት እስኪጠፋ ቅጥ አንባሩ ወጥቶ መተረማመስ ሆነ ። አንዳንዶቹ ‘ ኳድሪል ’ መጫወት ይጀምሩና ወዲያው ቁጢጥ ብለው ፣ የእግር አጣጣላቸውን በመለወጥ ፣ ፈጠን ባለ ምት እግሮቻቸውን ተራ በተራ ወደፊት እየዘረጉና እየወነጨፉ የሩሲያን የባህል ጭፈራ ይያያዙታል ። አረንጓዴ የለበሰችው አክሲኒያ መሬት ለመሬት በሚጐተተው ቀሚሷ ነፋሱን እያራገበች ወዲያ ወዲህ ሽው ሽው ትላለች ።

---

* ኳድሪል ፡ ከጥንታዊ የዳንስ ዐይነቶች አንዱ ሲሆን ፣ በመጀመሪያ ጊዜ በነበረው ሕግ አምስት ሰዎች ፣ የኋላ ኋላ ተሻሽሎ በወጣው ሕግ መሠረት አራት ሰዎች በአንድነት ሆነው በቡድን የሚጫወቱት ነው ። ዛሬ እየቀረ ሔዷል ።

የአክሲኒያ ግራጫ ዐይኖች ገራገር ብጤ ናቸው ።
ሽፋሏን ሳትሰብር ትክ ብላ የማየት ጠባይ አላት ። ሁል
ጊዜ ከፊቷ ላይ የማይጠፋው ፈገግታ የደስ ደስ ያለው ዐይ
ነት ነው ። በነዚያ ትክ ብለው የሚያስተውሉ ዐይኖቿ ፡
ሙቃ በመሰለው ረጅም አንገቷ ላይ ቂብ ባለችው ትንሽ
ጭንቅላቷና ፡ እንደ ልብ በሚታዘዝላት ኩሩ ባለ ግርማ
አካሏ ላይ ፡ አንዳች ከአባብ ቅርፅ ጋር የሚመሳሰል ነገር
ይታይባቸዋል ። በተለይ በአረንጓዴው ቀሚሷ ወገብ ላይ
ፈካ ያለው ቢጫ ቀለምና ፡ መቼም መች የማያቋርጥ ፈገ
ግታዋ ደግሞ ፡ በፀደይ ወቅት ዐላፊ አግዳሚውን ለማስ
ተዋል ከጠመዥ ቡቃያ መኻል አንገቱን የሚመዝ አባብ
አስመስሏታል ። በርሷና በሀሪሚን ትንሹ ቤተሰብ መኻል
ያለው ዕውቂያ በጣም መቀራረቡ ነጻ ከሆነው ጠቅ
ላላ ሁኔታቸው ይታወቃል ። በተለይ ከወንድማማቾቹ
መኻል ከትልቅየው ጋር የቆየና ጥብቅ የሆነ ልዩ ዐይነት
ግንኙነት እንዳላት ለማንም በግልጽ ይታያል ። ከዚያ ሁሉ
ሰው መኻል ይህን ሁኔታ የማይረዳ ቢኖር ደንቆሮው ባሏ
ብቻ ነበር ። ስቴፋን ሚስቱን ቀና ብሎ ሊያያት እንኳን
አይጨነቅም ። ብቻ በተቀመጠበት እግሩን አነባብሮ በጸ
ጥታ ለውዝ ይበላል ። የለውዙን ቅርፊት ሲሰብረው ደግሞ
ልክ እንደ ጥይት ይጮሃል ።

ጭፈራውና ፈንጠዝያው እንዲያ ተጧጡፎ ሳለ ፡ ሽማ
ግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች በዳንሱ ተካፋይ ለመሆን መሻ
ቱን ለመግለጥ መሐረቡን እያራገበ ወደ ወለሉ መኻል
ገባ ። ሰው ሁሉ ጉምጉምታውን ከክፍል ክፍል ይቀባበ
ለው ጀመር ። ጉምጉምታው ከቤት ወጥቶ ደጅ ሲደርስ ፡

“ እሱ ራሱ ሊደንስ ነው ! ራሱ ሊገባበት ነው ! ”
ወደሚል ጫጫታ ተለወጠ ። ግሪጎሪ ፔትሮቪች ከሚስቱ
ጋር መደነስ ጀመረ ። ቫርቫራ በደንብ ስትደንስ ሽማግ



ሌው ግን ፡ በሙዚቃው ስልት ልክ መሐረቡን እያራገበ በተ
ረከዙ መሬቱን መደለቅ ብቻ ነበር ። ይሁን እንጂ ፡ ከውጭ
ሆኖ በመስኮቶቹ በኩል የሚመለከተው ሕዝብ በሁኔታው
ከመደሰት አልተቆጠበም ። ሁሉም ሰው ይቅር ለግዜር
ያለው ይመስላል ። ለሀብቱም ሆነ ለበደለኛነቱ ፡ ለስስቱም
ሆነ ለፍርደ ገምድልነቱ በዚያች ቅፅበት ይቅርታ ያደ
ረገለት ይመስላል ።

“እንዲያ ነው ግሪጎሪ ፔትሮቪች ! በርታ ! ” ከውጭ
ያሉት መጮህ ጀመሩ ። “ ያዝ እንግዲህ ! ቀጥል ! በአ
ሮጌው ውሻ ውስጥ ገና ሕይወት ትር ትር ትላለች ማለት
ነው ጃል ! አሃ—ሃ—ሃ ! ”

ጠቅላላው ጨዋታና ድግስ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት
በኋላ አበቃ ። አኒሲም እየተንገዳገደ ወደ ሙዚቀኞቹ በመ
ቅረብ ፡ ለያንዳንዳቸው አዳዲስ የግማሽ ሩብል ሳንቲሞች
አበረከተላቸው ። የስንብት ስጦታ ነበር ። ሽማግሌውም
ለይቶለት አይንገዳገድ እንጂ ፡ በመጠኑ ዘመም ዘመም
እያለ እንግዶቹን መሸኘት ጀመረ ። ተሰናብቶት ለሚወ
ጣው ሁሉ ፡

“ ከሁለት ሺህ ሩብል በላይ የፈጀ ሠርግ ነው! ”
እያለ ደጋግሞ እየነገረ ፡ ተጋባዡ ሁሉ ወደ የቤቱ በመ
መለስ ላይ ሳለ ፡ ከሺካሎቮ መንደር የመጣው የመጠጥ ቤት
ባለንብረት በዳንሱ ጊዜ ወንበር ላይ አስቀምጦት በነ
በረው አዲስ ኮት ምትክ ፡ አሮጌ ተቀምጦ በመገኘቱ ድን
ገት ጫጫታ ተፈጠረ ። ይህን ያደረገው ማን እንደሆነ
ግን ሊታወቅ አልተቻለም ። ወዲያው አኒሲም በከፍተኛ
ቅልጥፍና ፡ “ ሁላችሁም አንድ ጊዜ በያላችሁበት ቁሙ!
ሌባውን አሁኑኑ አገኘዋለሁ ! ኮቱን የወሰደውን ዐውቃ
ለሁ ! ቁሙ ነው የምለው ! ” እያለ መንዠባረር ጀመረ ።

ቶናግሮም ሳያበቃ ፡ ተንደርድሮ ወደ ዋናው መንገድ በመውጣት ወደየቤታቸው በመመለስ ላይ ካሉት እንግዶች በአንደኛው ላይ ለመድረስ ይሮጥ ጀመር ። ግን ብዙም ሳይርቅ ተከታትለው በመያዝ ወደ ቤት መለሱት። ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ፡ ፊቱ በንዴት ሳምባ መስሎና በላብ ወርዝቶ ወደ ሜጉላው ክፍል ገፋፍተው አስገቡት ። አክስትየዋ ፡ የሊፓን ልብስ አወላልቃላት በአንድነት ሙሽራውን ይጠብቁ ነበር ። አኒሲም እንደ ገባ በሩ በላያቸው ተዘጋ ።

—4—

አምስት ቀናት ዐለፉ ። ወደ ሥራው ለመመለስ የተነሣው አኒሲም ቫርቫራን ለመሰናበት ወደ ፎቁ ወጣ ። ከቅዱሳኑ ሥዕሎች ፊት ለፊት የተተከሉት መብራቶች በሙሉ ተለኩሰው የደመቀ ብርሃን ይንቦገቦጋል ። የዕጣን ሽታ ቤቱን አውዶታል ። ቫርቫራ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ በቀይ የሱፍ ክር እግር ሹራቦች ትሠራለች ።

“ መቼም አብረኸን ብዙ መቆየት አልቻልክም ፤ ሰለቸንህ መሰለኝ ? ” አለች ። “ ገጠር ቢሆንም እዚህ ኑሯችን በጸጋ ነው ። ምንም ችግር የለብንም ፤ ሁሉም ሞልቷል ። ጥሩ ሠርግም ደግሰንልሃል ። የጐደለ ነገር አልነበረም ፤ የተሳካ ይመስለኛል ። አባትህም ሁለት ሺህ ሩብል ፊጅ ይላሉ . . . . እርግጥ እዚህ ሕይወት ለዛዛ ነውና ያሰለች ይሆናል ። ይሁን እንጂ ከከተማ የተሻለ እንኖራለን ። ብቻ ደንበኞቻችንን በደንብ አናስተናግድም ። በሚገባ አንይዛቸውም ። እዚህ ካለው ነገር ሁሉ የሚከብደኝ ይኸ ጉዳይ ብቻ ነው ። አኒሲም ፡ በእግዜር ስም እልሃለሁ ፤ ሰዎ



ችን እንዴት እንደምናደርጋቸው ፥ እንዴት እንደምንቀልድባቸው ስተዋልሁ ቁጥር ዘወትር ልቤ በኀዘን ይቆስላል ። ፈረስ በዕቃ ስንለውጥ ፡ ወይ አንዳች ነገር ስንገዛ ፡ ሌላው ቀርቶ የሚረዳን ሠራተኛ ስንቀጥር እንኳን ሐቅን ተከትለን አናውቅም ። ነግቶ እስኪመሽ ማጭበርበር ፡ ማማታት ነው ። በሁሉም ነገር ላይ በተቻለ መጠን ማታለል የቤታችን ባህል ሆኗል ። በኛ ሱቅ ጥሩ ዐይነት እየተባለ ከሚሸጠው የአትክልት ዘይት ይልቅ ፡ አንድያውን የለየለት ቅጥራን የተሻለ ጣዕም ሳይኖረው አይቀርም ። እስቲ እንዲያው በሞቴ እውነቱን ንገረኝ ! አሁን የኛ ዐቅም ጥሩ ዘይት አምጥተን ለመሸጥ የማይበቃ ሆኖ ነው?” አለችው በትካዜ አነጋገር ።

“ ለሁሉም እንደየሥራው እናት ! ” አለ አኒሲም ለዘብ ባለ አንደበት ።

“ ግን በምንሞትበትስ ጊዜ ? ምንድነው የሚውጠን ፤ እንዲያው ከአባትህ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ብትነጋገሩበት ምናለ ! ” የቫርቫራ አነጋገር የጭንቀት መሆኑ ያስታውቃል።

“ አንቺ ራስሽ ለምን አታነጋግሪውም ? ”

“ አይ አኒስም ! እኔማ በልቤ ያልውን ስነግራቸው ፡ ሳማክራቸው ፡ ልክ አሁን አንተ እንዳልከው የመሰለ መልስ ነው የሚሰጡኝ ። ‘ ለሁሉም እንደ ሥራው ’ የሚል ፈሊጥ አላቸው ። ታዲያ በወዲያኛው ዓለም ደግሞ ፡ ለእገሌ ምን ይገባዋል ፡ ምንስ አይገባውም እያለ የሚያሚግትና የሚያማርጥ ያለ ይመስልሃል? አትሞኝ ልጄ ! የጌታ ፍርድ አንድ ነው ! ”

“ እሱንማ ዐውቃለሁ ። ግን እስከዚህ ብዙም አትጨነቂ እናት ። እግዚአብሔር የሚሉት ነገር ስለሌለ፡ጥያቄውን የሚያቀርብም አይኖርም ” አለና በከባዱ ተነፈሰ።

ቫርቫራ እየሣቀች በመገረም ተመለከተችውና ፣ ሁለቱንም እጆቿን ዘረጋቻቸው ። አሣሣቋና አስተያየቷ እንደ ዕብድ የቆጠረችው መሆኗን የሚጠቁም ዐይነት ነበር ። አኒሲም የመጨነቅ ስሜት አደረበት ።

“ አዎ ፣ ምናልባት እግዚአብሔር የሚባል ይኖር ይሆናል ። ግን ዛሬ ብዙም የሚያምንት የለም ። ” አኒሲም ንግግሩን ቀጠለ ። “ እኔ እንኳን የሥርጌ ዕለት እሥቂኝ የሆነ ነገር ሲሰማኝ ነበር ። ሁኔታው ሁሉ አንድ ሰው ከሲካካ ዶሮ ጉያ ዕንቁላል እንደሚወስድና ካልተሰበረው ዕንቁላል ውስጥ ድንገት የጫጩቷን ድምፅ እንደሚሰማ ዐይነት ነበር ። እኔም የሥርጌ ዕለት ሕሊናዬ ከውስጥ የጫጩት ድምፅ ሲያሰማ ሰማሁት ። የጋብቻችን ሥነ ሥርዓት በሚካሔድበትም ወቅት ፣ ‘ እግዚአብሔር አለ ! ’ የሚል ሐሳብ መጣብኝ ። ግን ከቤተ ክርስቲያኑ ስወጣ ሁሉም ነገር ተረሣ ። ወደ ኋላዬ ቀረ ። እና ታዲያ እንዴት አድርጌ የእግዚአብሔርን መኖር አለመኖር ለማወቅ እችላለሁ። ሕፃናት ሳለን እንዲህ ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ያስተማረን ሰው አልነበረም ። እራስ ከናቱ ዕቅፍ እስከ ወጣ ድረስ የሚሰማውና የሚማረው ነገር ቢኖር ፣ ‘ ለሁሉም እንደ የሥራው ’ የሚሉትን ቃላት ብቻ እንጂ ሌላ የለም ።አባቴ ደግሞ፣ እግዜር በሚሉ ነገር በፍጹም አያምንም ። አንድ ጊዜ ከጐንቶሬቭ ቤተሰብ ስለ ተሰረቁ በጐች ነግረሽኝ የነበረው ትዝ ይልሻል ? ባይገርምሽ እንግዲህ ሁሉንም ነገር ተከታትዬ ደርሼበታለሁ ። በጐቹን የሰረቃቸው በሺካሎቮ መንደር የሚኖር ገበሬ ነው ። ቆዳዎቹ ግን ፣ የት እንደ ደረሱ ታውቂያለሽ ? ቆዳዎቹ የትም አልሔዱ ፤ እዚሁ አባቴ ሱቅ ነው የገቡት . . . . ይኸውልሽ እምነት ፣ ሃይማኖት ይሉሻል ይህ ነው !” አላት ።



አኒሲም ዐይኑን ጠቀስ አድርጐ ራሱን ነቅነቀና ንግግሩን ቀጠለ ።

“ የወረዳው ሹምና ጸሐፊውም በእግዚአብሔር እያምኑም ። ገበዙም ቢሆኑ እንደዚያው ናቸው ። ሁሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው የሚሳለሙትና ቀን ቆጥረው የሚጾሙት ወደው አይደለም ። ከሰው አፍ ፣ ከመንደሩ ሐሜት ለመዳንና ምናልባት ምጽአት ቢመጣ ፣ የመጨረሻው ፍርድ ቀን እውነት ቢሆን ይጠቅመናል በሚል ጥርጣሬ ነው ። ሰዎች ደካማነታቸው እያየለ ፣ እየጐላ በመምጣቱና ወላጆቻቸውን ማክበር በመተዋቸው ፣ የዓለም ፍጻሜ እየተቃረበ ነው እያሉ አንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ ። ግን ሁሉም ፍሬ ከርስኪ ፣ ባዶ ወናፍ ነው ። እኔ እማስበው ምን መሰለሽ እናት ? እኔ እማስበው እንዲህ ነው ። የኛ ችግር የሚባባሰው ሕሊና ያጡ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና እያደገ በመሔዱ የተነሣ ነው ። አየሽ እኔ ሰዎችን ከውጭ ብቻ ሳይሆን ውስጣቸውንም ጭምር ጥርት አድርጌ ዐውቃቸዋለሁ እናቴ ፤ ዐውቃቸዋለሁ ። የተሰረቀ ሸሚዝ በማይበት ጊዜ ፣ የተሰረቀ መሆኑን ለማወቅ የዐይን ጥቅሻ የሚጠይቀውን ያህል ጊዜ እንኳን አይወስድብኝም። አንድ ሰው መጠጥ ቤት ቁጭ ብሎ ሻይ ሲጠጣ ብታይው ፣ ምናልባት ሻይ ይጠጣል ብለሽ ብቻ ይሆናል የምታስቢው። ለእኔ ግን ሻይ መጠጣቱ ብቻ አይደለም የሚታየኝ ። ሕሊና የሌለው መሆኑም ነው ። የውስጡም ጭምር እንጂ የውጪው ብቻ አይደለም ። ቀኑን ሙሉ እግርሽ እስኪነቃ ልትዞሪ ትችያለሽ።ግን አንድም ሕሊና ያለው ሰው አታገኚም ። እና የዚህ ሁሉ ሰበብ ማንም የእግዜርን መኖርና አለመኖር የማያውቅ መሆኑ ነው ። እስቲ እንግዲህ ለማናቸውም ደኅና ሁኚ እናቴ ። ጤናሽን ተንከባከቢ ፤ የመንፈስሽን

ጽናት እንደ ወትሮው ጠብቂ ፤ እኔንም ሁልጊዜ በቅን አስ ቢኝ ” አለ አኒሲም ።

ወዲያው መሬት እስቲነካ ለጥ ብሎ እጅ ነሣት ።

“ ስለ ተደረገው ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ እናት ። አንቺ ለቤተሰባችን ጥሩ ነሽ ። በዚህ ላይ ደግሞ ጨዋነ ትሽና ነገረ ሥራሽ ሁሉ በጣም ደስ ይለኛል ” አለ ፡ ከልብ በመነጨ ስሜት ።ከክፍሉ ሲወጣ ትካዜ ልቡን መውረር ጀምሮት ነበር ። ድንገት ቆም አለና ወደ ቫርቫራ ዞሮ፣

“ ያ ሳሞሮዶቭ ያልኩሽ ጓደኛዬ በአንድ ጉዳይ ውስጥ እጄን እንዳስገባ አድርጎኛል ። ጉዳዩ ወይ ያከብረኛል ወይም ከናካቴው ያወድመኛል ። እና እንዲያው እንዳ ጋጣሚ ፡ በሰስ ሳይቀናኝ ቀርቶ ክፉ ነገር ቢደርስብኝ፡አንቺ ቤተሰቦቼን እንደምታጽናኚልኝ ተስፋ አለኝ ” አላት ።

“ እንደሱ አትበል እስቲ ! እግዜር መሐሪና ይቅር ባይ ነው ። ግን አኒሲም ለሚስትህ ትንሽ ርኅራኄና ፍቅር ብታሳያት ደስ ይለኛል ። ሁለታችሁም የምትተያዩት ልክ እንደ ዱር አውሬ ነው ። ፈገግታ እንኳን ስትለዋወጡ አይቼ አላውቅም ” አለችው ።

“ እሷም ነገሯ ሁሉ ከሰው የማይገጥም ልጅ ናት ። ምንም ነገር አይገባትም ። ምንም ቃል አትተነፍስም ። ደግሞ ዕድሜዋም ገና ነው ። በሚገባ ማደግ ይኖርባታል” አለ አኒሲም ፡ በከባዱ እየተነፈሰ ።

አንድ ረጅም በደንብ የተቀለበ ነጭ ሡንጋ ፈረስ የሚጎትተው ጋሪ ፡ በረንዳው ፊት ለፊት ቆሞ ይጠብቀ ዋል ። ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች በቄንጥ ዘሎ ጋሪው ላይ ቁብ አለና ልጓሙን በጁቹ ያዘ ። አኒሲም ቫርቫራን አክሲንያንና ደንቆሮ ወንድሙን በየተራ ሳማቸው ።



ሊፓም እንደ ሌሎቹ በረንዳው ላይ ቆማ ያላንዳች እን ቅስቃሴ በጸጥታ ወደ ሌላ አቅጣጫ ትመለከታለች ። ተለ ይቷት የሚሔድ ባሏን ለመሸኘት ሳይሆን፡በአጋጣሚ ከቤት ብቅ ያለች የሚያስመስላት ነው ፡ አኳኋንዋ ። አኒሲም ሌሎቹን ስሞ ሲያበቃ ፡ ወደ ሊፓ ተጠግቶ ረጋ ባለ ሁኔታ ጉንጯን በከንፈሮቹ ዳሰስ አደረገና ፡

“ ደኅና ሁኚ ” በማለት አንሾካሾከ ።

ሊፓ አልተመለከተችውም ። ብቻ አንድ ልዩ ዐይነት ፈገግታ መሳ ገጿን ወረሰው ፤ ወዲያው ፊቷ በሙሉ ይን ቀጠቀጥ ጀመር ። ምክንያቱን ሳያውቁት በሥፍራው የተ ሰበሰቡት ሁሉ ፡ ስለርሷ ኀዘን ተሰማቸው ። አኒሲም እንዳ ባቱ ጋሪው ላይ ወጣና በመልካም አቋሙ ፡ መልኩና አለ ባበሱ እንደሚተማመን ሰው ፡ እጆቹን ወገቡ ላይ አሳርፎ ቁጭ አለ ።

ጋሪው ፡ ከሸለቆው ለመውጣት በኰረብታው ላይ በተዘረጋው መንገድ አቀበቱን ሲያያዘው አኒሲም በመ ደጋገም እየተገላመጠ መንደሩን ይመለከት ጀመር ። ሞቃት ፀሐይማ ቀን ነው ። በዚያ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ለግ ጦሽ ወደ መስክ የወጡት ከብቶች እዚህም እዚያም ተበ ታትነው ተሠማርተዋል ። በእረኝነት የተከተሏቸው ሴቶ ችና ልጃገረዶችም በዐውዳመት እንደሚለብሷቸው ያሉ ፀዓዳ ልብሶች ለብሰዋል ። በነጻነቱ የተደሰተ ይመስል አንድ ቀይ በሬ በኃይል አገሣና መሬቱን በሰኰናው መጐ ድፈር ጀመረ ። ታች ሸለቆው መኻልና ላይ ኰረብታው አፋፍ ዘልቆ በየሥፍራው አዕዋፍ ይዘምራሉ ። በታላቅ ግርማ የተኰፈሰውን ቤተክርስቲያን አኒሲም ዞር ብሎ ተመ ለከተው ። በኖራ የታደሰው በቅርቡ ነበር ። ከአምስት ቀናት በፊት በዚያ ቦታ ያደረገው ጸሎት ትውስ አለው ።

አረንጓዴ ጣሪያ ያለውን ትምህርት ቤትና በልጅነቱ ዋና እየዋኘ ዓሣዎች ያጠምድበት የነበረውን ጅረት ተመለከተ ። ልቡ በደስታ ስሜት ጮቤ ይረግጥ ጀመር ። ወዲያው አንዳች ግዙፍ ግድግዳ ከፊት ለፊቱ ተጋርጦ ርቆ ከመሔድ ቢያግደው ተመኘ ።

አባትና ልጅ ፡ ባቡር ጣቢያው ከደረሱ በኋላ ፡ ወደ መዝናኛው ቤት በመግባት አንዳንድ ብርጭቆ የወይን ጠጅ አዝዘው ተጎነጩ ። ሽማግሌው ፡ የመጠጡን ሒሳብ ለመክፈል የገንዘብ ቦርሳውን ከኪሱ ሲያወጣ አኒሲም አቋረጠውና ፡ “ የኔ ግብዣ ነው ” አለው ።

በሁኔታው ልቡ የተነካው ሽማግሌ ፡ የልጁን ትከሻ መታ መታ አደረገና ፡ “ እንደምን ያለ ልጅ እንዳለኝ አየህ !” በሚል ዐይነት አስተያየት ፡ ባሪስታውን በዐይኑ ጠቀሰው ።

“ ከኔው ጋር ቆይተህ በንግዱ ሥራ ብታግዘኝ እንደምን ደስ ባለኝ ነበር ። አንዱና ዋናው ምኞቴም ይኸው ነው ። ያንተ ከጐኔ መሆን ምንኛ እንደሚጠቅመኝ የማውቅ እኔ ብቻ ነኝ ። ቃሌን ሰምተህ እዚሁ ብትቀር እኔም በወርቅ ባንቆጠቆጥኩህ ነበር ልጄ ” አለ ፡ ሽማግሌው ።

“የለም ፡ የለም አባባ ። በፍጹም አልችልም !” የልጅየው መልስ ቁርጥ ያለ ነበር ። የቀረበላቸው የወይን ጠጅ መራር ከመሆኑ ሌላ የሰም ሽታ ቃናውን በርዞታል ። ግን አንዳንድ ብርጭቆ ከመድገም አልተገቱም ።



ሽማግሌው ፡ ልጁን ሸኝቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ ፡ አዲሷ ምራቱን ልዩና እንግዳ ሆና አገኛት ። ባሏ ከቤት ከወጣበት ቅጽበት አንሥቶ ሊፓ ፡ ፍጹም ሠራተኛ ወደ ሆነች ወጣት ሴት ተለውጣ ነበር ። አሮጌ ቀሚስ አጥልቃ እጅጌውን ወደ ላይ በመሰብሰብ ባዶ እግሯን ሆና የበረንዳውን ደረጃዎች በውሃ ታጥባለች ። እየሠራች ደግሞ ድምጿን ከፍ አድርጋ ትዘፋፍናለች ። ወለሉ የታጠበበትን ቆሻሻ ውሃ ከንጨት በተሠራው ባልዲ ሞልታ ለመድፋት ተሸክማ ስትሔድ ደግሞ ፡ ወደ ሰማይ ቀና ብላ የሕፃን በሚመስል ፈገግታ ፀሐይዋን ትመለከታለች ።

እንደ አጋጣሚ ፡ በበረንዳው በኩል የሚያልፍ አንድ ሽማግሌ ሠራተኛ ፡ ራሱን ነቅንቅ አድርጎ ጉሮሮውን ጠራረገና ፡

“ እንዴት እንዴት ያሉትን ምራቶች ነው እግዜር የሰጠህ ግሪጎሪ ፔትሮቪች ! እውነተኛ ሀብት ናቸው !” አለ ።

## —5—

ሐምሌ በገባ በስምንተኛው ቀን ዓርብ ዕለት ነው ፡ ሊፓና ጉጠት ካዛንስኩዬ መንደር ድረስ ሔደው ፡ የካዛን ማርያምን ካነገሡ በኋላ ፡ ወደ መንደራቸው መመለስ ይዘዋል ። ከነርሱ ኋላ ራቅ ብላ የሊፓ እናት ፕራስኮቭያ እያዘገመች ትከተላቸዋለች ። ሕመምተኛ በመሆኗ ትንፋሽ አጥሯታል ። ጀንበር እየዘቀዘቀች ደንገዝገዝ ብሏል ።

“ አሄ ሄ ሄ ሄ! . . . በጄ !” ይላል ጉጠት በማዳነቅ፡ የሊፓን ንግግር እያዳመጠ ። “ መቼም የማርመላታ ነገር አይሆንልኝም ። በጣም ነው የምወደው ኢሊያ ማካሪች !” እያለች ከልቧ ታወራለች ሊፓ ። “ እና ታዲያ ሁልጊዜ

አንድ ጥግ ይገኙ እቀመጥና ሻይ እየጠጣሁ ማርመላታ
መብላት ነው ። ወይም ደግሞ ሻዩን ፉት እያልኩ ሻር
ሻራ ኒኮላየቭና የምትነግረኝን የሚያሳዝኑና የሚያስደንቁ
ታሪኮች አዳምጣለሁ ። መቼም ለግምት የሚያታክት ማር
መላታ ነው ያላቸው ። አራት እንስራ ሙሉ !ታዲያ እነ
ሱም ‘ አይዞሽ ሊፓ አትፍሪ ፤ የቻልሺውን ያህል ብዪ !’
ይሉኛል ” ትለዋለች ።

“ ያንት ያለህ ! አራት እንስራ ሙሉ ! ” ይላል ጉጠት፣
አሁንም በማዳነቅ ።

“ እህሳ ! ሀብታሞች አይደሉ ! ሞልቷቸዋል ። ከሻይ
ጋር የሚቀርበው ጥጥ የመሰለ ነጭ ዳቦ ነው ። የሥጋ ነገር
አይነሣ ። ሁሉም ያምሮቱን ሳይሆን የሚበቃውን ያህል
ሊበላ ይችላል ። የተረፉቸው ናቸው ። ግን በኔ በኩል
ለምን እንደሆነ እንጃ ሁልጊዜ ፍርሃት ይሰማኛል ።
በጣም እፈራለሁ !”

“ ምኑ ነው የሚያስፈራሽ የኔ ልጅ ? ” አለ ጉጠት፣
ፕራስኮቭያ ደርሳባቸው እንደሆን ለማየት ወደ ኋላ እየ
ተገላመጠ ።

“ በመጀመሪያ የሠርጉ ሰሞን የሚያስፈራኝ አኒሲም
ግሪጎሪች ነበር ። በርግጥ ጥሩ ሰው ነው ። ይህን መካድ
አይቻልም ። አንድም ቀን ተተናኩሎኝም ሆነ አስቀይ
ሞኝ አያውቅም ። ግን ወደ አጠገቤ በቀረበ ቁጥር ለምን
እንደሆነ እንጃ የሠራ አካላቴ ሽምቅቅ ይላል ። ዘወትር
እንቅልፍ ባይኔ አይዞርም ። ሌሊቱን በሙሉ ቁልጭ ብዬ
እየተንቀጠቀጥሁ ስጸልይ ነው የማድረው ። እሱ ከሔደ
በኋላ ፍርሃት የምታሳድርብኝ ደግሞ አክሲኒያ ናት ።
በርግጥ እስከ ዛሬ ባየሁት ደኅና ሴት መሆኗን ነው የማ
ውቀው ። ፈገግታ ሁልጊዜ አይለያትም ። ግን አንዳንዴ
የምታደርገው ሁሉ ልዩና ግራ የሚያገባ ነው ። መስኮቱ



አጠገብ ትቆምና ወደ ውጭ በጸጥታ ታስተውላለች ።
ድቅድቅ ባለ ጨለማ ውስጥ የበግ ዐይኖች እንደሚፈነ
ጥቁት ያለ አረንጓዴ ብርሃን በነዚያ ኀይለኛ መሳይ ዐይ
ኖቿ ውስጥ ይንጸባረቃል ። ከሀሪሚን ትንሹ ቤተሰብ ጋር
ያላት ግንኙነት ጥብቅ ነው ። እየመከሩና እያግባቧትም
መሰለኝ ። ‘ ሽማግሌ አማትሽ ፤ ቡቲኪኖ ላይ ከአንድ ጋሻ
የሚበልጥ መሬት አለው ። ዐፈሩ አሸዋማ ስለ ሆነና በአ
ቅራቢያውም ወንዝ ስለሚፈስ ፤ ለምን የጡብ ማምረቻ
ለግልሽ አታቋቁሚም ? እኛም ሸርካዎችሽ እንሆናለን ’
ይሏታል — አክሲኒያን ዘወትር ። ዛሬ የአንድ ሺህ ጡቦች
ዋጋ ደግሞ እስከ ሐያ ሩብል ደርሷል ይባላል ። ትናንትና
ታዲያ ራት ስንበላ አክሲኒያ ‘ ቡቲኪኖ ላይ የጡብ ማም
ረቻ አቋቁሜ የራሴን ንግድ ለመጀመር እፈልጋለሁ ’
አለቻቸው ሽማግሌውን ፤ እንደ ቀልድ አድርጋ እየሣቀች ።
የግሪጎሪ ፔትሮቪች ፊት ግን ፤ ወዲያው ልውጥውጥ አለና
ጠቋቆረ ። ነገሩ ጨርሶ አላስደሰታቸውም ነበር ። ‘ በሕ
ይወት እስካለሁ ድረስ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ የተነጣጠለ
ንግድ አይኖርም ። ሁላችንም አንድ ላይ መሆን አለብን ’
ሲሏት ፤ ባይኗ ከፉኛ ገረመመቻቸውና ጥርሶቿን አፋጨ
ቻቸው ። ከዚያ በኋላ የቀረበላትን ምግብ ንክች ሳታደር
ገው ተመለሰ ። ”

“እሃ! እምቢ ብላ ተወችው ማለት ነው ? ” አለ
ጉጠት ።

“ እንዲያው እኔስ ምን ሰዓት እንደምትተኛም ለማ
ወቅ ነው የምፈልገው ” ሊፓ ንግግሯን ቀጠለች ።
“ ሰው ሁሉ ከተኛ በኋላ እሷም ለወጉ ያህል ጋደም ትልና
አንድ ሰዓት እንኳን ሳትቆይ ብድግ ትላለች ። ከዚያ በኋላ
ቤቱን ከዳር እስከ ዳር ማሰስ ነው ። መንጐራደድ ፤ መመ
ላለስ ፤ መሔድ ፤ መምጣት ማንጐዳጐድ ምኑ ቅጡ ።

እያንዳንዱን ጥጋትና ሥርቻ ትፈትሻለች ። ገበሬዎቹ ያቃጠሉት ወይም የሰረቁት ነገር እንዳለ ለማየት ይሁን ለሌላ ፥ ብቻ ምክንያቱ እስከ ዛሬ አይገባኝም ። እና ይኸውሎት አሊያ ማካሬች ፤ በጣም ነው አክሲኒያ የምታስፈራኝ ።”

አንዲት አነስተኛ ጢሻ አጠገብ ደረሱና ፥ ፕራስኩቭያን ለመጠበቅ ያህል ዐረፍ አሉ ። የሊሳሮቭ በዕድሜው ሙሉ ፈረስ ስላልነበረው ፥ በኮንትራት የሚይዛቸውን ሥራዎች ሲያከናውን የኖረው ወረዳውን በእግሩ እያዳረሰ ነበር። ምንጊዜም በማትለየው ትንሽ ከረጢት ውስጥ ዳቦና ሽንኩርቱን ይዞ በረጃጅም ቅልጥሞቹ ቃዳ ቃዳውን እያፈሰው ሲውዘገዘግ የሚደርስበት አልነበረም ።

በጢሻው መጨረሻ ጠርዝ ላይ የመንገዱን ርቀት የሚገልጽ አንድ ድንጋይ ተተክሏል ፤ ጥንካሬውን ለመፈተሽ ያህል ጉጠት ነቅነቅ ነቅነቅ አደረገው ። ወዲያው ፕራስኩቭያ ቁና ቁና እየተነፈሰች ደርሳ ተቀላቀለቻቸው ። የጠወለገውና ሁልጊዜ የድንጋጤና የሽብር መንፈስ የሚታይበት ጨምዳዳ ፊቷ አለ ወትሮው ፈካ ፥ ወዛ ብሏል ። ከቤተ ክርስቲያን መልስ ገበያው ቦታ ላይ ትንሽ ክባስ* መቅመሷ ያስታውቃል ። የሚበቃቸውን ያህል ዕረፍት አድርገው ጣመናቸውን ካበረዱ በኋላ፥ሦስቱም ጐን ለጐን ሆነው መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ጨርሳ በመጥለቅ ላይ ካለችው ፀሐይ የሚፈነጠቀው ጨረር ትንሿን ጢሻ ዘልቆ በስተማዶ የዛፎቹን ግንዶች አድምቋቸዋል ። ከወደሚሔዱበት አቅጣጫ የሚመጣ የብዙ ሰዎች ድምፅ ሲተም

* ክባስ ፥ እንደ አገራችን ጠላ ሆኖ ከእህል የሚሠራ የሩሲያውያን የባህል መጠጥ ነው ።



ተሰማቸው ። ከፊታቸው በሚገኘው ሌላ ጢሻ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያሉ እንጉዳይ የሚሰበስቡ የኡክሌየቮ ልጃገረዶች ናቸው ።

“እህና የኔ ጉብሎች !” አለ የሊሳሮቭ ድምፁን ከፍ አድርጎ ። ልጃገረዶቹ በሰላምታ መልክ አጸፋውን በሣቅ መለሱለት ።

“ ጉጠት እየመጣ ነው ! ሽማግሌዉ መጣ ! ” እያሉ ተንጫጩ ። የአካባቢው የገደል ማሚቶም አብሮ አስተጋባ ። መንገደኞቹ ጢሻውን ወደ ኋላቸው ትተው ገሠገሡ። የፋብሪካው ጭስ መውጫዎች ቀስ በቀስ ብቅ እያሉ ቁመታቸውም እየጨመረ ሲሔድ ፥ ቤተ ክርስቲያኑ ጉልላት ላይ የተገተረውም መስቀል በምታሽቆለቁለው ፀሐይ ብርሃን ሲያንጸባርቅ ታያቸው ። መንገዳቸው እየተገባደደ ነው ። ወደ ሸለቆው ቁልቁል ትንሽ ከተንደረደሩ በኋላ ፥ በየቤታቸው ይገባሉ ። ረጅሙን መንገድ በባዶ እግራቸው ሲያስነኩት የዋሉት ሊፓና ፕራስኮቭያ ቦት ጫማዎቻቸውን ለማጥለቅ ቁጭ ቁጭ ሲሉ ፥ የሊሳሮቭም አጠገባቸው በሚገኝ ለምለም ሣር ላይ ዐረፍ አለ ። መንደራቸው በቅርብ ያለች ይመስል ወለል ብላ ትታያለች ። ከላይ ወደ ታች ሲያስተውሉት የኡክሌየቮ አካባቢ ልዩ ደስታን ይሰጣል ። ግርማ ሞገሱን እጥፍ ድርብ በሚያደርገው የኩራ ዐፀድ መኻል ጉብ ያለው ፥ ነጭ ቀለም የተቀባ ቤተ ክርስቲያንና ትንሿ ኸረት በአንድነት ሆነው የተዋበ ሥዕል ይፈጥራሉ። ከመኻል ተሰንቅሮ በዚህ ውበት ላይ የሚያስጠላ ነገር ቢኖር ፥ ለቁጠባ ተብሎ ጣሪያው ፈዛዛ ቀለም የተቀባው ወፍጮ ቤት ብቻ ነው ። ከሸለቆው ተነሥቶ በሚያሻቅበው ዳገት ላይ የጠመኸ እርሻ ተንጣሏል ። ገሚሱ ታጭዶ ነዶው እየታሠረ ተቀምጧል ። ገሚሱ ተከምሯል ። ገና አዲስ የታጨደው ደግሞ በመስመር ሆኖ እዚያው መሬቱ

ላይ ተረፍርፏል ። በሌላውም ወገን ለመሰብሰብ የደረሰው የአጃ አዝመራ በመጥለቅ ላይ ባለችው ፀሐይ ብርሃን ውስጥ ይንጸባረቃል ። በግራም በቀኝም መኸር ደረስኩ ደረስኩ እያለ ነው ። ዛሬ በዓል ሆኖ ውሏል ። ነገ ጠመኞና ድርቆሹን ይሰበስባሉ ። የሚቀጥለው ቀን ደግሞ እሑድ ስለሆነ እንደገና ሌላ ዕረፍት ነው ። በየዕለቱ ነጐድጓድ በሩቅ ሲያስገመግም ይሰማል ። በቅርቡ ዝናብ መጣል እንደሚጀምር ሁሉ ፣ አየሩ ከባድና ሞቃት ሆኖ ነው የሰነበተው ። ስለዚህም እያንዳንዳቸው ወደ ማሳዎቹ ፊታቸውን ባዞሩ ቁጥር ፣ ሰብሉ በወቅቱ ተሰብስቦ በገባ የሚል ሐሳብ ይመጣባቸውና ልባቸው በደስታ ስሜት ይሸበራል ።

“ እህል አጫጆቹ ዘንድሮ ቀንቷቸዋል ። ጥሩ ዋጋ እያገኙ ነው ። በቀን አንድ ሩብል ከዐርባ ኰፔክ ቀልድ አይደለም ” አለች ፕራስኰቭያ ።

ከካዛን ማርያምና ከካዛንስኩየ ገበያ የሚጐርፈው ሕዝብ ዕልቆ መሣፍርት የለውም ። ሴቶች ፣ አዳዲስ ኮፍያ ያደረጉ የጥጥ ማባዘቻው ሠራተኞች ፣ ነዳያን ፣ ሕፃናት . . . ለእርሻ ቦታ እንዲሆን ተብሎ የተሠራ ጋሪ አቧራውን ከግሩ ሥር በኃይል እያስነሣ ዐለፈ ። ገኸ አጥቶ የተመለሰ ፈረስ ከጋሪው በስተኋላ በሶምሶማ ይከተላል ። ባለመሸጡ የተደሰተ ይመስላል ። አንድ አስቸጋሪ ብጤ ላም ቀን ዷን ተይዛ እየተጐተተች ዐለፈች ።እግራቸው ወደ መሬት ተንጠልጥሎ እዚያና እዚህ የሚላጋና ሙትት ብለው የሰ ከሩ ገበሬዎች የተጫኑበት ሌላ ጋሪ ተከተለ ። ትልቅ ኰፍያና ከዐቅሙ በላይ የሆነ ቦት ጫማ ደንቅሮ የሚደነቃቀፍ ትንሽ ልጅና አንዲት ባልቴት እየተጓተቱ መጡ ። ጉልበቱን እንደ ልብ አላሳጥፍ ባለው ጫማ ክብደትና በፀሐይዋ ሙቀት ቢዳከምም ፡ ልጁ ያለ ማቋረጥ የመጫወቻ



ጡሩንባውን ይነፋል ። ቁልቁለቱን አገባደው በመገን ጠያው በኩል በመጠምዘዝ ወደ ዋናው መንገድ ከገቡም በኋላ ፣ የጡሩምባው ድምፅ አየሩን እየሰነጠቀ ይሰማል ።

“ እነዚህ የመንደራችን ከበርቴዎች የጤናም አይደሉ ! አንዳች ነገር ለክፏቸዋል ” አለ ጉጠት ። “ ይቅር በለን ብቻ ፣ ደኅና ቀን አምጣ ጌታዬ ! ይገርማችሁዋል ኮ! አሁን በዚያ ፊት ከኰስትየኰቭ ጋር ብዙ ተዳርሰን ነበር። ‘ ኰርኒሱን ለመሥራት ብዙ ዕንጨት ያላግባብ አባክነሃል ’ ይለኛል ከምድር ተነሥቶ ። ‘ ብዙ ? ’ ስል ጠየቅሁት ። ‘ እኔ የተጠቀምኩበት ለሥራው ነው ቫሲሊይ ዳኒሊች ፤ መቼም ዕንጨት ከገንፎዬ ጋር አደባልቄ እንደ ማልበላ ታውቃለህ ’ አልኩት ። ‘ እንዴት ብትደፍር ነው እንዲህ የምትናገረኝ ። አንተ አጋሰስ ! በኮንትራት እንድትሠራ ያደረግሁህ እኔ መሆኔን ዘነጋኸው መሰል !’ አለ ። ‘ እና ታዲያ ምን ይጠበስ? ባንተ ብቻ የኖርኩ መሰለህ ! ያንተን ሥራ ከመጀመሬም በፊት ጦሜን አድሬ አላውቅም ። ዕድሜ ለእጄ ! ’ ልልኩት ። ‘ እናንተ እኮ አጭበርባሪዎች ናችሁ ! አንዱ ካንዱ የማይሻል አላቴ ሁሉ ፣ መች አጣሁዋችሁ ’ አለኝ ። ዝም አልኩት ። ‘እኛ በዚህ ዓለም አታላዮች፣ አጭበርባሪዎች ነን።እናንተ ደግሞ በወዲያኛው ዓለም ተራችሁን ትጋለጣላችሁ’ አልኩ በሐሳቤ ። ታዲያ በማግሥቱ ስንገናኝ ትንሽ ተሽሎት ነበር ። እንዳለፈው ቀን ከአፉ ቀደድ ቀደድ አላለም ። ‘ እባክህ አትቀየመኝ ማካሪች ። ትናንት ከፉ ቃል ተናግሬህ እንደሆነ አጥፍቻለሁ ። መቼም እኔ ትልቅ ነጋዴ እንደ መሆኔ መጠን ላንተም የበላይህ ነኝ ።እና ብናገርም ልትታገሠኝ ይገባል ’ አለኝ ። ‘እርግጥ ነው ። አንተ ትልቅ ነጋዴ ፣ እኔ ደግሞ ተራ አናጢ ነኝ ። ግን ቅዱስ ዮሴፍም አናጢ እንደ ነበር አትዘንጋ ። አናጢነት ጌታን ሳይቀር

የሚያስደስት ትልቅና ክቡር ሙያ ነው ። ሆኖም ራስህን
የኔ የበላይ አድርገህ መቁጠር የሚያረካ ከሆነ ፣ በበኩሌ
ተቀብያለሁ ቫሲሊይ ዳኒሊች ’ አልኩት ። ከዚያን ቀን
ንትርካችን በኋላ ግን ማሰብ ማሰላሰል ጀመርኩ ። ማና
ችን ነን የበላይ ? ነጋዴ ወይስ አናጢ እያልኩ ማውጠን
ጠን ያዝኩ ። በኔ አስተያየት የበላይነቱን የሚይዘው እና
ጢው ነው ልጆቼ ! ሠራተኛው ነው ” አለ ።

ጉጠት ፣ ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ተውጦ ቆየና ፣

“ አዎን ልጆቼ ሁልጊዜ የሚሠራ ፣ ዘወትር ሳይ
ታክት ወገቡን አጥብቆ የሚታገል እርሱ ነው አሸናፊ
የሚሆን ” በማለት ደመደመ ።

አሁን ፀሐይዋ ሙሉ በሙሉ ከእይታቸው ተሰወረች ።
እንደ ወተት የነጣ ጭጋግ ከትንሿ ኸረት አናት ፣ ከቤተ
ክርስቲያኑ ዐፀድና በወፍጮ ቤት ዙሪያ ካለችው ሜዳ
በዝግታ ወደ ላይ እያሠገገ መነሣት ጀመረ ። ምሽቱ ይበ
ልጥ እየጨለመ ሲሔድ ፣ ከታች ብርሃናት ሲስለመለሙ ፣
ጭጋጉም መጨረሻና መድረሻ የሌለውን ጥልቅ ገደል
የሚደብቅ ይመስል ሲያይል ፣ በመረረ ድኅነት ውስጥ
ተወልደው በፍርሃት ከሚሸማቀቁና ጨዋ ከሆኑ ነፍሶ
ቻቸው በስተቀር ፣ ያላቸውን ሁሉ ለሌሎች ገብረው ሕይ
ወታቸውን ሙሉ ከችግር ቁራኛ ሳይላቀቁ ዕድሜያቸ
ውን ለማጠንፈፍ የተዋዋሉት ሊፓና እናቷ አንዳች ነገር
በልባቸው ጠልቆ ይሰማቸው ይሆናል ። እነሱም እንደ
ሌላው በዚህ ምስጢረኛ የፍጥረተ ዓለም ጢውጢዋ
ዘለዓለማዊ በሆነውና በማያቋርጠው የሕያዋን ሰንሰለት
ውስጥ አንዳች ነገር እንደሆኑ እነሱም የበላይነት ያላቸው
ፍጡራን እንደሆኑ ለተወሰነች ቅፅበት ተሰምቷቸው
ይሆናል ። የማታ ማታ ወደ ሸለቆው መኻል መው



ረድ እንደሚኖርባቸው ለጊዜው ዘንግተውና ፍንድቅድቅ
ብለው እየተሣሣቁ በዳገቱ አፋፍ ላይ ቁጭ ብለው የቆ
ዩትም በዚህ መነሾ ሊሆን ይችላል ።

በመጨረሻም ወደ ቤታቸው ደረሱ ። ለእህል አጨ
ዳው የተቀጠሩት ሠራተኞች በዋናው በር አጠገብና ከሱቁ
ፊት ለፊት በሚገኘው ሥፍራ ላይ ተኮልኩለዋል ። በኡ
ክሌየቮ መንደር የሚኖሩ ገበሬዎች አብዛኛውን ጊዜ ለግ
ሪጎሪ ፔትሮቪች ተቀጥረው መሥራት ስለማይፈልጉ ፣
ሽማግሌው ፣ ሠራተኛ ሲያሻው ከሌላ መንደር ነበር የሚቀ
ጥረው ። በዚያ ምሽት ፣ በብርሃን ውጋጋን የሚታዩትም
ሰዎች በረጃጅምና ጥቋቁር ሪዣቸው ከሌላ ሠፈር የመጡ
መሆናቸው ይለያል ። ሱቁ ገና ስላልተዘጋ ፣ ደንቆሮው
የአክሲኒያ ባል ከአንድ ትንሽ ልጅ ጋር ዳማ ሲጫ
ዋት በተከፈተው በር በኩል ይታያል ። እህል አጫጆቹ
ለስለስ ባለ ዝቅተኛ ድምፅ ያንጐራጉራሉ ። ዐልፎ
ዐልፎ ደግሞ በትናንትናው ዕለት የሠሩበት ዋጋ እንዲ
ከፈላቸው አቤቱታቸውን ወርወር ያደርጋሉ ። የጀመሩ
ትን ሥራ ሳያገባድዱ ወደ መንደራቸው ይሔዳሉ በሚል
ሥጋት ያለፈው ሒሳባቸው አልተከፈላቸውም ። ከበረ
ንዳው ትይዩ በሚገኘው የሸመል ዛፍ ጥላ ሥር የሸሚዙን
እጅጌ ጠቅልሎ የተቀመጠው ፔትሮቪች ከአክሲኒያ ጋር
ሻይ ይጠጣል ። ጠረጴዛው ላይ ከተቀመጠው ፋኖስ የሚ
ወጣው ብርሃን ቦግ—ስልም —ቦግ —ይላል ።

በዋናው በር በኩል ከተኮለኰሉት እህል አጫጆች
መሐል አንዱ ፣ “ አባታችን ! ” አለ ፣ ተንኮል የተቀላ
ቀለበት በሚመስል ድምፅ ። “ ግማሹን እንኳን ስጠን እባ
ክህ ! ግማሹን ብቻ ! አባታችን ! ”

የብዙ ሰዎች ሣቅ በአንድነት እስተጋባና ከቀድሞው ይበልጥ የለሰለሰ እንጉርጉሮ እንደገና ቀጠለ ። ጉጠት ፣ ሻይ ለመጠጣት ወደ ጠረጴዛው ሔዶ ተቀመጠ ።

" ተመስገን ! ዛሬ ከዛንስኩዬ ውለን መጣን " አለ ጉጠት ። " ሁሉም ነገር ደኅና ነበር ። አንድ ደስ የማይል ነገር ባያጋጥመን ኖሮ ጥሩ ነበር . . . . . ሳሻን ታውቁት የለ ? ያ ቀጥቃጩ ! ባለ እጁ ሳሻ ! ምን ይሆናል መሰላችሁ ? እዚያው ገበያው መሐል ሳሻ ሆዬ ትምባሆ ገዝቶ ሲያበቃ የግማሽ ሩብል ሳንቲም ለነጋዴው ይሰጣል ። ሳንቲሙ ደግሞ የሐሰት ገንዘብ ሆኖ መገኘት ! " ጉጠት ፣ በሹክሹክታ ለመናገር ፈልጎ ወደ ኋላው ገልመጥ በማለት አስተዋለ ። ግን በዚያ ሻካራና በከፊል ታፍኖ የሚያስገመግም ድምፁ እንደ ምንም አድርጎ ቢናገር ማንሾካሾክ አይችልም ነበር ። " እና እንዳልኳችሁ የሐሰት ገንዘብ መሆኑ እንደ ታወቀ ፋታም አልሰጡት ። ' ከየት ነው ያገኘኸው ? ' በሚል ጥያቄ ያዋክቡት ጀመር ። ' አኒሲም ፂቡኪን ነው የሠርጉ ዕለት የሰጠኝ ' ሲል ይመልሳል ። ወዲያው ፖሊስ ተጠርቶ ሳሻን አንጠልጥሎ ወሰደው ። ስለዚህ ትንሽ ጠንቀቅ ማለቱ አይከፋም ፔትሮቪች ። ጣጣ ውስጥ እንዳትገባ ። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች ወሬ ማናፈስ ጀምረዋል " አለ ጉጠት ።

" አባ —ታ —ች —ን ! " የመጀመሪያው ድምፅ አሁንም ከወደ ዋናው በር በኩል ተሰማ ። " ኧረ . . . . አባ ታ—ች—ን ! "

እንደገና ደግሞ ጸጥታ ሆነ ።

" ኧረረ —ረ— ረ— ረ ! አቤት !" ጉጠት በተፋጠነ ሁኔታ እያጉረመረመ በዝግታ ከመቀመጫው መነሣት ጀመረ ። እንቅልፍ ተጫጭኖት ነበር ።" እግዜር ይስ



ጣችሁ ልጆቼ ፣ ስለ ሻዩና ስለ ስኳሩ በጣም አመሰግናለሁ ። ታሁን በኋላ የመኝታ ሰዓት ነው ። ሽማግሌና ዶሮ በጊዜ ተብሎ የለ ? ከእንግዲህ እኮ እያረጀሁ ነው ። የሠራ አካላቴ እየዛገ ፣ እየላሸቀ ነው . . . . እህህህ ! " አለና የሞት ሞቱን እያቃሰተ ከቅምጡ ተነሥቶ ቆመ ። ከመሔዱ በፊት ግን ፣

" የዚህ ትርጉሙ ምን መሰላችሁ ? ሞት ተቃረበ ማለት ነው " አለና እንደ መንሡቅሡቅ ሞካከረው ።

ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች የጀመረውን ሻይ ሳይጨርስ ፣ በተቀመጠበት በሐሳብ ጭው ብሎ ነጐደ ። ጉጠት ፣ ከግቢው ወጥቶ ቢርቅም እንኳን የኮቴው ድምፅ ገና በአጠገቡ እንዳለ ሆኖ ይሰማዋል ።

" ሳሻ ብረት ቀጥቃጩ የተናገረው ሁሉ ውሸት መሆን አለበት " አለች አክሲኒያ ፣ አማቷ በዚያ ቅጽበት የሚያስበውን በመገመት ።

ግሪጎሪ ተነሥቶ ወደ ቤት ገባና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሲመለስ ፣ ትንሽ የተጠቀለለች ነገር በእጆቹ መሐል ይዟል ። ጥቅሉን ሲፈታው አዳዲስ ሳንቲሞች ጠረጴዛው ላይ ተዘርግፈው ያብለጨልጩ ጀመር ። አንዱን አንሥቶ በጥርሶቹ ነክስ በማድረግ ከሞከረው በኋላ ፣ መልሶ ትሪው ላይ ወረወረው ። እንደገና ሌላ አነሣና እንደ መጀመሪያው ወረወረው ።

" የሐሰት ሳንቲሞች ናቸው . . . . " አለ አክሲኒያን በመደነቅ ሁኔታ እየተመለከታት ። " እነሱው ናቸው . . . . አኒሲም ያመጣቸው ፣ የርሱው ገጸ በረከቶች ናቸው ። ይኸውልሽ ልጄ ፣ አንቺ . . . . ውሰጂው " አለ ሽማግሌው በሹክሹክታ ፣ ጥቅሉን በሙሉ

አክሲኒያ እጆች ውስጥ እየወሸቀ ። “ ውስጇና በሙሉ
ውሃ ጉድጓድ ውስጥ ጨምሪው ። ከእንግዲህ ማን ይፈ
ልጋቸዋል ? ወሬ እንዳይዛመት ግን ተከታተይ ። ችግር
ሊፈጠር ይችል ይሆናልና አደራ ። በይ ልጄ ፣ ሳሞቫሩን
አንሺና ፋኖሱንም አጥፊው . . . . ” ብሏት ሔደ ።

የዋናው መኖሪያ ቤት መብራቶች አንድ ባንድ
ሲጠፉ ፣ ሊፓና እናቷ ፕራስኮቭያ ጋሪ በሚቆምበት ታዛ
ውስጥ ቁጭ ብለው ያስተውላሉ ። ፎቁ ላይ ከሚገኘው
የቫርቫራ ክፍል ውስጥ በመስኮቱ በኩል የሚታየው መብ
ራት ብቻ ሳይጠፋ ቀየ ። በቫርቫራ መኝታ ቤት ውስጥ በቅ
ዱሳን ምሥሎች ፊት ለፊት ቀይና ሰማያዊ መብራቶች
እየተንቦገቦጉ ሰላምን ፣ ርካታንና የዋህነትን የሚያንጸባ
ርቁ ይመስላሉ ።

ሊፓ ፣ ከሀብታም ሰው ጋር የፈጸመችው ጋብቻ ለና
ትየዋ በፍጹም ሊዋጥላትም ሆነ ሊጥማት አልቻለም ።
ልጅዋን ልትጠይቅ በምትመጣ ጊዜ ቤቱ ደጃፍ ላይ ቁጢጥ
ብላ ለስሙ ፣ ለወጉ ያህል የግዷን ፈገግ ትላለች ። የማታ
ማታም ሻይና ስኳር አለችበት ድረስ ይላክላታል ። የሊፓም
ስሜት ከናቷ የተለየ አይደለም ። የጋብቻዋ ነገር እም
ብዛም አልተወሐዳትም ። ይባስ ብላ አኒሲም ወደ ሥራው
ከተመለሰበት ቀን አንሥቶ አልጋዋ ላይ መተኛቱን እርግፍ
አድርጋ ትተዋለች ። በተመቻት ሥፍራ ጋደም ትላለች ።
ማድ ቤት ፣ ታዛው ውስጥ . . . . ዘወትር የቤቱን ወለል
ስትፈገፍግ ወይም የቤተሰቡን ልብስ ሰብስባ ስታጥብ
ትውላለች ። ራሷን የምትቆጥረው እንደ ቤተሰብ ሳይሆን
እንደ ቅጥር ሠራተኛ አድርጋ ነበር ። ከናቷ ጋር የካዛን
ማርያምን አክብረው የተመለሱ ዕለት ከወጥ ቤት ሠራ
ተኛይቱ ጋር ሻያቸውን ከጠጡ በኋላ፣ወደ ታዛው በመሔድ
ወለሉ ላይ ጋደም ጋደም አሉ ። ታዛው ውስጥ በቆመው



ተንሸራታች የበረዶ ሠረገላና በግድግዳው መሐል ጨለ
ማው ጥቅጥቅ ብሏል ። የበቅሎና የፈረስ ዕቃ ሽታ ያለማ
ቋረጥ አፍንጫን ይወጋል ። የዋናው ቤት መብራቶች ሙሉ
በሙሉ ከጠፉ በኋላ ፣ ደንቆሮው ስቴፓን ሱቁን ሲቆላልፍ
ግቢውን የሞሉት እህል አሜጆች ደግሞ ለመተኛት ይተ
ረማመሱ ጀመር ። ራቅ ብሎ ከሀሪሚን ትንሹ ቤተሰብ
መኖሪያ አካባቢ ውድ የሆነው አኮርዲዮን ድምፅ ይሰ
ማል ። ብዙም ሳይቆዩ ሊፓና እናቷን ድብን አድርጎ እን
ቅልፍ ወሰዳቸው ።

የአንድ ሰው ኮቴ በአጠገባቸው ሰምተው ሲባንኑ
አካባቢያቸው ብርሃን ብቻ ሆኗል ። ጨረቃዋ ፣ መሐል
ሰማይ ላይ ተንጠልጥላ ስታንጸባርቅ የምታሾፍባቸው ትመ
ስላለች ። አክሲኒያ ፣ የአልጋ ልብሶቿን በእጅዋ ይዛ ታዛው
መግቢያ ላይ ቆማ አይዋት ።

“ ከቤቱ ይልቅ እዚህ ትንሽ ቀዝቀዝ ሳይል አይቀ
ርም ” አለች አክሲኒያ ፣ ወደ ታዛው እንደ መዝለቅ በማ
ለት መድረኩ ላይ ለመተኛት እየተዘገጃጀች ። አካሏ ሙሉ
በሙሉ በጨረቃዋ ብርሃን ጉልቶና ደምቆ ይታያል ።

አየሩ በጣም ስለሚወብቅ ፣ አክሲኒያን እንቅልፍ ሊወ
ስዳት አልቻለም ። አሁንም አሁንም በከባዱ እየተነፈሰች
ትገላበጣለች ። ልብሷን በሙሉ ከላይዋ ላይ ወርውራ
በዚያ የጨረቃ ብርሃን ራቁቷን ስትታይ ፣ አክሲኒያ ውብ
ብቻ ሳይሆን ኩሩ አውሬም ትመስላለች ። ብዙም ሳይ
ቆይ የሌላ ሰው ኮቴ ተሰማ ። ሽማግሌው ከላይ እስከ
ታች ነጭ ለብሶ ደጃፉ ላይ ተገትሯል ።

“ አክሲኒያ ! የት ነው ያለሽው ? እዚህ ነሽ?” ተጣራ።

“ ምንድነው እሱ ?” አለች ፣ በቁጣ አነጋገር ።

“ ያን ገንዘብ ፡ ውሃ ጉድጓድ ውስጥ እንድትጨምሪው ነግሬሽ ነበር . . . እንዳልኩሽ አረግሽ ”

“ ለምን ብዬ ! ሰው እንዴት ንብረቱን ውሃ ጉድጓድ ይጨምራል ። ገንዘቡን ለእህል አጫጆቹ አከፋፍያቸዋለሁ ። ምኑ ሞኝ ነው እቴ! ”አለች ።

“ አቤት እመ ብርሃን ! ” አለ ሽማግሌው መሽበርና መደናገጡን በሚገልጥ የጐላ ድምፅ ። “ አንቺ የተረገምሽ ሴት ! . . . አቤት አምላኬ ! ”

ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ እጆቹን በአንድ ላይ አጣምሮ እያጉረመረመ በዝግታ ተመልሶ ሔደ ። ብዙም አልቆየች አክሲኒያም ከተኛችበት ተነሥታ የአልጋ ልብሶቹን ሰብስባ ከታዛው ወጥታ ሔደች ።

“ ከእንዲህ ዐይነቱ ቤተሰብ ጋር ለምን አጋባሽኝ እናቴ ?” አለች ሊፓ ።

“መቼም ሰው ሆኖ ከጋብቻ የሚቀር የለም ልጄ ። የዚህ ወሳኞቹ ደግሞ እኛ ሳንሆን ሌሎች ናቸው ። ” ፕራስኰቭያ መለሰችላት ።

በመጽናናት ሊመለስ የማይችል ዐይነት የኀዘን ስሜት ሁለቱንም ዋጣቸው ። ብቻ ከዋክብቱ በተንጠለጠሉበት ሰማያዊ ሰማይ ላይ ሆኖ ቁልቁል በአክሌየቮ የሚካሔደውን ሁሉ የሚያስተውል መኖሩ ይሰማቸዋል ። እና ምንም እንኳን ክፋትና ጥፋት ቢገንም ፡ ምሽቱ ግን የረጋና እጅግ የተዋበ ነው ። የጨረቃዋ ብርሃን ከምሽቱ ጋር እንደ ተዋሐደ ፡እንደ ሠመረ ሁሉ በምድር ላይ ያለው ማናቸውም ነገር ከፍትሕ ፡ ከእውነትና ከትክክለኝነት ጋር ለመዋሐድ ቀኑን ፡ጊዜውን ይጠብቃል ።



ሊፓና እናቷ መንፈሳቸው ጸጥ ብሎ ሲረጋጋ እንደ ተቃቀፉ የሰላም እንቅልፍ ወሰዳቸው ።

—6—

አኒሲም የሐሰት ገንዘብ አዘጋጅቶ በማሠራጨቱ ተከሶ ወደ እስር ቤት የመግባቱ ዜና ኢክሊየቮ ከደረሰ ሰነበተ ። ወራት ተቆጠሩ ። አንድ መንፈቅ ዐለፈ ። ረጅሙ ክረምት ወጣና ፀደይ ባተ ። አንድ ሰሞን የመንደርተኛው አፍ ማሟሻ የነበረው የአኒሲም ወሬ በቤተሰብ ዘንድ ሳይቀር እየተረሳ መሔድ ጀመረ ። ግን በግሪጎሪ ፔትሮቪች መኖሪያ ቤትና በሱቁ አጠገብ የሚያልፍ ማናቸውም ሰው የአኒሲም እስረኛነት ትውስ ሳይለው አይቀርም ። ሰውሞቶ የፍትሐት ደወል ባስተጋባ ቁጥር፣አኒሲም ከወህኒ ቤት ግድግዳዎች ጋር ተፋጥጦ ፍርዱን በመጠባበቅ ላይ መሆኑን የሚያስታውስ ሌላ መረዋ በሁሉም የመንደሩ ነዋሪ ሕሊና ያቃጭላል ።

በሽማግሌው ፔትሮቪች ቤተሰብ ላይ ከባድ ጥላ ያንዣብባል ። የቤቱ ግድግዳዎች ሁሉ ከዕለት ወደ ዕለት በጽልመት እየተዋጡ የሚሔዱ መሰሉ ። የጣሪያው ቆርቆሮዎች መዛግ ጀመሩ ። በብረት ተጠናክረው የተሠሩት የሱቁ መዝጊያዎች ቀለማቸው እየለቀቀ ብረቶቹም ተወለቃቀሙ ። የሽማግሌው መጠጻቆርና መጐሳቆል ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት ሔደ ። ጠጉሩን መስተካከልና ጢሙን መላጩት ከተወ ረጅም ጊዜያት በማለፉ ፊቱን ጭጉጉት የወረሰው መሰለ ። ቀድሞ ጋሪው ላይ በሚዣፈር ጊዜ የሚያሳየው መጀነንና ቄንጥ ከነቅልጥፍናው ቀረ ። ደጃፉ ላይ ቆመው ቁራሽ እንዲጥልላቸው በሚማጠኑት ነዳያን ላይ

“ እግዜር ይስጣችሁ ” እያለ ማንባረቁን እርግፍ አድርጎ ተወው ። ከዕለት ወደ ዕለት እየደከመና እየዛለ ከሚሔደው ኃይልና ጉልበቱ ጋር የመንደሩ ሰዎች ቀድሞ ያሳዩት የነበረው ፍርሃትና አክብሮትም እየሟሟ ሔደ ። ያካባቢው ፖሊስ እንኳን የተለመደ ወፍራም ጉቦውን ማግኘቱ ባይቋረጥም በሱቁ ውስጥ ስለሚካሔደው ሕገ ወጥ ንግድ ክስ ከመመሥረት አልተቆጠበም ። ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በሱቁ ውስጥ የአረቄ ንግድ ያካሒዳል ተብሎ በቀረበበት ክስ የተነሣ ፣ ሽማግሌው ሦስት ጊዜ ያህል ከተማ ድረስ እየሔደ ፍርድ ቤት ቀረበ ። ብቻ ሦስቱንም ጊዜ ምስክሮች አልተሟሉም እየተባለ በቀጠሮ ቀረ ። እንግልቱ ግን ሽማግሌውን በአካልና በመንፈስ ይበልጥ አደቀቀው ።

ዘወትር ወደ ከተማ እየሔደ እስረኛ ልጁን ይጠይቃል። ጠበቃም አቆመለት ። በዚያ ላይ ለየባለሥልጣኑ አቤቱታውን ፥ለየታቦታቱ ደግሞ ጧፍ ዕጣኑን ስለት ያገባል ። ልጁ ለታሰረበት ዘብጥያ አዛዥ ሳይቀር ፥ “ ነፍስ ርኅራኄን ታውቃለች ”የሚል ዐረፍተ ነገር የተቀረጸበት ከብር የተሠራ የብርጭቆ ማቅረቢያና ረጅም የብር ማንኪያ በስጦታ አቀረበለት ።

“ የሚረዳን፥ ሔደን የምንማፀነው እገሌ የሚባል ሰው የለንም ” ትላለች ቫርቫራ ሁል ጊዜ ። “ ሌላው ቢቀር በዋስ እንዲፈታ ለባለሥልጣኖች ደብዳቤ እንዲጽፉልን ያካባቢውን ባላባቶች መለመን ይገባናል . . . . ያ ምስኪን ልጅ ምን በወጣው ነው እስር ቤት የሚማቅቀው ? ” ትላለች ።

ቫርቫራ ጥልቅ ኀዘን ቢሰማትም፥ይበልጥ እየወፈረችና እያማረባት መሔድ ጀመረች ። እንደ ተለመደው በቅዱሳት ምሥሎች ፊት ለፊት ያሉትን ሻማዎች ሳታስተጓጉል ትለኩሳለች ። ቤቱ ውስጥ ያለው ማናቸውም ነገር በሥነ ሥር



ዓት መጠበቁን ከመከታተል አትቦዝንም ። እንግዶች በሚጐበኟቸውም ጊዜ ከማርመላትና አትክልት የተዘጋጁ ጣፋጭ ምግቦችን አቅርባ ትጋብዛለች ። አክሲኒያና ደንቆሮ ባሏም እንደ ተለመደው በሱቁ ውስጥ ንግዱን ያካሒዳሉ ። በተለይ ደግሞ ቡቴኪኖ የጡብ ማምረቻ የማቋቋሙን ሥራ ጀምረው ያጣድፉታል ። አክሲኒያ የሽማግሌውን ጋሪ ራሷ እየነዳች በየቀኑ ወደ ሥራው ቦታ ትመላለሳለች።ሊፓም ዐቢይ ጦም ከመግባቱ ቀደም ብሎ ከወለደችው ሕፃን ልጅዋ ጋር ቀኑን ሙሉ ስትጫወት ትውላለች ። ኒኪፎር የሚል ስም ያወጡለት የአኒሲም ልጅ ቀጫጫና በሽተኛ ብጤ ነበር ። ሊፓ ልጅዋን ከማጫወት በስተቀር ሌላ የሚያረካት ነገር ያለ አይመስልም ። ሕፃኑ ትንሽ አልጋው ውስጥ ተንጋሎ ሲጫወት እናቱ ወደ በሩ አጠገብ በመሔድ ጐንበስ ብላ እጅ ትነሣውና ፥

“ እንደ ምን ዋልክ ኒክፎር አኒሲሚች ” ትለዋለች ። ወዲያው ተንደርድራ ወደ አልጋው በመመለስ ዕቅፍ ኦድርጋ በናትነት ፍቅር ትስመዋለች ። ደግሞ ወደ በሩ ተመልሳ በመሔድ እንደገና እጅ እየነሣች እንደ ቀድሞው ታጫውተዋለች ። ሕፃኑም ትንንሽ ቀያይ እግሮቹን ፍርግጥ ፍርግጥ እያደረገ ይሥቃል ። እየሣቀ ደግሞ ያለቅሳል ። እያለቀሰም ይሥቃል - ልክ እንደ አናጢው የሊሳሮቭ ።

በመጨረሻም አኒሲም ለፍርድ የሚቀርብበት ቀን ታወቀ ። ዕለቱ ከመድረሱ አምስት ቀናት ቀደም ብሎ ሽማግሌው ወደ ከተማ ሔደ ። መጥሪያ የደረሳቸው ጥቂት የመንደሩ ገበሬዎችና ግሪጐሪ ፔትሮቪች ዘንድ ተቀጥሮ የሚሠራ አንድ ሽማግሌ ፥ ለምስክርነት ከተማ መውጣታቸው ተጋኖ ይወራ ጀመር ።

የውሳኔው ቀጠሮ የዋለው ሐሙስ ላይ ቢሆንም እሑድ ፥ ቅዳሜ ፥ሰኞ ዐለፉ ። ሽማግሌው ግን ወደ ቤቱ አልተመለ

ሰም ። ወሬም አልነበረም ። ማክሰኞ ወደ ማታ ገደማ ቫር
ቫራ በተከፈተ መስኮት አጠገብ ተቀምጣ ጀሮቿን ቀስራ
ወደ ውጭ እያዳመጠች የሽማግሌውን መምጣት ትጠ
ባበቃለች ። እሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ሊፓ ሕፃን ልጅዋን
ጉልበቷ ላይ አስቀምጣ እያስጨፈረች በዜማ ታጫውተ
ዋለች ።

“ የኔ አንበሳ! ታድግልኝና ትልቅ . . . ትልቅ ትሆ
ንልኝ የለ? ትልቅ ሰው ስትሆንልኝ ደግሞ አብረን እንሔ
ድና አንዱጋ ተቀጥረን እንሠራለን ። እሺ ! አብረን አንድ
ላይ እሺ! ”ትለዋለች ።

“ወየው ጉድ ! ምንድነው ይሄ መሔድ ፡ መቀጠር ብሎ
ነገር ቂል ! ልጁ እንደሆነ ሲያድግ ትልቅ ነጋዴ ቱጃር ነው
የሚሆን ” አለች ቫርቫራ ፡ ሌላው ክፍል ሆና ።

ሊፓ ፡ ወዲያው ለስለስ ባለ ድምፅ ታንጐራጉር
ጀመር ። ግን ብዙም አልቆየች ፤ ሁሉንም ነገር ረስታው ፡

“ ስታድግ ትልቅ ትሆንልኛለህ ! ያኔ ታዲያ አብረን
እንወጣና አብረን እንሠራለን ! ” ማለቷን ቀጠለች ።

“ጤናም አልያዘሽ አንቺ ። ጀመረሽ ደግሞ እንደገና”
ቫርቫራ አሁንም ከሌላው ክፍል ጮኸችባት ።

ሊፓ ኒኪፎርን በእጇቿ ታቅፋ ቫርቫራ ወዳለችበት
ክፍል በሚያስገባው በር ላይ ቆም አለችና ፡

“ለምንድነው እንዲህ ነፍሴ ምንጥቅ እስክትል የም
ወደው እናቴ? ምንድነው ምክንያቱ ? ” ስትል ጠየቀች
ቫርቫራን ። ግን ድምጿ ድንገት ጉረሮዋ ውስጥ ተሰነቀረና
ተቋረጠ ። በዐይኖቿ ግጥም ያለው እንባ እንደ ዕንቊ ያን
ጸባርቅ ጀመር ። “ ለመሆኑ ማነው እሱ? ምንድነው እሱ?



እንዲህ ያለ እንደ ላባ የቀለለ ሚጢጢ ነገር ። እኔ ደግሞ
ልክ እንደ ደንበኛ ሰብአዊ ፍጡር እየቆጠርኩት ከእን
ጀቴ ውድድ አደርገዋለሁ ። እይው እስቲ ፤ አንዲት ቃል
እንኳን መተንፈስ አይችልም ፤ ግን ዐይኖቹን በማየት
ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ አውቅለታለሁ ” አለቻት ።

ቫርቫራ እንደገና ጆሮቿን ወደ ውጭ ቀሰረቻቸው ።
የምሽት ባቡር መግባቱን የሚያስታውቅ ድምፅ ሰማች ።
ሽማግሌውን ይዞ ይሆናል ። ሊፓ የምትናገረውን አንዷንም
ቃል አልሰማችውም ። ደቂቃዎቹ እየተከታተሉ ሲያል
ፉም አልታወቃትም ። ብቻ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ
ትንቀጠቀጣለች ። የሆነውን ሁሉ ለማወቅ ካደረባት
ጉጉት እንጂ ፡ ከፍርሃት የተነሣ አልነበረም ። ጥቂት ገበ
ሬዎች የተሣፈሩበት ጋሪ በኃይል እየተንኳኳ በግቢው
በኩል ሲያልፍ ተሰማት ። ምስክሮቹ ወደ ቤታቸው መመ
ለሳቸው ነበር ። የነርሱ ሠራተኛ የሆነው ሽማግሌ ከጋሪው
ወርዶ ወደ ግቢው ገባ ። ሰዎች ሰላም ሲሉትና ጥያቄ
ሲያቀርቡለት ይሰማታል . . . .

“ ማንኛውንም መብቱን ተገፎና በንብረቱ ከመጠ
ቀምም ታግዶ ሳይቤሪያ ! . . . . . ስድስት ዓመት ፅኑ እሥ
ራት ”አለ ሽማግሌው ሠራተኛ ፡ ጐላ ባለ ድምፅ ለጥያ
ቄው ሲመልስ ።

አክሲኒያ በስተኋላ በር በኩል ከሱቁ ወጣች ። ላምባ
ስትሸጥ በመቆየቷ በአንድ እጅዋ ጠርሙስ ፡ በሌላው
ማንቆርቆሪያ ፡ በጥርሶቿ ደግሞ ጥቂት ሳንቲሞች ነክሳ
ይዛለች ።

“ ታዲያሽ አባባሽ የታየ?” እየተንተባተበች ጠየ
ቀች ።

“ማዶ ጣቢያ ቀርቷል ። በደንብ ላይን ሲይዝ ነው የምመጣው ብሏል ” አለ ሽማግሌው ሠራተኛቸው ።

በአኒሲም ላይ ጽኑ እሥራት እንደ ተፈረደበት ሲረጋገጥ ፣ ምግብ አብሳይዋ ማዕድ ቤት ውስጥ ሆና እሪታዋን ለቀቀችው ። ሰው የሞተባት ትመስላለች ። የግቢው ውሾችም መጯጯህ ቀጠሉ ። ቫርቫራ ወደ መስኮቱ ተንደርድራ ድምጿን ሰለል በማድረግ ወጥ ቤት ሠራተኛዋ ላይ አንባረቀችባት ።

ያን ዕለት የሻይ ማፊያውን ሳሞቫር ለማሞቅ የሚጨነቅ ሰው አልነበረም ። ሁሉም ራሳቸውን የዘነጉ መሰሉ ። ስለ ተፈጠረው ሁኔታ ምንም ያልገባት ሊፓ ብቻ ነበረች ። ረጋ ባለ መንፈስ ሕፃን ልጅዋን እያቆላመጠች ማጫወቷን ቀጠለች ።

ሽማግሌው ፣ ከባቡር ጣቢያው ወደ ቤቱ ሲመጣ ስለ ምንም ጉዳይ የጠየቀው ሰው አልነበረም ። እሱም ሰላምታ ብቻ አቅርቦላቸው ከገባ በኋላ ፣ ከክፍል ክፍል በጸጥታ መንጐራደድ ጀመረ ። ራት ቢቀርብለትም አልበላ አለ ።

“ከእንግዲህ ወደ ማን እንሔዳለን ። ያኔ ያካባቢውን ባላባቶች መማጠን እንዳለብዎ ስነግርዎ ሊሰሙኝ አልፈቀዱም ። አቤቱታዎን ለበላይ መላክ ነበረብዎ . . . ” አለች ቫርቫራ ፣ ኋላ ለብቻቸው በሆኑ ጊዜ ።

“በበኩሌ የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ሞክሬአለሁ ።” አለ ሽማግሌው ፣ እጁን በማወናጨፍ ። “ የፍርዱ ቃል ከተነበበ በኋላ ወደ ጠበቃው ሔጄ ነበር። ከአሁን በኋላ ምንም ለማድረግ አትችልም ። ሁሉም ነገር ዘግይቷል አለኝ ። አኒሲም የተናገረኝም ልክ እነዚሁኑ ቃላት ነበር ። ‘ነገሩ ሁሉ ዘግይቷል ’ ግን ከፍርድ ቤቱ በኋላ ከአንድ ሌላ ነገረ



ፈጅ ጋር ተነጋግሬአለሁ ። ሊረዳኝ ተስማምቶን ጥቂት ገንዘብ ቀብድ ሰጥቼዋለሁ ። እና ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደዚያው ተመላሽ ነኝ ። ለማንኛውም እግዜር ያውቃል እስቲ!” አለ ።

ሽማግሌው እንደገና ከክፍል ክፍል ሲንጐራደድ ፣ ሲንቆራጠጥ ከቆየ በኋላ ፣ ወደ ቫርቫራ ዘንድ ተመለሰ ።

“ ግድ የለሽም ሳያመኝ አልቀረም ፤ አንጐሌ ልክ በጭጋግ እንደ ታፈነ ዐይነት ሆኖ ነው የሚሰማኝ ። በደንብ ማሰብ ሁሉ ተስኖኛል ” አለ ፔትሮቪች ፣ ለሚስቱ ወዲያው የሚነጋገሩትን ሊፓ እንዳትሰማቸው በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘጋና ።

“ የገንዘቤ ነገር በጣም እያሳሰበኝ ነው ። ከሠርጉ በፊትና ከዳግማዊ ትንሣኤ በኋላ ፣ አኒሲም ያመጣልኝን አዳዲስ ሳንቲሞች አይተሻቸው የል? አንድ ጥቅል የሚሆነውን ጥየዋለሁ ። ቀሪው ከራሴ ገንዘብ ጋር ተደባልቋል . . . . ነፍሱን ይማረውና አጐቴ ዲሚትሪ ፊላቲች በሕይወት ሳለ ሸቀጣ ሸቀጥ ለመግዛት አንዴ ወደ ክራይሚያ አንዳንዴም ወደ ሞስኮ ይሔድ ነበር ። የሚገርምሽ ግን ፣ እሱ ለገበያው እዚያና እዚህ በሚል ጊዜ ሚስቱ ከሌሎች ወንዶች ጋር ትማግጣለች ። ስድስት ልጆች ነበሯቸው ። ታዲያ አጐቴ መቼም ግድየለሽ ነበርና መጠጥ ደኅና አድርጎ ወስዶሞቅ በሚለው ጊዜ እየሣቀ፣ እኔኮ የራሴ ልጆች የትኞቹ እንደሆኑ ፣ የኔዎቹ ያልሆኑት ደግሞ የትኞቹ እንደሆኑ ለመለየት አልችልም እያለ ይናገር ነበር ። እና አየሽ ፣ እኔም አሁን ከገንዘቤ ውስጥ የትኛው ትክክለኛ ፣ የትኛው ደግሞ የሐሰት እንደሆነ ለመለየት አቅቶኛል ። እንዲያውም ገንዘቤ በሙሉ የሐሰት እየመሰለኝ መሔድ ጀምሯል ”አላት ።

“ስለ አምላክ ይሁንብዎና እንዲህ አይበሉ ” አለች ።
ቫርቫራ በልመና መልክ ። “ምን ላድርግ ብለሽ ነው ።
ወድጄ መሰለሽ! ለምሳሌ ወደ ባቡር ጣቢያው ሔጄ ቲኬት
ለማስቆረጥ ሦስት ሩብል ከኪሴ ፡ ሳወጣ እነዚህም የሐሰት
ገንዘቦች ቢሆኑስ እያልኩ እሠጋለሁ ። ታዲያ ነገሩ በጣም
ያስፈራኛል ። ግድ የለሽም ዘንድሮ ሳልታመም አልቀ
ረሁም ”አላት ።

“ምንም ይሁን ምን ሁላችንም በግዜር እጅ ነው
ያለነው ” አለች ቫርቫራ ፡ ራሷን እየነቀነቀች ። “ስለ
እር
ጉዳዩ ልናስብበት ይገባል ግሪጎሪ ፔትሮቪች . . . . እር
ስዎ ከእንግዲህ ወጣት እየሆኑ አይሔዱም ። መቼም ሰውና
ዕንጨት ተሰባሪ ነውና ድንገት ሞት ቢመጣ ይሄ የልጅ
ልጅዎም ብዙ ነገር ሊደርስበት ይችላል ። ለኒኪፎር ዘወ
ትር እየተጨነቅሁ ነው ። አባቱ ባጠገቡ ስለሌለ ፡አባት
አልባ ከሆነ ልጅ ምንም ያህል አይሻልም ። እናቱም እን
ደምታውቂት ገና ልጅነቷን ያልጨረሰች ቂል ነገር ናት ።
. . . ከአሁኑ አንድ ነገር በስሙ ሊናዘዙለት ይገባል ።
ቢያንስ ቢያንስ የቡቴንኮን ርስት በስሙ ማዛወር ይኖ
ርብዎታል ። ” አለች ቫርቫራ በማስገደድ ዐይነት አነጋገር ፡
ባሏን ውጥር አድርጋ ይዛ። “ ኒኪፎር ደስ የሚል ልጅ ነው
በጊዜ ካልታሰበበት ኋላ ነገሩ አሳፋሪ ይሆናል ። ሲሆን
ሲሆን ነገሩን ወደ ከተማ ሔደው የውርሱንና የስም ማዛ
ወሩን ጉዳይ ቢጨርሱ አይከፋም ። ቸል ማለቱና መዘ
ግየቱ አይበጅም ” አለች ።

“ እውነትሽን እኮ ነው ። የልጁን ነገር ጭራሽ እር
ስት አድርጌዋለሁ ። እንዲያውም ከመጣሁ አላየሁትም ፤
እንዳልሽው ጥሩ ልጅ ነው ። ብቻ እስቲ ይሁን ። ጤና ሆኖ
ይደግ ። የግዜር በረከት አይለየው ”አለ ሽማግሌው ግሪ
ጎሪ ፔትሮቪች ።



በሩን ከፈተና በአመልካች ጣቱ ጥቅሻ ሊፓን ጠራት።
ልጅዋን ታቅፋ ብቅ አለች ። “ የምወድሽ ሊፓ፡የምትፈል
ጊውን ነገር ሁሉ ሳትፈሪ ጠይቂኝ ። በቤቱ ውስጥ ደስ
የሚልሽን ነገር ሁሉ አግርጠሽ መብላት ትችያለሽ ፤ በኛ
በኩል ካንቺ የምንፈልገው ደኅንነትሽን ብቻ ነው ” አለና
በሕፃኑ ላይ አማተበበት ። “ እና የልጅ ልጄን ነገር አደራ!
በደንብ እንድትይዥው እፈልጋለሁ ። ተጠንቅቀሽ ጠብ
ቂው ። የምወደውን ልጄን ባጣም በዚህኛው እጽናናለሁ ”
አላት ።

በጉንጮቹ ላይ እንባው ኮለል እያለ መውረድ ጀመረ።
ወዲያው እየተንሠቀሠቀ ትቷቸው ወጣ ። ወደ መኝታ
ክፍሉ ገብቶ አልጋው ላይ ጋደም ከማለቱ ሰባት ቀናት
ሙሉ እንቅልፍና ዕረፍት በማጣት ፡ የደከመው አካሉ
ብዙም ሳይቆይ በከበደ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ሰጠመ ።

—7—

ግሪጎሪ ፔትሮቪች ወደ ከተማ በመሔድ ጥቂት ቀናት
ቆይቶ ነበር የተመለሰው ። አክሲኒያ የጡብ ምርት ሥራ
የጀመረችበትን የቡቴኪኖውን ርስት ሽማግሌው ለልጅ
ልጁ ለኒኪፎር ያወረሰው መሆኑንና ወደ ከተማ የሔደውም
ከአንድ የሕግ ሰው ጋር ስለ ኑዛዜው ለመወያየት እንደ
ነበር ወሬ የሰማ ሰው ለአክስኒያ ሹክ ይላታል ። ወሬው
የደረሳት ወደ ጧት ገደማ ነበር ። ሽማግሌውና ቫርቫራ
በረንዳው ፊት ለፊት ካለው ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጠው
ሻያቸውን ፉት ይላሉ ። አክስኒያ የሱቁን የፊት ለፊትና
የጓሮ በሮች ጥርቅም አድርጋ ከዘጋች በኋላ ፡ እርሷ ዘንድ
የሚገኙትን ቁልፎች በሙሉ ሰብስባ ሽማግሌው እግሮች
ሥር መሬቱ ላይ ዘረገፈቻቸው ።

“ ከአሁን በኋላ አንዴት ሥራ የማልሠራልዎ መሆኑን እንዲያውቁት ” በማለት አንባረቀችና ወዲያው ዕንባዋን እያዘራች ትንሠቀሠቅ ጀመር ። እኔ ገረድዎ እንጂ ምራትዎ አለመሆኔ ተረጋግጧል ። ሰው ሁሉ ፡ ‘ አያችሁ የፔትሮቪች ቤተሰብ ያገኛትን ሎሌ ’ እያለ የሚዘባበትብኝና የሚሣለቅብኝም ለዚሁ ነው ። ልጅዎ አገባኝ እንጂ የገዛኝ እንዳይመስልዎ ። ደግሞም ለማኝ ወይም ከሜዳ የተገኘሁ ማንዘራሽ ጋለሞታ አይደለሁም ። እንደ ዐቅሜ እናት አባት አለኝ ። ከወላጆቼ ጉያ ነው እናንተም የወሰዳችሁኝ ” እያለች ከልቅሶዋ ጋር አወረደችው ።

እንባዋን ሳትጠርግ በእልክና በንዴት ፡እሳት የሚተፉ የመሰሉ ዐይኖችዋን እያጉረጠረጠች ሽማግሌውን ታስተውለው ጀመር ። ግቢው እስቲናጋ ስትጮህ አንገቷ ላይ የደም ሥሮቿ እንደ ሲባጎ ተገታትረው ፊቷ ድልህ መሰለ ።

“ ከአሁን በኋላ ለዚህ ቤት ምንም አገልግሎት አልሰጥም ። ጉልበቴን ሁሉ አሟጥጣችሁታል ። ምናለ ለሥራው ጊዜ የምፈለገው እኔ ነኝ ። ከቀን እቀን ሱቅ ውስጥ ተጐልቶ ለመዋል ሲባል ፡ በድቅድቅ ጨለማ ቮድካ ለማምጣት ሲባል የምፈለገው እኔ ነኝ ። ለውርሱ ለጉርሱ ጊዜ ግን ፡ ተፈላጊዎቹ የዚያ እስረኛ ሚስትና ልጅዋ ናቸው ። እሷ እመቤት ፡ዘበናይ ፡ እኔ ደግሞ አገልጋይዋ መሆኔ ነው ። ይቀጥሉ፤ አሁንም በርቱ፤ ንብረትዎን ሁሉ ስጧት ። እኔም ወደ ወላጆቼ እሔዳለሁ ። ከአሁን ወዲያ ሞኛችሁን ፈልጉ፤ የተረገማችሁ አረመኔዎች ” አለች አክስኒያ ፡ እሳት መስላ እሳት ከአንደበቷ እየተፋች ።

ሽማግሌው፡በሕይወቱ ሙሉ ልጆቹን መቅጣት ቀርቶ ተቆጥቷቸው እንኳን አያውቅም ነበር ። ከቤተሰቡ መሐል



እንዲህ ከፍ ዝቅ አድርጎ ያዋርደኛል ፡ ይሰድበኛል ብሎ የሚገምተው ሰው አልነበረውም ። ስለዚህ የአክሲኒያን ውርጅብኝ ሲሰማ ፡ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ቤት በመግባት ከቁም ሳጥኑ ጀርባ ተደበቀ ። ቫርቫራ መብረቅ እንደ ሳተው ሰው ክፉኛ በመደንገጧ ፡ ከወንበሯ መነሣት ተስኗት ቁጭ ባለችበት ዝንብ እንደሚከላከል ሰው እጆቿን ታወናጭፋለች ። ዐልፎ ዐልፎ ብቻ ፡

“ ኧረ እንዲያው ነገሩ ምንድነው ? ጉዳዩ ምንድነው? እንደዚህ መጮህስ ይገባል? ሰው ቢሰማ ምን ይለናል በሉ? እንደበትዋን ትንሽ ብታለዝበው ፡ ድምጿን ትንሽ ብትቀንሰው ምን ይጐዳታል ” እያለች ታጉተመትማለች ። ክፉኛ መሸበሯ በድምጿ ያስታውቃል ።

“ የቡቴኪኖን ርስት ለዚያ ወንጀለኛ ሚስት ሸለሙዋት . . . በርቱ ግፉበት ! የቀረዎትን ሁሉ ጨምሩላት እንጂ ! ” አክስኒያ ጩኸቷን ቀጠለች ። “ በበኩሌ ካንቱ የምፈልገው ሰባራ ስንጥር የለም ። እናንተም ገንዘባችሁም ገሀነብ ግቡ ። መንጋ ሌባ ሁሉ ። እስከ ዛሬ ድረስ ሌብነታችሁን እስኪበቃኝ ተመልክቻለሁ ። አሁን ግን አንገፍግፎኛል ። ዐላፊ አግዳሚውን ስትዘርፉት አንድም ሳይቀር ስትመዘብሩት አይቻለሁ ። ልጅ ካዋቂ ሳትለዩ ሕዝቡን ስትገፉት ፡ ውቃቢ ስታስርቁት ስመለከት ኖሬ አለሁ ። አሁን ግን አንገቴ ደርሷል ። ጃውሳ ሁሉ! . . . . ምናለ አሁንማ ሳጥኖቻችሁ በሐሰት ገንዘብ አብጠውላችኋል ። ከእንግዲህ የኔ መኖር አይጠቅምም ። አክሲኒያ አታስፈልጋችሁም ! ” እያለች ታዥጎደጉደው ቀጠለች ።

ቀስ በቀስ ብዙ ሰው ከአጥሩ ውጭ ተሰብስቦ ብርግድ ብሎ በተከፈተው ዋና በር በኩል ወደ ግቢው መመልከት ጀመረ ።

"ጉዳችሁን ሰው ሁሉ ይታዘበው ። ሕዝቡ ፊት ነው
የማዋርዳችሁ! ድፍን ኢክሴየቮ ፊት ነው በኃፍረት ነበ
ልባል የማጋያችሁ !" አክሲኒያ እንደ ዕብድ መጮሁዋን
ቀጠለች ። "ስማ ስቴፓን" ደንቆሮ ባሏን ጠራችው ። "ከአ
ሁኗ ደቂቃ ጀምሮ እዚህ ቤት አንቀመጥም ። ወደ ወላጆቼ
ቤት እንሔዳለን ። ዕቃችንን ሰብስብ " አለች ።

ግቢው ውስጥ በተዘረጋው ሽቦ ላይ ጥቂት የታጠቡ
ልብሶች ተሰጥተዋል ። የራሷ የሆኑ ቀሚሶችና የውስጥ
ልብሶችን ከሽቦው ላይ እየመነጨቀች ከነርጥበቱ ለባሏ
ታሸክመው ጀመር ። ናላዋ በንዴት ብጥብጥ ብሎ ሁለ
መናዋ በብስጭት ይቃጠላል ። አንዴ ወደ ላይ አንዴ ወደ
ታች እየተመላለሰች ፣ የእርሷ ያልሆኑ ጨርቆችን መሬት
ላይ በመወርወር በእግሯ ትረግጣቸው ጀመር ።

" ኧረ እባካችሁ አንድ በሏት ! አሁን እስቲ ምን
ነካት ይባላል ? ግሪጎሪ ፔትሮቪች ስለ ክርስቶስ ብለው
የቡቴኪኖን ርስት ፍቀዱላት " ትላለች ቫርቫራ ፣ አሁንም
አሁንም ።

"እንዴት ያለችው ሴት ናት ጃል! እንዴት ያለችው
አለብላቢት ነች በሉ ፤ ሆሆይ ! . . . .ወይ ዕብደት ! እንዲህ
ያለ ጉድ አይታችሁ ታውቃላችሁ ?" ይባባል ጀመር ፣ ዋና
ውን በር ከብቦ የቆመው መንደርተኛ ።

አክሲኒያ እየሮጠች ወደ ማዕድ ቤቱ ጥልቅ አለች ።
ሊፓ ብቻዋን ልብስ ታጥባለች ። ምግብ አብሳይዋ ሌሎች
ጨርቆችን ይዛ ወንዝ በመውረዷ ማንም አልነበረም ።
ልብስ ከሚታጠብበት ሣፋ እና ምድጃው ፊት ለፊት ከተ
ቀመጠ ትልቅ ጋን ውስጥ እየተግፈጠፈጠ የሚተነው
እንፋሎት ክፍሉን አፍኖት እየሩ እንዲሞቅ አድርጎታል ።
በቂ ብርሃን ባለመኖሩ ደብዘዝ ብሏል ። አንድ አግዳሚ ወን



በር ላይ ሕፃኑ ኒክፎር በጀርባው ተንጋሎ ቀያይ ጥራር
እግሮቹን ፍርግጥ ፍርግጥ ያደርጋቸዋል ። አግዳሚው ሾር
ወለሉ ላይ ያልታጠቡ ጨርቆች ተከምረዋል ። ኒክፎር
ድንገት የወደቀ እንደሆነ ወለሉ እንዳይጎዳው ሆን ተብሎ
የተደረገ ጉዝጓዝ ነው ። ሊፓ ከክምሩ ጨርቅ ውስጥ አንድ
ያደፈ ሸሚዝ መዘዝ አድርጋ ሣፋው ውስጥ ከጨመረች
በኋላ ፣ የፈላ ውሃ የሞላበትን ባልዲ ልታነሣ እጅዋን ሰደድ
ስታደርግ አክሲኒያ ዘው አለች ።

"እሱን ወዲህ በይ" አለቻት ፣ ከሣፋው ውስጥ ሸሚ
ዙን ላጥ አድርጋ በመውሰድ ። ሊፓን የጥላቻ ነበልባል
በሚንቀላቀልባቸው ዐይኖች እየገላመጠቻት፣ "የኔን ልብስ
እንዳንቺ ዐይነቱ ምናምንቴ አይነካውም ። አንቺ የወንጀለኛ
የእስረኛ ሚስት ነሽ ። ማንነትሽን ማወቅ አለብሽ ፤ የምት
ሔጅበት ሔደሽ ካሁኑ ቦታሽን መፈለግ ነው " አለቻት ።

ሊፓ ፣ ከመደንገጧ የተነሣ አንዳችም ነገር ሊገባት
አልቻለም ። ብቻ እንደ ጅብራ በመገተር ዐይኖቿን ብል
ጥጥ አድርጋ አክሲኒያን ትመለከታለች ። ግን ወዲያው
አክሲኒያ ዐይኖቿን ወደ ሕፃኑ ስትወረውር ባየቻት ጊዜ
ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኖ ገባት ። የሠራ አካላቷ በፍርሃት
ደነዘዘ ።

"ርስቴን ስለ ነጠቅሽኝ የሚከፈልሽ ዋጋ ይኸ ነው።"
አክሲኒያ ይህንን እየተናገረች የፈላ ውሃ የያዘውን
ባልዲ ከመ ቅጽበት ብድግ አድርጋ በሕፃኑ ኒክፎር ላይ
እንዳለ ከለበሰችው ።

ከዚያ ዕለት በፊት በኢክሴየቮ መንደር ተሰምቶ የማ
ያውቅ ፣ ልብ የሚያሸብር ፣ ሆድ የሚያንቦጫቡጭ እሪታ
ተሰማ ። እንደ ሊፓ ካለ ትንሽ ፣ ዐቅመቢስና ኰስማና ፍጥ
ረት እንደዚያ ዐይነት የዋይታ ድምፅ ይወጣል ብሎ ለመ

ገመትም ሆነ ለማመን ያዳግታል ፡፡ ብዙም አልቆየ ፤ ወዲ
ያው በግቢው ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ ፡፡ ፍጹም ጸጥታ ፡፡ አክ
ሲኒያም ከማዕድ ቤት ወጥታ የተለመደ ፡ገራገር ዐይ
ነት ፈገግታዋን እያሳየች ወደ ዋናው ቤት ገባች . . .
ሚስቱ ያሸከመችውን ርጥብ ጨርቆች በእጆቹ እንደ
ታቀፈ በግቢው ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲንጐራደድ የቆ
የው ስቴፋን ደንቆሮው ፤ በርጋታና በጸጥታ ጨርቆቹን
መልሶ ሽቦው ላይ ማስጣት ጀመረ ፡፡ የወጥ ቤት ሠራተኛዋ
ከወንዝ አጠባ እስክትመለስ ድረስ በማዕድ ቤቱ ውስጥ
የተፈጸመውን ድርጊት ለማየት ደፍሮ ወደዚያ ጠጋ ያለ
እንኳን አንድም ሰው አልነበረም ፡፡

—፰—

ኒኪፎር ወደ ወረዳው ሆስፒታል ተወስዶ ሕክምና
ሲደረግለት ቢቆይም ፤ መሽትሽት ሲል ሕይወቱ ዐለፈ ፡፡
ሊፓ የሚያጅባት ፤ የሚረዳት ሰው ከቤት እስኪመጣላት
መጠበቅ አልፈለገችም ፡፡ የምትወደው ልጅዋን ትንሽ
አስከሬን በብርድ ልብስ ጠቅልላ አንገቷ ሥር ሽጉጥ በማ
ድረግ ብቻዋን ወደ ቤት መጓዝ ጀመረች ፡፡

በኮረብታ ላይ የተሠራው ትልልቅ መስኮቶች ያሉት
አዲሱ ሆስፒታል ሰዓቷን ጠብቃ ማዘቅዘቅ በጀመረችው
ፀሐይ ብርሃን በመጥለቅለቁ በእሳት ተያይዞ በመጋየት
ላይ ያለ ይመስላል ፡፡ ከበታቹ አንዲት አነስተኛ መንደር
አለች ፡፡ ሊፓ መንገዱን ተከትላ ስትጓዝ ከቆየች በኋላ ፤
ከመንደሩ ወዲህ በሚገኝ አነስተኛ ኩሬ አጠገብ ዐረፍ
አለች ፡፡ አንዲት ሴት ፈረስ እየጐተተች ውሃ ለማጠጣት
መጣች ፡፡



"ለምን አትጠጣም ? ምን ሆነሃል ?" አለች ሴትየዋ፤
ፈረሱን ለስለስ ባለ የመገረም አነጋገር ፡፡

ቀይ ሸሚዝ የለበሰ ብላቴና ኩሬው ጠርዝ ላይ ቁጢጥ
ብሎ የአባቱን ቦት ጫማዎች ያጥባል ፡፡ ከነርሱ ሌላ ግን ፤
በመንደሩ ሆነ በኮረብታው አካባቢ ልውሽ የሚል ሰው
አይታይም ፡፡

"አይጠጣም . . ." አለች ሊፓ ፤ ፈረሱን እያስተ
ዋለች ፡፡

ብዙም ሳይቆይ ሴትየዋና ቦት መጫሚያ የሚያጥበው
ልጅ ወደ ሠፈራቸው ሔዱ ፡፡ በአካባቢው ዝር የሚል ሰው
አልነበረም ፡፡ ፀሐይዋ የወርቅና የእሳት ቅይጥ በመሰለ
ውብ ብርሃን ተሽሞንሙና ወደ ቤቷ ተከተተች ፡፡ በሰማዩ
ግርጌ ደርበብ ብለው የተንጣለሉት በቀይና በሐምራዊ
የቀለሙ ደመናዎች የሚታዘቧት ይመስላሉ ፡፡ ራቅ ካለ
ሥፍራ በር ተዘግቶባት እንደምትጣራ ላም የመሰለ የሚ
ያሳዝን የአሞራ ጩኸት ረጋ ብሎ ያስገመግማል ፡፡ ዓመት
ቆጥራ ፀደይ ሲጠባ ብቻ ብቅ የምትለው ምስጢሯ የማ
ይታወቅ ወፍ ድምፅ ከነለዛው አየሩን እየገመሰ ይንቆረ
ቆራል ፡፡ ምን ዐይነት ወፍ እንደ ሆነች ወይምየት ሥፍራ
እንደምትኖር የሚያውቅ የለም ፡፡ ሆስፒታሉ ባለበት ኮረ
ብታ ላይ ፤ በኩሬው ዙሪያ ፤ ከመንደሩ ባሻገር አፋፉን
ይዞ ፤ ታቹን ፤ በየመስኮቹ . . . በሁሉም ሥፍራ የአዕዋፍ
ዜማ ይሰማል ፡፡ በየጣልቃው ግን የዋኔ ድምፅ ለብቻው
ይለያል ፡፡ ዋኔዋ የአንድ የሆነ ሰው ዕድሜ የምትቆጥር
ትመስላለች ፡፡ ግን ወዲያው ቁጥሩ ይጠፋትና እንደገና
መቁጠር ትጀምራለች ፡፡ በኩሬው ውስጥ የሚተራመሱት
ዕንቁራሪቶች በሻከረ ድምፅ እርስ በርስ ይጠራራሉ ፡፡
አገሩ በሙሉ ድምፅ ብቻ ነው ፡፡ እነዚህ ፍጥረታት በኅብ
ረት የሚጮሁና የሚዘምሩት ያለ ምክንያት እንዳልሆነ

ሁኔታቸው ያሳስባል ። ምክንያታቸው በዚህ የፀደይ ምሽት ማንም እንዳይተኛና እንዳያንቀላፋ ለማድረግ ዕንቁራሪቶቹ ሳይቀሩ ያሳለፉት የጋራ ውሳኔ ይመስላል . . . . . ሕይወትን የምንኖራት አንድ ጊዜ ብቻ ነውና ሁሉም ፍጡር እያንዳንዷን ቅጽበት በደስታ እንዲያሳልፉት ፣ እንዲጠቀምባት ፣ እንዲንከባከባት ለማንቃት የታደሙ . . . ቃል የገቡ ይመስላሉ ።

በከዋክብት በተንቆጠቆጠው ሰማይ ላይ ብርማ ቀለም ያላት ሩብ ጨረቃ ፈገግ ብላለች ። ሊ.ፓ ፣ ኩሬው አጠገብ ለምን ያህል ጊዜ እንደ ተቀመጠች አልታወቃትም ። መብራቶቹ ሁሉ ጨላልመዋል ። ክፉኛ ቢደክማትም አክሌየቮ ለመድረስ የሚቀራት መንገድ የዋዛ አለመሆኑን ታውቃለች ። የምትጓዘው በትክክለኛው መንገድ ይሁን በተሳሳተ አቅጣጫ ለማረጋገጥ አልተጨነቀችም ። ብቻ እንዳገኘች ወደፊት መራመድ ጀመረች ። የጨረቃዋ ብርሃን አንዴ ከፊት ለፊቷ ይተከላል ። አንዴ ከበስተኋላዋ ይቀራል ። ዋኔዎቹ ደግሞ ምሽቱ በገፋ ቁጥር እየጐረነነ በሔደው ድምፃቸው ሲጮሁ ' መንገዱን ስተሻል ! መንገዱን ስተሻል ! ' እያሉ የሚያሾፉባት ይመስላል ። ሊ.ፓ ፣ በፍጥነት ተፍ ተፍ እያለች ስትራመድ ፣ ሻሹዋ ከጠጉርዋ ላይ ተንሸራቶ ወደቀ ። ወደ ሰማዩ ቀና ብላ በአትኩሮት ተመለከተች ። የልጇዋ እርም ታህል ነፍስ የት እንዳለች ለማወቅ በአእምሮዋ ጥያቄ መመላለስ የጀመረው ያኔ ነበር ። ትናንት እየሣቀ ያጫውታት የነበረ ዛሬ እንደባዳ ዝም ያላት የልጅዋ ነፍስ ይከተላት ይሆን ? ወይስ እናቱን እርግፍ አድርጎ ረስቶ እዚያ ላይ ፣ ሰማዩ ጥግ በከዋክብቱ አጠገብ ይንሳፈፋል?

ለመሆኑ ግን ፣ በጨለማና በአውላላ ሜዳ መኖር ምንኛ ብቸኝነትን ያከብደዋል ። በተለይ ደግሞ የደስታ ማኅሌት



በደመቀበት ተቀላቅሎ ለራስ መዘመር ፣ ተሳታፊ መሆን ሳይቻል ሲቀር ፣ የማያቋርጥ ፈንጠዝያ በደራበት ሠርግ ለራስ መደሰት ፣ ከሌላው መቋደስ አዳጋች ሲሆን ፣ እውን ብቸኝነት እንደ ምን አድርጎ እንደ ጥንብ ይከብዳል ። ይብሱን ደግሞ ለሰዎች ሞትና ሕይወት ፣ ለክረምትና በጋው ፈረቃ እቻ የሌላት ጨረቃ ብቸኛ ሆና ብቸኛን ሰው ቁልቁል ስታስተውል ማየት ፣ ብቸኝነትን እንደምን ኃያልና ግዙፍ ያደርገዋል? በተለይማ ልቦና በኀዘን ለበቅ ሾጥ ተደርጎ ፣ ኀዘንና እህህን አቁሮ በያዘ ጊዜ፣ብቸኝነት ከተደመረ ከሁሉም የከፋ ጫና የሚሆን እሱ ነው ። ሊ.ፓ ፣ በዚያ ምሽት ከእናቷ ወይም ከጉጠት አለያም ከወጥ ቤት ሠራተኛዋ ብቻ ከማንም ይሁን ከማን ፣ ከአንድ ሰው ጋር ብትሆን እንደምን ደስ ባላት ነበር ። ወይም በተጽናናች ።

ድንገት በጨለማው ውስጥ የአንድ ሰው ድምፅ ቁልጭ ብሎ ተሰማት ። "እኮ በል ቫቬላ ተነሣና ፈረሶቹን ለጉም" አለ ድምፁ ። ባሻገር ጥቂት ርምጃዎች ራቅ ብሎ መንገዱ ጠርዝ ላይ አንድ ትንሽ ደመራ በእሳት ተያይዞ ይንቀለቀላል ። ቀስ በቀስ እሳቱ እየጠፋ የሚታየው ፍሙ ብቻ ሆነ ። ፈረሶች ምናምን ሲጐረዳድሙ ይሰማል ። በጨለማው ውስጥ የሁለት ጋሪዎች ቅርጽ ተለይቶ ይታወቃል ። አንደኛው ላይ በርሜል ፣ ሌላኛው - አነስ ያለው - ላይ ደግሞ ጆንያዎች ተጭነዋል ። ሁለት ሰዎችም ይታያሉ ። አንደኛው ፣ ወደ ጋሪዎቹ አግጣጫ ፈረስ ይጐትታል ። ሌላው እጆቹን ወደ ኋላ አጣምሮ እተንደረከከው ፍም ፊት ለፊት ያለንቅስቃሴ ተገትሯል ። ጋሪዎቹ አጠገብ አንድ ውሻ ያላዝናል ። ፈረሱን የሚጐትተው ሰው ቆም አለና ፣

"በመንገዱ በኩል ሰው እየመጣ ይመስለኛል" አለ ።

" ዝም በል ሻሪክ !" ሌላው ውሻውን ተቆጣው ።

ሁለተኛዉ ተናጋሪ ሽማግሌ መሆኑ ከድምፁ በግልጽ ያስ ታውቃል ። ሊፓ ቆም ብላ ፤

"እግዜር ከናንተ ጋር ይሁን " አለች ። ሽማግሌው ተጠጋት ። ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ከቆየ በኋላ ፤

" እንደምን አመሸሽ " አለ ።

"ውሻው ይናከስ ይሆን አባቴ? "

"የለም አይናከስም ፤ ማለፍ ትችያለሽ ። "

" ሆስፒታል ቆይቼ ነው የምመጣው " አለች ሊፓ ፤ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ ። " ልጄ እዚያው ስለ ሞተብኝ ፤ አስከሬኑን ወደ ቤት እየወሰድኩ ነው ። "

ሽማግሌው በንግግሯ በመደናገጡ ካጠገቧ ፈንጠር አለና ፤

" መበርታት ነው እንግዲህ የኔ ልጅ ፤ መቼም የእ ግዜርን ፈቃድ መቀበል እንጂ ሌላ ምን ያደርጋል" አለ በተቻኮለ አነጋገር ። ወዲያው ቀጠለና ፤ " በል እንጂ አንተ! ፈጠን ማለት አትችልም? "በማለት አብሮት ያለውን ሰው ጮኸበት ።

" የጋሪውን አግድሞሽ የሚያገናኘው ቅስት እዚህ የለም ። ላገኘው አልቻልኩም " አለ ሁለተኛው ሰው ። በዕድሜው ወጣት ነው ።

" አይ ቫቪላ እርባና ቢስ ፍጡር ነህ " አለው ።

ሽማግሌው አንድ ቅንጣት ፍም አነሣና እፍፍፍ ሲለው አፍንጫውና ዐይኖቹ ላይ ቀይ ብርሃን ፈካ ። ጠፋ የተባለውም ቅስት ከተገኘ በኋላ፣ ሽማግሌው ከሰሉን በእጁ እንደያዘ ወደ ሊፓ ተጠግቶ ያስተውላት ጀመር። በዐይኖቹ ርኅራኄና ደግነት ይነበባሉ ።



" መቼም የናት ሆድ ነውና ትንሽ ይከብዳል ።እናት ልጅዋን ትወዳለች " አላት ። በከባዱ ተንፍሶ ራሱን ነቀ ነቀ ። ቫቪላ የሆነ ነገር እሳቱ ላይ ወረወረና በእግሩ እየ ረገጠ አጠፋው ። ወዲያው ሁሉም ነገር በጨለማ ተዋጠ ፤ ትርዒቱ ሁሉ ጠፋ ። የሚታይ ነገር ቢኖር በከዋክብት ያጌጠው ሰማይ ፤ የሚሰማ ነገር ቢኖር አንዱ አንዱን እን ቅልፍ እየነሣ እርስ በርስ የሚጯጯሁት አዕዋፍ ድምፅ ብቻ ነው ።

ከአንድ ወይ ሁለት ደቂቃ በሁዋላ፣ የሁለቱ ጋሪዎችና የሽማግሌው ፤ እንዲሁም የባቢላ ጠቅላላ ቅርጽ እንደገና ደብዘዝ ብሎ መታየት ጀመረ ። ጋሪዎቹ እየተንሳጠጡና እየተንጿቁ ወደ መንገዱ ገቡ ።

" ቅዱሳን ናችሁ?"አለች ሊፓ ፤ ሽማግሌውን ።

" የለም የፊርሳኖቮ ነዋሪዎች ነን ።"

"ቅድም እንዲያ ትክ ብለው ባስተዋሉኝ ጊዜ ልቤ ትንሽ እሮይ አለ ። መንፈሴ የተጽናና መሰለኝ።እና ደግሞ ከእርስዎ ጋር ያለው ልጅ ዝምተኛ በመሆኑ ቅዱሳን ሳት ሆኑ አትቀሩም ብዬ አሰብሁ ።"

"ለመሆኑ ወዴት ነው የምትሔጅ የኔ ልጄ? ሩቅ ነው?"

" ኢክሌየቮ ነው "

" እንግዲያውስ ጋሪው ላይ ተሣፈሪና እስከ ኩዝሜ ንኮ እንሸኝሻለን ። ከዚያ በኋላ ቀጥታውን ይዘሽ ትሔጃ ለሽ ። እኛ ወደ ግራ ነው የምንታጠፍ "አላት ሽማግሌው።

ቫቢላ በርሚል በተጫነበት ጋሪ ላይ ሲሣፈር ሊፓና ሽማግሌው ደግሞ አነስተኛው ጋሪ ላይ ወጡ ። የቫቢላ ጋሪ ከፊት እየመራ በዝግታ መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

" ልጁ ቀኑን ሙሉ ሲሠቃይ ነው የዋለው " አለች ሊ.ፓ ። " አንዳች ነገር ሊነግረኝ ፈልጎ አልወጣልህ ያለው ይመስል ፤ እነዚያን የምወዳቸው ዐይኖቹን እያንከራተተ ሲያየኝ ነበር ። የሰማየ ሰማያት ጌታ! ቅድስት ወላዲተ አምላክ ! ኀዘኔ ስለ በረታ መሬቱ ላይ ስፈጠፈጥ ፤ አልጋ ውን አንቄ ስወድቅ ስነሣ ዋልሁ ። እንዲያው አባቴ እስቲ ይንገሩኝ ። ገና አንድ ፍሬ ጨቅላ ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ለምን እንደዚህ ክፉኛ ይሠቃያል ? ትልልቅ ሰዎች ሥቃይ ሲበዛባቸው ኃጢአታቸው ሥርየት ያገኛል ይባላል ። ታዲያ ምንም የማያውቅ ሕፃን በምን አበሳው እንዲያ ይሠ ቃያል ?ለምን ? "

" ማን ያውቃል ብለሽ!" አላት ሽማግሌው ።

ለግማሽ ሰዓት ያህል በጸጥታ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

"የሁሉንም ነገር ሰበብና ምክንያት ማወቅ አዳጋች ነው ። ወፍ ሁለት እንጂ አራት ክንፍ የላትም ። ለምን ቢሉ ለመብረር ሁለቱ በቂ ስለሆነ ነው ። ልክ እንደዚሁ የሰው ልጅም ሁሉን ነገር እንዲያውቅ አልተፈቀደለትም ። ግማ ሹን ወይ ሩቡን ብቻ ነው ። ሰው የሚያውቀው በሕይወቱ ጉዞ ውስጥ ለመዝለቅ የሚያስችለውንና የሚያስፈልገውን ያህል ብቻ ነው " አለ ሽማግሌው ።

"በእግሬ ብሔድ ትንሽ ቀለል የሚለኝ ይመስለኛል አባቴ ! ጋሪው በተንገጫገጨ ቁጥር ልቤም አብሮ እየተን ሰፈሰፈ አስቸገረኝ " አለች ሊ.ፓ ።

" ግድ የለም ፤ ባለሽበት እርጊ!"አለና ሽማግሌው እያማተበ ያፋሽክ ጀመር ።

" አይዞሽ ምንም አይል" አላት በድጋሚ ።"ኀዘንሽ ግማሽ ኀዘን ነው ። ሕይወት ረጅምና ሰፊ ስለ ሆነች ፤ ገና



ብዙ ክፉና ደግ ማየት አለ።አይ ትልቋ እናት ሩሲያ!" አለ በማጋነን አነጋገር ፤ የመንገዱን ግራና ቀኝ በጨለማው ውስጥ ለማየት እየሞከረ ። " ይገርምሻል ልጄ ! ሩሲያን ከዳር እስከ ዳር አዳርሻታለሁ ። በውስጧ ያለውን መታየት የሚገባውን ሁሉ አንድ ባንድ አይቼዋለሁ ልጄ! ገና ብዙ ክፉና ደግ ይመጣል ። ሳይቤሪያ ድረስ በእግሬ ተጉዣለሁ ። በአሙር ወንዝ ላይ ቀዝፌአለሁ ፤ የአልታይ ተራሮችን ወጥቻለሁ ። ሳይቤሪያ ላይ ተከዬ ጥቂሩን አፈር ወዜ ጨፍ እስቲል እያረስኩ ኖሬአለሁ ። ግን የናት ሩሲያ ናፍቆት አላስቀምጥ ስላለኝ ፤ ተመልሼ ወደ ትውልድ መንደሬ መጣሁ ። ስንመለስም ያው እንዳካሔዳችን አብዛኛውን በእግር ነበር የተጓዝነው ። ታዲያ ትዝ የሚለኝ አንድ ወንዝ በጀልባ ስናቋርጥ የገጠመኝ ነው ። ከስቼ ተጎሳቁያ ለሁ ፤ ልብሴ ሁሉ ላዬ ላይ አልቋል ፤ መጫሚያ የለኝም ፤ ለስንቅ የያዝሁት ትንሽ ቁራሽ ነበር ። እና አንድ አብሮን በጀልባው የተሳፈረ ጨዋ መሳይ አዛውንት — ሞቶም እንደሁ ነፍሱን ይማረውና —በኀዘኔታ እያስተዋ ለኝ ፤ " ዳቦህ ጥቁር ፥ሕይወትህም ጥቁር!" ይለኝ ነበር ። ወደ አገሬ ስመለስ ቤትም ትዳርም አልነበረኝም ። ሚስ ቴን እዚያው ሳይቤሪያ ቀብሬ ነበር ። ስለዚህ ቀን ቀን ተቀጥሬ መሥራት ጀመርሁ ። እና ፤ ከዚያ በኋላ ብዙ ክፉና ደግ ነገሮች በሕይወቴ ውስጥ ተፈራርቀዋል ። ግን ፤ አየሽ ልጄ ! አሁንም ቢሆን መሞት አልሻም ። ገና ሃያ ዓመታት ተጨማሪ ብኖር ደስ ይለኛል " . . . .ብቻ ያም ሆነ ይህ እናት ሩሲያ ትልቅ ናት !" አለ ሽማግሌው ፤ የመጨረሻ ውን ፀረፍተ ነገር እየደጋገመ ፤ግራና ቀኙን በጨለማው ውስጥ በማስተዋልና አንዳንዴም ወደ ኋላ ገልመጥ እያለ ።

" አባቴ!"አለች ሊ.ፓ ። " ለመሆኑ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ፥ ነፍሱ እስከ ስንት ቀን ድረስ ነው በምድር ላይ የም ትቆየው? "

“ ማን ያውቃል ብለሽ ልጄ! እኔ መቼም እንዲህ ያለውን ነገር አላውቅም ። እስቲ ቆይ ቫቪላን እንጠይቀ ዋለን ። ተማሪ ስለሆነ እሱ አያጣውም ። መቼም ዛሬ ጊዜ እዚያ ተማሪ ቤታቸው ውስጥ የማያስተምሯቸው ነገር የለም ። ስማ ቫቪላ ” አለ ሽማግሌው ።

“ እ ! ”

“ስማ ! አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ፥ ነፍሱ ለስንት ቀን ነው መሬት ላይ ስትንከላወስ የምትቆየው ?”

ቫቪላ መልስ ከመስጠቱ በፊት ልጓሙን ሳበና ፈረ ሱን እንዲቆም አደረገው ።

“ ለዘጠኝ ቀን ነው ። ግን አጐቴ ኪሪላ የሞቱ ጊዜ ነፍሳቸው በኛ ጎጆ ውስጥ ዐሥራ ሦስት ቀን ሙሉ ቆይታለች አለ ።

“ በምን ዐወቅህ?”

“ ዐሥራ ሦስት ቀን ሙሉ ምድጃው ውስጥ የሚን ዳን ድምፅ ነበር !”

“ እ — እ — ደኅና ነው ” አለ ሽማግሌው ።ቫቪላ የተናገረውን አንዱም አምኖ እንዳልተቀበለው ካነጋገሩ ያስታውቃል ።

ኩዝሚንኪ አጠገብ ሲደርሱ ፥ ጋሪዎቹ ግራቸውን በመያዝ ወደ አውራ ጐዳናው ገቡ ። ሊፓም ከጋሪው ወርዳ ጉዞዋን በእግሯ ቀጠለች ። ንጋት እየተቃረበ ነበር ። ወደ ሸለቆው የተደፋውን ቁልቁለት መውረድ ስትጀምር ቤተክርስቲያኑና የመንደሩ ጐጆዎች በሙሉ በጭጋግ ተውጠው አየቻቸው ። ብርዱ አጥንት ይሰብራል ። አንዲት ዋኔ አሁንም በሩቁ የምትጣራ መሰሎ ተሰማት ።



ሊፓ ፥ ቤቷ ስትደርስ ኩበቶች ገና ከበረት አልወጡም ነበር ። ሰው ሁሉ እንደ ተኛ ነው ። በረንዳው ላይ ኩርምት ብላ መጠበቅ ጀመረች ። በቅድሚያ ሽማግሌው ነበር ብቅ ያለው።ገና ሲያያት የሆነውን ነገር ሁሉ በግልጽ ተረዳው ። ለጥቂት ጊዜ ያህል ቃል መተንፈስ ተስኖት በቆመበት ሲያጉመተምት ቆየ ። በመጨረሻው ፥

“ አይ ሊፓ! የልጅ ልጄን በደንብ መጠበቅ እንኳን አቃተሽ ! ” አላት ።

ቫርቫራ ተቀስቅሳ ተነሣች ። እጆቿን እያወናጨፈች ስታለቅስ ከቆየች በኋላ ፥ የሕፃኑን አስከሬን በማጣጠብና በመገነዝ ለቀብር ማዘጋጀት ጀመረች ። “ እኔን ዐፈር ይብላኝ! እንዴት ያለ ወርቅ ልጅ ነበር . . .” ትላለች ቫር ቫራ ዐሥር ጊዜ ። “አንድ ልጅ በጥንቃቄ መያዝ ትልቅ ነገር ሆኖ ለዚህ አበቃሽው ። እንከፍ !”ትላለች ።

የዚያን ዕለት ረፋዱ ላይና እንደ ገናም ወደ ማታ ለኒ ኪፎር ሙሉ ፍትሐት ተደረገለት። በማግሥቱ የቀብሩ ሥር ዓት ተፈጸመ ። ከቀብር መልስ ቀሳውስቱና ለቀስተኞቹ በተዘጋጀው ድግስ ላይ ይረባረቡ ገቡ ። ከዳር ሆኖ አበ ላላቸውን ሊታዘበ እህል ከቀመሱ ብዙ ቀናት ያለፉቸው ይመስሉ ነበር ። ሊፓ ስታልፍ የተመለከተ አንድ ቄስ በሹካ ወግቶ ያነሣውን ከኮምጣጤ ጋር የተዘጋጀ እንጉዳይ ወደ አፏ እያስጠጋ ፥

“እንግዲህ ኀዘኑን በልክ ማረግ ነው ። ይበቃል ። የግዜር መንግሥት እንዲህ ነው”አላት ።

ሰው ሁሉ ከሔደ ነበር ኒኪፎር በአጠገቧ እንደሌለና እስከ ወዲያኛውም እንደ ማይኖር ሊፓ ያረጋገጠችው ። የልጅዋ ነገር ማከተሙን በደንብ ስትረዳው ምርር ብላ አለ

ቀሰች ። ወደ የትኛው ክፍል ገብታ ማልቀስ እንደምትችልም አታውቀውም። ልጅዋ ከሞተ በኋላ በዚያ ቤት ውስጥ ሥፍራ እንደሌላትና እንደማትፈለግ ተገንዝባለች ።በዚያ ቤት ውስጥ የምትሠራው ሥራ አልነበራትም ። ምንም የቀራት ነገር የለም ። በዚያ ቤት የማትፈለግ መሆኗም ግልጽ ሆኖላታል ። የቤቱ ሰው በመላ ስለርሷ ያለው አስተያየትና ስሜትም ከዚሁ ያልተለየ መሆኑን ተረድታዋለች ። ከዚህ ሁሉ ጋር ተዳምሮ ብሶቷ እየከፋ ፣ ልቅሶዋ እየበረታ ሔደ ።

“እኮ አሁን እዚህ የምታላዝኝብኝ ምን ልሁን ነው! እባክሽ ዝም በይ ! ”አለቻት አክሲኒያ ፣ በሩ ላይ ብቅ ብላ በጩኸት ። ስለሕፃኑ ቀብር ስትል አዲስ ልብስ ለብሳ ፊቷ ላይ ፓውደር ነስንሳለች ።

ሊፓ፣ልቅሶዋን ለማቆም ብትሞክርም አልሆን አላት ። ይበልጥ በገነነ ድምፅ መጮህ ማልቀሷን ቀጠለች ።

“ ትሰሚኛለሽ ? አትሰሚኝም ! ”አለች አክሲኒያ ። “ለማን የምናገር መሰለሽ? . . . እንዲያውም ከዚህ ሥፍራ ውጪ ነው የምለው! ከአሁን በኋላ እዚህ አካባቢ ዐይንሽን እንዳላየው ! መጥፎ ፊልፊላ !”አለች ፣ በንዴት መሬቱን እየደቃች ።

“ ረጋ በይ አክሲኒያ ልጄ! እስቲ እንዴ ታገሽ! . . . . መቼም ማልቀስ የተፈጥሮ ደንብ ነው . . . .ልጅዋ ነው የሞተው. . . ” አለ ሽማግሌው ።

“ተፈጥሮ! ተፈጥሮ!” አለች አክሲኒያ ፣ ቃሉን በለበጣ መንፈስ እየደጋገመች ። “በጄ የዛሬን እዚሁ ማደር ትችላለች ። ነገ ግን ወፍ ሳይንጫጫ ይህን ቤት መልቀቅ አለባት . . . ሁ-ሁ ደግሞ ተፈጥሮ! ” አለች አክሲኒያ



ቃሉን እየደጋገመችና በረጅሙ እየሣቀች ። በዚያው ወደ ሱቁ ሔደች ።

ሊፓም በማግሥቱ ማለዳ ወደ ቱርጉያቮ እናቷ ዘንድ ተመለሰች ።

## —9—

ሦስት ዓመታት ዐለፉ ። የሱቁ ጣሪያና ከብረት የተሠሩት በሮች አዲስ ቀለም ተቀብተው ያንጸባርቃሉ ።ዐይን የሚማርኩ የፈኩ አበቦች እንደ ቀድሞው በመስኮት መቃን ላይ ተቀምጠዋል ። ከሦስት ዓመታት በፊት ቤተሰቡን ያጋጠመው ነገር በሙሉ ፈጽሞ ተረስቷል ።

አሁን ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች፣ላይ ላዩን የቤት ንብረቱ ሁሉ ባለቤት ነው ተብሎ ይገመት እንጂ ማናቸውም ነገር በአክሲኒያ እጅ ገብቷል ። አስፈላጊውን ነገር የምትገዛም የምትሸጥ እሷ ናት። ያለሷ ፈቃድና ስምምነት አንዲት ርምጃ መንቀሳቀስ አይቻልም ። ፈላጭ ቆራጭ ሆናለች ። የጡብ ማምረቻው ድርጅት ሥራውን በሚገባ ማከናወን ቀጥሏል ። በተለይ ደግሞ ለባቡር ጣቢያው በርካታ ጡብ የሚፈለግ በመሆኑ ፣ ቀድሞ ሐያ ሩብል የነበረው የአንድ ሺህ ጡብ ዋጋ ወደ ሐያ አራት ሩብል ከፍ ብሏል ። በቀን ሐያ አምስት ኮፔክ የጉልበት ዋጋ የሚከፈላቸው ሴቶችና ልጃገረዶች ጡቦችን በጋሪና በትልልቅ መኪኖች እየጫኑ ወደ ጣቢያው ያግዛሉ ።

አክሲኒያ ከህሪሚን ቤተሰብ ጋር ሽርክና ገብታ ፣ የጥጥ መዳመጫውም ፣ “ ህሪሚን ትንሹና ኩባንያው ” እየተባለ መጠራት ጀምሯል ። ጣቢያው አጠገብ አንድ የመጠጥ

ቤት በመከፈታቸው የዚያ ውድ አኰርድዮን ድምፅ የሚ ሰማው እንደ ቀድሞው ከመኖሪያቸው ቅጥር ግቢ ሳይሆን ከመጠጥ ቤቱ ሆኗል ። የህሪሚን ትንሹ ቤተሰብ ለዶን ቆሮው የአክሲኒያ ባል የወርቅ ሰዓት ገጸ በረከት ስለ ሰጠው፥ ስቴፋን አሁንም አሁንም ከኪሱ እያወጣ ወደ ጆሮው በማስጠጋት ድምፁን ለማዳመጥ ይሞክራል ።

አክሲኒያ ኃይል እያገኘች መሔዷን የመንደሩ ሰዎች በፍርሃት ስሜት ያወራሉ ። ውበቷ ደምቆና ደስ ብሏት ያ ገራገር ፈገግታዋ በከናፍሯ ላይ እየታየ ፣ በጠዋት ተነ ሥታ ወደ ጡብ ማምረቻው በጋሪዋ ስትንዝም ሆነ በሥ ራው ቦታ ተገኝታ ልዩ ልዩ ትእዛዞችን ስትሰጥ ፣ ያ የሚወ ራለት ኃያልነቷ በርግጥ በጣም ጉልቶ ይታያል ። በቤት ውስጥ ፣ በፋብሪካውና በመንደሩ ሳይቀር ሁሉም ይፈ ራታል።ገንዘብ ያለው ደግሞ፥ በሌላ መንፈስ ይፈልጋታል። ለወዳጅነት ለፍቅር ይከጅላታል ። አክሲኒያ በዚህም በኩል ሰነፍ አልነበረችም ።

ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች በንግድ ሥራ ጣልቃ መግባቱን እርግፍ አድርጎ ትቶታል ። የሐሰቱን ገንዘብ ከእውነተኛው መለየት ስለ ተሳነውም ገንዘብ የሚባል በእጁ እንዳይነካ ተደርጓል ። ይህ ድክመቱ እንዳይታወ ቅበት በመፍራት ስለ ጉዳዩ ለማንም ትንፍሽ አይልም ። ዝንጉነቱም ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት ሔደ ። ቤተሰቦቹ አውቀው ምግቡን ካልሰጡት ጠይቆ መመገቡን ካቆመ ቆየ ። ቤተሰቡም እርሱ በሌለበት መመገቡን ስለ ለመደው የቀድሞው አባ ወራ ቁርስ ፥ራት ፥ ምሳውን በላ ፥አልበላ ብሎ የሚጨነቅ አልነበረም ። ቫርቫራ ብቻ አንዳንዴ ፥

" ትናንትም እንደ ልማዳቸው ራታቸውን ሳይበሉ ነው የተኙት " ከማለቷ በስተቀር ነገሬ የሚለው የለም ።



እቷም ብትሆን የአፍ ዐመል ሆኖባት እንጂ ፣ [illegible] በረም ። ክረምት ከበጋ ሳይል ጠጉር ያለው ወፍራም ኮት ለብሶ መዞር ነው ሥራው ። በበጋዎቹ ሞቃት ቀናት [illegible] በስተቀር ቤት ውስጥ ዐርፎ ይቀመጣል ማለት ሐሰት ነው ። የጠጉራም ኮቱን ኮሌታ ወደ ላይ ይቀለብስና የመንደሩን መንገዶች አንድ ባንድ ሲያዳርስ ይውላል ። ወይም ወደ ባቡር ጣቢያው የሚወስደውን ጎዳና ይዞ ያለ መድረሻ ፣ ያለ ዓላማ ይጓዛል።አንዳንድ ቀን ደግሞ፥ ከጧት እስከ ማታ ያለውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ በሚገኝ አግዳሚ ወንበር ላይ ተጐልቶ ያሳልፈዋል ። ያላንዳች እንቅስቃሴ ሐውልት መስሎ ቊጭ ይላል ። በአጠገቡ የሚያልፉ ፣ የሚያ ገድሙት ሁሉ ሰላምታ ያቅርቡለት እንጂ አጸፋውን አይ መልስላቸውም ። አሁንም ልክ እንደ ዱሮው ለገበሬዎች ያለው ንቀት አልለቀቀውም ። ሰዎች ሲያነጋግሩት እጥር ምጥን ያሉ ትክክለኛ መልሶችን በጨዋ ደንብ ይሰጣል ።

ምራቱ በቤቱ ውስጥ ያለውን ሥልጣን ስለ ገፈፈች ውና ምግቡንም እንደ ልብ ስለማትሰጠው ፣ ዐልፎ ዐልፎ የሚያገኘውን ምጽዋት ብቻ ቀምሶ እንደሚያድር መን ደረተኛው ማውጋት ከጀመረ ውሎ አደረ ። ወሬው ብዙ ዎቹን አስደስታቸው ። ያዘኑለትም ነበሩ ።

ቫርቫራ ከቀድሞው ይበልጥ እየወፈረችና እያማረባት ሔደ ። ችሮታና ምጽዋት የመስጠት ተግባሯን የቀጠለች ቢሆንም ፣ የአክሲኒያ ተቃውሞ አልገጠማትም ። አሁንም እንደ ቀድሞው የበጋው ወቅት በመጣ ቊጥር በጣም ብዙ መርመላት ይዘጋጃል ። ግን በልተው ሳይጨርሱት የተ ጸታዩ ዓመት ፍሬዎች ይጐመራሉ። የተዘጋጀው መርመላት የሚበላው እጥቶ ፣ ወደ ስኳርነትና ክረሜላነት ሲለወጥ በምቃይ ጊዜ ቫርቫራ ኀዘን ያድርባታል ።

የቤቱም የውጪውም ሰው እስረኛው አኒሲምን በጭራሽ ረሳው ። አንድ ጊዜ በትልቅ ወረቀት ላይ በግጥም የጻፈው መልዕክት ለቤተሰቡ ደረሰ ። የአጻጻፉ ስልት እንደ ቀድሞው የአቤቱታ ዐይነት ሲሆን ፥ የተጻፈውም በዚያው በሚያውቁት ቆሎ የመሰለ የእጅ ጽሑፍ ነበር ። ጓደኛዬ ነው እያለ ሲያወራለት የነበረው ሳሞሮዶቭ አብሮት በእስር ላይ ለመሆኑ የእጅ ጽሕፈቱ ማስረጃ ሆኗቸው ። በግጥሙ መጨረሻ ላይ ፈጽሞ በማይነበብ አስቀያሚ አጻጻፍ፥ “ እዚህ ባለሁበት ሥፍራ ሁልጊዜ በሽተኛ ነኝ ። ደስታ የለኝም ። በክርስቶስ ይሁንባችሁና እባካችሁ ርዱኝ!” የሚሉ ቃላት ተሞነጫጭረዋል ።

አንድ ፀሐይማ የበልግ ቀን ከቀትር በኋላ፥ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች ቤተክርስቲያኑ ዋና በር አጠገብ በሚገኘው አግዳሚ ላይ ቁጭ ብሏል ። የጠጉራም ኮቱ ኮሌታ አንገትዬ እንደ ተለመደው ተቀልብሶ ኮፍያ በማድረጉ ፥ የሚታይ ነገር ቢኖር የአፍንጫው ጫፍና የኮፍያው ቁንጮ ብቻ ነበር ። በረጅሙ አግዳሚ ሌላ ጠርዝ ላይ አናጢው የሊሳሮቭና ወደ ሰባ ዓመት በመጠጋቱ ጥርሱ ሁሉ ረግፎ ድዱ ብቻ የቀረው የትምህርት ቤቱ ዘበኛ ያኮቭ ጎን ለጎን ተቀምጠዋል ። ጉጠትና ዘበኛው የሞቀ ወሬ ይዘዋል ።

“ልጆች፥ አረጋውያን ዘመዶቻቸውን መርዳት፥ መጦር አለባቸው . . . ‘ አክብር አባከ ወእመከ ! ’ አለ ያኮቭ ኮስተር ብሎ ። ግን ያቺ ከይሲ የገዛ አማቷን ከሥራው ቤት አስወጥታ እንፈራጣበታለች ። እሷ ጠግባ ስታድር ሽማግሌው ግን የሚልስ የሚቀምሰው የለውም ። ምግብ ባፉ ከዞረ ሦስት ቀኑኮ ነው ” አለ የትምህርት ቤቱ ዘበኛ ።

“ሦስት ቀን! ” የጉጠት ንግግር በማዳነቅ ዐይነት ነበር ።



“እንግዲያስ ! አታየውም ። አንዲት ቃል እንኳን አይተነፍስ ፤ ብቻ እንዲሁ ተለጉሞ ተጐልቷል ። ስለ ደከመው ነው መሰል መናገርም አልቻለ ። ግን እኮ ለምንድን ነው ዝም ያላት ? መክሰስ ነበረበት ። ፍርድ ቤት ብትቀርብ ከጉኗ ታገኘው ነበር ” አለ ያኮቭ ።

“ምኑን ነው ከፍርድ ቤት የምታገኘው ?” ጉጠት የዘበኛውን ንግግር በጥሞና ባለመከታተሉ፥ ጥያቄው እንደ ነገሩ ነበር ።

“ ምንድነው ያልከው?”

“ ግን እኮ እስከዚህም መጥፎ ሴት አይደለችም ። ስትሠራ መቼም ከልቧ ነው። ኃይለኛ ሠራተኛ ነች ። ታዲያ ምን ፋይዳ አለው፤ ሴቶች ደግሞ እንዲያ ካላደረጉ አይሆንላቸውም ። ትንሽ ሸር ካልደባለቁባት . . . ማለቴ . . . እ” አለና ጉጠት እንጠልጥሎ ተወው ።

“ ላቡን ጠብ አድርጎ ከሠራው ቤት ማስወጣት ግን አይቻልም ” አለ ያኮቭ ፥ በብስጭት አነጋገር ። “ሰዎችን ማባረር ስትፈልግ ቤት ሥርተህ ነው . . . በሰው ንብረት አይደለም። ኧረ ለመሆኑ እሷ ማነኝ ባይ ናት ?ተባይ! ” አለ ዘበኛው እየተወራጨ ።

ሽማግሌው ግሪጎሪ ፔትሮቪች ንቅንቅ ሳይል ያዳምጣቸዋል ።

“ቤቱ ያንተ ሆነ የሌላ ሰው ፥ ምን ለውጥ ያመጣል ። እስከ ሞቀህና ሴቶች ንትርክ እስካልፈጠሩ ድረስ ሁሉም ያው ነው . . . ” አለ ጉጠት እየሣቀ ።

“ያ ደንቆሮ ባሏም ቢሆን፥ እዚህ ግዳ የማይባል ደደብ ነው” ያኮቭ የጀመረውን ንግግር ቀጠለ ። ጉጠት ፥ የሚቀ

ባጥረውን ከቁም ነገር ሳይጥቆር "የለየለት ፡ የነጠረ ፡ ዕውነተኛው ደደብ ነው ። አንጐሉም ከዝይ አንጐል የማይሻል አንኮላ . . . እንዲያው ለመሆኑ ። ነገር ይገባው ይሆን? ዝይ ራሱን በዱላ ቢመታ እንኳን ምን ነገር ይገባዋል? እሱም እንዲሁ ነው — ደደብ !" አለ ።

ጉጠት ፡ ወደ ቤቱ ለመሔድ ተነሣ ። ያኰቭም ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በአንድነት ጉዞአቸውን ቀጠሉ ፤ እያወሩ ፡ እያወጉ ፡ ጓደኞቹ ሃምሳ ርምጃ ያህል ራቅ እንዳሉ ፡ ሽማግሌው ግሪጐሪ ፔትሮቪችም ከተቀመጠበት ተነሥቶ ተከተላቸው ። በበረዶ ላይ እንደሚሔድ ሰው ርምጃዎቹ የጥርጣሬ ዐይነት ነበሩ ።

የኢክሌየቮ መንደር በምሽቱ ዶብዛዛ ብርሃን ውስጥ መስረግ ጀምራለች ። የፀሐይዋ ብርሃን ፡ የዳገቱን ወገብ ይዞ እንደ እባብ እየተጠማዘዘ ወደ አፋፍ በሚወጣው መንገድ አናት ላይ ብቻ ዐርፏል ። በዕንጉዳይ የተሞሉ ቅርጫቶች ተሸክመው ከጢሻዎቹ አካባቢ ወደ የቤታቸው በሚያዘግሙ ዕድሜያቸው የገፉ ሴቶች ዙሪያ ትንንሽ ልጆች ይሯሯጣሉ ። ወጣትና አሮጊት ሴቶች በመኪናች ላይ ጡብ ችን ሲጭኑ ከዋሉበት የባቡር ጣቢያ ወደየቤታቸው መመለስ ጀምረዋል ። አፍንጫዎቻቸውና ጉንጮቻቸው በጡብ ቀይ አቧራ ተልኮስኩሰው እየዘፈኑ መንገዱን ይኳኩታል ። እንደ ዋሽንት በሚስረቀረቅ ድምፅ እያቀነቀነች ከፊት ለፊት ሆና የሠራተኞቹን ሠልፍ የምትመራው ሊፓ ናት ። ዕሊቱ ተገባዶ ዕረፍት በመተካቱ ደስ ያላት ትመስላለች ። እናቷ ፕራስኰቭያም የተጠቀለለ ነገር ይዛ እንደ ልማዷ ቁና ቁና እየተነፈሰች ከሌሎቹ ሴቶች ጋር ታዘግማለች ።

"እንደምን አመሹ ኢሊያ ማካሪች !" አለች ሊፓ፡ ከጉጠት ጋር ስትገናኝ ።



" እንዴት አመሸሽ ሊፓዬ ! " አለ በደስታ ፡ [illegible] ስና ሞቅ ባለ ሁኔታ ። ደግሞ አንድ ሁለት ያልተሰ[illegible]ትን በፈዝና በፍቅር መልክ ወርወር አደረገ ።

ጉጠትና ያኰቭ እያወሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ ፡ ንግ ግራቸው ለሁሉም ሰው ይሰማል ። ብዙም ሳይቆይ ሴቶቹ ከግሪጐሪ ፔትሮቪች ጋር ፊት ለፊት ግጥም አሉ ። ድንገተኛ ጸጥታ በአካባቢው ሰፈነ ። ሁሉም ነገር ጭጭ እርጭ አለ ። ሊፓና እናቷ ከሴቶቹ ኋላ ስለ ነበሩ ፡ በመጀመሪያ አላዩትም ። አጠገባቸው ሲደርስ ግን ፡ ሊፓ ወገቧ እስኪሰበር ለጥ ብላ እጅ ነሣችና ፡

"እንደምን አመሹ ፡ ግሪጎሪ ፔትሮቪች !" አለች ።

እናትየዋም እጅ ነሣች ። ሽማግሌው ባለበት ቀጥ ብሎ በመቆም ፡ እናትና ልጅን በጸጥታ ትክ ብሎ ያስተውላቸው ጀመር ። ድንገት ከንፈሮቹ ተንቀጠቀጡና እንባው ባይኖቹ ተንቸረፈፈ ። እናቷ ከያዘችው ጥቅል ውስጥ ሊፓ ትንሽ የምግብ ቁራሽ አወጣችና ለሽማግሌው በትሕትና ሰጠችው ። ግሪጐሪ ፔትሮቪች ሳያንገራግር ተቀብሎ መብላት ጀመረ ።

ፀሐይዋ ሙሉ በሙሉ ጠለቀች ። በመንገዱ አናት ላይ የነበረውም ብርሃን ጠፋ ። እየጨለመ ፡ እየራም እየበረደ ሔደ ። ሊፓና ፕራስኰቭያም በጸጥታ መንገዳቸውን ቀጠሉ — አሁንም አሁንም ደጋግመው እያማተቡ ።

1909 ዓ. ም. 1975 ዓ. ም.